# መጽሐፈ ሆሴዕ

## ከጥናት መመሪያዎች ጋር

ሀንድስ ቱ ዘ ፕሎ አገልግሎት

Hands To ThePlow.org

የሆሴዕ መጽሐፍ የሰባኪ መመሪያ

# ሀንድስ ቱ ዘ ፕሎ አገልግሎት

# Hands To ThePlow.org

የቅጂ መብት © 2019 by Hands to the Plow, Inc.

አሳታሚ–ሀንድስ ቱ ዘ ፕሎ

Published by Hands to the Plow, Inc.

P.O. Box 567 • Webster, WI 54893

First printing, 2019

የመጀመሪያ ኅትመት 2019

መብቱ በሕግ የተጠበቀ ነው።

አሳታሚው የጽሁፍ ፈቃድ ካልሰጠ በስተቀር

የዚህ እትም የትኛውንም ክፍል በሙሉ ወይም በከፊል ማባዛት

ወይም በሙሉም ሆነ በቁንጽል ማባዛት በኤለክትሮኒክስ

ውጤቶች መቅረጽና ማራባት ፈጽሞ የተከለከለ ነው።

በዚህ ትርጉም ሥራ በሙሉ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች እና ጥቅሶች የተወሰዱት በኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር በብርሃንና ሰላም በ1962 ከታተመው የመጽሐፍ ቅዱስ እትም መሆኑን ለአንባቢያን በቅድሚያ ማስታወቅ እንወዳለን።

ትርጉም
ጥር 2024
በመጋቢ ፍቅሬ ኃይለማሪያም ኖርቻ
ሚዙሪ ሰሜን አሜሪካ

**አስተዋጽዖ አበርካቾች**

**ቶም ኬልቢ – የጥናት ማስታወሻዎች**
*ፕሬዚዳንት፣ ሀንድስ ቱ ዘ ፕሎ ሚኒስትሪስ (Hands to the Plow Ministries, Webster, WI USA)*
**ማርክ ያገር – ዲዛይን እና ሕትመት**
*የፈጠራ ዳይሬክተር (Creative Director, DKY, Inc., Mpls, MN USA)*
**ሎሪ ሰጆኲስት – ምርት**
*የምርት ሥራ አስኪያጅ (Production manager, DKY, Inc., Mpls, MN USA)*

---

ውድ አንባቢ ሆይ፡-

ይህ የሰባኪ መመሪያ የሆሴዕ መጽሐፍ (ትንቢተ ሆሴዕ) አንባቢው እንዲረዳና እንዲጠቀምበት ለመርዳት የታለመ ነው። ምንም እንኳን ይህ የሰባኪ መመሪያ የሚያተኩረው በሆሴዕ መጽሐፍ ላይ ቢሆንም ሰባኪው ወይም አስተማሪው ሌሎች የመጽሐፍ ቅዱስ መጻሕፍትንም እንዲያነብ እና እንዲረዳም ለመርዳት ታስቦም ነው። ይህ መጽሐፍ በእርግጥም የቀሩትን "ትንንሽ ነቢያት" ማለትም (ከሆሴዕ እስከ ሚልክያስ) ያሉትን አንባቢው እንዲገነዘብ ይረዳዋል። ደግሞም ይህ መጽሐፍ አንባቢው "ዋና ዋናዎቹንም ነቢያት" ማለትም (ኢሳይያስ፣ ኤርሚያስ፣ ሕዝቅኤል) የመሳሰሉትም የበለጠ እንዲገነዘብ ያግዘዋል። ይህንን አንድ ነቢይ ማለትም ነቢዩ ሆሴዕን በማጥናት ሁሉንም ነቢያቶች በተለይም አንባቢው ኢየሱስን በተሻለ ሁኔታ እንደሚረዳ ተስፋ እናደርጋለን።

ባጠቃላይ ይህ መጽሐፍ አንባቢው እነዚህ ልዩ "ትንቢታዊ" መጽሐፍት የበለጠ ለመረዳት ይረዳዋል። አብዛኛውን ጊዜ ሆሴዕ ከሙሴ መጽሐፍ (ከዘፍጥረት እስከ ዘዳግም) ደጋግሞ ይጠቅሳል። ስለዚህ የትንቢተ ሆሴዕ አንባቢ ይህንን የሰባኪ መመሪያ መጽሐፍ ካጠና በኋላ የሙሴን ጽሑፎች በደንብ ይገነዘባል። በሆሴዕ ላይ የተገለጹት ጉዳዮች በ ፲ኛ እና በ 2ኛ  ነገሥት ውስጥ በተጠቀሰው የጊዜ ገደብ ውስጥ በእሥራኤልና በይሁዳ የሚኖሩ ሰዎች ስለ እግዚአብሔር ያመኑትን እንደዚሁም እግዚአብሔርንና ሌሎች አማልክትን ያመለኩበትን መንገድ በትክክል ያሳያል። ስለዚህ የትንቢተ ሆሴዕ አንባቢ ይህንን መጽሐፍ ካጠና በኋላ ፲ኛ እና 2ኛ ነገሥትን በደንብ ይረዳል ማለት ነው። በመጨረሻም ሆሴዕ በአዲስ ኪዳን ውስጥ በኢየሱስ እና በሐዋሪያት ተጠቅሷል። በመሆኑም ሰባኪው ይህንን መጽሐፍ መረዳቱ የአዲስ ኪዳን መጻሕፍትን፣ የኢየሱስንና የሐዋሪያትን ሥነ-መለኮት የበለጠ እንዲረዳ ይረዳዋል።

ሆኖም የዚህ መጽሐፍ ግብ በመጨረሻ የእግዚአብሔርን ቃል በተሻለ ሁኔታ መረዳት ብቻ አይደለም። የእግዚአብሔር ቃል መረዳቱ ጠቃሚ ቢሆንም፤ እንደ ሆሴዕ ያለ መጽሐፍን በማጥናት ግን በራሱ የመጨረሻ ግብ መረዳት ብቻ አይደለም። ይልቅስ የመጨረሻው ግብ አምልኮ ነው እንጂ። ፀሎታችን የዚህ መጽሐፍ ጥናት አንባቢውን ሥላሴ የሆነውን እግዚአብሔርን ወደ ማምለክ እንዲመራው ነው። በተጨማሪም ፀሎታችን አንባቢው የዚህ መጽሐፍ ጥናት ቤተክርስቲያንን የበለጠ እንዲወድ እንዲረዳው ነው። ደግሞም ፀሎታችን በዚህ መጽሐፍ ትምህርት በመበረታታት  አንባቢው ደግሞ ለሌሎች ብዙዎች መበረታታት ምክንያት እንዲሆንም ጭምር ነው።

በዚህ መጽሐፍ የተጠቀሰው ማስታውሻ ፍፁም አይደለም። ስለሆሴዕ መጽሐፍ ብዙ ማለት ይቻል ነበርና። በመሆኑም የደራሲው ውስንነት በሁሉም ገጾች ላይ ሊታይ እንደ ሚችል እንርግጠኛ ነኝ። ይሁን እንጂ የእግዚአብሔር በጎ ቃል ፍጹም መሆን የኛን ፍጹም ያለምሆን ጥረት ቢገልጥ ይህ ተገቢ ነገር ነው። ይህም ደግሞ በምንጽፈበት ጊዜ፣ በምናጠናበት፣ በስብከትና በማስተማርም  ጊዜ ቢሆን እውነት ነው። የእግዚአብሔርን በጎ ቃል ለመረዳት እና ለማወጅ መፈለግ ይኖርብናል፤ እግዚአብሔርም ደግሞ ከሰማይ ጠንካራ እርዳታ እንደሚሰጠን መተማምን ደግሞ አለብን። በሆሴዕ ውስጥ የሚገኙትን እውነቶች ስታጠና፣ ስታመልክ፣ ደግሞም ስትታዘዝ እና ስትሰብክ በጠንካራ ረዳኤቱ ፍለጋህ ደስ ይበልህ።

ቶም ኬልቢ

ታህሳስ 4 ቀን 2018 ዓ . ም

## ይህን መመሪያ እንዴት መጠቀም እንደሚገባ

1. ይህ መጽሐፍ የትንቢተ ሆሴዕ መጽሐፍ ጽሑፍ ይዟል። መጽሐፉንም በተለያዩ ክፍሎች ከፍለነዋል። በዚህ ጥናት ውስጥ ካለው እያንዳንዱ ክፍል በፊት አንባቢው የዚህን ክፍል አጭር መግለጫ ያገኛል።

2. ከአጠቃላይ እይታ በኋላ ደግሞ አንባቢው ቀጥታ የሆሴዕ የራሱ ጽሑፍ ያገኛል። የሆሴዕ ጽሑፍ በገጹ **የላይኛው ክፍል** ላይ ይገኛል።

3. በተጨማሪም ይህ መጽሐፍ በሆሴዕ ምዕራፍ ውስጥ የሚገኙትን አንዳንድ ቃላት ወይም ጥቅሶች ወይም ክፍሎች የሚያመለክቱ የጥናት ማስታወሻዎችን ይዟል። እነዚህ ደግሞ የጥናት ማስጣወሻዎች በገጹ **ታችኛው ክፍል** ላይ ባለው ከሆሴዕ ጽሑፍ ሥር ይገኛሉ። የጥናት ማስታዎሻዎቹ ስብከቶች አይደሉም። ነገር ግን እነዚህ ማስታወሻዎች ሰባኪው የሆሴዕን ትርጉም እንዲያገኝ ለምረዳት የታሰቡ ናቸው።

4. በገጹ **ታችናው ክፍል** ላይ የሚገኙው የጥናት ማስታዎሻዎች በግርጌ ማስታወሻ ቁጥር ተለይቷል። እነዚህም ቁጥሮች በቀይ ቀለም ተመልክተዋል። ከእያንዳንዱ የጥናት ማስታወሻ ቀጥሎ ያሉት ቀይ ቁጥሮች በሆሴዕ ጽሑፍ ውስጥ ከሚታየው **ከላይኛው** ቀይ ቁጥር ጋር የሚዛመዱ ናቸው። ቁጥሮቹ አብረው የሚሄዱ ናቸውና።

5. የጥናቱ ማስታውሻዎች አንዳንድ ጊዜ ሌሎች የቅዱሳት መጽሕፍት ምንባቦችንም ይዘረዝራሉ። እነዚህ ማስታወሻዎች አንዳንድ ጊዜ ከብሉይ ኪዳን በሌላ ጊዜ ደግሞ ከአዲስ ኪዳን የተወሰዱ ናቸው። እንግዲህ እነዚህ ክፍሎች እየተጠና ካለው ከሆሴዕ ምንባብ ጋር የተገናኙ በመሆናቸው በጥንቃቄ መመርመር ይኖርባቸዋል።

## ሆሴዕን በሚያነቡበት ጊዜ

## ማስታወስ ያለብዎ 20 ነግሮች

1. *ሆሴዕ ነቢይ ነው።* የነቢዩ ዋና "ሥራ" ደግሞ የእግዚአብሔር ቃል አቀባይ ሆኖ መናገርና እነደዚሁም ለእግዚአብሔር እንደ "እጁ እና እግሩ" መሆን ነው። ስለዚህም ነቢዩ የሚናገረውና ነቢዩ የሚያደርገውም እግዚአብሔር የሚናገርውና እግዚአብሔር በሕዝቡ መካከል የሚያደርገውን ነው (ሆሴዕ 6፡5 ይመልከቱ)። ሆሴዕ የተነበየው በ750 ዓክልበ አካባቢ ነው። በጥንቷ እሥራኤል ይኖር የነበረ እውነተኛ ሰው ነበር። ስለዚህ "ሆሴዕ ነቢይ ነበር" ማለት ትክክለኛ ነገር ነው። እንዳውም ሆሴዕ ነቢይ ነው ቢባልም ትክክል ይሆናል። ምክንያቱም በመልዕክቱ እስካሁን ለእግዚአብሔር ሕዝብ እየተናገረ ነውና (1 ጴጥሮስ 1፡10–12 ይመልከቱ)። ትንቢቱ አሁንም ቢሆን ልናስብበትና ልንታዘዘውም ይገባል።

ኢየሱስ በምድር በነበረበት ጊዜ ሰዎች በሆሴዕ ውስጥ ያለውን ቃል እንዲያነቡ እና ትንቢቱንም በሕይወታቸው ላይ እንዲተገብሩ ይጠበቅ ነበር፤ (በማቴዎስ 9፡13 እና 12፡7 ውስጥ ከሆሴዕ ጠቅሶ የተናገረውን ይመልከቱ)። ኢየሱስ በመጀመሪያው መቶ ክፍለ ዘመን ይኖሩ ከነበሩት ሰዎች ጋር ሆሴዕን በተጠቀመበት መሠረት ሆሴዕ ለእሥራኤል የተናገረው ቃል ከሆሴዕ ዘመን በኋላም ባሉት ዘመናት ውስጥ የሚኖሩ ሰዎችን እንደሚመለከትም ግልጽ ነው። የሆሴዕ መልዕክት ለእኛም እንደ ተነገረን አድርገን ማንበብ እና በውስጡ ተጽፎ የሚገኘውንም መታዘዝ አለብን። ስለዚህ ሰባኪ ወይም አስተማሪ የሆሴዕን መልዕክት በጥንቃቄ በመመልከት፣ ትርጉሙንም ለመረዳት በሚያስችል መንገድ ማስረዳትና ቃሉንም በዚህም ዘመን በእግዚአብሔር ሕዝቦች ዘንድ ተግባራዊ እንዲሆን ማድረግ ይኖርበታል።

የእግዚአብሔር ቃል አቀባይ እንደመሆኑ ነቢዩ እግዚአብሔር ከእነርሱ ጋር የገባውን ቃል ኪዳን ለሕዝቡ ያስታውሳቸዋል፣ ሕዝቡም ቃል ኪዳኑን ጠብቀው ወይም አፍርሰው እነደሆነ  የሰማይ ፍርድ ያውጃል። ሰዎችንም ወደ ቀጣይ ታማኝነት (ታዘው ከነበሩ) ወይም ወደ ንስሐ (ያልታዘዙም ከነበሩ) እና ለታዛዦች የሚመጡትን የበረከት ምስል እንደዚሁም ለማይታዘዙት ደግሞ የሚመጣው እርግማን ስዕል ያቀርባል።

ስለ ወደፊቱ ጊዜ “መተንበይ” የነቢይ ሥራ አካል ቢሆም፤ ብቸኛው ሥራቸው ወይም በጣም አስፈላጊው ሥራቸው ያ ብቻ አልነበርም። ይልቁንም የነቢዩ ዋና ሥራ እሥራኤልን ለቃል ኪድኑ እንዲታዘዙ እና እግዚአብሔርን እንዲያመልኩ መጥራት ነበር።

ደግሞም ነቢያት የክርስቶስ ነጸብራቅ መሆናቸውን ማወቅ አስፈላጊ ነው። ኢየሱስ ታላቅ ነቢይ ነውና (ለምሳሌ ሉቃስ 4፡24 እና 7፡16 ይመልከቱ)። እሱም የእግዚአብሔር ዋና ቃል አቀባይ ነው። ስለዚህ ኢየሱስ ትንቢቶቻቸው በጽሑፍ ከሰፈረው ነቢያት (ሙሴ፣ ኢሳይያስ፣ ኤርምያስ፣ ሕዝቅኤል፣ ሆሴዕ፣ ወዘተ) ጋር ተመሳሳይ ነው። ደግሞም እሱ ተአምራትና ታላላቅ ነገሮች ካደርጉት ነቢያትም ሁሉ (ሙሴ፣ ኤልያስ፣ ኤልሳዕ ወዘተ) ጋር ተመሳስይ ነው። ክርስቶስ ነቢይ እነደሆነ በብሉይ ኪዳን በትንቢት ተነግሯል። እሥራኤላውያን ወደ ተስፋይቱ ምድር ከመሄዳቸው በፊት ሙሴ *እሱን የሚመስል* ነቢይ እንደሚመጣ ተናግሯል። “አምልካህ እግዚአብሔር ከአንተ መካከል ከወንድሞችህ እንደ እኔ ያለ ነቢይ ያስነሣልሃል እርሱንም ታዳምጣለህ።ቃሌንም በአፉ አደርጋለሁ ያዘዝሁትንም ቃል ሁሉ ይነግራቸዋል፤ በስሜም የሚናገረውን ቃሌን የማይሰማውን ሰው እኔ እበቀልለታለሁ።” (ዘዳግም 18፡15–19 ይመልከቱ)። ሙሴ የተናገረው ስለ ክርስቶስ መምጣት ነው! ልብ ማለት የሚያስፈልገው ነገር ቢኖር ከክርስቶስ በፊት የነበሩት ነቢያት ሁሉም የሱን ሥራ የሚያንጸባርቁ መሆናቸውን ነው። ብቻ በሆነ መንገድ ስለ ክርስቶስ ያስታውሱናል።

2. **የነቢያት መልዕክት በአጠቃልይ በእሥራኤል ሕዝብ ዘንድ ተቀባይነት አልነበረውም።** ስለዚህ ነቢይ መሆን አስተማማኝ ወይም ቀላል አልነበረም። ኢየሱስ ራሱ እሥራኤልውያን ነቢያትን ሁሉ እንዳሳደዱ ተናግሯል (በተጨማሪም ማቴዎስ 23፡3–4፣37፤ ማርቆስ 12፡1–12፤ ሉቃስ 11:47–49 እና 13፡34 ይመልከቱ)። እንደዚሁም የሐዋሪያት ሥራ 7፡52 ይመልከቱ። ነቢይን መግደል ትልቅ ኃጢአት ነበር፤ ምክንያቱም እግዚአብሔርን ዝም ለማሰኘት የሚደረግ ሙከራ ነበርና። ያስታውሱ ነብይ የእግዚአብሔር ቃል አቀባይ ብቻ ነበርና። ስለዚህ ነብይን መግደል የእግዚአብሔርን ድምፅ “ለመግደል” ሙከራ ማድረግ ነበር። አብዛኛው ሰው የነቢያትን ቃል አይቀበልም ነበርና። ይህ በብሉይ ኪዳን እውነት ነበር እንደዚሁም ኢየሱስ ታላቁም ነቢይ በምድር ላይ ሲያገለግልም እውነት ነበር። ሆኖም ጥቂት ቅሬታ የሆኑ ሰዎች ነቢያትን አምነው ለመልዕክቶቻቸው ምላሽ ይሰጡ ነበር። ይህም በብሉይ ኪዳን እውነት ነበር። ኢየሱስም በምድር ላይ ሲያገለግል እውነት ነበር። ዛሬም ደግሞ እውነት ነው። የእግዚአብሔር ሰዎች የነቢያትን መልዕክት ሰምተው ለቃላቸውም ምላሽ ሰጥተዋል። ቤተክርስቲያንንም በሐዋሪያትና በነቢያት መሠረት ላይ ታንጻለችና

(ኤፌሶን 2፡20 ይመልከቱ)። (በኤፌሶን 2፡20 ላይ "ሐዋሪያት" የሚለው ቃል በመጀመሪያ የተጻፈበት ምክንያት ሐዋሪያት የነቢያትን መልዕክት ለአማኞች በመተርጎም ረገድ ትልቅ ሚና ስላላቸው ነው።)

3. ሆሴዕ ትንቢት በተናገረበት ዘመን የግዚአብሔር ሕዝብ ለሁለት የተከፈለ ሕዝብ ነበር፤ እሥራኤልና ይሁዳ። በእርግጥ ሁለቱ ሕዝቦች ግኑኝነት ነበራቸው። እሥራኤል በሰሜን በኩል ትገኝ ነበር። ይሁዳ ደግሞ በደቡብ በኩል ሰፍሮ ነበረ። ሆሴዕ ደግሞ ከእግዚአብሔር ወደ እሥራኤል የተላከ ነቢይ ነበር። ይሁን እንጂ ሆሴዕ እየተናገረ የነበረው ለሰሜኑ እሥራኤል መንግሥት ቢሆንም መልዕክቱ ግን በይሁዳም እንደሚሰማ ያውቅ ነበር። በመሆኑም በይሁዳ ያሉትንም ሰዎች (በደቡብ ያለው ሕዝብ) ቃሉን ሰምተው በሰሙት መሠርት እንዲተገብሩ ሆሴዕ ይጠብቅ እንደ ነበር ግልጽ ነው። አንዳንድ ጊዜም ሆሴዕ በቀጥታ ለይሁዳ ሕዝብም ይናገር ነበር (ሆሴዕ 4፡15 ይመልከቱ)። ልክ እንደ ሆሴዕም ሌሎች ነቢያትም ትኩረታቸው በእሥራኤል ወይም በይሁዳ ላይ ያደርጉ ነበር። የሚገርመው ነቢዩ ኢሳያስ ስለ ይሁዳ ነው የተናገረው (ኢሳይያስ 1፡1 ይመልከቱ)። ይሁን እንጂ ኢሳይያስ አንዳንዴ በመልዕክቶቹ ውስጥ "እሥራኤል" የሚለውን ስም ሲጠቀም እንመለከታለን (ኢስይያስ 1፡3 ይመልከቱ)። ይህ የሚያመለክተን እግዚአብሔር "ሁለት" የተለያዩ ሕዝቦች እንደዚሁም ሁለት የተለያዩ ዕቅዶች እንዳልነበረው ነው። የእግዚአብሔር ዕቅድ ሁል ጊዜ አንድ ሕዝብ በአንድ ንጉሥ ሥር በደስታ እንዲኖር ነበርና። ዛሬ የእግዚአብሔር ሕዝብ የተለያየ ሕዝብ በመሆን መከፋፈል አቁሟል። አሁን ይልቅስ የእግዚአብሔር ሕዝብ በአንድ ንጉሥ ሥር ማለትም ኢየሱስ ክርስቶስን ተከትለው አንድ "ሕዝብ" ናቸውና። ይህንንም የእግዚአብሔር ሕዝብ አንድነት በሆሴዕ ትንቢትና በብሉይ ኪዳን ሁሉ ተነግሯል (ሆሴዕ 1፡11 እና ሕዝቅኤል 36፡22–28 ይመልከቱ)። በክርስቶስ ሥራ ምክንያት የእግዚአብሔር ሕዝብ አንድ ሆነዋልና (ኤፌሶን 2፡11–22 ይመልከቱ)። ምንም እንኳን እኛ ክርስቲያኖች የምንኖረው በተለየ ዘመን ውስጥ ቢሆንም ለእሥራኤልና ለይሁዳ የተነገረውን ቃል መስማት ይኖርብናል። ዛሬም ቃሉ ለሁሉም የእግዚአብሔር ሕዝብ ተግባራዊ መመሪያ ነውና።

4. ሆሴዕ ከሙሴ መጽሐፍ (ከዘፍጥረት እስከ ዘዳግም) ብዙ ነገሮችን ወስዷል። የሙሴ መጽሐፍ ማለትም (ዘፍጥረት፣ ዘጸአት፣ ዘሌዋውያን፣ ዘኁልቁ እና ዘዳግም) የተጻፈው ከሆሴዕ ዘመን 600 ዓመታት ቀደም ብሎ ነው። የሙሴ መጽሐፍ በእሥራኤል ዘንድ በሰፊው ይታወቅ ነበር ምክንያቱም የሙሴ መጽሐፍ ከሙሴ ዘመን በኋላ በነበሩት ነቢያት ዘወትር ተጠቅሷልና። እንደ

ሌሎቹም ነቢያት ሆሴዕ ሕጉን (የሙሴ መጽሐፍ ሌላኛው ስም ማለት ነው) አንብቧል፣ ተርድቶታል፣ አምኖበትም እንደነበረ ግልጽ ነው፤ ስለዚህ የእግዚአብሔር ሕዝብ በውስጡ የተጻፈውን እንዲታዘዙ ይጠብቅ ነበር።

ሆሴዕ ሕጉን በመልዕክቱ ውስጥ በዘዴ አካቶታል። ሆሴዕ በተደጋጋሚ ከሕጉ የተወሰደ ቋንቋ ሲጠቀም እንመለከታለን። እንደዚሁም ደግሞ የሙሴ መጽሐፍን ታሪካና ሰዎችን ለመልዕክቱ ሲጠቀም እናስተውላልን። በተለይም በሲና ተራራ በእግዚአብሔርና በእሥራኤል መካከል የተደረገውን ቃል ኪዳን ለሕዝቡ ዘወትር ያሳስባቸዋል። ደግሞም በሙሴ መጽሐፍ ውስጥ የተገለጹትን ነገሮች ወደፊት ለሚፈጸሙ ክንውኖች እንደ አብነት ይጠቀማል። ለምሳሌ ሆሴዕ ስለ **ሁለተኛው ዘጸአት ክስተት** በተደጋጋሚ እያነሳ ይናገራል። የመጀመሪያውን ዘጸአት ቃላቶችን እና አንዳንድ ዝርዝሮችን በመውሰድ ስለሚመጣው ሁለተኛው የዘጸአት ክስተት በመልዕክቱ ውስጥ ተጠቅሞባቸዋል። ስለዚህ በሆሴዕ የሙሴ ሕግ አጠቃቀም ላይ ተመስርተን ሆሴዕ አንባቢዎቹን የሙሴን መጽሐፍ በደንብ እንዲረዱት እነደሚፈልግ በግልጽ መመልከት እንችላልን። ሆሴዕ የሙሴ መጽሐፍን ሥልጣን እንዳለው አድርጎ እንደሚቆጥርም ግልጽ ነው። በሙሴ መጽሐፍና በሆሴዕ መጽሐፍ መካከል ስላለው ብዙ ትስስር ሰባኪ ወይም አስተማሪ የሙሴን መጽሐፍ ከሆሴዕ ጋር ማጥናቱ ትልቅ እገዛ ይሆንለታል ማለት ነው።

5. **ሆሴዕ በብሉይ ኪዳን የሚገኝ መጽሐፍ ነው።** ምንም እንኳን የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት የተጻፍት ከክርስቶስ መምጣት በፊት ቢሆንም እስከ ዛሬም ቢሆን ለእግዚአብሔር ሕዝብ ጠቃሚዎች ናቸው። ይሁን እንጂ ሆሴዕ ከክርስቶስ መምጣት በፊት የተጻፈ መጽሐፈ በመሆኑ፣ እንደ አዲስ ኪዳን መጽሐፍ መቁጠርና መጠቀም አይቻልም። የአዲስ ኪዳን መጻሐፍት የተጻፉት ከክርስቶስ ሕይወት፣ ሞትና ትንሣኤ በኋላ ነው። ሁሉም የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት እነዚህን ሁነቶች በጉጉት ይጠባበቁ ነበር። የትኛውም የብሉይ ኪዳን መጽሐፍ (እና የትኛውም የብሉይ ኪዳን የትንቢት መጽሐፍ) ጥናት የሚጀመርበት ቦታ አዲስ ኪዳን ውስጥ ነው።እንደ ክርስቲያኖች፣ አዲስ ኪዳን እንዳልተጻፈ አድርገን ወደ ብሉይ ኪዳን አናዘነብልም። አዲስ ኪዳን ተጽፏል፤ በመሆኑም በውስጡም ከብሉይ ኪዳን ሰፊ ጥቅሶችን እናገኛለን፣ ደግሞም ትክክለኛ ጥቅሶችን በማይሰጡ ምንባቦች ውስጥ ለቃላቶችና ጭብጦች ብዙ ተመሳሳይ ይዘት ያላቸው ጥቅሶችን እናገኛለን። አዲስ ኪዳን አንድን ትንቢት እንዴት እንደተፈጸመ በተደጋጋሚ ይነግረናል። በብሉይ ኪዳን ውስጥ ያሉ አንዳንድ ክንዎኖች እንዴት በአዲስ ኪዳን ጥላ እንደሆኑ ተነግሮናል። በአጭሩ፣ ብሉይ ኪዳንን እንዴት ማንበብ እና መረዳት እንዳለብን ከኢየሱስና ከሐዋሪያት በቀር በማንም አልተነገረንም።

ኢየሱስና ሐዋሪያት የብሉይ ኪዳን ትንቢት ፍጻሜ ያገኘው በኢየሱስ እንደሆነ በግልጽ ይናገራሉ (ሉቃስ 24፡25–27 እና 44–49 ይመልከቱ)። ይሁን እንጂ ይህ ማለት እያንዳንዱ ገጽ ስለ ሚመጣው ክርስቶስ ግልጽ ማጣቀሻን ያካትታል ማለት አይደለም። አብዛኛውን ጊዜ ይህ አይሆንም። ሆኖም ደግሞ ብሉይ ኪዳን በሙሉ በሆነ መንገድ ስለ ኢየሱስና ስለ ኢየሱስ ታሪክ ይናገራል ማለት ነው።

ብሉይ ኪዳን የክርስቶስን ታሪክ የሚናገርባቸው አንዳንድ መንገዶች በቀላሉ የሚታውቁ ናቸው። ለምሳሌ የሚከተለውን ትንቢት ከሚኪያስ ይመልከቱ፡-

> *አንቺ ቤተ ልሔም ኤፍራታ ሆይ አንቺ በይሁዳ አእላፋት መካከል ትሆኚ ዘንድ ታናሽ ነሽ ከአንቺ ግን አወጣጡ ከቀድሞ ጀምሮ ከዘላለም የሆነ በእሥራኤልም ላይ ገዥ የሚሆን ይወጣልኛል* (ሚክያስ 5፡2)።

ይህ ትንቢት በእግዚአብሔር የተቀባው ገዥ (በአዲስ ኪዳን ውስጥ ደግሞ “ክርስቶስ” ተብሎ የሚጠራው) የሚወለድበትን ትክክለኛ ከተማ በዝርዝር ይገልጻል። እንግዲህ እንደዚህ ዓይነት ብዙ ምንባቦች ደግሞ አሉ። እነዚያም ደግሞ የክርስቶስን መምጣት በዝርዝር ይናገራሉ።

ሌሎች የብሉይ ኪዳን ክፍሎች ግን እንደዚህ በግልጽ አይናገሩም ወይም የበለጠ አስቸጋሪ ናቸው። ለምሳሌ የመሳፍንት መጽሕፍ ስለ ክርስቶስ መምጣት የሚናገረው እንዴት ነው (በሚክያስ 5፡2 እንዳለው ግን አይደለም)? በመጽሐፉ የመጨረሻ ክፍል ላይ ፍንጭ ሊታይ ይችል ይሆናል ለምሳሌ “በዚያን ዘመን በእሥራኤል ዘንድ ንጉሥ አልነበርም፤ ሰው ሁሉ በፊቱ መልካም መስሎ የታየውን ያድርግ ነበር” (ኢያሱ 21፡25) እንደ ሚለው ማለት ነው። የመሳፍንት መጽሐፍ በእሥራኤል ንጉሥ እንዲቋቋም የሚያሳስብ መጽሕፍ ነው። መጽሐፉ የእሥራኤል ችግር ሊፍታ የሚችለው በእግዚአብሔር ሕዝብ ላይ የሚገዛው በእግዚአብሔር የተቀባ ንጉሥ በዙፋኑ ላይ ሲሆን መሆኑን አውቆ ለአንባቢው በማስታውስ ያቆማል። ያም መምጣት የነበረበት ንጉሥ ኢየሱስ ነው።

እንግዲህ ሁሉም የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ስለ ክርስቶስና ስለ ወንጌል ይናገራሉ ማለት ነው። ይሁን እንጂ እነዚህ መጻሕፍት ግን ስለ ክርስቶስና ስለ ወንጌል ሁሉም በተመሳሳይ መንገድ ግን አይናገሩም። ስለዚህ እንደ ሰባኪና አስተማሪ የእኛ ሥራ እያንዳንዱ የብሉይ ኪዳን መጻሕት የክርስቶስን ታሪክ እንዴት እንደሚናገሩ ማወቅና ይህንንም ለሌሎች በጥንቃቄ ማስረዳት ነው።

በእርግጥ የንባቦቹን ትርጉም ለመገመት መሞከር የለብንም። ለዚህም ነው ሐዋሪያትና መንፍስ ቅዱስ የተሰጠን። አዲስ ኪዳንን ስናነብ ሐዋሪያት ብሉይ ኪዳንን ሲተረጉሙ የሚያደርጉትን እንመለከታለንና። ጥቅሶችን እንዴት እንደሚጠቅሱ እና ታሪኮችንና ግጥሞችን ለክርስቶስ እና ለቤተክርስቲያን እንዲተገበሩ እንዴት እነደሚረዱ ማየት እንችላለን። እንደዚሁም በዚህ ሂድት ውስጥ መንፍስ ቅዱስ እንደሚረዳን ማመን አለብን። መንፈስ ቅዱስ ደግሞ በሁሉም ቅዱሳት መጻሕፍት ክርስቶስን እንድናይ እና እንድናውጅ ይፈልጋልና።

6. **ብሉይ ኪዳን በትውፊት ወይም በተለምዶ በሦስት ክፍሎች የተከፈለ ነው፡- ሕግ፣ ነቢያት እና ጽሑፎች።** (ጽሑፍ በመባል የሚታወቀው የብልይኪዳን ክፍል አንዳንዴ መዝሙረ ዳዊት ይባላል። በብሉይ ኪዳን ውስጥ መዝሙረ ዳዊት ትልቁ ክፍል ስለሆነ ይህ ተገቢ ሊሆን ይችላል።) ኢየሱስ በሉቃስ 24፡44 ላይ የብሉይ ኪዳንን ሦስቱንም ክፍሎች ጠቅሷል፡- “እርሱም፡-ከእናንተ ጋር ሳለሁ በሙሴ ሕግና በነቢያት በመዝሙራትም ስለ እኔ የተጻፈው ሁሉ ይፈጸም ዘንድ ይገባል ብዬ የነገርኋችሁ ቃሌ ይህ ነው አላቸው።” ኢየሱስ የተናገረው በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የሚገኙትን እነዚህን ሦስት ክፍሎች እንደሚያስገነዝብ ያሳያል። የኢየሱስ ንግግር ከእርሱ በኋላ እንደ ነበርው ሐዋሪያው ጳውሎስ ሦስቱን ክፍል ራሱ እንደ መለኮታዊ “ረዳት” እንደተጠቀመበት ምንም ጥርጥር የለውም።[1]

በአጠቃላይ ሦስቱ የብሉይ ኪዳን ክፍሎች እና በእያንዳንዱ በሦስቱ ክፍሎች ውስጥ ያሉት ግለሰባዊ መጻሕፍት በጥንቃቄ የተደረደሩ ስለመሆኑ ብዙ ማስረጃዎች አሉ። ስለዚህ ሕጉ ሆን ተብሎ በመጀመሪያ ላይ፣ ነቢያት በሁለተኛ ደረጃ፣ ጽሑፎች ደግሞ ሆን ተብሎ በሦስተኛ ደረጃ ተቀምተዋል። በብሉይ ኪዳን የሚገኙትን የመጻሕፍቱን ሦስት ክፍሎች እንደ እግዚአብሔር ስጦታ መመልከት ጠቃሚ ነው። አንባቢው በክርስቶስ እንዲያምንና በእርሱም ደግሞ እንዲደሰት መጽሐፎቹ እንዴት እንደተዘጋጁ መመርመሩ የሰባኪው ወይም የአስተማሪው ደስታ ነው።

ምናልባት በአንዳንድ በዘምናዊ የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉሞች ብሉይ ኪዳን በእነዚህ ሦስት ዋና ዋና ክፍሎች የተደረደሩ እንዳልሆኑ ልብ ማለት ያስፈልጋል። ይልቁንም ዘመናዊ መጽሕፍ ቅዱሶች በአብዛኛው በጊዜ ቅደም ተከተል ይደረድሯቸዋል። ይህ ማለት ደግሞ ነብያት ውስጥ ያሉ መጻሕፍት እና ጽሑፎች በዘመናዊ መጽሕፍ ቅዱሶች ተደባልቀዋል ማለት ነው። ይሁን እንጂ

[1] ኢየሱስ በተናገረው ቃል ላይ ሦስቱንም ክፍሎች ስለ ክርስቶስ እንደሆነ የሰጠውን በጣም አስፈላጊ መግለጫ ጨምሮ ያስረዳል።

በመጽሐፍቱ ውስጥ ያሉት ትክክለኛ መልዕክት ተመሳሳይ ነው። ልዩነቱ መጽሐፍቱ እንዴት እንደተደረደሩ ነው።
ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን በእያንዳንዱ ሶስት ክፍሎች የሚገኙ መጽሐፍቶች ናቸው። አሁንም ማስታውስ ያለብን በዚህ ጥናት ወስጥ የተዘረዘሩት ቅደም ተከተል በአብዛኛው በዘመናዊ መጽሐፍ ቅዱሶች ውስጥ ካለው ቅደም ተከተል የተለየ መሆኑን ልብ ማለት ያስፈልጋል።

ሕግ፡- ኦሪት ዘፍጥረት፣ ኦሪት ዘጸአት፣ ኦሪት ዘሌዋውያን፣ ኦሪት ዘኁልቁ፣ ኦሪት ዘዳግም፤

**ነቢያት፡-** መጽሐፍ ኢያሱ ወልደ ነዌ፣ መጽሐፈ መሳፍንት፣ መጻሐፈ ሳሙኤል ቀዳማዊ፣ መጽሐፈ ሳሙኤል ካልዕ፣ መጽሐፈ ነገሥት ቀዳማቂ፣ መጽሐፈ ነገሥት ካልዕ፣ ትንቢተ ኤርምያስ፣ ትንቢተ ሕዝቅኤል፣ ትንቢተ ኢሳይያስ፣ ትንቢተ ሆሴዕ፣ ትንቢተ ኢዩኤል፣ ትንቢተ አሞጽ፣ ትንቢተ አብድዩ፣ ትንቢተ ዮናስ፣ ትንቢተ ሚኪያስ፣ ትንቢተ ናሆም፣ ትንቢተ ዕንባቆም፣ ትንቢተ ሶፎንያስ፣ ትንቢተ ሐጌ፣ ትንቢተ ዘካሪያስ፣ ትንቢተ ሚልክያስ፤

**ጽሑፎች፡**[2]- መጽሐፈ ሩት፣ መዝሙረ ዳዊት፣ መጽሐፈ ኢዮብ፣ መጽሐፈ ምሳሌ፣ መጽሐፍ መክብብ፣ መኃልየ መኃልይ ዘሰሎሞን፣ ሰቆቃው ኤርምያስ፣ ትንቢተ ዳናኤል፣ መጽሐፈ አስቴር፣ መጽሐፈ ዕዝራ፣ መጽሐፈ ነህምያ፣ መጽሐፈ ዜና ቀዳማዊ፣ መጽሐፈ ዜና ካልዕ፤

ሦስቱ ክፍሎች እያንዳንዳቸው እኩል የእግዚአብሔር ቃል አካል ናቸው። እነዚህ ሦስቱም ክፍሎች “ለትምህርትና፣ ለተግሳጽ፣ ልብንም ለማቅናት፣በጽድቅም ላለው ምክርም” ይጠቅማሉ። ሦስቱንም ክፍሎች ሰዎችን ወደ ክርስቶስ ለመምራት እና በእርሱም ወደ ብስለት እንዲደርሱ የታሰቡ ናቸው (2 ጢሞቴዎስ 3፡14–17)።

7. **ሆሴዕ በብሉይ ኪዳን ነቢያት ተብሎ በሚጥራው ክፍል ውስጥ ይገኛል። ነቢያት በሁለት ሊከፈሉ ይችላሉ። የመጀመሪያው ክፍል የእሥራኤልን ታሪክ በሚናገሩ መጻሕፍት የተዘጋጀ ነው። ይህ ዓይነቱ ሥነ ጽሑፍ አንዳንድ ጊዜ “ትረካ” ተብሎ ይጠራል። ሁለተኛው ክፍል ደግሞ የስብከት ስብስቦች በሆኑ መጽሐፍት የተዘጋጀ ነው።**

[2] ጽሑፎች ተብሎ በሚጠራው ክፍል ውስጥ ያሉት መጻሕፍት በተለያዩ የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ዝርዝር ውስጥ በተለያየ መንገድ ተደርድረዋል።

ይህ **የመጀመሪያው የነቢያት ክፍል** መጽሐፈ ኢያሱ ወልደ ነዌ፣ መጽሐፈ መሳፍንት፣ መጻሐፈ ሳሙኤል ቀዳማዊ፣ መጽሐፈ ሳሙኤል ካልዕ፣ መጽሐፈ ነገሥት ቀዳማቂ፣ መጽሐፈ ነገሥት ካልዕ፣ ያጠቃልላል። እነዚህ መጽሐፍት ስለ እሥራኤል ወደ ተስፍይቱ ምድር እንደ ገቡ፣ በምድሪቱም እንደ ኖሩ እናም በመጨረሻም ከምድሪቱ እንደ ተባረሩ ታሪክ ይናገራሉ። እነዚህ "ታሪካዊ" መጻሕፍት በእሥራኤል ውስጥ የተፈጸሙትን ክስተቶች ለአንባቢው ይተነትናሉ። **ሁለተኛው የነቢያት ክፍል** ብዙ ስብከቶችን የያዙ መጽሐፎችን ያቀፈ ነው (እነዚህም አንዳንድ ጊዜ የማብራሪያ መጽሐፍት ተብለው ይጠራሉ)። እነዚህም ትንቢተ ኤርምያስ፣ ትንቢተ ሕዝቅኤል፣ ትንቢተ ኢሳይያስ፣ ትንቢተ ሆሴዕ፣ ትንቢተ ኢዩኤል፣ ትቢተ አሞጽ፣ ትንቢተ አብድዩ፣ ትንቢተ ዮናስ፣ ትንቢተ ሚኪያስ፣ ትንቢተ ናሆም፣ ትንቢተ ዕንባቆም፣ ትንቢተ ሶፎንያስ፣ ትንቢተ ሐጌ፣ ትንቢተ ዘካሪያስ እና ትንቢተ ሚልክያስ ናቸው። እነዚህ የማብራሪያ መጽሐፍቶች ክስተቶቹ እንዲፈጸሙ ያደረጋቸው ምክንያቶች ለአንባቢው ይናገራሉ።

8. **በነቢያት ውስጥ ያሉትን የ "ትረካ" መጻሕፍት (መጽሐፈ ኢያሱ ወልደ ነዌ፣ መጽሐፈ መሳፍንት፣ መጻሐፈ ሳሙኤል ቀዳማዊ፣ መጽሐፈ ሳሙኤል ካልዕ፣ መጽሐፈ ነገሥት ቀዳማቂ፣ መጽሐፈ ነገሥት ካልዕ) በጊዜ ቅደም ተከተል ተቀምጠዋል።** ይህም ማለት መጻሕፍቱ በታሪክ ውስጥ በተከሰቱት ቅደም ተከተል ይገኛሉ ማለት ነው። ለምሳሌ መጽሐፈ ኢያሱ በመጽሐፈ መሳፍንት ውስጥ ከተመዘገቡት ክንውኖች በፊት ስለተፈጸሙ ክንውኖች ይናገራል። ለዚህም ነው መጽሐፈ ኢያሱ በነቢያት ውስጥ ከመሳፍንት በፊት የተደረደረው። እንደዚሁም ደግሞ መጻሐፈ መሳፍንት፣ ከመጻሐፈ ሳሙኤል ቀዳማዊና መጽሐፈ ሳሙኤል ካልዕ በፊት ተቀምጧል ምክንያቱም መጽሐፈ መሳፍንት ከመጽሐፈ ሳሙኤል ቀዳማዊና መጽሐፈ ሳሙኤል ካልዕ ውስጥ ተመዝግበው ከሚገኙት ክንውኖች በፊት ስለተፈጸሙ ታሪኮች ስለሚናገር ነው። እንደዚሁም ደግሞ መጻሐፈ ሳሙኤል ቀዳማዊና መጽሐፈ ሳሙኤል ካልዕ ከመጽሐፈ ነገሥት ቀዳማቂና ከመጽሐፈ ነገሥት ካልዕ በፊት ተደርድሯል ምክንያቱም በመጻሐፈ ሳሙኤል ቀዳማዊና መጽሐፈ ሳሙኤል ካልዕ፤ የተጻፉት ክንውኖች ከመጽሐፈ ነገሥት ቀዳማቂና ከመጽሐፈ ነገሥት ካልዕ በፊት የተፈጸሙ በመሆናቸው ነው።

9. **በነቢያት መጻሕፍትም (መጽሐፈ ኢያሱ፣ መጽሐፈ መሳፍንት፣ መጽሐፈ ሳሙኤል ቀዳማዊ፣ መጽሐፈ ሳሙኤል ካልዕ ፣መጽሐፈ ነገሥት ቀዳማቂ፣ መጽሐፈ ነገሥት ካልዕ) ውስጥ ባሉት "ትረካዎች" የተመዘገቡት ክንውኖች በጊዜ ቅደም ተከተል ተቀምጠዋል።** ለምሳሌ ያህል በኢያሱ

ምዕራፍ 4 ላይ የተከናውኑት ነገሮች የተፈጸሙት በኢያሱ ምዕራፍ 3 ላይ ከተመዘገቡት ክንውኖች በኋላ ነው። እንደዚሁም በመጽሐፈ ሳሙኤል ቀዳማዊ ምዕራፍ 1 ላይ የተፈጸሙት ድርጊቶች የተከናወኑት ከመጽሐፈ ሳሙኤል ቀዳማዊ ምዕራፍ 2 እና ሌሎችም ሁኔታዎች በፊት ነው። እንደዚሁ እያለ ይቀጥላል።

10. በነቢያት ውስጥ ያሉትን የ "ስብከት" ወይም የማብራሪያ መጻሕፍት (ትንቢተ ኤርምያስ፣ ትንቢተ ሕዝቅኤል፣ ትንቢተ ኢሳይያስ፣ ትንቢተ ሆሴዕ፣ ትንቢተ ኢዩኤል፣ ትንቢተ አሞጽ፣ትንቢተ አብድዩ፣ ትንቢተ ዮናስ፣ ትንቢተ ሚኪያስ፣ ትንቢተ ናሆም፣ ትንቢተ ዕንባቆም፣ ትንቢተ ሶፎንያስ፣ ትንቢተ ሐጌ፣ ትንቢተ ዘካሪያስ፣ ትንቢተ ሚልክያስ) በጊዜ ቅደም ተከተል የተደረደሩ አይደሉም። ይህ ማለት የመጽሐፍ ቅዱስን ግለሰባዊ ጽሑፎች አንድ ላይ ያደረጉ አርታኢዎች ወይም አዘጋጆች እነዚህን ልዩ መጻሕፍት በተጻፉበት ቅደም ተከተል መሠረት ለማዘጋጀት የተለየ መንገድ መርጠዋል ማለት ነው። እነዚህ መጽሐፍት ደግሞ እንዴት እንደ ተያያዙ ማወቅ ለሰባኪው ደስታ ነው።

11. በነቢያት ውስጥ የተካተቱት (ትንቢተ ኤርምያስ፣ ትንቢተ ሕዝቅኤል፣ ትንቢተ ኢሳይያስ፣ ትንቢተ ሆሴዕ፣ ትንቢተ ኢዩኤል፣ ትንቢተ አሞጽ፣ ትንቢተ አብድዩ፣ ትንቢተ ዮናስ፣ ትንቢተ ሚኪያስ፣ ትንቢተ ናሆም፣ ትንቢተ ዕንባቆም፣ ትንቢተ ሶፎንያስ፣ ትንቢተ ሐጌ፣ ትንቢተ ዘካሪያስ፣ ትንቢተ ሚልክያስ) የ "ስብከት" (ወይም ማብራሪያ) መጻሕፍት ውስጥ የተጻፈው መልዕክት ብዙ ጊዜ የሚጠቀስ ነው፤ ይሁን እንጂ በጊዜ ቅደም ተከተል የተቀመጠ አይደለም። እንደገና ለማስታውስ ያህል በእነዚህ መጻሕፍት ወስጥ ያሉትን ጽሑፎች እንደ ስብከቶች ናቸው። ልክ እንደ አንድ መጋቢ የሕዝቡን ፍላጎት መሠረት በማድረግ በየሳምንቱ ስብከቱን እንደሚቀይር ሁሉ የነቢያት "ስብከቶች" በአንባቢዎች ላይ ከፍተኛ ተጽዕኖ እንዲያሳድሩ ተደርገው ይደረደራሉ። ከዚህ አንጻር ስንገመግማቸው መልዕክቶቹ በርዕስ የተደረደሩ ይመስላሉ። ይህ ዓይነቱ ሁኔታ አንዳንድ ጊዜ የነቢያት ክፍል መጽሐፍት ለመረዳት ለአንባቢዎች አስቸጋሪ የሆነበትን ምክንያት ያብራራል። አንባቢው ምናልባት በጊዜ ቅደም ተከተል እንዲቀመጡ ይመኝ ይሆናል። ይሁን እንጂ የነቢያት መልዕክቶች ታሪክ አይደሉም። ነገረ ግን መልዕክቶቹ የበለጠ እንደ ስብከት ወይም ማብራሪያ ናቸውና።

12. ሆሴዕ "ከአሥራ ሁለቱ መጽሐፍ" ውስጥ የመጀመሪያው ነው። የአሥራ ሁለቱ መጽሕፍት በትናንሽ ነቢያት የተጻፉ የመጽሐፍት ስብስብ ነው። ትናንሽ ነቢያት የተባሉበት ምክንያት "

ከዋንኞቹ ነቢያት” (ከኤርምያስ፣ ሕዝቅኤል፣ እና ከኢሳይያስ) በመጠናቸው ያነሱ በመሆናቸው ነው። የዕብራይስጥ መጽሐፍ ቅዱስ አዘጋጆች አሥራ ሁለቱን ትናንሽ ነቢያት በአንድነት ጠቅልለው፣ ይህንን የመጻሕፍት ስብስብ “የአሥራ ሁለቱ መጽሐፍ” ወይም “አሥራ ሁለቱ” በማለት ሰይመዋቸዋል።

እነዚህ አሥራ ሁለቱ መጽሐፍት በይዘት ላይ ተመስርተው የተደረደሩ ይመስላል። ለምሳሌ ትንቢተ ኢዩኤል ትንቢቱን ሊያጠናቅቅ ሲል በኢዩኤል 3፡16 “እግዚአብሔርም በጽዮን ሆኖ ድምፁን ከፍ አድርጎ ይጮኻል በኢየሩሳሌምም ሆኖ ቃሉን ይሰጣል” ይላል። የሚቀጥለው መጽሐፍ ማለትም ትንቢተ አሞጽም በተመሳሳይ መንገድ ይጀምራል፡- “እግዚአብሔር በጽዮን ሆኖ ድምፁን ከፍ አድርጎ ይጮኻል በኢየሩሳሌምም ሆኖ ቃሉን ይሰጣል” (አሞጽ 1፡2)። ይህ ሁለቱንም መጽሕፍት ያገናኛል። አርታኢው ወይም አዘጋጁ ይህንን የመሳሰለ ግኑኝነት (እና ሌሎችንም) አይቷል፤ ስለዚህ መጽሐፎቹን በዚህ ምክንያት አንድ ላይ አስቀምጧቸዋል። አሞጽ የጨረሰው የእግዚአብሔር ሕዝብ ኤዶምን እንደያዙ በመጥቀስ ነው (አሞጽ 9፡12 ይመልከቱ)። አብድዩ ደግሞ ስለ ኤዶም ፍርድ መጽሐፍ ነው (አብድዩ 1፡1)። ዮናስ፣ ሚኪያስ እና ናሆም ከአሦር ጋር የተያያዙ ናቸው። ዮናስ ደግሞ በአሦር ውስጥ ትገኝ ለነበርችው ለነነዌ ስለ ተደረገላት ምሕረት ይናገራል። ሚኪያስ የሚያተኩረው በአሦር ፍርድ ላይ ሲሆን፤ ናሆም ደግሞ ስለ ነነዌ ውድቀት ይናገራል። እነዚህ ሁሉ አንድ አርታኢ መጽሐፎቹን በጥንቃቄ እንዳዘጋጀ የሚያሳይ ተጨማሪ ፍንጭ ነው።

13. ሆሴዕ ስለ ጣዖት አምልኮት ማስጠንቀቂያ የሚሰጥ መልዕክት ነው። በሆሴዕ ዘመን የነበሩት እሥራኤላውያን ብዙ አማልክቶችን ያመልኩ ነበር። ስለዚህ የሆሴዕ መልዕክት ሕዝቡ ከጣዖት አምልኮት ኃጢአት ንስሐ መግባት እንዳለባቸው ማስጠንቀቂያዎች ነበሩ። የሆሴዕ ቃል በዘመኑ ለነበሩት ሰዎች የታለመ ነበር። ይሁን እንጂ የሆሴዕ መልዕክት በዛሬውም ጊዜ ለሚኖሩ ሰዎች ተግባራዊ ማስጠንቀቂያ ነው። እግዚአብሔር ቀናተኛ አምላክ ነውና። እሱ የትኛውንም ተቀናቃኞችን አይታገሥም። እሥራኤላውያን ብዙ ጊዜ ያህዌንና ጣዖታትን ያምልኩ እንደነበር ማወቅ አስፈላጊ ነው። ይህ የዕምነት መቀላቀል አንዳንዴ ሲንክሪትዝም ይባላል። በእውነተኛ አምላክ ላይ ያለውን ትንሽ እምነት በሐሰት አማልክቶች ላይ ካለው ትንሽ እምነት ጋር ማጣመር ማለት ነው። ይህ በመሰረቱ ሌላ አዲስ ሃይማኖት ይፈጥራል። ይህ ዓይነቱ “አምልኮ” በሆሴዕ ዘመን ተቀባይነት አላገኘም ነበር፤ ዛሬም ቢሆን ተቀባይነት የለውም። ትንቢተ ሆሴዕ ለእንዲህ

ዓይንቱ በማደባለቅ ለሚደረግ አምልኮት ማስጠንቀቂያ የሚሰጥ ነው። እንደገና ለማስታውስ ያህል እግዚአብሔር በእርግጥ ቀናተኛ አምላክ ነው። ክብሩን ከሌላ "አማልክት" ጋር አይካፈልምና።

በሆሴዕ ዘመን የእሥራኤል ሕዝብ ባአል በመባል የሚታወቀውን አማልክት ያመልኩ ነበር። ባአልን ማምለክ ደግሞ በተወሰነ ደረጃም ቢሆን ከሴተኛ አዳሪዎች ጋር የዝሙት ድርጊቶችን ከሚፈጽሙ ሰዎችን የሚያጠቃልል ነው። እነዚህ ህገወጥ የፆታ ግኙኝነት ይፈጸሙ የነበረው ባአል ከአናት (ባአል ያገባት ሴት አምላክ ማለት ነው) ጋር ተመሳሳይ ነገር በማድረግ ለእነዚህ ድርጊቶች ምላሽ ይሰጣል ተብሎ ስለሚታመን ነበር። ስለዚህ በምድር ላይ የሚደረገው የሰው ልጆች ግብረሥጋ ግኙኝነት አማልክቶች በሰማይ ውስጥ የግብረ ሥጋ ግኙኝነት እንዲፈጽሙ ያነሳሳቸዋል፤ ይህም ደግሞ ተስማሚ የአየር ጸባይ እና የግብርና ብልጽግና ያስገኛል ተብሎ ይታምን ስለነበር ነው። ስለ ባአል የተነገሩ አያሌ ቁጥር ያላቸው ጥንታዊ ታሪኮች ተገኝቷል። ከእነዚህም አንዳንዶቹ ታሪኮች የባአልን ከያም ከባሕር አምላክ ጋር ያደረገውን ጦርነት ይዘረዝራሉ። አንዳንዶቹ ታሪኮች ደግሞ በበጋ ወቅት ድርቅን ያመጣል ተብሎ ከሚታመነው አምላክ ከሞት ጋር ያደርገውን ጦርነት ይተርካሉ። በእነዚህ ታሪኮች መሠረት የባአል ዋንኛ ረዳት የሆነችው አናት የትባለች ሴት አምላክ እሷም የፆታ ግኙኝነት የፈጸምባት ሴት ነች። ደግሞም አናት የባአል እህቱም ሚስቱም ነበረች።

ያህዌ ወይም እግዚአብሔር የእስራኤልን "ድብልቅ" አምልኮት አይቀበልም ነበር። በአንድ ጊዜ በባአል መታመን እና በግዚአብሔርም መታመን ፈጽሞ የማይቻል ነገር ነበርና። እግዚአብሔር የእሥራኤል ባል ሆኖ ሚስቱን ለመንከባከብ ቃል ገብቶ ነበርና። ይህም ከእርሷ (ማለትም ከእሥራኤል) ጋር የገባው ኪዳን አካል ነበር። እሷ ማለት እሥራኤል ግን የእግዚአብሔር ሚስት እንደመሆኗ መጠን በእግዚአብሔር እንክብካቤ ላይ እምነት አልነበራትም። ነገር ግን ምግብና መጠጥዋ እንደዚሁም መጽናናትዋም ከባአል የሚመጣ መስሏት ነበር። ስለዚህ እሥራኤል ለባአል ባላት ታማኝነት የተነሳ እግዚአብሔርን እንደ ጥሩ ባል እንደ ማትቆጥረው አስመስክራለች።

14. ሆሴዕ ሰዎችን ወደ እምነት እየጠራ ነው። የትንቢተ ሆሴዕ ሙሉውን መልዕክት ስንመለከት ሆሴዕ ሕዝቡ ለእግዚአብሔር በእምነት ምላሽ እንዲሰጥ ይጠራል። እውነተኛ መጽሕፍ ቅዱሳዊ እምነት እግዚአብሔር የተናገረውን እውነት ነው ብሎ ከማመን የዘለለ ነው። እውነተኛ መጽሕፍ ቅዱሳዊ እመነት ተግባራዊነትንም ያካተተ ነውና። ነቢዩ ሆሴዕ ሰዎች የእግዚአብሔርን ቃል እንዲሰሙ፣ እግዚአብሔር የተናገረውንም እውነት እንዲያምኑ፣ ከጣዖት አምልኮት ንስሐ እንዲገቡ እና

የእግዚአብሔርን ቃል ሁሉ በመታዘዝ እንዲሄዱ ይጠራ ነበር (ለምሳሌ ሆሴዕ 6፡1–3 እና 14፡1–3 ይመልከቱ)። በሆሴዕ ውስጥ ያሉትን የመጨርሻው ጥቅስ የመጽሐፉ ዓላማ “ጥበበኞችን” ወደ እውቀትና ታዛዥነት መጥራት እንደሆነ ያሳያል፡- “ይህን ነገር የሚያስተውል ጠቢብ የሚያውቃትም አስተዋይ ማን ነው? የእግዚአብሔር መንገድ ቅን ነው ጻድቃንም ይሄዱባታል ተላላፊዎች ግን ይወድቁባታል” ይላል (ሆሴዕ 14፡9 ይመልከቱ)። እነዚህ ስዎች ጥበበኞች እና ታዛዦች እንዲሆኑ የሚጠሩት የሆሴዕ መልዕክት የመጀመሪያ ጊዜ አድማጮች ለነበሩት ብቻ አይደለም። ነገር ግን የሆሴዕን መልዕክት ለሚሰሙ ሁሉ ነው እንጂ። ስለዚህ እኛም እንደ ሆሴዕ መጀምሪያ ተደራሲዎች የሆሴዕን መልዕክት ሰምተን ለሆሴዕ መልዕክት በእምነት ምላሽ መስጠት ይኖርብናል ማለት ነው።

15. **በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ያለው ትንቢት ብዙ ጊዜ ለአንባቢው በግጥም መልክ ይቀርባል።** ይህም በትንቢተ ሆሴዕ ውስጥ እውነት ነው። በመጽሐፉ ውስጥ ካሉት ጥቂት የትረካ ክፍሎች በስተቀር (ሆሴዕ 1 እና 3 ይመልከቱ) ሆሴዕ ሙሉ በሙሉ የተጻፈው በግጥም መልክ ነው። ይህ ለአንባቢና ለሰባኪ ወይም ለአስተማሪ ታላቅ ስጦታ ነው።

ከትረካ ቀጥሎ (በታሪክ መልክ የቀረበ የጽሑፍ ዓይነት ማለት ነው) ግጥም በብሉይ ኪዳን ውስጥ በጣም የተለመደ የአጻጻፍ ስልት ነው። ኢዮብ፣ መዝሙረ ዳዊት፣ ምሳሌ፣ መክብብ፣ መኃልየ መኃልይ፣ ኢሳይያስ፣ ኤርምያስ፣ ሰቆቃው ኤርምያስ፣ ሕዝቅኤል፣ ዳናኤል፣ ሆሴዕ፣ ኢዩኤል፣ አሞጽ፣ አብድዩ፣ ዮናስ፣ ሚክያስ፣ናሆም፣ ዕንባቆም፣ ሶፎንያስ እና ዘካሪያስ ሁሉም ጥሩ ግጥሞችን ያካትታሉ። ግጥም በሌሎችም የብሉይ ኪዳን መጽሐፍት ተበታትኖ ይገኛል (ዘጸአት 15፡1–18 ይመልከቱ)። ከዚህ ባሻገር በብሉይ ኪዳን ውስጥ ያሉ ብዙዎቹ ግጥሞች በአዲስ ኪዳን ውስጥ ተጠቅሰዋል (የሐዋሪያት ሥራ 28፡26–27 ይመልከቱ)። ስለዚህ ለሰባኪ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ቅኔዎችን ማወቅ፣ መረዳትና መተግበር መቻል አስፈላጊ ነገር ነው።

መጽሐፍ ቅዱሳዊ ቅኔ ልዩ የሆኑ ቃላትን እና የቃላት ዘይቤዎችን ስለሚጠቀም አንባቢው በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ያሉትን ግጥሞች በቀላሉ ማወቅና መማር ይችላል። በብሉይ ኪዳን የሚገኘው ቅኔ በእንግሊዝኛ ቋንቋ ከሚታወቀው የግጥም ዓይነት የተለየ ነው። በአብዛኛው ግጥም አይደለም። ነገር ግን በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ያለው ግጥም በጥቅስ ትይዩ በሚባለው የግጥም መልክ ተጽፏል። ትይዩነት አንድ መስመር አንድ ነገር የሚናገርበት መዋቅር ሲሆን በኋላ ያለው

መስመር ወዲያው ሀሳቡን ከመጀመሪያው መስመር በመቀበል ይደግመዋል እና የተለያዩ ቃላትን በመጠቀም ሀሳቡን በሆነ መንገድ ያጠናከረዋል ማለት ነው። ይህ በትይዩ ከተቀመጡት ሁለት የባቡር ሀዲዶች ጋር ተመሳሳይ ነው። አንዳቸው ለሌላው (አንዳንድ ጊዜ ሦስት መግለጫዎች እርስ በርሳቸው ትይዩ ናቸው)። በባቡር ሀዲዱ ውስጥ ያለው ሁለተኛው ሀዲድ ከመጀመሪያው ሀዲድ በተሻለ ሁኔታ ጠንካራ እንደሆነ ያስቡ። እንግዲህ ትይዩነት የሚሠራው በዚህ መንገድ ነው።

ስለ ትይዩነት የሚያስቡበት ሌላው መንገድ እንደ ገደል ማሚቶ ነው። ሁለተኛው መስመር የመጀመሪያውን መስመር የሚያስተጋባ እንደ ገደል መሚቶ ነው። ነገር ግን በተለመደው ማሚቶ አንድ ሰው የሆነ ነገር ብሎ ሲጮኽ ምላሽ የሚሰጠው የሚያስተጋባው የገደል ማሚቶ ተመሳሳይ ነገር ነው። በመጽሐፍ ቅዱሳዊ ግጥም የገድል ማሚቶው ትንሽ ሊቀየር ይችላል! ይሁን እንጂ ከሞላ ጎደል ተመሳሳይ ነው። ነገር ግን የሚታዩ ልዩነቶች ቢኖሩም የመጀመሪያው መስመር በሁለተኛው መስመር በእርግጥ ይስተጋባል።

ለምሳሌ ከመዝሙራት አንዱ የመጽሐፍ ቅዱስ ቅኔ እንመልከት። ሁለተኛው መስመር በመጀመሪያው መስመር ላይ የተገኙትን ሃሳቦች እንዴት እንደሚደግም ደግሞም ይህን ለማድረግ ጠንከር ያሉ ቃላትን እንደሚጠቀም ያስተውሉ።

> *አቤቱ በቁጣህ አትቅሠፈኝ*
> *በመዓትህም አትገሥጸኝ!* መዝሙር 38፡ 1

አሁንም ለማስታውስ፤ ያህል ልክ እንደ ሁለት የባቡር ሀዲዶች ትይዩ እንደሆኑ፤ ሁለተኛው መስመር ከመጀመሪያው መስመር ጋር ትይዩ ነው። ይህም ጥቅም ላይ በሚውሉት ቃላት ውስጥ ሊታይ ይችላል። እርስበርሳቸው ይመሳሰላሉ። በመጀመሪያው መስመር ላይ “አትቅሠፈኝ” የሚለው ቃል በሁለተኛው መስመር ላይ “አትገሥጸኝ” ከሚለው ቃል ጋር ይመሳሰላል። ልብ ብለን ስንመለከት ሁለቱም የግጥም መስመሮች እንደ ባቡር ሀዲዶች ናቸው፤ እርስ በእርሳቸውም ትይዩ ናቸው ነገር ግን “ሁለተኛው የባቡሩ ሀዲድ” ከመጀመሪይው የባቡር ሀዲድ የበለጠ ጠንካራ ሆኖ ይታያል። እንደዚሁም በመዝሙር 38፡1 መስመር ሁለት ላይ ያለው “አትገሥጸኝ” የሚለው ቃል በመስመር አንድ “አትቅሠፈኝ” ከሚለው ጋር ተመሳሳይ እንደሆነ ሁሉ፤ በመስመር ሁለት ላይ ያለው “በመዓትህም” የሚለው ደግሞ በመስመር አንድ ላይ ካለው “በቁጣህ” ከሚለው ቃል ጋር ተመሳሳይ ነው። ነገር ግን በትይዩነት እንደሚጠበቀውም “በመዓትህ” የሚለው ቃል “በቁጣህ”

ከሚለው ቃል ጋር ቢመሳሰልም “በመዓትህ” የሚለው ቃል ግን “በቁጣህ” ከሚለው የበለጠ ጠንካራ ነው።

በሆሴዕ 6፡2 ላይ ደግሞ ሌላ ተመሳሳይነት ያለውን ምሳሌ እንመልከት፡-

*ከሁለት ቀን በኋላ ያድነናል፤*

*በሦስተኛውም ቀን ያስነሣናል፤ በፊቱም በሕይወት እንኖራለን።*

በሁለተኛው መስመር የተጠቀሰው “ሦስት” ቁጠር በመጀመሪያው መስመር ከተጠቀሰው “ሁለት” ቁጥር እንዴት እንደሚበልጥ ልብ ይበሉ። እንዲህ ዓይነቱ የቁጥሮች አጠቃቀም በትይዩ የተለመደ ነው። ሁለተኛው ከመጀመሪያው ይበልጣልና። ለዚህም ይመስላል በመጽሐፈ ምሳሌ ተመሳሳይ ነገር የሚታየው፤ “እግዚአብሔር የሚጠላቸው ስድስት ነገሮች ናቸው፤ ሰባትንም ነፍሱ አጥብቃ ትጸየፈዋለች፤” (ምሳሌ 6፡16)። እግዚአብሔር የሚጠላቸው ስድስት ወይም ሰባት ነገሮች እንደሆኑ ግራ አያጋባም። ይልቁንም ይህ ጥንታዊ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ቅኔ ነው። ሁለተኛው መስመር ከመጀምሪያው መስመር ጋር ትይዩ ነው፤ ነገር ግን የመጀመሪያው መስመር በሆነ መንገድ ያጠናክረዋል። (እንደዚሁም ደግሞ እግዚአብሔር “በሚጠላውና” በእርሱ ዘንድ “አስጸያፊ” በሆነ ነገር መካከል ያለውን ልዩነት ያሳያል። ስለዚህ ሁለተኛው መግለጫ የበለጠ ጠንካራ ነው።)

እግዚአብሔር ነቢያትን በቅኔ ላይ በጣም እንዲታመኑ ለምን አነሳሳቸው? ለዚህ ጥያቄ ምናልባትም ብዙ መልሶች ሊኖሩ ይችላሉ? ምናልባት አንደኛው መልስ የነቢያት መልዕክት በባሕሪው የቅኔ አነጋገር የሚፈልግ በመሆኑ ሊሆን ይችላል። ሰዎች የነቢያትን መልዕክት አይሰሙም ነበርና። ይህም ደግሞ እግዚአብሔርም አይሰሙም ነበር ማለት ነው! የትይዩ አካል የሆነው የማያቋርጥ ድግግሞሽ በተለይም አንድን ነጥብ ለማጉላት በጣም ተስማሚ ነው። ዋና ዋና ነጥቦቹ በመደጋገም በጠንካራ ቃላት ይነገራሉ እና እንደገና ተደግመው ይነገራሉ። ሌላው ምክንያት ሊሆን የሚችለው ግጥም ከመደበኛ ንግግር ይልቅ አስደንጋጭ የሆኑ ቃላትን ይጠቀማል። ስለዚህ የቃላቶቹ አስደንጋጭ ተፈጥሮ ግጥሞችን ችላ ለማለት አስቸጋሪ ያደርገዋል። የመጨረሻው ምክንያት ደግሞ የመጽሕፍ ቅዱስ ቅኔ ወይም ግጥም ቃላት የማይረሱ በመሆናቸው ነው። ስለዚህ ብዙ ሰው ማንባብ በማይችልበት ዘመን የነቢያት መልዕክት ሕዝቡ ሊደጋግመውና ሊያስታውሰው በሚችለው መልኩ ይመጣ ነበር።

16. ነቢያት ቋንቋን የሚጠቀሙት አንባቢዎችን ለማስደንግጥ በታሰበ መንገድ ነበር። ሕዝቡ “በተለመደ” የቃላት አጠቃቀም ስለማይሰማ ስለዚህ ነቢያት በመደበኛነት የሚጠቀሙባቸው

በጣም ጠንካራ ቃላት ምክንያታዊ መሆናቸውን መረዳት ይቻላል። ሕዝቡ “የተለመደ” ቃላትን ስለማይሰሙ ነቢያት መልዕክታቸውን ለማስተላለፍ ጠንከር ያሉ ቃላትን ለመጠቀም ይገደዱ ነበር። ለምሳሌ ያህል የእሥራኤል ሕዝብ ጣዖትን ያመልኩ ነበር። ስለዚህም ኃጢአት በተደጋጋሚ ማስጠንቀቂያ ተሰጥቷቸውም ነበር። ነቢዩ ሆሴዕም ስለ ጣዖት አምልኮት እንዲያስጠነቅቃቸው እና ንስሐም እንዲገቡ እንዲለምናቸው ተልኮ ነበር። ሆሴዕ በተወሰነም መልኩ ቢሆን ለእሥራኤል የመጨረሻ ተስፋ ነበር። ነገር ግን እሥራኤላዎያን በሙሴ መጽሐፍ ውስጥ እንደ ተጻፈላቸው የእግዚአብሔርን ቃል ለረጅም አመታት ለመስማት ፈቃደኞች አልነበሩም። እንደዚሁም እሥራኤላውያን በቀደሙት ነቢያት በኩል ወደ እነርሱ የመጣውንም የእግዚአብሔርን ቃል ለመስማት ፈቃደኞች አልነበሩም። ለዚህም ሊሆን ይችላል ነቢዩ ሆሴዕ ችላ ሊባሉ በማይቻሉ ቃላት ተጠቅሞ ለመናገር የተገደደው። ሆሴዕ በቀላሉ “ከጣዖት አምልኮት ተመለሱ” ማለት ይችል ነበር።ይህንንም ጥሪው የእግዚአብሔር ፀጋ ሆኖ ባዳናቸው ነበር። ይሁን እንጂ ሆሴዕ ግን ለእሥራኤል ስለ ጣዖት አምልኮታቸው ሲናገር እነዚህን በመሳሰሉ “የተለመዱ” ቃላት በዘፈቀደ አይጠቀምም። እንደዛ ቢሆን ኖሮ እሥራኤል የነቢዩ ሆሴዕ መልዕክት ባልሰማችም ነበር። ይልቁንም ሆሴዕ የሕዝቡን ድርጊት ከጣዖት አምልኮ የበለጠ አስከፊ መሆኑን ለመግለጽ አንድ አስደንጋጭ ቃል ይጠቀማል። ሕዝቡ ምንዝርና እንደሚያደርግ ያውጃል። ይህን የመሳሰሉት ቃላት እና ሌሎችም ሆሴዕ የተጠቀመባቸው ብዙ ቃላት የሕዝቡን ቀልብ እንደሚስቡ ምንም ጥርጥር የለውም!

እስቲ የእሥራኤልን የጣዖት አምልኮት የሚገልጹትን የሚከተለውን በግጥም የተቀመጠውን ጥቅስ ይመልከቱ። ደግሞም እርሶ በሆሴዕ ዘመን የሚኖሩ እሥራኤላዊ ቢሆኑ እነዚ ቃላት ሲሰሙ ምን ሊሰማዎት እንደሚችል ለአንድ አፍታ አሰብ ያድርጉ።

> *እናታችሁ ሚስቴ አይደለችምና፤*
> *እኔም ባልዋ አይደለሁምና፤*
> *ተሟገቱ ከእናታችሁ ጋር ተሟገቱ።*
> *ግልሙትናዋን ከፊትዋ፤*
> *ምንዝርናዋንም ከጡቶችዋ መካከል ታስወግድ. . . ፤*
> **ሆሴዕ 2፡ 4** *(ይህ ጥቅስ በእንግሊዝኛ መጽሐፍ ቅዱስ ቁጥር 2 ላይ ነው የተጠቀሰው)*

እዚህ ጋ ሆሴዕ እሥራኤልን እንደ ጋለሞታ እየገለጻት ነው! የዚህን ግጥም ክብደት ለመረዳት እስቲ አንድ ሰው እናቶትትን በዚህ መልኩ እንደሚገልጣት ያስቡ! ስለዚህ ሕዝቡ በእንደዚህ ዓይነት መልኩ የሚናገሩትን ነቢያት ለመግደል መፈለጋቸው አያስደንቅም። የነቢያቱ ጠንካራ ቃል ሕዝቡ የእግዚአብሔርን ቃል እንዲሰሙ በጥልቅት ለመቁረጥ የታለመ ነበር። እግዚአብሔር ራሱ ነቢያትን ሲልክ እንድዚሁ ያደርግ እንደ ነበር ተናግሯል። እስቲ ቀጥሎ የተጠቀሰውን ግጥም ይመለከቱ (ይህ የሦስት መስመሮች ግጥም ምሳሌ ነው ደግሞ አንዱ ከሌላው ጋር ትይዩ ነው)።

*ስለዚህ በነቢያት እጅ ቆረጥኋቸው፤*

*በአፌም ቃል ገደልኋቸው፤*

*ፍርዴም እንደ ብርሃን ይወጣል።* ሆሴዕ 6፡5

በሆሴዕ ዘመን ይኖሩ የነበሩት ሰዎች እነዚህን ጠንካራ ቃላት መስማት ያስፈልጋቸው ነበር፤ እንደዚሁም በዚህም ዘመን የሚኖሩ ሰዎች እነዚህን የመሳሰሉ ጠንካራ ቃላት መስማት ያስፈልጋቸዋል። እነዚህን ጠንካራ ቋንቋ በሆሴዕ ዘመን ይኖሩ ለነበሩት ሰዎች ጥቅም ብቻ እንዳልነበር ልብ ማለት ጠቃሚ ነው። በዚህም ዘመን ቢሆን ሰዎች እንዚህን ተመሳሳይ ቃላት መስማት አላባቸው። ብዙውን ጊዜ ከድንጋጤና ከግድየለሽነት ልንወጣ ይገባናል! የነቢያት ቃል ከእግዚአብሔር ከራሱ የሚመጣ ነውና። ይህን ሕዝብ የእግዚአብሔርን መልካም ቃል እንዲሰማ፣ ንስሐም እንዲገባ እና ለቃሉም በመታዘዝ እንዲራመዱ የሕዝቡን ትኩረት ለመሳብ በጥንቃቄ ተመርጦ የሚመጣ ነበርና (ዕብራውያን 4፡12 ይመልከቱ)።

17. **የነቢዩ ዋና አገልግሎት በእሱ ዘመን በሕይወት ለነበሩት ብቻ አልነበረም። ይልቁንም ከነቢዩ ዘመን በኋላ ለሚኖሩት ነበር እንጂ።** የነቢያት አንዱ ሥራ በእነሱ ትውልድ ዘመን ለሚኖሩትን ሰዎች በኃጢአታቸው ምክንያት ስለሚመጣባቸው ፍርድ ማስጠንቀቅ ነበር። ስለዚህም ሆሴዕ በእግዚአብብሔር የተጠራው በእሱም የሕይወት ዘመን ለሚኖሩት ሰዎችም ነበር። ነገር ግን ሆሴዕ በሕይወት በነበረበት ጊዜ የሰሙት ቢበዛ ጥቂት ሺህ ሰዎች ብቻ ሊሆኑ እንደሚችል ያስቡ። ሆኖም ግን በእሥራኤል ውስጥ ሆሴዕ ለሕዝቡ የነበረውን አገልግሎት ከጀመረበት አንስቶ በሺዎች በሚቆጠሩ አማታት ውስጥ በሚሊዮን የሚቆጠሩ ሰዎች የሆሴዕን ቃል ሰምተዋል። ስለዚህ ከዚህ እውነታ እንኳን በመነሳት ብቻ ብናስብ የሆሴዕ አገልግሎት ከፍተኛ ተጽዕኖ በዘመኑ በነበሩት ሰዎች ላይ እንዳልነበር ግልጽ ነው። ይልቁንስ ከሱ በኋላ ለሚኖሩት ሰዎች (እኛንም ተጨምሮ) ማለት ነው! የዛሬ የሆሴዕ አንባቢዎች ሆሴዕ ለእሥራኤል ሕዝብ አገልግሎቱን ባከናወነበት ወቅት ከሰሙት ሰዎች በጣም የተለዩ ናቸው። ሆሴዕ በሚያገለግልበት ዘመን ይሰሙት ከነበሩቱ ሰዎች

የሰሙት ትንቢት ከመፈጸሙ በፊት በሕይወት የኖሩ ናቸው። እደዚሁም የሰሜናዊው የእሥራኤል መንግሥት ገና አልፈራረሰም ነበር፤ ማለትም የእሥራኤል ሕዝብ ገና አልተበተነም ነበርና። ከሁሉም በላይ ደግሞ ክርስቶስ ገና አልመጣም ነበር። ነገር ግን በዚህ ዘመን ያለን አንባቢዎች በዚህ ሁኔታ ውስጥ አይደለንም። እንግዲህ ሆሴዕ የተናገረው ነገር አስቀድሞ ተፈጽሟል። ስለዚህ የዚህ ዘመን አንባቢዎች ነቢዩ ሆሴዕ የተነበያቸው ነገሮች መፈጸማቸውን እያወቁ ወደ ኋላ እየተመለከቱ ነው የሚያነቡት ማለት ነው። ይህም ደግሞ በእግዚአብሔር ሕዝብ ላይ እምነትን የሚጨምር ጉዳይ ሊሆን ይገባል። ደግሞም ሆሴዕ ስለ እሥራኤል የተናገረው ቃል የተፈጸመ ከሆነ፤ ይህም ለእግዚአብሔር ሕዝብ ሁሉም የእግዚአብሔር ቃል በእርግጥ እንደሚፈጸም ታላቅ እምነት ሊፈጥርላቸው ይገባል! እንደዚሁም ታላቅ ፈሪሃ እግዚአብሔርም እንዲኖርን ማድረግ ይኖርበታል። እንግዲህ በዚህ ክፍል እግዚአብሔር አምላክ የገባውን ቃል እንደ ጠበቀና ሕዝቡ ግን ሌሎች አማልክቶችን ሲያመልኩ ደግሞ እንዳልራራላቸው ለማየት ችለናል። ስለዚህ እኛም ለሌሎች አማልክት ብንሰግድ እንደማይራራልን እንድናውቅ ሊያስጠነቅቀን ይገባል።

እንደገና ለማስታውስ ያህል ነቢያቱ ይናገሩ የነበሩት በራሳቸው ትውልድ ውስጥ የሚኖሩትን ለመርዳት ብቻ አልነበርም። እነደዚሁም የትንቢት መልዕክቶቻቸው ከተፈጸመም ከብዙ ጊዜ በኋላ ለሚኖሩም ሕዝቦች እንደሚጠቅምም ያውቁ ነበር። ሆሴዕ ዋና አድማጮቹ ወደፊት የሚኖሩት እንደሆነ ያውቅ ነበር። እስቲ የሚከተሉትን የ 1 ጴጥሮስ ጥቅሶች ይመለከቱ። ሐዋሪያው ጴጥሮስ ነቢያት ማለትም ሆሴዕም ጨምሮ እኛን እንደሚያገለግሉን ያውቁ እንደነበር ተናግሯል። ደግሞም ነቢያት በክርስቶስ ስለሚመጣው የእግዚአብሔር ጸጋ ትንቢት እየተናገሩ መሆናቸውን ያውቁ ነበር፤ እና መልዕክቶቻቸው ወደፊት ለሚኖሩ ሰዎች እንደሚጠቅም ያውቁ ነበር ማለት ነው።

> ለእናንተ ስለሚመጣው ጸጋ ትንቢት የተናገሩት ነቢያት ስለዚህ መዳን ተግተው እየፈለጉ መረመሩት፤ በእነርሱም የነበረ የክርስቶስ መንፈስ ስለ ክርስቶስ መከራ ከእርሱ በኋላ ስለሚመጣው ክብር አስቀድሞ እየመሰከረ በምን ወይም እንዴት ባለ ዘመን እንዳመለከተ ይመረምሩ ነበር።ለእነርሱም ከሰማይ በተላከ በመንፈስ ቅዱስ ወንጌልን የሰበኩላችሁ ሰዎች አሁን ባወሩላችሁ ነገር እናንተን እንጂ ራሳቸውን እንዳላገለገሉ ተገለጠላቸው፤ ይህንም ነገር መላዕክቱ ሊመለከቱ ይመኛሉ። 1 ጴጥሮስ 1፡ 10–12።

ስለዚህ ዛሬ የሆሴዕን ትንቢት አንባቢዎች እንደመሆናችን መጠን እነዚህን ቃላቶች ለእኛ እንደተጻፈ ቃል እንድንሰማው መጠንቀቅ አለብን። ለጥንቶቹ እሥራኤላውያን ብቻ የሚመለከት አልነበረምና።

18. **መጽሐፈ ነገሥት ካልዕ ከሆሴዕ ጋር በማዛመድ ማንበብ ትልቅ እገዛ ይሰጣል።** መጽሐፈ ነገሥት ካልዕ ሆሴዕ በኖረበትና ትንቢት በተናገረበት ዘመን የእሥራኤልና የይሁዳን ታሪክ አካቶ የያዘ መጽሐፍ ነው። በመጽሐፈ ነገሥት ካልዕ ያለውን ትረካ በሆሴዕ ውስጥ ከሚገኘው ቅኔ ጋር በማጣመር አንባቢው በሆሴዕ የሚገኙትን የቃላት አጠቃቀም ዳራ መገንዘብ ይችላል። መጽሐፈ ነገሥት ካልዕ የተጻፈው በእሥራኤል ለሚኖሩ ሰዎች ነው። በዚያ ዘመን በእሥራኤል የነገሠ ንጉሥ ነበረ። ንጉሡም ኢዮርብዓም ይባል ነበር። ኢዮርብዓም ኃያል ንጉሥ የነበረ ቢሆንም ኃይሉን ግን ለበጎ ዓላማ ያዋለ ንጉሥ አልነበረም። ደግሞም ሕዝቡን ወደ ክፋት የመራ ንጉሥ ነው። ደግሞም የእሥራኤል ሕዝብም የንጉሣቸውን ክፋት በሙሉ ልብ ይከተሉ ነበር። ይሁን እንጂ የእሥራኤል አምላክ–ያህዌ (እግዚአብሔር)–የእሥራኤልን አልመታዘዝ አልታገሠም። ስለዚህ ለእሥራኤላውያን እንዲተነብይ ሆሴዕን ጠራው። የሆሴዕ መልዕክት ዋና ሀሳብ እግዚአብሔር የእሥራኤል ታማኝ አለመሆን እንደማይቀበል ማስረዳት ነበር። ስለዚህ እነደሚጠፉ ነገራቸው። ሆሴዕ እንደሚጠፉ ብቻ ሳይሆን ደግሞም ተስፋም እንዳለ ይናገራቸው ነበር። እግዚአብሔር እንደሚያጠፋቸው ቢናገርም ግን መልሶ ደግሞ እንደ ሚምራቸውም ይናገር ነበር።

19. **ዘዳግም 4፡1–31፣ 12፡1–32፣ 28፡1–68፣ እና 30፡1–20 ያሉትን ከሆሴዕ ጋር በማዛመድ ማንበብ ጠቃሚ ነው።** ሆሴዕ ለእሥራኤላውያን አዲስ ነገር እየነገራቸው አልነበረም። በሙሴ መጽሐፍም ውስጥ ስለ ጣዖት አምልኮት ማስጠንቀቂያ ተሰጥቷቸዋልና። በአለመታዘዝ ቢሄዱ ምን እንደሚሆን ተነግሮአቸው ነበር። እንደዚሁም ደግሞ በመጨረሻውም ዘመን ሊሆን ያለውን የእሥራኤልን መመለስ የእግዚአብሔርን ተስፋዎች ሰምተው ነበር። ዛሬም ሆሴዕን ለሚያነቡ ሰዎች ተመሳሳይ ነው። ትንቢተ ሆሴዕ ለዚህ ዘመን አንባቢዎች ምንም አዲስ ነገር አይናገርም ማለት ይቻላል። ሰዎች የዘዳግም መጽሐፍ ከተረዱ ሆሴዕን ደግሞ ይረዳሉ ማለት ይቻላል። ስለዚህ ከላይ ከተገለጹት የዘዳግም ምዕራፎች ጎን ለጎን ሆሴዕን ማንበብ ለሰባኪው ትልቅ እገዛ ይሆናል።

20. **የዕብራይስጥ ትንቢት ገጽታ በተደጋጋሚ በአሉታዊ እና በአዎንታዊ መግለጫዎች መካከል መቀያየር ነው።** የተወሰኑ የጥቅሶች ምድብ አሉታዊ ነው። ደግሞም እነዚህ አሉታዊ ጥቅሶች ወዲያውኑ በቡድን በሆኑ አዎንታዊ ጥቅሶች ይከተላሉ። ይህ በአሉታዊና በአዎንታዊ መግለጫዎች

መካከል ያለውን ዑደት በእብራይስጥ መጽሐፍ ቅዱስ በትንቢት መጻሕፍት ውስጥ የተለመደ ነው። በትንቢተ ሆሴዕም ውስጥ የሚታየው ሁኔታ ይኸው ነው። ለምሳሌ ሆሴዕ 1፡1–9 ያለው አሉታዊ ነው። ስለእሥራኤል ጥፋት የተነገረ ማስተንቀቂያ ነው። ደግሞም ሆሴዕ 1፡10–2፡1 አዎንታዊ ነው። ይህ ክፍል ስለ እሥራኤል እንደገና መነሳት ይናግራልና። እንደዚሁም ደግሞ በተመረጠው መሪ አማካኝነት ወደፊት የሆነ ጊዜ ስለእሥራኤል መዳን እና ታላቅ የሆነ ሙብዛት ይናገራል። ይህም ስለወንጌል ተስፋ ነው። ደግሞም ሆሴዕ 2፡2–13 አሉታዊ ነው። በሌላ በኩል ደግሞ 2፡14–23 ደግሞ አዎንታዊ ነው። ለምንድር ነው የትንቢት መጽሐፍት እንደዚህ ያለ ይዘት ያላቸው? ለምንድር ነው ሁሉም አሉታዊ ክፍሎች አንድ ላይ ያልተቀመጡት ደግሞም ለምድር ነው ሁሉም አዎንታዊ ክፍሎችስ አንድ ላይ ያልተደርጉት? ምናልባትም ይህ በአወንታዊና በአሉታዊ መካከል ያለውን ተደጋጋሚ ለውጥ በመጽሐፉ ውስጥ መልዕክቶች–አዎንታዊ እና አሉታዊ–በአዲስ ቃላት ተደጋግመው እንዲነግሩ ስለሚያስችል ይሆናል። በመጽሐፉ ውስጥ ያሉትን መልዕክቶች መደጋገም አስፈላጊ ነው፤ ምክንያቱም የእግዚአብሔር ሰዎች እነዚህን መልዕክቶች ደጋግመው መስማት ይኖርባቸዋልና። ደግሞም ለሰባኪ ወይም ለአስተማሪ በጽሑፉ ውስጥ አንጻዖት እየሰጡ ያሉትን የከበሩ ነገሮች አጽንዖት ለመስጠት ቀላል ይሆንለታል። ደግሞ በተመሳስይ መልኩ በጽሑፉ ውስጥ አጽናዖት የሚሰጡትን አስቸጋሪ ነግሮችንም በቀላሉ ለመዝለል ያስችላል። በእርግጥ ይህ መልካም ጥበብ አይደለም። ነገር ግን ጠቢብ ሰባኪ ወይም አስተማሪ በሆሴዕ ውስጥ የተገለጹትን ነገሮች በሙሉ ትኩረት ይሰጣል።

# ሆሴዕ 1፡1–9

የሆሴዕ የእሥራኤል አየገልግሎት የጀመርው በ755 ዓክልበ ነው። ሆሴዕ በኖረበት በዚያ ዘመን 12ቱ የእሥራኤል ነገዶች እንደ አንድ ሕዝብ አይቆጠሩም ነበር። ገና ሆሴዕ አገልግሎት ከመጀምሩ ከ 180 ዓመታት በፊት የእሥራኤል ሕዝብ ወደ ሁለት መንግሥታትነት ተከፉፍሎ ነበርና (ይህም በ 1 ነገሥት 12፡ 16–24 ውስጥ ተጠቅሷል)። የሰሜኑ መንግሥት አሥር ነገዶችን ያቀፈ ሲሆን እሥራኤል (ወይም አንዳንዴ ኤፍሬም) ተብሎ ይጠራ ነበር። ይሁዳ እና ብንያም ያቀፈው የደቡብ መንግሥት ደግሞ ይሁዳ ተብሎ ይጠራ ነበር። ሆሴዕ በ 722 ዓክልበ በአሦር ከመያዟ በፊት ለሰሜኑ የእሥራኤል መንግሥት ትንቢት የተናገረው የመጨረሻው ነቢይ ነው። በእሥራኤል ውስጥ የሰበከው የመጨረሻው ነቢይ በመሆኑ፣ ፍርድ ከመምጣቱ በፊት ሕዝቡ ንስሐ እንዲገባ ይጠራ የነበረ የእግዚአብሔር የመጨረሻ መልዕክተኛ ነበር። ነገር ግን እንደ አለመታደል ሆኖ ሕዝቡ ሆሴዕን አልሰማም።

ሆሴዕ ለእሥራኤላውያን ይነገራቸው የነበረው ቃል ጠቃሚ ዳራ እሥራኤላውያን የዮርዳኖስ ወንዝ ተሻግረው ወደ ተስፍይቱ ምድር ከመግባታቸው በፊት ሙሴ የተናገራቸው ቃል ነበር።

> *“እናንተን ግን እንደ ዛሬው ሁሉ የርስቱ ሕዝብ ትሆኑለት ዘንድ እግዚአብሔር ወስዶ ከብረት እቶን ከግብፅ አወጣችሁ። እግዚአብሔርም በእናንተ ምክንያት ተቆጣኝ ዮርዳኖስንም እንዳልሻገር አምላክህም እግዚአብሔር ርስት አድርጎ ወደሚሰጥህ ወደ መልካሚቱ ምድር እንዳልገባ ማለ። እኔ ግን በዚህች ምድር እሞታለሁ ዮርዳኖስንም አልሻገርም እናንተ ግን ትሻገራላችሁ ያችንም መልካሚቱን ምድር ትወርሳላችሁ። አምላካችሁም እግዚአብሔር ከእናንተ ጋር የተማማለውን ቃል ኪዳን እንዳትረሱ፤ አምላክህም እግዚአብሔር የከለከለውን በማናቸውም ቅርጽ የተቀረጸውን ምስል እንዳታደርጉ ተጠንቀቁ። አምላክህ እግዚአብሔር የሚባላ እሳት ቀናተኛም አምላክ ነውና።”*

> *“ልጆችን የልጅ ልጆችንም በወለዳችሁ ጊዜ በምድሪቱም ብዙ ዘመን በተቀመጣችሁ ጊዜ፣ በረከሳችሁም ጊዜ፣በማናቸውም ቅርጽ የተቀረጸውን ምስል ባደርጋችሁ ጊዜ ታስቆጡትም ዘንድ በአምላካችሁ በእግዚአብሔር ፊት ክፉ የሆነውን ነገር በሠራችሁ ጊዜ፤ ትወርሱአት ዘንድ ዮርዳኖስን ተሻግራችሁ ከምትገቡባት ምድር ፈጥናችሁ እንድትጠፉ እኔ ዛሬ ሰማይና ምድርን በእናንተ አስመሰክራለሁ፤ ፈጽሞም ትጠፉላችሁ እንጂ ረጅም ዘመን አትቀመጡባትም። እግዚአብሔርም በአህዛብ መካከል ይበትናችኋል፤ እግዚአብሔር በውስጣቸው በሚያኖራችሁ በአሕዛብ መካከልም ጥቂቶች ሆናችሁ ትቀራላችሁ። በዚያም የማያዩትን የማይሰሙትንም*

*የማይበሉትንም የማያሸቱትንም በሰው እጅ ከእንጨትና ከድንጋይ የተሠሩትን አማልክት ታመልካላችሁ። ነገር ግን ከዚያ አምላካችሁን እግዚአብሔርን ትሻላችሁ በልብህም ሁሉ በነፍስህም ሁሉ የፈለግኸው እንደ ሆነ ታገኘዋለህ። ይህም ሁሉ በደረሰብህ ጊዜ ስትጨነቅ በዘመኑ ፍጻሜ ወደ አምላክህ ወደ እግዚአብሔር ትመለሳለህ ቃሉንም ትሰማለህ። አምላክህ እግዚአብሔር መሐሪ አምላክ ነውና አይተውህም አያጠፋህምም ለአባቶችህም የማለላቸውን ቃል ኪዳኑን አይረሳም።”* ዘዳግም 4፡20–31።

እሥራኤላውያን እግዚአብብሔር በእነዚህ ጥቅሶች ያስጠነቀቀውን ሁሉ አድርገዋል። እሥራኤልውያን ነቢያት ደጋግመው ማስጠንቀቂያ ቢሰጡዋቸውም በጣዖት አምልኮት ውስጥ ንቁ ተሳትፎ አድርገዋል! ልክ ሆሴዕ እንደ ተናገረውም ሌሎችን አማልክት በመከተል “አመነዘሩ”። ስለዚህ እግዚአብሔርም በቃሉ የታመነ ነውና ወደ “ሌሎች ሕዝቦች ሊበትናቸው ተቃርቦ ነበር”። ይህ ሆሴዕንም የሚያሳዝን መልዕክት ነበር፤ የሚበታተኑበት ጊዜ ደርሶ ነበርና። ይሁን እንጂ ሆሴዕ ወደ ፊት፡– ልክ በዘዳግም ላይ ቃል እንደገባው እግዚአብሔር አንድ ቀን ሕዝቡን ወደ ራሱ እንደሚመልስ የሚገልጽ መልዕክት ደግሞ ነበረው። ይህ የተስፋ ቃል፤ አዲስ ኪዳን ግልጽ እንደ ሚያደርገውም በኢየሱስ በኩል በክብር ተፈጽሟል። የኢየሱስ መሞት፣ መቀበሩንና ከሞት መነሳቱ የተበተኑትን የእግዚአብሔር ሕዝብ ወደ እርሱ እንዲመለሱ አስችሏልና።

መጽሐፈ ነገሥት ካልዕ ከትንቢተ ሆሴዕ ጋር በማዛመድ ማንበብ ትልቅ እገዛ ያደርጋል። ምክንያቱም በዚያ ዘመን የተከናወነው የእሥራኤልና የይሁዳ ታሪክ በመጽሐፈ ነገሥት ካልዕ ውስጥ ተመዝግቦ ይገኛልና። ስለዚህ በመጽሐፈ ነገሥት ካልዕ ያሉትን ክፍሎች በሆሴዕ ካሉት ክፍሎች ጋር በማገናዘብ አንባቢው በሆሴዕ መጽሐፍ ውስጥ የሚገኙትን ክፍሎች በደንብ መረዳት ይችላል።

ትንቢተ ሆሴዕ የተጻፈው በእሥራኤል ለሚኖሩ ሰዎች ነው። በዚያን ጊዜ ደግሞ በእሥራኤል ላይ በዙፋን ላይ የነበረ ንጉሥ ነበረ። ይህም ንጉሥ ኢዮርብዓም ይባላል። እሱ ኃያል ንጉሥ ቢሆንም ቅሉ ኃይሉን ግን ለበጎ ዓላማ አልተጠቀመበትም። ሕዝቡን ወደ ክፋት የመራ ንጉሥ ነበርና። ደግሞም የእሥራኤልም ሕዝብ ንጉሣቸውን በክፋት መንገዱ ተከተሉት። ይሁን እንጂ የእሥራኤል አምላክ–እግዚአብሔር– አለመታዘዝን አይታገሥም፤ ስለዚህ ለእሥራኤል መልዕክትን እንዲያመጣ ነቢዩ ሆሴዕን ጠራው። የሆሴዕ መልዕክት እግዚአብሔር የእሥራኤልን ታማኝነት የጎደለው ድርጊት ከእግዱህ እንደምይታገሥ የሚያስረዳ ነበር። በአለመታዘዝ የሚቀጥሉ ከሆነ እንደሚጠፉ የሚያስጠነቅቅም ነበር። የሆሴዕ መጽሐፍ የተሰፋ

መልዕክትንም ያካትታል (ለምሳሌ ሆሴዕ 1፡10–2፡1 ይመልከቱ)። ይሁን እንጂ በሆሴዕ 1፡1–9 ባለው ላይ ምንም የተስፋ ጭላንጭል አይታይም። በሁለቱም ማለትም በዕብራይስጥ (አንዳንዴ ማሶሬቲክ መጽሐፍ ወይም MT) እና በግሪክ (አንዳንዴ ሴፕቱጀንት ወይም LXX ይባላል) ሆሴዕ ምዕራፍ አንድ ቁጥር ዘጠኝ ላይ ይደመድማል። ነገር ግን ቀጥሎ ባለው ክፍል ትርጉም የሚሰጥ ሁኔታ ይከሰታል፤ ምክንያቱም መልዕክቱ ከቁጥር ዘጥኝ በኋላ በከፍተኛ ሁኔታ ስለሚለዋወጥ ነው። ለዚህም ይመስላል ይህ ክፍል በቁጠር ዘጠኝ ላይ የተጠናቀቀው።

እነዚህ በመጀመሪያ ላይ የሚገኙትን ዘጠኝ ቁጥሮች አንብበው ሲጨርሱ የእስራኤል ተስፋ አስቆራጭ ሁኔታ ሊሰማዎት ይችል ይሆናል። እግዚአብሔርን ስለተው እሱም ደግሞ ጥሏቸዋል። የእሥራኤልን ህመም ሊሰማዎት ካልቻሉ እስቲ ምንባቡን እንደገና ያንብቡት። እግዚአብሔር የጣዖት አምልኮትን ምን ያህል በቁም ነገር እንደሚመለከተው ተረድተዋልን? ኣሁንም ካልተረዱ ክፍሉን እንደገና ያንብቡ። እግዚአብሔር ከሕዝቡ መታዘዝን ይፈልጋል። ይህም በእነዚህ ጥቅሶች ውስጥ በጣም ግልጽ ነው። ሆኖም ግን ለእግዚአብሔር መታዘዝ ይገባ የነበረው በብሉይ ኪዳን ጊዜ ብቻ ነው ብለን ማሰብ ደግሞ የለብንም። እስቲ ኢየሱስ በዮሐንስ 14 ላይ እንዴት እንደተናገረ ልብ ይበሉ። እሱን የሚወዱ ሰዎች ትእዛዙንም መጠበቅ እንዳለባቸው ምን ያህል ጊዜ እነደሚናገር ልብ ይበሉ።

> *"ብትወዱኝ ትእዛዜን ጠብቁ። እኔም  አብን እለመናለሁ ለዘላለምም ከእናንተ ጋር እንዲኖር ሌላ አጽናኝ ይሰጣችኋል፤ እርሱም ዓለም የማያየውና የማያውቀው ስለ ሆነ ሊቀበለው የማይቻለው የእውነት መንፍስ ነው፤ ነገር ግን ከእናንተ ዘንድ ስለሚኖር በውሥጣችሁም ስለሚሆን እናንተ ታውቃላችሁ።"*
>
> *"ወላጆች እንደሌላቸው ልጆች አልተዋችሁም ወደ እናንተ እመጣለሁ። ገና ጥቂት ዘመን አለ ከዚህም በኋላ ዓለም ኣያየኝም እናንተ ግን ታዩኛላችሁ፤ እኔ ሕያው ነኝና እናንተም ሕያዋን ትሆናላችሁ። እኔ በአባቴ እንዳለሁ እናንተም በእኔ እንዳላችሁ እኔም በእናንተ በዚያን ቀን ታውቃላችሁ። ትእዛዜም በእርሱ ዘንድ ያለቻው የሚጠብቃትም የሚወደኝ እርሱ ነው፤ የሚወደኝም አባቴ ይወደዋል እኔም እወደዋለሁ ራሴንም እገልጥለታለሁ። የአስቆሮቱ ያይደለ ይሁዳ ጌታ ሆይ ለዓለም ሳይሆን ራስህን ለእኛ ልትገለጥ ያልህ እንዴት ነው? አለው። ኢየሱስም መለሰ አለውም የሚወደኝ ቢኖር ቃሌን ይጠብቃል፤ አባቴም ይወደዋል ወደ እርሱም እንመጣለን በእርሱም ዘንድ መኖሪያ እናደርጋለን። የማይወደኝ ቃሌን ኣይጠብቅም፤ የምትሰሙትም ቃል የላከኝ የአብ ነው እንጂ የእኔ ኣይደለም።"* ዮሐንስ 14፡ 15–24።

ጌታችንን መታዘዝና ሕዝቡም እንዲታዘዘው መጥራት አለብን። የእግዚአብብሔር ሕዝብ ሁሉም ስለ ጣዖት አምልኮትና ለታዛዥነት ያለው አመለካከት ተለውጧል ብለን መደምደም ሞኝነት ነው። እንግዲህ በአንድ ወቅት በሆሴዕ ዘመን ይህ ምዕራፍ እሥራኤልን ይመለከት ነበር። ይሁን እንጂ በአሁኑ ዘመን ደግሞ የእግዚአብሔር ሕዝብ ሁሉንም ይመለከታል። ስለዚህ እንደ ሰባኪነታችንና አስተማሪነታችን ሕዝቡን ስለ ጣዖት አምልኮት አደገኛነት ማስጠንቀቅ አለብን።

## ሆሴዕ 1፡1–9[3]

1፡1 በይሁዳ ነገሥታት በዖዝያንና[4] በኢዮአታም በአካዝና በሕዝቅያስም ዘመን በእሥራኤልም ንጉሥ[5]
በዮአስ ልጅ በኢዮርብዓም[6] ዘመን ወደ ብኤሪ ልጅ[7] ወደ ሆሴዕ የመጣ የእግዚአብብሔር ቃል ይህ ነው።
2 እግዚአብሔር መጀመሪያ በሆሴዕ በተናገረ ጊዜ እግዚአብሔር ሆሴዕን፡–ምድሪቱ ከእግዚአብሔር ዕርቃ

[3] *ሆሴዕ አሁን አንዳንድ ጊዜ* ትናንሽ ነቢያት *እየተባለ በሚጠራው መጽሐፍ ውስጥ የመጀመሪያው መጽሐፍ ነው። በጥንት ጊዜ ደግሞ ይህ የአጭር መጽሐፍት ስብስብ "የ 12ቱ መጽሐፍ" ተብሎም ይታወቅ ነበር፤ ምክንያቱም በትናንሽ ነቢያት ውስጥ 12 መጻሕፍት አሉና። አይሁዶች ደግሞ ይህንን ስብስብ እንደ አንድ መጽሐፍ አድርገው ይመለከቱት ነበር።*

[4] *ሆሴዕ በአገልግሎቱ ዘመን በሥልጣን ላይ የነበሩትን ነገሥታት ዝርዝር በመዘርዘር ይጀምራል። ይህም ነቢያት በሚባለው የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል የተለመደ ነው። ኤርምያስም፣ ኢሳይያስ፣ አሞጽ፣ ሚክያስ፣ ሶፎንያስ፣ ሐጌ እና ዘካሪያስም በአገልግሎታቸው ዘመን በስልጣን ላይ የነበሩትን ነገሥታት ዘርዝረው መጽሐፋቸውን ጀምረዋል። ሆሴዕ እንደ አሞጽም ከይሁዳ ነገሥታት (ዖዝያን፣ ኢዮአታም፣ አካዝ፣ ሕዝቅያስ) እና ከእሥራኤል ደግሞ ንጉሥ (ኢዮርብዓም) ዘርዝሯል። የሆሴዕ አገልግሎት በዋናነት የሚያተኩረው በእሥራኤል ላይ ቢሆንም ቅሉ ይህን አድርጓል። በትንቢት መጽሐፍት ውስጥ ያሉትን የነገሥታት ዝርዝሮች ለሰባኪው ትልቅ እገዛ ያደርጋል። ስለዚህ ሰባኪው በመጽሐፉ መጀመሪያ ላይ ያሉትን የነገሥታት ዝርዝር በ 2ኛ ነገሥት ውስጥ ካሉት ነገሥታት ገለጻ ጋር በማነጻጸር ነቢዩ በተናገረበት ጊዜ በምድሪቱ የነበረውን ሁኔታ መረዳት ያስችለዋል ማለት ነው።*

[5] *ሆሴዕ የይሁዳን ነገሥታትና የእሥራኤል ንጉሥ መናገሩ መጽሐፉ ከሁለቱም ሕዝቦች (ማለትም ከይሁዳና ከእሥራኤል) ጋር የተያያዘ መሆኑን ያሳያል። ሆሴዕ ምንም እንኳን በዋንኛነት ለእሥራኤል እየተናገረ በነበረበት ወቅት አብዛኛው የተናገረው መልዕክት በይሁዳ ላይ ያነጣጠረ ነበር። ስለዚህ በይሁዳም የነበሩት ሰዎች ሆሴዕ የተናገረውን መልዕክት ሰምተው ምላሽ እንዲሰጡ እንደሚጠብቅ ግልጽ ነው።*

[6] *በሆሴዕ አገልግሎት መጀመሪያ ላይ ቢያንስ እስራኤል የበለጸገች ትመስል ነበር። ከነቢያቱና መልዕክታቸውን ደግሞ ካመኑቱ በቀር የእስራኤል ፍጻሜ የተቃረበ መሆኑን አይረዱም ነበር። በእርግጥም ኢዮርብዓም የእሥራኤልን ድንበር በማስመለስ የእስራኤል ስፋት እንዲጨምር አድርጎ ነበር (2 ነገሥት 14፡ 23–29 ይመልከቱ)። ሆኖም እሥራኤል ለእግዚአብሔር ያላትን ታዛዥነት እንዲጨምር አላደረገም። በተቃራኒው መጽሐፈ ነገሥት ካልዕ እንደ ሚነግረን "በእግዚአብሔር ፊት ክፉ ነገር አደረገ።" የእግዚአብሔር ሕዝብ ተወካይ እንደ መሆኑ መጠን ሕዝቡን የእግዚአብሔርን ቃል ኪዳን እንዲጠብቅ መምራት አልቻለም። ይልቁንም መጽሐፍ ቅዱስ እንደ ሚነግረን " እሥራኤልንም ካሳተው ከናባጥ ልጅ ከኢዮርብዓም ኃጢአት ሁሉ አልራቀም" ይላል። "የናባጥ ልጅ ኢዮርብዓም" የመጀመሪያው የእሥራኤል ንጉሥ ነበር። የመጀመሪያው ኢዮርብዓም እሥራኤላውያንን ወደ ጣዖት አምልኮ የመራ ንጉሥ ነበር። በሆሴዕ መፅራፍ አንድ ላይ የተጠቀሰው ሁለተኛው ኢዮርብዓም ደግሞ የመጀመሪያው የንጉሥ ኢዮርብዓምን የኃጢአት ልምምድ መንገድ እሱም ቀጠለበት። ይህም ሁለተኛው ኢዮርብዓም በእሥራኤል በ793–753 ዓክልበ መካከል እሥራኤልን ያስተዳደረ ንጉሥ ነበር።*

[7] *የሆሴዕ የእሥራኤል አገልግሎት (እሥራኤል አንዳንድ ጊዜ በትንቢተ ሆሴዕ* ኤፍሬም *ተብሎ ይጠራል) የጀመረው በ755 ዓክልበ አካባቢ ነው። ሆሴዕ በ722 ዓክልበ በአሦር ከመወረሯ በፊት ለሰሜን የእሥራኤል መንግሥት ትንቢት የተናገረው የመጨረሻ ነቢይ ነው። ይህ የመጀመሪያው ቁጥር ሆሴዕ ለእሥራኤል ነቢይ እነደነበረ አይገልጽም። ሆኖም ይህ እውነታ በቁጥር 4–7 ላይ ግልጽ ተደርጓል።*

ታላቅ ግልሙትና ታደርጋለችና[8] ሂድ፤ ጋለሞታን[9] ሴትና የግልሙትናን ልጆች[10] ለአንተ ውሰድ[11] አለው።

[8] ምንም እንኳን ስለጎሜር ግልሙትና ምንነት ለአንባቢው ባይነገርም፤ የብሉይ ኪዳን አንባቢዎች ግን ስለ እሥራኤል ግልሙትና ምንነት በጣም ብዙ ጊዜ ተዘርዝሮ ተነግሯል። ዋና ቁም ነገሩ ግን በሆሴዕና በጎሜር መካከል የነበረው ጋብቻ በእግዚአብሔርና በእሥራኤል መካከል ስለነበረው "ጋብቻ" ትንሽ ስዕል እንዲሆን መታሰቡ ነበር። ሆሴዕና ጎሜር እንደተጋቡ ሁሉ፤ እግዚአብሔርና እሥራኤል በቃል ኪዳን ተጣምረው ነበር። በዚህ መልኩ እርስ በእርሳቸው "የተጋቡ" ነበሩ። በሲና ተራራ የተሰጠው ቃል ኪዳን (በዘጸአት፣ በዘዳግም ውስጥ ተገልጿል) ያ የእነርሱ "የጋብቻ ውል" ነበር። እግዚአብሔር እሱን የሚመለከተውን የቃል ኪዳኑን ክፍል ጠበቀ። ስለዚህ ለእሥራኤል ፍቅርን፣ ምግብን፣ መጠሊያን እና እንክብካቤን ሰጥቷዋቸል። ነገር ግን ገና ከመጀመሪያው እሥራኤል የጋብቻ ቃል ኪዳንን አፍርሳለች። ብዙ ብዙ የመጽሐፍ ቅዱስ ምንባቦች እሥራኤላውያን እንዴት ለእግዚአብሔር ታማኝ እንዳልነበሩ በዝርዝር ይዘረዝራል (ለምሳሌ 1 ሳሙኤል 7፡3–6 ይመልከቱ)። የሆሴዕ ጠንካራ ቋንቋ በመዋስ ስትገለጽ እሥራኤል መንፈሳዊ ጋለሞታ ነበረች። ሕዝቡም ከእውነተኛው ባል እግዚአብሔር ይልቅ ሌሎች አማልክቶችን ይወድ ነበር። "ግልሙትና" ተብሎ የተተረጎመው ቃል ልብ ማለት ያስፈልጋል፤ በቁጥር ሁለት ላይ በብዙ ቁጥር ነው የተገለጸው። ስለዚህ የጎሜር "ግልሙትና" እንደ አንድ ጊዜ ክስተት ተደርጎ አይደለም የቀረበው። ነገር ግን እንደ ሕይወት መንገድ (የሁልጊዜ ተግባር) ተደርጎ ቀርቧል። በጎሜር ውስጥ ይህ እንዴት እውነት እንደ ነበር ለአንባቢው ምንም ዓይነት ነገር ባይነገረውም፤ በእሥራኤል ስለነበረው "ግልሙትና" ምሳሌ ግን ለአናባቢው ብዙ ተነግሮታል። የእሥራኤል "ግልሙትና" የአንድ ጊዜ ክስተት አልነበረም። እሥራኤል ከእግዚአብሔር ጋር ያላትን ግኑኝነት ላለማቋረጥ ታማኝ አልነበረችም። ስለዚህ እሥራኤል በድርጊቶችዋ እግዚአብሔርን እንደ ማትወደውና እንደ ማታምነውም እያሳየች ነበር።

የእሥራኤል መንፈሳዊ ግልሙትና ደግሞ ሕዝቡ ታላቅ ፆታዊ የዝሙት ኃጢአይት እንዲሰሩ አድርጓቸዋል። ዝሙት የበኣል ኃይማኖታዊ በዓላት ዋንኛ ገጽታ ነበር፤ ምክንያቱም እሥራኤላውያን በሰዎች መካከል የሚደረግ የፆታ ግኑኝነት አማልክት የእርስ በርስ የፆታ ግኑኝነት እንዲፈጽሙ ስለሚያደርግ ይህ ደግሞ ምድሪቱ ለም እንድትሆን ያደርጋል ብለው ያምኑ ስለነበር ነው። እነዚህ ድርጊቶች የተከለከሉ ከመሆናቸውም በላይ እግዚአብሔር እሥራኤልን የሚንከባከብ ባል መሆኑን ደግሞ መካድ ነበር። ሚስት የሆነችው እሥራኤል ባልዋ የሆነውን የእግዚአብሔር እንክብካቤ አለማመን ነበር።

[9] ስለ ጎሜር ከጋብቻዋ በፊትም ሆነ በኋላ ብዙ ዝርዝሮች አልተሰጡም። ስለዚህ ጎሜርን በተመለከተ "ጋለሞታ ሚስት" ማለት ምን ማለት እንደሆነ በትክክል ማወቅ አስቸጋሪ ነው። ይህ ምሳሌ የሚያስረዳን ሰባኪው የክፍሉን ነጥብ (የእሥራኤልን መንፈሳዊ ታማኝነት የጎደለውን ድርጊት) ትኩረት ሊሰጠው የሚገባ መሆኑንና በመጨረሻም የአጠቃላይ የንባቡን ትርጉም በማይነካ ዝርዝር ጉዳዮች ትኩረቱ ሊከፋፍል እንደ ማይገባው ነው። ስለዚህ ሰባኪው ስለጎሜር ብዙ ዝርዝሮችን ሳያውቅ የሆሴዕ ዋና ነጥብ በግልጽና በትክክል ማስተማር ይችላል። ነጥቡን ለማንሳት ለሰባኪው ወይም ለአስተማሪው ስለ ጎሜር ተጨማሪ መረጃ ቢያስፈልገው ኖሮ መጽሐፉ ላይ ይጠቀስ ነበርና!

[10] ሆሴዕ ከጎሜር ሦስት ልጆች ነበሩት። ለሶስቱም ልጆች ደግሞ ምሳሌያዊ ስሞች ተሰጥቷቸዋል። ሆኖም አንባቢው ስለ ልጆቹ ማወቅ የሚፈልገውን ያህል ምንም ዝርዝር መረጃ አልተነገረም። ስለልጆቹ ጠቃሚ መረጃ ያለው በተሰጣቸው ስም ላይ ነው። ለልጆቹ የተሰጣቸው ስሞች ለሀገሩ ጠንካራ መልዕክቶችን ለማስተላለፍ ታስቦ ነው።

[11] አብዛኛው የሆሴዕ ክፍል ቅኔ ቢሆንም የመጀመሪያው ምዕራፍ ግን ትረካ ነው (ማለትም ታሪክ ነው)። በዚህ ምዕራፍ ውስጥ ያለው ታሪክ የሚዘረዝረው ሆሴዕ ጎሜር ከተባለች ሴት ጋር ስላደረገው ጋብቻ እና ከሆሴዕና ከጎሜር የተወለዱት ልጆችና ለልጆቹ ስም ማውጣት ነው። ይህ የሆሴዕ እና "የጋለሞታ ሚስት" ታሪክ ታማኝ የሆነው እግዚአብሔርና ካልታመኑት እሥራኤላውያን ጋር ያደረገውን ጋብቻ የሚያሳይ ምሳሌ ነው።

3 እርሱም ሄዶ የዴቤላይምን ልጅ ጎሜርን አገባ፤ እርስዋም ፀነሰች ወንድ ልጅንም ወለደችለት።

4 እግዚአብሔርም፦ከጥቂት ዘመን በኋላ የኢዝራኤልን ደም በኢዩ ቤት ላይ እበቀላለሁና[12] ከእሥራኤልም መንግሥትን እሽራለሁና ስሙን ኢዝራኤል ብለህ ጥራው፤

5 በዚያም ቀን በኢዝራኤል ሸለቆ ውስጥ የእሥራኤልን ቀስት እሰብራለሁ አለው።

6 ደግሞም ፀነሰች ሴት ልጅንም ወለደች። እግዚአብሔርም፦ ይቅር እላቸው ዘንድ
የእሥራኤል ቤት ከንግዲህ ወዲህ አልምርምና ስምዋን ሎሩሃማ[13] ብለህ ጥራት፤

---

[12] ኢይዝራኤል በእሥራኤል ውስጥ የታዋቂ ከተማ እና ሸለቆ ስም ነበረ። ብዙ ጉልህ የሆኑ ክፉ ነገሮች እዚያ እንደተከሰቱ ግልጽ ነው (ለምሳሌ 1ኛ ነገሥት 21 ይመልከቱ)። ከዚህም ባሻገር በይሁዳ ታሪክ ውስጥ በተለይም የጨለማ ጊዜ የጀመረው በኢይዝራኤል በተፈጸሙ ክንውኖች ነው (2ኛ ነገሥት 9፡14–10፡11 ይመልከቱ)። ሆሴዕ ልጁን ኢይዝራኤል ብሎ እንዲጠራው በማዘዝ እግዚአብሔር በዚያ አካባቢ የተፈጸመውን ክፋትና ደም መፋሰስ እንዳየ እና "በኢይዝራኤል ሸለቆ የእስራኤልን ቀስት እንደሚሰብር" ለእሥራኤላውያን ምልክት ይሰጣቸው ነበር። ስለዚህ የሆሴዕ ልጅ ኢይዝራኤል ተብሎ የተጠራው ይህ ኢይዝራኤል የተባለውን ቦታ ለሕዝቡ ለማስታውስ ታቅዶ ነበር። እግዚአብሔር በዚያ ቦታ ክፋትን እንዳየ እና በዚያም ቦታ ላይ ጥፋት እንደሚያመጣ ምልክት ነበር። ነገር ግን ቃሉን በጥንቃቄ ያንብቡ። ጥፋቱ በኢይዝራኤል ላይ ብቻ የመጣ አይደለም፤ ነገር ግን ትንቢቱ በተጨማሪ የሚለው " **የእሥራኤልን** *መንግሥት* አጠፋለሁ" እንደዚሁም በኢይዝራኤል ሸለቆ ውስጥ **የእሥራኤልንም ቀስት እሰብራለሁ**" ይላል! ስለዚህ ወደዚህች ሥፍራ (ወደ ኢይዝራኤል) የሚመጣው ጥፋት በመላው ምድሪቱ ላይ ሊመጣ ያለውን ጥፋት ያመለክታል። ብዙ ሊቃውንት ኢይዝራኤል የሚለው ስም እሥራኤል ከሚለው ስም ጋር ተመሳሳይ እንደሆነ አስተውለዋል። ይህም ሆን ተብሎ የተደረገ ሳይሆን አይቀርም። ምክንያቱም ሰዎች የሆሴዕን ልጅ ስም **ኢይዝራኤል** የሚለውን ሲሰሙ ስለ መላው **እሥራኤል** እንዲያስቡ ተፈልጎ ነበርና። ስለዚህ ሆሴዕ ብላቴናውን ኢይዝራኤል ብሎ በጠራው ጊዜ እሥራኤላውያንን ፈጽሞ እንደሚያጠፋ የሚያስጠነቅቅ ምልክት እየሰጣቸው ነበር ማለት ነው። ይህችን አንዲት ከተማ የእስራኤልን ከተሞች በሙሉ እንድትወክል ተደርጋ ነበር የቀረበችው።

ኢይዝራኤል የሚለው ስም በሆሴዕ 1፡11 እና 2፡22 (እነዚህ ጥቅሶች በአዲሱ መደበኛ ትርጉም ይመልከቱ) ላይም ጥቅም ላይ ውሏል። ሆኖም በእነዚህ ቁጥሮች ውስጥ ግን ስሙ በአዎንታዊ በሆነ መልኩ ነው ጥቅም ላይ የዋለው። ያስታውሱ የትንቢት መጻሕፍት ባሉታዊና በአዎንታዊ መልዕክቶች መካከል ብዙ ጊዜ ይለዋውጣሉ። የሆሴዕ መጽሐፍ በአንድ ላይ ተሰብስቦ ጭብጦችን ከአንድ ምዕራፍ ወደ ሌላው የሚሸጋገርበት አንዱ መንገድ ነው። በተደጋጋሚ የሚከሰተው የስም አጠቃቀም አንባቢው የሆሴዕን ቃል በትኩረት እንዲከታተል የሚያሳስብ ነው። እግዚአብሔር ክፉ የሆነውን ስም በሚያምርና በአዎንታዊ መንገድ በመጠቀም ክፉውን ወደ መልካም ነገር መለወጥ እንድሚችልም ያሳያል።

[13] የጎሜር ሁለተኛ ልጅ ስም አስገራሚ ሊመስል ይችላል፤ ምክንያቱም እግዚአብሔር ራሱን መሐሪ አምላክ አድርጎ የገለፀበት ነውና። እግዚአብሔር የማይምር አምላክ ተብሎ አይታወቅም። ሆኖም ግን እግዚአብሔር **ምሕረት የማድረግ ግዴታ የለበትም**። ምሕረት በትርጉሙ እዳ እንደ መክፈል ማለት አይደለም። እግዚአብሔር በመረጠው ጊዜ በመረጠው ቦታ እና ለመረጠው ሰው ምሕረትን ማድረግ ይችላል። ደግሞም ምሕርትንም መከልከል መብቱ ነው። እግዚአብሔር ለሙሴ እንደተናገረው "እኔ . . . ይቅርም የምለውን ይቅር እላለሁ የምምረውንም እምራለሁ" ብሎታልና (ዘጸአት 33፡19 ይመልከቱ)። እንደዚሁም ደግሞ በዘጸአት 34፡6–7ለ እግዚአብሔር እንደ መሐሪ አምላክ ቀርቧል፡- "እግዚአብሔርም በፊቱ አልፎ፡-እግዚአብሔር፣ እግዚአብሔር መሐሪ ሞገስ ያለው ታጋሽም ባለ ብዙ ቸርነትና እውነት እስከ ሺህ ትውልድም ቸርነተን የሚጠብቅ አባሳንና መተላለፍን ኃጢአትንም ይቅር የሚል . . ." ነገር ግን በዘጸአት 34፡7 ሁለተኛው አጋማሽ ላይ እሥራኤልውያን የረሱትን ነገር በጣም የተለየ ነገር ይናገራል፡- ". . . ነገር ግን በደለኛውንም ከቶ የማያነጻ የአባቶችንም ኃጢአት በልጆች እስከ ሦስትና እስከ አራት ትውልድም በልጅ ልጆች የሚያመጣ አምልክ" ይላል። እሥራኤላውያን እግዚአብሔር ምሕረት እንዳደረገላቸው አድርገው ነበር የሚመላለሱት። ነገር ግን ይህ ትክክል አልነበረም። የሆሴዕ ልጅ "ይቅር እላቸው ዘንድ አልምርም" የሚለው ስም ለእሥራኤል ምልክት ነበረች፤ ቢያንስ በሆሴዕ ዘመን ይኖሩ ለነበሩት

7 ነገር ግን የይሁዳን ቤት እምራለሁ፤ በአምላካቸውም በእግዚአብሔር አድናቸዋለሁ[14] እንጂ በቀስት
ወይም በሰይፍ ወይም በሰልፍ ወይም በፈረሶች ወይም በፈርሰኞች አላድናቸውም አለው።[15]
8 ሎሩሃማም ጡት ባስጣለች ጊዜ ደግሞ ፀነሰች ወንድ ልጅንም ወለደች።

---

እሥራኤላውያን ከአሁን በኋላ መሐሪ አምላክ እንደማይሆንላቸው የሚያሳይ ምልክት ነበር። የምሕረት ዘመናቸው አብቅቶ ነበርና። ነገር ግን እግዚአብሔር ለእሥራኤል የሰጠው ተስፋስ? እንግዲህ እግዚአብሔር ከእሥራኤል ጋር በገባው ቃል ኪዳን ምክንያት መሐሪ የመሆን ግዴታ አልነበረበትምን? በቃል ኪዳን የታሰረባት ሚስት ለሆነቸው እሥራኤል ሊምር የተገባው አልነበረምን? አይደልም እስዋ በቃል ኪዳን የጸናች ሚስት ካልነበረች እሱ ግዴታ የለበትም ማለት ነው። እሥራኤል ቃል ኪዳንዋን አፍርሳለችና። ስለዚህም ነው እዚህ ጋ እግዚአብሔር የፍቺዋን ወርቀት እየሰጣት የነበረው። ከዚህ በኋላ ከእግዚአብሔር የሆነውን ምሕረትና ይቅርታ እና ከእግዚአብሔር ጋር የነበራትን "የጋብቻ መብት" አታገኝም።

[14] በቁጥር 7 ላይ በእሥራኤልና በይሁዳ መካከል ልዩነት አለ። ይሁዳ ከእሥራኤል በተለየ ሁኔታ አሁንም ከእግዚአብሔር ምሕረትን ታገኛለች። ሆሴዕ በዋንኛነት የሚናገረው ለእሥራኤላውያን ቢሆንም፣ የይሁዳ ሰዎችም ቃሉን እየሰሙ እንደነበር ማስታውስ ጠቃሚ ነው። ይሁን እንጂ ሆሴዕ ሁለቱንም ማለትም የይሁዳና የእሥራኤል ስዎችን ወደ እግዚአብሔር እንዲመለሱ ይጠራ ነበር። ከዚህ ባሻገር በእሥራኤል ውስጥ ያሉት ሰዎች እግዚአብሔር ለይሁዳ ስላለው ዕቅድ መስማት ይኖርባቸው ነበር። በሆሴዕ ውስጥ ስለ ይሁዳ የተነገሩ ልዩ ማጣቀሻዎች በሚከተሉት ጥቅሶች ውስጥ ይገኛሉ፤ ( በሆሴዕ 1፡ 1፣ 1፡7፣ 1፡11፣ 4፡15፣ 5፡5፣ 5፡10–14፣ 6፡4፣ 6፡11፣ 8፡14፣ 10፡11፣ 11፡12፣ እና 12፡2)።

ስለ ይሁዳ መዳን የሚናገረው ይህ የተለየ ማጣቀሻ ይሁዳ በኃጢአቱ ፈጽሞ እንደማይቀጣ ቃል ኪዳን ተደርጎ ሊወሰድ አይገባውም። ምንም እንኳን እሥራኤል በተሸነፈችበትና በአሶራውያ ለምርኮ በተወሰደችበት ጊዜ (በሆሴዕ 1፡4–5 ላይ እንደ ተገለጸው ማለት ነው) ይሁዳ በውቅቱ ያልተሸነፈች ቢሆንም በመጨረሻ ግን በባቢሎናውያን እጅ ሥር ወድቃ ወደ ባቢሎን በግዞት ተወሰደች።

[15] "በቀስት ወይም በሰይፍ ወይም በሰልፍ ወይም በፈረሶች ወይም በፈርሰኞች አላድናቸውም" የሚለው ቃል ይሁዳ በጦር ኃይሏ ምክንያት አትድንም ማለት ነው። ይልቁንም ከአሦራውያን መዳን "ከአምላካቸው ከእግዚአብሔር" ብቻ ይመጣል ማለት ነው። በሆሴዕ 1፡7 ላይ ያለው የሆሴዕ ትንቢት ፍጻሜ ያገኘው በሕዝቅያስ ዘመን ነው (በሆሴዕ 1፡1 ከተጠቀሰው ከይሁዳ ነገሥታትት አንዱ ነውና)። በሆሴዕ 1፡7 ላይ ያለውን የዚህ ትንቢት ፍጻሜ ዝርዝር መግለጫ ለማግኘት 2ኛ ነገሥት 18–19 እና ኢሳይያስ 36–38ን ይመልከቱ። ልብ ልንለው የሚገባ ነገር ቢኖር ይሁዳ በዚህ ጊዜ የዳነቸው በጽድቅዋ አለመሆኑን ነው። ይልቁንም እግዚአብሔር ይሁዳን እንደሚያድናት ነግሯዋታልና "ስለ እኔም ስለ ባሪያዬም ዳዊት ይህችን ከተማ አድናት ዘንድ እጋርዳታለሁ" (2 ነገሥት 19፡34 ይመልከቱ)። በ 2ኛ ነገሥት 19 ላይ ያለውን ይህ ቃል በተነገረ ጊዜ ዳዊት በሕይወት አልነበረም። ይህ ከዳዊት ዘር ስለሚመጣው ንጉሥ ለዳዊት የገባለትን ቃል የሚያመለክት ነበር። ይህም የመጨረሻ የሆነው የክርስቶስና የመንግሥቱ ማሳሰቢያ ነበር። እግዚአብሔር ለዳዊት የገባለት ተስፋ በብዙ ምንባቦች ተጠቅሷል። በመጀመሪያ የተጠቀሰው ደግሞ በ 2 ሳሙኤል 7፡1–17 ተዘርዝሯል።

9 እግዚአብሔርም፡–ሕዝቤ አይደላችሁምና[16] እኔም አምላክ አልሆናችሁምና[17] ስሙን ሎዓሚ ብለህ

---

[16] የሆሴዕ ሦስተኛው ልጅ " ሕዝቤ አይደላችሁም" የሚል ነው። ይህ ስም የተሰጠበት ምክንያት እግዚአብሔር እሥራኤላውያንን ከእንግዲህ የተመረጣችሁ ሕዝቤ አይደላችሁም ለማለት ስለፈለገ ነው። መንፈሳዊ ግልሙትና በመፈጸማቸው እግዚአብሔር ከእስራኤልውያን ጋር ያለውን ዝምድና እያቋረጠ ነበርና። ስለዚህም በዚህ ምክንያት እንደ ማንኛውም ሕዝብ ነበሩ ማለት ነው። ከእግዚአብሔር የነበራቸው ነገር ተቆርጦ ነበር ማለት ነው። ስለዚህ በዚህ ዘመንም ሰባኪ ወይም አስተማሪ ይህ ምን ማለት እንደሆነ የእግዚአብሔር ህዝብ እንዲገባቸው መርዳት በጣም አስፈላጊ ነው! እስቲ አሰብ ያድርጉ ይህንን ቃል ከእግዚአብሔር እርሶ ቢሰሙስ!

በቁጥር ዘጠኝ ሁለተኛ አጋማሽ ላይ ቋንቋው እንዴት እንደሚቀየር ልብ ይበሉ። በዚህ ምዕራፍ ውስጥ ለመጀመሪያ ጊዜ እግዚአብሔር የእስራኤልን ሕዝብ በቀጥታ ሲናገር እንመለከታለን። እስከዚህም ድረስ በሆሴዕ በኩል ስለ ሕዝቡ ይናገራል። ነገር ግን ህዝቡን በቀጥታ አላናገረም። እዚህ ጋ ግን በቀጥታ ለሰዎቹ "እናንተ ሕዝቤ አይደላችሁም እኔም አምላካችሁ አይደለሁም" ሲል ተናግሯል። በዘዳግም ላይ የተተነበዩት አስፈሪ እርግማኖች ተፈጽመዋል፡-"በዚያም ቀን ቁጣዬ ይነድባቸዋል እተዋቸውማለሁ ፊቴንም እሰውርባቸዋለሁ ለአሕዛብም ሙብል ይሆናሉ፤ በዚያም ቀን፡– በእውነት እግዚአብሔር በእኛ መካከል የለመና ይህ ክፉ ነገር አገኘን እስኪሉ ድረስ ብዙ ክፉ ነገርና ጭንቀት ይደርስባቸዋል" (ዘዳግም 31፡17–18 ይመልከቱ)።

ቃል ኪዳኑን በመጠበቅ ረገድ እግዚአብሔር ለእስራኤልውያን የገባቸው ተስፋዎች ተሽረዋል! "ሕዝቤ አይደላችሁም" የሚለው ቃል እሥራኤል ከአሁን በኋላ የእግዚአብሔር ልዩ ሕዝብ እንዳልሆነ ያመለክታል። ስለዚህ ራሳቸውን የእግዚአብሔር ልዩ ሕዝብ ብለው መጥራት አይችሉም። እንዴት ያለ አሳዛኝ ነገር ነው! እግዚአብሔር በታሪካቸው ቀደም ባሉት ዘመናት እንዴት እንደተናገራቸው ይመልከቱ። የእግዚብሔር ሐሳብ እነርሱ––በምድር ላይ ካሉት ሰዎች ሁሉ–– ለእርሱ የተለዩ ሕዝቦች እንዲሆኑ ነበር (ዘጸአት 6፡7, 19፡4–6; ዘሌዋውያን 26፡12 እና ዘዳግም 27፡9 ይመልከቱ)። ይህ ከአሁን በኋላ እውነት አይደለም። "ሕዝቤ አይደላችሁም" የሚለው በምክንያታዊነት "ምሕረት አይገባችሁም" ማለትን ይከተላልና፤ ምክንያቱም ያለ ምሕረት እሥራኤል የእግዚአብሔር ሕዝብ መሆን አትችልም። እንዲያውም ያለ ምሕረት በፊቱ ለአፍታ እንኳን መቆም አትችልም።

እግዚአብሔር አብ በኢየሱስ የውሃ ጥምቀት ጊዜ " በእርሱ ድስ የሚለኝ የምወደው ልጇ ይህ ነው፤ " ብሎ የተናገረውን ማወቁ በጣም አስፈላጊ ነው (ሉቃስ 3፡22)። በአብ ቃል ላይ በመመስረት፣ **ኢየሱስ የእግዚአብሔር ሕዝብ** እንደሆነ ግልጽ ነው። እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር በመተባበሩ አያፍርም። ኢየሱስ የእግዚአብሔር ሕዝብ በመሆኑ ደግሞ፣ ክርስቲያኖች፣ በሆሴዕ ዘመን እንደነበሩት ሰዎች ኃጢአተኞች ቢሆኑም፣ ከእግዚአብሔር ጋር እንዴት ምሕረትና ኅብረት ማድረግ እንደሚችሉ ያብራራል። ክርስቲያኖች እነዚህ ነገሮች ሊኖራቸው የሚችለው "በክርስቶስ"፣ ታዛዥ የእግዚአብሔር ልጆች ስለሆኑ ብቻ ነው። ስለዚህ ሰባኪ ወይም አስተማሪ ይህን ሀሳብ መገንዘብ አስፈላጊ ነገር ነው።

[17] በዚህ ምዕራፍ ውስጥ ስም የወጣላቸው የሆሴዕ ልጆች ብቻ አይደሉም። እንደዚሁም ደግሞ እግዚአብሔር ለራሱ ስም ሲሰጥ እንመለከታለን። እግዚአብሔር የሆሴዕን ሦስተኛ ልጅ "ሕዝቤ አይደላችሁም" ብሎ እንዲጥራው ለሆሴዕ ከነገረው በኋላ ወዲያውኑ እግዚአብሔር **"እኔም አምላክ አልሆናችሁም"** ብሏል። "አምላክ አልሆናችሁም" የሚለው ስም! "ሕዝቤ አይደላችሁም" ለሚለው ስም አቻ ነውና። ነገር ግን በእንግሊዝኛው ESV ውስጥ ጥቅም ላይ የዋሉት ቃላት (በተጨማሪም NIV፣ NTL፣ CSB ይመልከቱ)፤ ሙሉውን የዕብራይስጡን ማሴሮቲክ ጽሑፍ (MT) ወይም የግሪኩን ሰፕቱጀንት (XLL) ትርጓሜ አያካትቱም። የዕብራይስጡን ማሴሮቲክ ጽሑፍ (MT) ላይ ያለው ወደ አማራኛ ሲተረጎም **"ሕዝቤ አይደላችሁም" (ሎረሃማ)** ብለህ ጥራው ነው የሚለው፤ ምክንያቱም እግዚአብሔርም እኔ ለእናንተ **"አምላክ አይደለሁም"** ብሎዋቸዋልና– የዚህ መጽሐፍ ጸሐፊ ይህንን ትርጉም ቀጥታ "ያለና የሚኖር" ከሚለው ጋር አገናኝቶታል። "ያለና የሚኖር" የሚለው ስም የእግዚአብሔር የቃል ኪዳን ስም ነው። ይህም በሚነድደው በቁጥቋጦ እሳት ውስጥ ለሙሴ በተናገረበት ጊዜ እግዚአብሔር ራሱን የጠራበት ስም ነበር (ዘጸአት 3፡14 ይመልከቱ)። ሙሴ ስሙስ ማነው ብለው ቢጠይቁኝ ምን እላለሁ ብሎ በጠየቀው

ጥራው አለው።

**ሆሴዕ 2፡1–3**

ሆሴዕ 1፡1–9 የተጠናቀቀው እሥራኤላውያን ከእግዚአብሔር “መፋታታቸው” እና በመላው የእሥራኤል ሕዝብ ላይ ጥፋት እንደሚመጣ በማመልከት ነው። ስለዚህ እዚህ ጋ አንባቢው ስለ እሥራኤል ማዘን የለበትም። ምክንያቱም እሥራኤልውያን መንፈሳዊ ግልሙትና ይፈጽሙ ስለነበር ከቁጥር 1–9 ባለው ክፍል የተነገረው ሁሉ ተገቢ ነገር ነበር። ከግብጽ ያወጣቸው እግዚአብሔር የተመረጠ ሕዝብ እንዲሆኑለት ሲሆን እነርሱ ግን ከእርሱ ጋር የገቡትን ቃል ኪዳን አፍርሰዋል። በውጫዊ ተግባራቸው ውስጣዊ ምኞታቸውን በመግለጽ ከሌሎች አማልክቶች  ጋር ቅርርብ ነበራቸውና።

አስተዋይ አንባቢ በእግዚአብሔርና በሕዝቡ መካከል የነበረውን “ጋብቻ” በዚህ መንገድ መጠናቀቁ ሊያስደንቀው አይገባም፤ ምክንያቱም እሥራኤላውያን ከእግዚአብሔር ጋር ያደረጉት “ጋብቻ” ፈጽሞ ጤናማ አልነበርምና። እሥራኤላውያን ወደ ተስፋይቱ ምድር ከገቡበት ጊዜ አንስቶ እሥራኤል ከእግዚአብሔር ጋር ታማኝ የቃል ኪዳን አጋር አልነበረችም።

በሆሴዕ 1፡1–9 እንደ ተገለጸው ምንጊዜም በጣም አስጨናቂ የነበረው ጋብቻ ፍጻሜውን አግኝቷል። እግዚአብሔር ታማኝ ነበር፤ ነገር ግን ሕዝቡ ራሳቸውን ለእግዚአብሔር ፍጽሞ አላስገዙም ነበር። ከብዙ አማልክቶች ጋር ይወዳጁ ነበራና። በእግዚአብሔር ቸርነት፣ በጥበቃው እና እንክብካቤው አልታመኑም። ደግሞም በጣም አስደናቂ በሆነው ፍቅሩ አልረኩም። በዚህ ምክንያት በመጨረሻም ከእርሱ ተለዩ። ስለዚህም የእግዚአብብሔር ሰዎች አልነበሩም። እግዚአብብሔር ከእንግዲህ ለእነርሱ “ያለና የሚኖር” አምላክ አይደለም። ይህ የሆሴዕ 1፡1–9 መልዕክት ነው።

---

ጊዜ  እግዚአብሔር “ያለና የሚኖር እኔ ነኝ” ብሎ ነው የመለሰለት። በዘጸአት መጽሐፍ ውስጥ እግዚአብሔር ለእሥራኤላውያን የዚህን ስም ትርጉም ደረጃ በደረጃ ገልጾላቸዋል። ለምሳሌ በዘጸአት 6፡2–8 ላይ እግዚአብሔር የቃል ኪዳኑ ስም እንደሆነ በሰፊው ገልጿል። እግዚአብሔር በሚከተሉት መንገዶች ራሱን ያስታውቃል፡- ሕዝቡን ይወዳል፣ ሕዝቡን ይቤዠል፣ህዝቡን ያድናል፣ ለሕዝቡም የሚያስፈልገውን ደግሞ ይሰጣል። እግዚአብሔር ያለና የሚኖር በመሆኑ የራሱን ሕዝብ ምን እንደሚያስፈልገው ሁሉ ያሟላል። በዚህ በሆሴዕ ክፍል ግን ስሙን መልሶ ወሰደ። እኔም ያለና የሚኖር (አማላካችሁ አይደለሁም)። ከእንግዲህ የእግዚአብሔር እሥራኤል “ያለና የሚኖር” ሊሆንላቸው አይችልም፤ ምክንያቱም ከእነርሱ ጋር አይሆንምና። እሥራኤል አሁን እንደሌሎችም አሕዛብ በዚህ ዓለም ላይ ያለ እግዚአብሔር እና ያለ ተስፋ ናቸው ማለት ነው (ኤፌሶን 2፡12 ይመልከቱ)። እነሱ ሕዝቦቹ አይደሉም፤ እሱም አምላካቸው አይደለም። የግሪኩ ሰፕቱጀንት (XLL) ዕብራይስጥን ያንጸባርቃል። ወደ አማርኛ ሲተርጎም ስሙን “ሕዝቤ አይደላችሁም” ብለህ ጥራው ነው የሚለው ስለዚህ እኔም ለእናተ ያለና የሚኖር (አምላካችሁ አይደለሁም) ነው ያላቸው።

እንግዲህ የሚያስደንቀው ደግሞ ሆሴዕ 2፡1–3 ያለውን ክፍል ነው። የእግዚአብሔርን ፍርድ ካወጁ ዘጠኝ ቁጥሮች በኋላ ደግሞ የተስፋ ጭላንጭል በዚህ ክፍል ላይ ይታያል!

> *የእሥራኤልም ልጆች ቁጥር እንደማይሰፈርና እንደማይቆጠር እንደ ባሕር አሸዋ ይሆናል፤ እንዲህም ይሆናል፤ እናንተ ሕዝቤ አይደላችሁም ተብሎ በተነገረበት በዚያ ስፍራ የሕያው አምላክ ልጆች ይባላሉ። የይሁዳ ልጆችና የእሥራኤል ልጆች በአንድነት ይሰበሰባሉ ለእነርሱም አንድ አለቃ ይሾማሉ ከምድሪቱም ይወጣሉ፤ የኢይዝራኤል ቀን ታላቅ ይሆናልና። ወንድሞቻችሁን፡– ዓሚ እህቶቻችሁንም፡– ሩሃማ በሉዋቸው።*

ይህ ክፍል በሆሴዕ 1፡1–9 ካለው ጋር ስናስተያየው በጣም አስደናቂ ክፍል ነው። በዚህ ክፍል እግዚአብሔር እሥራኤልውያንን ለማብዛት ቃል ሲገባ እንመለከታለን–ቀደም ሲል ስለመጥፋታቸው ሲናገር የነበርው– አሁን ግን መቁጠር እስከ ማይቻል ስለመብዛታቸው ይናገራል። ቅድም ሕዝቤ አይደሉም ያላቸው አሁን ግን “የሕያው አምላክ ልጆች” ተብለው ይጠራሉ ይላል። እንደዚሁም ይሁዳ እና እሥራኤል ዳግመኛ እንደማይለያዩ ይናገራል። ደግሞም እነዚህ ሁለቱ ህዝቦች በአንድ መሪ እንደሚመሩ ያስረግጣል።

ከዚህ የበለጠ አስገራሚ ለውጥ ሊኖር ይችላልን? ይህ ከሞት ከመነሳት አይተናነስም። ነገር ግን ይህ ትንሣኤ እንዴት ሊሆን ቻለ? እና እነዚህ ነገሮችስ የሚፈጸሙት መቼ ነው? ፍጻሜያቸውስ ምን ይመስላል?

በእርግጥ ሰባኪው ወይም አስተማሪው በሆሴዕ 2፡1–3 ውስጥ ያለውን ተሃድሶ እና እድገት ተስፋዎች እንዴት እንደሚፈጸሙ ማሰብ የለበትም። በአዲስ ኪዳን ውስጥ ሁለት ሐዋሪያት እነዚህን ጥቅሶች ይጠቅሳሉ። ስለዚህ እነዚህ የእግዚአብሔር ተስፋዎች እንዴት ፍጻሜያቸው እንዳገኙና አሁንም እየተፍጸሙ እንዳሉ ለመርዳት የሐዋርያት መልዕክቶች ትልቅ እገዛ ያደርጉልናል።

ሐዋሪያው ጳውሎስ በሮሜ 9 ላይ እነዚህን ጥቅሶች እንዴት እንደተጠቀመ ይመለከቱ፡-

> *ነገር ግን እግዚአብሔር ቁጣውን ሊያሳይ ኃይሉንም ሊገልጥ ወዶ አስቀድሞ ለክብር ባዘጋጃቸው በምሕረት ዕቃዎች ላይ የክብሩን ባለጠገነት ይገልጥ ዘንድ ለጥፋት የተዘጋጁትን የቁጣ ዕቃዎች*

*በብዙ ትዕግሥት ከቻለ እንዴት ነው? የምሕረቱ ዕቃዎችም ከአይሁድ ብቻ አይደሉም፤ ነገር ግን ከአሕዛብ ደግሞ የጠራን እኛ ነን። እንዲሁ ደግሞ በሆሴዕ፤*

*"ሕዝቤ ያልሆነውን ሕዝቤ ብዬ ያልተወደደችውንም የተወደደችው ብዬ እጠራለሁ፣"*

*"እናንተ ሕዝቤ አይደላችሁም በተባለላቸውም ስፍራ በዚያ የሕያው እግዚአብሔር ልጆች ተብለው ይጠራሉ ይላል።"* **ሮሜ 9፡22–26**

በግልጽ ለማየት እንደሚቻለው ጳውሎስ ይህ የሆሴዕ ተስፋ በሱ ዘመን ፍጻሜ እንዳገኘ ይናገራል። ከዚህም በተጨማሪ ጳውሎስ በዚህ የተስፋ ቃል ውስጥ አሕዛብንም እንደሚያጠቃልል ያስገነዝባል። ይህ በጣም አስደናቂ ነገር ነው፤ ምክንያቱም በሆሴዕ 2፡2 ላይ ያለውን የተስፋ ቃል የመጀመሪያው ክፍል ለ"ይሁዳ ልጆች" እና "ለእሥራኤል ልጆች" የተነገሩ ናቸው። የእሥራኤል ልጆች የሚለው ሐረግ ትርጉም ጳውሎስ በሰፊው አስፍቶ፤ አይሁዶችን እና አሕዛብን በሚያጠቃልል መልኩ ተመልክቶታል! በእርግጥ የሆሴ የመጀመሪያ አድማጮች ማለትም በሆሴ ዘመን የነበሩቱ ሰዎች ይህን ፈጽሞ አይጠብቁም ነበር ማለት ይቻላል። ጳውሎስ ወደዚህ መደምድሚያ ላይ የደረሰው እንዴት እንደሆነ ከመመርመራችን በፊት የቀረውን ሆሴዕ 2፡1 እንመልከት።

*እናንተ ሕዝቤ አይደላችሁም ተብሎ በተነገረበት በዚያ ሥፍራ የሕያው አምላክ ልጆች ይባላሉ።* **ሆሴዕ 2፡1ለ**

እንዴት ያለ ድንቅ ተስፋ ነው! በሆሴዕ 1፡1–9 ከተጠቀሱት የእሥራኤል ልጆች በስተቀር ለዚህኛው ግዙፍ የ"እሥራኤል ልጆች" ቁጠር አስፈሪ ስም አይሰጥም። ይልቁንም የሆሴዕ ሦስተኛ ልጅ ("ሕዝቤ አይደላችሁም") የሚለውን ስም በመገልበጥ በሆሴዕ 1፡10 የተገለጹት ሰዎች "የሕያው አምላክ ልጆች" ይባላሉ ይላል።

በጴጥሮስ የመጀመሪያ መልዕክት ውስጥ ይህ ክፍል እንዴት እነደተጠቀመበት ልብ ይበሉ። እነዚህ ቃላት የተናገረው "በጳንጦስ፣ በገላትያ፣ በቀጳዶቅያ፣ በእስያና በቢታንያ ለተበተኑት ለተመረጡት" ነው (በ 1 ጴጥሮስ 1፡1)። እንዲህ ሲል ጽፏል፤

*እናንተ ቀድሞ ወገን አልነባራችሁም አሁን ግን የእግዚአብሔር ወገን ናችሁ፤ እናንተ ምሕረት ያገኛችሁ አልነበራችሁም አሁን ግን ምሕረትን አግኝታችኋል።*

**1 ጴጥሮስ 2፡10**

እነዚህ ቃላቶች የተወሰዱት ከሆሴዕ 1፡6፣ 1፡9 እና 2፡1 ላይ ሲሆን (በተጨማሪ ሆሴዕ 2፡23ን ይመልከቱ)። ጴጥሮስ ልክ እንደ ጳውሎስም በሆሴዕ የተነገረውን ክፍል ለቤተ ክርስቲያን ተግባራዊ ሲያደርግ እንመለከታለን! እሱ ልክ እንደ ጳውሎስ በሆሴዕ 2፡1–3 ላይ የተሰጠውን ተስፋ እንደ ተፈጸመ ይቆጠረዋል። ከዚህ በተጨማሪ ይህ ፍጻሜ አሕዛብን እንደሚጨምር ያውጃል!

በሆሴዕ መጽሐፍ የተወሰነን ቢሆን ኖሮ የጳውሎስና የጴጥሮስ ትርጓሜዎች አንጠባበቅም ነበር። እንዳውም ሆሴዕ በሆሴዕ 2፡1–3 ባለው ክፍል ውስጥ አሕዛብ የሚለውን ቃል አልተጠቀመም። ነገር ግን እሱ “የእሥራኤልን ልጆች ቁጥር” የሚለው ተጠቅሟል። ይሁን እንጂ የእነዚህ ሁለት ሐዋሪያት ትርጓሜ በሆሴዕ ውስጥ አለምኖሩ ሐዋሪያትን እነዚህን ቃላት በተሳሳተ መንገድ ተርድተው አዲስ ነገር እንዲናገሩ “ተገደዋል” ብለን እንድናስብ ሊያደርገን አይገባም። ከዚህ ይልቅ እግዚአብሔር ሁልጊዜ የተስፋውን ቃል በዚህ መንገድ ለመመለስ አስቦ እንደነበር ማየት አለብን። አሕዛብንም ከአይሁዶች ጋር ማዳን የምንግዜም የእግዚአብሔር እቅዱ ነበርና።

በአዲስ ኪዳን ውስጥ ትንቢቶች በሚያስደንቅ ሁኔታ ሲፈጸሙ እናያለን። ብዙውን ጊዜ አንድ ትንቢት ከመጀምሪያው ከተነገረበት ጊዜ አንስቶ ወደ መፈጸም እስኪደርስ ድረስ “እያደገ” ይሄዳል። ስለዚህ የትንቢቱ ፍጻሜ መጀመሪያ ሲነገር ከነበርበት የበለጠ አንድነና ተብራርቶ በልጦ እናገኘዋለን። በግልጽ

እንደምናየውም በሆሴዕ 2፡1–3 ላይ የሆነውም ይኸው ነው። በሆሴዕ ውስጥ የተነገሩት ትንቢቶች በሆሴዕ ዘመን የነበሩቱ እሥራኤላውያን በሚረዱት መንገድ ነበር። ነገር ግን የትንቢቶቹ አፈጻጸም የሆሴዕ የመጀመሪያ አድማጮች ፈጽመው ሊገምቱት ከሚችሉት በላይ እጅግ የተለየ እና እጅግም የላቀ ነው። ክርስቲያንም ይሁኑ፣ አይሁዳዊ ወይም አሕዛብ ይህ መልዕክት ለእርሶም ነው!

የሚቀጥለውን የሆሴዕ መልእክት ከመመልከታችን በፊት እስቲ ጥቂት ጊዜ ወስደን ጳውሎስና ጴጥሮስ እነዚህ በሆሴዕ የሚገኙት ትንቢቶች በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ፍጻሜያቸውን አግኝተዋል የሚያስብል መደምደሚያ ላይ የደረሱበትን ምክንያት እንመልከት።

ቀላሉ መልስ ኢየሱስ ነው የሚል ነው። ጳውሎስና ጴጥሮስ እግዚአብሔር ለእሥራኤላውያን የሰጣቸው ተስፋዎች በኢየሱስ ሲፈጸሙ አይተዋል። ጳውሎስ እያንዳንዱ የእግዚአብሔር ቃል ኪዳን (ማለት እየተናገረ ያለው በብሉ ኪዳን ስላለው ተስፋዎችን ነው) ፍጻሜውን ያገኘው በክርስቶስ ነው እስከ ማለት ድረስ ሄዷል።

> *እግዚአብሔር ለሰጠው የተስፋ ቃል ሁሉ አዎን ማለት በእርሱ ነውና፤ ስለዚህ ለእግዚአሔር ስለ ክብሩ በእኛ የሚነገረው አሜን በእርሱ ነው።*
>
> **2 ቆሮንቶስ 1፡20**

በሐዋሪያት እይታ የወንጌል ክስተት– ማለትም የኢየሱስ ሕይወት፣ ሞት፣ እና ትንሳኤ– የእግዚአብሔርን የብሉይ ኪዳን ተስፋዎች ፍጻሜያቸውን አመጣ ( በሆሴዕ 1 ላይ እንደ ተመለከትናቸው ተስፋዎች ማለት ነው)። ይህ በአዲስ ኪዳን ውስጥ ተደጋግሞ ተገልጿል።

> *እኛም ለአባቶቻችን የተሰጠውን ተስፋ የምስራቹን ለእናንተ እንሰብካለን። ይህን ተስፋ እግዚአብሔር በሁለተኛው መዝሙር ደግሞ፤ አንተ ልጄ ነህ እኔ ዛሬ ወለደሁህ ተብሎ እንደ ተጻፈ፤ ኢየሱስን አስንሥቶ ለእኛ ለልጆቻቸው ፈጽሞአልና፤*
>
> **የሐዋሪት *ሥራ* 13፡32–33**

እንግዲህ ከዚህ የበለጥ ግልጽ ሊሆን ይችላልን? እግዚአብሔር ኢየሱስን ከሞት በማስነሳት ለአባቶች የገባውን ቃል ፈጽሟል። ስለዚህ የወንጌል ክስተት እነዚህን ተስፋዎች ወደ እውነታነት የተቀየሩበት ክስተት ነው።

ነገር ግን ስለ አሕዛብስ? እነዚህ ጥቅሶችስ ስለ "የእሥራኤል ልጆች" እንደሆኑ አድርገው መናገራቸውስ እንዴት ነው? ቤተ ክርስቲያን እንደምንም እሥራኤልን ትተካለች ብለን ማሰብ የለብንም። ቤተ ክርስቲያን እሥራኤልን አላፈናቀለችም ወይም ገፍታ አላስወጣችም፤ እንደዚሁም ለእሥራኤል የተባለውንም ተስፋ ለራስዋ አልወሰደችም። ለእስራኤል የተባሉት ተስፋዎች አሁንም ፍጻሜያቸውን የሚያገኙት በእሥራኤል ብቻ ነው። ስለዚህ ተስፋዎቹን ለማግኘት ደግሞ እሥራኤላዊ መሆን ያስፈልጋል። በሚቀጥሉት ጥቅሶች መሠረት በክርስቶስ ያሉት አሕዛብ የሆኑት ያ ነው። አሕዛብ በክርስቶስ በኩል እውነተኛ "የአብርሃም ልጆች ሆነዋልና።"

*እንግዲያስ ከእምነት የሆኑት እነዚህ የአብርሃም ልጆች እንደ ሆኑ እወቁ። መጽሐፍም እግዚአብሔር አሕዛብን በእምነት እንዲያጸድቅ አስቀድሞ አይቶ፤ በአንተ አሕዛብን ሁሉ ይባረካሉ ብሎ ወንጌልን ለአብርሃም አስቀድሞ ሰበከ። እንደዚህ ከእምነት የሆኑት ካመነው ከአብርሃም ጋር ይባረካሉ።* ገላትያ 3፡7–9

*በእንጨት የሚሰቀል ሁሉ የተረገመ ነው ተብሎ ተጽፎአልና ክርስቶስ ስለ እኛ እርግማን ሆኖ ከሕግ እርግማን ዋጀን፤ የመንፈስን ተስፋ በእምነት እንድንቀበል የአብርሃም በረከት ወደ አሕዛብ በኢየሱስ ክርስቶስ ይደርስላቸው ዘንድ።* ገላትያ 3፡13–14

*ነገር ግን በኢየሱስ ክርስቶስ ከማመን የሆነው የተስፋ ቃል ለሚያምኑ ይሰጥ ዘንድ መጽሐፍ ከኃጢአት በታች ሁሉን ዘግቶታል።* ገላትያ 3፡22

*አይሁዳዊ ወይም የግሪክ ሰው የለም፣ ባሪያ ወይም ጨዋ ሰው የለም፣ ወንድም ሴትም የለም፣ ሁላችሁ በክርስቶስ ኢየሱስ አንድ ሰው ናችሁና። እናንተም የክርስቶስ ከሆናችሁ እንኪያ የአብርሐም ዘር እንደ ተስፋውም ቃል ወራሾች ናችሁ።* ገላትያ 3፡28–29

በሌላ መንገድ ለመግለጽ ያህል፤ ጳውሎስ ለሮም ቤተ ክርስቲያን በጻፈው ደብዳቤ ላይ "አይሁዳዊነት" ውጫዊ ሳይሆን የውስጥ ጉዳይ መሆኑን ተናግሯል።

*በግልጥ አይሁዳዊ የሆነ አይሁዳዊ አይደለምና፤ በግልጥ በሥጋ የሚደረግ መገረዝ መገረዝ አይደለምና፤ ዳሩ ግን በሥውር አይሁዳዊ የሆነ አይሁዳዊ ነው፤ መገረዝም በመንፈስ የሚደረግ የልብ መገረዝ ነው እንጂ በመጽሐፍ አይደለም፤ የእርሱ ምስጋና ከእግዚአብሔር እንጂ ከሰው አይደለም።* ሮሜ 2፡28–29

ይህ አስገራሚ የሆነው የአሕዛብን የአብርሃም ዘር መሆን ጉዳይ በሌሎች መንገዶች ወዲያውኑ ግልጽ ባልሆነበት ሁኔታ ታይተዋል። ለምሳሌ የጴጥሮስን የመጀመሪያ መልዕክት መግቢያ ይመልከቱ። አንባቢዎቹ "ለተበተኑ መጻተኞች" ብሎ በተለምዶ ለአይሁዶች ብቻ የሚሠራውን የአነጋገር ዘይቤ በመጠቀም በሮም ግዛት ውስጥ ለነበሩቱ (አብዛኛዎቹ አሕዛብ ነበሩ) በማለት ይጠራቸዋል!

*የኢየሱስ ክርስቶስ ሐዋሪያ ጴጥሮስ . . . ለተመረጡት በጳንጦስና በገላትያ፣ በጳቀዶቅያም በእስያም፣ በቢታንያም ለተበተኑ መጻተኞች፤ . . .* 1 ጴጥሮስ 1፡1–2

ያዕቆብም በተመሳሳይ መንገድ መልዕክቱን "ለተበተኑ ለአሥራ ሁለቱ ወገኖች" በማለት ገልጿል ያዕቆብ 1፡ 1። አንባቢው ግን ይህ ለቤተ ክርስቲያን የተላከ ደብዳቤ መሆኑን ልብ ሊል ይገባል! እንግዲህ ያዕቆብ እንደ ጳውሎስም እና እንደ ጴጥሮስም ስለ አሕዛብ ክርስቲያኖች ሲናገር የእሥራኤል ሕዝብ አካል እንደሆኑ አድርጎ ተናግሯል።

እንግዲህ በግልጽ ለማየት እንደሚቻለው ሐዋሪያት የሚያምኑት አሕዛብ "የአብርሃም ልጆች" እንደሆኑ አድርገው ነበር፤ ነገር ግን ይህ የሆነው እንዴት ነው? እንዴትስ አይሁዶች ሊባሉ ይችላሉ? መልሱ በኢየሱስ ነው የሚል ነው። በአዲስ ኪዳን በተደጋጋሚ የሚያምኑ አሕዛብ (እና አይሁዶች) "በክርስቶስ" እንደሆኑ ተነግሮናል። "በክርስቶስ" የሆነ ማንም (አይሁዳዊ ወይም አሕዛብ) የአብርሃም ልጅ በመሆን ለእሥራኤል የተገባውን የተስፋ ቃል ወራሽ እንደሆነ ተቆጥሯል። ኢየሱስም የአብርሃም እውነተኛ ዘር ነው።

*ለአብርሃምና ለዘሩም የተሰፋው ቃል ተነገረ። ስለብዙዎች እንደሚነገር፡–"ለዘሮቹም አይልም፤" ስለ አንድ እንደሚነገር ግን፡– "ለዘርህም ይላል።" እርሱም ክርስቶስ።* ገላትያ 3፡16

በሌላ አነጋገር ኢየሱስ ራሱ እሥራኤል ነው ማለት ነው። ይህ አንድ ሰው እርሱም ኢየሱስ በዚህ መልኩ የእግዚአብሔር ሕዝብ ነው። በብሉይ ኪዳን የተነገሩት ተስፋዎች ሁሉ ፍጻሜያቸውን የሚያገኙትም በእርሱ ነው። መሲሑ (ኢየሱስ) በኢሳይያስ መጽሐፍ ውስጥ ካሉት "የአገልጋይ መዝሙሮች" በአንዱ በግልጽ እሥራኤል ተብሎ ተጠቅሷል፡-

*እርሱም፡– እሥራኤል ሆይ አንተ ባሪያዬ ነህ በአንተም እከበራለሁ አለኝ።* ኢሳይያስ 49፡3

ይህ ጥቅስ ትልቅ እንድምታ አለው። መሲሑ እሥራኤል መሆኑን ብቻ ሳይሆን እንደ እሥራኤልም እግዚአብሔር የሚከብርበት እርሱ እንደሆነም ይናገራል። እግዚአብሔር ለእሥራኤልውያን ያለውን ዓላማ የሚፈጽመው በእርሱ ነውና።

በእሥራኤል ሕዝብ (በብሉይ ኪዳን) እና በኢየሱስ መካከል ያለውን መመሳሰል ግምት ውስጥ ማስገባት ወሳኝ ነው። እነዚህ በአጋጣሚ አይደሉም። የኢየሱስ ሕይወት ሆን ተብሎ የእሥራኤልን ታሪክ ያስተጋባል። ለምሳሌ እሥራኤላውያን የእግዚአብሔር ልጅ ተብሎው ነበር ሆኖም ይህ ስም በሆሴዕ 1፡9 ላይ ተሽሯል። ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጅ ተብሎ ተጠርቷል (ማርቆስ 1፡11 ይመልከቱ)– ይህ ስም መቼም ቢሆን አይሻርም። የእሥራኤል ወንድ ሕፃናት በፈርዖን ለመታረድ ኢላማ ተደርገዋል እናም የተወልዱት በዕብራውያን አዋላጆች ታማኝነት ምክንያት ነው (ዘጸአት 1፡15–22 ይመልከቱ)። ኢየሱስም በሄሮዱስ ለመታረድ ዒላማ ተደርጎበታል እናም ነጻ ወጣ (ማቴዎስ 2፡1–18 ይመልከቱ)። ኢሳይያስ አሕዛብ ወደ እሥራኤል መጠተው የወርቅና የእጣን ስጦታዎች እንደሚያመጡላት ትንቢት ተናግሯል (ኢሳይያስ 60፡1–6 ይመልከቱ)። ሰብአ ሰገል የኢየሱስን ክበር በመገንዘብ ወርቅና ዕጣን በማምጣት ይህንን ትንቢት ተፈጻሚ እንዲሆን አድርገዋል (ማቴዎስ 2፡1–12 ይመልከቱ)። እግዚአብሔር እሥራኤልን ከግብፅ ጠራቸው (ዘጸአት 1–15 ይመልከቱ)። እግዚአብሔር ኢየሱስንም ከግብፅ ጠራው (ማቴዎስ 2፡13–15 እና ሆሴዕ 11፡1 ይመልከቱ)። የእሥራኤል በቀይ ባሕር ውስጥ ማለፍ (በሐዲስ ኪዳን የጥምቀት ምሳሌ ሆኖ አገልግሏል)፤ እሥራኤል ወደ ምድረበዳ ተውስዶ ለ40 አመታት እንደ ተፈተነ። ኢየሱስም በዮርዳኖስ ወንዝ ከተጠመቀ በኋላ ወዲያውኑ ወደ ምድረበዳ ተውስዶ ለ40 ቀናት ተፈትኗል። ኢየሱስ  የሰይጣንን ፈተናዎች በሙሉ ከዘዳግም ጥቅሶች በመጥቀስ ምላሽ የሰጠ ሲሆን ይህም ደግሞ በምድረበዳ በሙሴ ዘመን በነበረው የእሥራኤል ሕዝብ መካከል ያለውን ንጽጽር ያስረዳል። እሥራኤል 12 ነግዶችን ያቀፈ ነበር። ኢየሱስ ደግሞ– አዲሱ "እሥራኤል" 12 ሐዋሪያትን ሾሟል። እሥራኤል– በአሉታዊ መልኩ– በእግዚአብሔር መልካም ፍሬ የሚያፍራ ወይን ነው ተብሎ ተጠርቷል። ኢየሱስ ደግሞ እርሱ ራሱ እንደ እውነተኛ የወይን ግንድ እንደሆነ ተናግሯል (ዮሐንስ 15)። ኢየሱስ ብቻ መልካም ፍሬ ያፈራል። ኢየሱስ በአዲስ ኪዳን ጸሐፊዎች እንደ እሥራኤል በግልጽ ቀርቧል። የመጀመሪያው እሥራኤል ሊመጣ ያለውን የእውነተኛው እሥራኤል ምሳሌ ነበር እንላለን። የእሥራኤል ሕዝብ እውነተኛውን እሥራኤል እንዲያውቁ ለማድረግ መለኮታዊ ዕቅድ ነበርው። ኢየሱስ ግን በብሉይ ኪዳን ከነበሩት የእሥራኤል ሕዝብ በተለየ ሁኔታ የእግዚአብሔርን ትእዛዛት ፍጹም አድርጎ በመጠበቅ በቃል ኪዳኑ ተመላልሷል። ሁልጊዜ አባቱን ድስ የሚያሰኘውን ያደርግ ነበር። ለእሥራኤል የተባለው የቃል ኪዳን ተስፋዎች በሙሉ በኢየሱስ በትክክል ተፈጽመዋል፤ ምክንያቱም እሱ ቃል ኪዳኑን በፍፁም ስለሚጠብቅ ነው። ሁሉም ተስፋዎች ፍጻሚያቸውን የሚያገኙት በእርሱ ብቻ በመሆኑ "በእርሱ" ተብለው የተጠሩት ብቻ የእግዚአብሔር ተስፋዎች ተቀባይ ሊሆኑ ይችላሉ። በእርሱ የሆኑቱ ከእርሱ ጋር አብረው ይወርሳሉ። የኢየሱስ ለቃል ኪዳኑ መታዘዝ የእነርሱም መታዘዝ ሆኖ ይቆጠርላቸዋል። ይህ የእሥራኤል ልጆች እንደ "ባሕር አሸዋ" ሕዝብ የመሆን ተስፋ መፈጸም የጀመረው ኢየሱስ ከሙታን ተለይቶ በተነሳ ጊዜ እና ቤተ ክርስቲያ ደግሞ

በተመሠረተችበት ጊዜ ነው። የሐዋሪያት ሥራ መጽሐፍ የቤተ ክርስቲያንን እድገት ለመግለጽ ብዙ እርቀት ይሄዳል። ስለ ቤተ ክርስቲያን እድገት የሚናገሩትን እንዚህን ጥቅሶች አስደሳች ነገር ግን በአንጻራዊነት አስፈላጊ ያልሆኑ እውነታዎች አድርገን ማንበብ የለብንም። እግዚአብሔር በመጀመሪያ ለአብርሃም የተናገረውን የተስፋ ቃል እንዴት እንደሚፈጽም ማሳያዎች ሆነው ሊታዩ ይገባልና። እስቲ በሐዋሪያት ሥራ ውስጥ የሚከተሉትን ጥቅሶች እንመልከት፤

> *በዚህም ወራት ጴጥሮስ መቶ ሀያ በሚያህል በሰዎች ማኅበር አብረው በነበሩ በወንድሞቹ መካከል ተነሥቶ አለ . . .* የሐዋሪያት ሥራ 1፥15
> *ቃሉንም የተቀበሉ ተጠመቁ በዚያም ቀን ሦስት ሺህ የሚያህል ነፍስ ተጨመሩ፤* የሐዋሪያት ሥራ 2፡41
>
> *ጌታም የሚድኑትን ዕለት ዕለት በእነርሱ ላይ ይጨምር ነበር።* የሐዋሪያት ሥራ 2፡47ለ
>
> *ነገር ግን ቃሉን ከሰሙት ብዙዎች አመኑ የወንዶችም ቁጥር አምስት ሺህ ያህል ሆነ።* የሐዋሪያት ሥራ 4፡4
>
> *ሕዝቡ ግን ያከብሩዋቸው ነበር፤ የሚያምኑትም ከፊት ይልቅ ለጌታ ይጨመሩለት ነበር፤ ወንዶችና ሴቶችም ብዙ ነበሩ።* የሐዋሪያት ሥራ 5፥14
>
> *የእግዚአብሔርም ቃል እየሰፋ ሄደ በኢየሩሳሌምም የደቀ መዛሙርት ቁጥር እጅግ እየበዛ ሄደ፤ ከካህናትም ብዙ ሰዎች ለሃይማኖት የታዘዙ ሆኑ።* የሐዋሪያት ሥራ 6፡7
>
> *በይሁዳም ሁሉና በገሊላ በሰማሪያም የነበሩት አብያተ ክርስቲያናት በሰላም ኖሩ ታነጹም፤ በእግዚአብሔርም ፍርሃትና በመንፈስ ቅዱስ መጽናናት እየሄዱ ይበዙ ነበር።* ሐዋሪያት ሥራ 9፡31

የሐዋሪያት ሥራ ጸሐፊ ሉቃስ ቤተ ክርስቲያን እያደገች መሆንዋን ለማሳየት ፍላጎት እንደነበረው በግልጽ ያሳያል። ይህን መረጃ እንዲጨምር እግዚአብሔር ለምን አነሳሳው? የእሥራኤል ልጆች “እንደ ባሕር አሸዋ” እንደሚሆን የገባቸው ተስፋዎች እየተፈጸሙ እንደነበር በግልጽ ለማሳየት እነዚህን ጥቅሶች እንዲጨምር

እግዚአብሔር በመንፈሱ አነሳስቶታል! ደግሞም ይህ አስደናቂ እድገት ከክርቶስ ትንሳኤ ጋር መገናኘቱን ማስተዋል አስፈላጊ ነው።

የዘጸአት መጀመሪያ ከሐዋሪያት ሥራ መጀመሪያ ጋር ማነጻጸር አስደሳች ነው። ዘጸአት እንደ የሐዋሪያት ሥራ ሁሉ "የእሥራኤል ልጆች" እድገት ጎላ አድርጎ ይገልጻል።

*የእሥራኤልም ልጆች አፈሩ እጅግም በዙ ተባዙም እጅግም ጸኑ ምድሪቱም በነርሱ ሞላች።* **ዘጸአት 1፡7**
*ነገር ግን እንዳስጨነቁዋቸው መጠን እንዲሁ በዙ እጅግም ጸኑ፤ ከእሥራኤልም ልጆች የተነሳ ተጸይፈዋቸው ነበር።* **ዘጸአት 1፡12ሀ**

*ሕዝቡም በዛ እጅግም ጸና።* **ዘጸአት 1፡20ለ**

የዘጸአት ጸሐፊ (ሙሴ) ልክ እንደ ሐዋሪያት ሥራ ጸሐፊ የእሥራኤል ልጆች እየበዙ መሆናቸውን ለማሳየት ፍላጎት ነበረው። እሱም ቢሆን ይህን መረጃ እንዲጨምር እግዚአብሔር ለምን ይሆን ያነሳሳው?

የእሥራኤል ልጆች "እንደ ባሕር አሸዋ" እንደሚበዙ የተነገረውን የተስፋ ቃል እንደሚፈጸም በግልጽ ለማሳየት እነዚህን ጥቅሶች እንዲካተቱ እግዚአብሔር በመንፈሱ ያነሳሳው ይመስላል!

በዘጸአትና በሐዋሪያት ሥራ መካከል ያለውን ግኑኝነት ሊታለፍ አይገባም። ቤተክርስቲያን እንደ አዲስ "የእሥራኤል ልጆች" ትመስላለችና። አንተም ክርስቲያን ከሆንክ የዚያ የተስፋ ቃል አንዱ ክፍል ምላሽ ተሰጥቷል ማለት ነው። "የእሥራኤል ልጆች" እንደ ባሕር አሸዋ እጅግ በጣም ብዙ ሆነዋል። አሁንም ይህ የሆነው ቤተ ክርስቲያን እሥራኤልን ስለተካች አይደለም። አይሁዳውያንና አሕዛብ ወደ እውነተኛው እሥራኤል ማለትም ወደ ኢየሱስ በንድነት ስለግቡ ነው እንጂ ፤ እግዚአብሔር የሰጣቸው ተስፋዎች ሁሉ ፍጻሜያቸው የሚያገኙትም በኢየሱስ በኩል ነውና።

በሆሴዕ 2፡1–3 ላይ የተነገረው "የእሥራኤል ልጆች" አስደናቂ እድገት ብቻ አይደለም። ይህ ምዕራፍ ደግሞ የእሥራኤል ልጆች አንድ አለቃ (ማለትም አንድ መሪ) እንደሚኖራቸው ይናግራል።

*የይሁዳ ልጆችና የእሥራኤል ልጆች በአንድነት ይሰበሰባሉ፤ ለእነርሱም አንድ አለቃ ይሾማሉ፤ ከምድሪቱም ይወጣሉ፤ የኢዝራኤል ቀን ታላቅ ይሆናል።* **ሆሴዕ 2፡2**

የአዲስ ኪዳን አንባቢዎች ይህ ትንቢት በሆነ መንገድ በክርስቶስ ተፈጻሚ እንደሚሆን አስቀድመው ሊጠባበቁ ይገባል። በእርግጥም ይፈጸማል። በዚህ ቁጥር የተጠቀሰው አለቃ ኢየሱስ ነው። የይሁዳና የእሥራኤል ልጆች እንዲመራቸው የሾሙት እሱ ነው።

በሆሴዕ ዘመን እንደነበርው ሁሉ ራሳቸውን "የእግዚአብሔር ልጆች" ብለው የሚጠሩ ሁለት ዓይነት ሰዎች ከዚህ በኋላ አይኖርም። ከዚህ ይልቅ "የይሁዳ ልጆችና የእሥራኤል ልጆች" ወደ አንድ ሕዝብ ይሰበሰባሉ። አንድምታው ግን እግዚአብሔር ነው የሚሰበስባቸው። ሄዶ የጠፉትን የእስራኤልን በጎች ሰብስቦ "በአንድ መሪ" ወይም እረኛ ሥር ያደርጋቸዋል። ይህ ጥቅስ ግን ስለ መሪው ወይም እረኛው ብዙ አይናገርም። ነገር ግን የሆሴዕ የመጀመሪያ አድማጮችን ፍላጎት ለማርካት እዚህ የተጠቀሰው መልዕክት በቂ ነገር ነው። እነዚህ ጥቅሶች እየጨመረ የመጣውን የእግዚአብሔር ሕዝቦችን የሚመራውን አምላካዊ ንጉሥ እንዲናፍቁ የበለጠ ሊያደርጋቸው ይገባ ነበር። ነገር ግን ይህ መልዕክት ለሆሴዕ ለመጀመሪያ አድማጮች ብቻ የታለመ አልነበረም።  የኢየሱስን ንግሥና ዘመን ለምናከብር ለእኛም ጭምር ነው እንጂ። ይልቅስ መልዕክቱ የኢየሱስ መምጣት ከረጅም ዘመን ጀምሮ እንደ ተነገረ ያስታውሰናል።
ኢየሱስ በእግዚአብሔር እቅድ ውስጥ በኋላ የተጨመረ ሐሳብ አይደለም። እሱ ኢየሱስ ግን ሁልጊዜ በእግዚአብሔር ሲታሰብ የነበር የሕዝቡ "መሪ" ነው። ነገሥታት ቢቀያየሩም የእግዚአብሔርን ሕዝብ በአግባቡ መጠበቅ አልቻሉም ነበር። ምክንያቱም ነገሥታቱ ራሳቸው ሕዝቡን ወደ ኃጢአት ይመሩት ነበርና። ይህ በተለይ በሰሜናዊው የእስራኤለ መንግሥት እውነት ነበር። ምናልባት በምድሪቱ ላይ የነበሩ ፈሪሃ እግዚአብሔር የነበራቸው ሰዎች ሁሌም እንደዚያ የሚቀጥል ሳይመስላቸው አይቀርም። የሆሴ መጽሐፍ ሁሉም የእግዚአብሔር ሰዎች ስለሚቀበሉት ስለሚመጣው መሪ ለአንባቢዎች ይናገራል። ደግሞ ሆሴዕ ስለሚመጣው ንጉሥ ሲናገር ይህ ለመጨረሻ ጊዜ አይደለም።

እስቲ ይህንን በሆሴዕ 1፡10–2፡1 ያለውን ረጅም መግቢያ ከመደምደማችን በፊት በሆሴዕ 1፡11 ላይ ያለውን የመጨርሻውን ትንቢት እንመልከት።

*ይሾማሉ፤ ከምድሪቱም ይወጣሉ፤ የኢዝራኤል ቀን ታላቅ ይሆናል።* **ሆሴዕ 2፡2ለ**

በተቀረው ጥቅስ ላይ በመመስረት ስንመለከተው ይህ ትልቅ ተስፋ እንደሆነ ግልጽ ነው፤ ነገር ግን ምን ማለት ነው? ይህንን የተስፋ ቃል ከማየታችን በፊት ኢይዝራኤል የሚለው ስም በአሉታዊ ስሜት በሆሴዕ ፣4–5 ተጠቅሶ እንመለከታለን። በንጉሡና በእሥራኤል ሕዝብ ላይ የሚመጣውን ፍርድ ያመለክታልና። እዚህ ጋ ደግሞ ኢይዝራኤል የሚለው ስም በአዎንታዊ መልኩ ጥቅም ላይ ሲውል እናገኘዋለን። እንግዲህ ይህ ስም በሁለት የተለያዩ መንገዶች እንዴት ጥቅም ላይ ሊውል ይችላል? ይህ አንዱ የግጥም ባህሪ ነው! ዕብራውያን ነቢያት እያንቀላፉ ያለን አንባቢ ትኩረት ለመሳብ በሚመስል መልኩ በሚያስገርም መንገድ ቃላትን ይጠቀማሉ። በሆሴዕ ፣4–5 ላይ በመመርኮዝ አንባቢው ኢይዝራኤል የሚለው ስም አሉታዊ እንዲሆን እየጠበቀ ሊሆን ይችላል። ነገር ግን አሁን እዚህ ጋ በአዎንታዊ መልኩ ጥቅም ላይ እየዋለ ስለሆነ አንባቢው ሊያስገርመው ይችል ይሆናል።

ኢይዝራኤል የሚለው ስም "እግዚአብሔር ይዘራል ማለት ነው። የስሙ ትርጉም በሆሴዕ ፣4–5 ላይ ባለው ትኩረት አለማድረጉ ጠቃሚ ነገር ነው። "እግዚአብሔር ይዘራል" ስንል እግዚአብሔር ይተክላል" ማለት ነው። ስለዚህ "የኢዝራኤል ቀን" እግዚአብሔር አንድን ነገር ወይም አንድን ሰው በአንድ ቦታ ላይ የሚተክልበትምን የጊዜ ገደብ የሚያመለክት ነው። ግን ምን እየዘራ ወይም እየተከለ ነው? ከዐውዱ – ጽሑፉ በመነሳት ስንመለከተው ሰውን – ሕዝቡን እየዘራ ወይም እየተከለ መሆኑ ግልጽ ነው! የት ነው የሚተክላቸው? መልሱ የሚገኘው "ከምድሪቱም ይወጣሉ የኢዝራኤል ቀን ታላቅ ይሆናል" የሚለውን ሐረግ ስንመለከት ነው። "ከምድሪቱ ይወጣሉ" የሚለው ቃል በተለምዶ ከግብፅ ከሚወጡት እሥራኤላውያን ጋር የተገናኘ መሆኑ በጣም አስፈላጊ ነው። ይህ ክፍል የሚናገረው እግዚአብሔር ሕዝቡን እንደገና ስለሚያድንበት ጊዜ ነው። ከዲሱ "ግብፅ" እንዲወጡ በማድረግ በመልካም ሥፍራ ይተክላቸው ነበር። ይህ ስለወደፊቱ መውጣት አስደናቂ ተስፋ ነው! ምንም እንኳን እሥራኤልውያን በመንፈሳዊ ግልሙትና ምክንያት ከምድሪቱ ቢባረሩም (ሆሴዕ ፣፣–9) በመጨረሻም እግዚአብሔር ሕዝቡን በማዳን ወደ ምድሪቱ ይመልሳቸዋል።

ይህ በመጀመሪያ በጨረፍታ የአይሁዳዊያን ዘር ወደ ዘመናዊቷ የእሥራኤል አገር መመለሳቸውን የሚያመለክት ቢመስልም ሐዋሪያት ግን እንደነዚህ ያሉትን ትንቢቶች በዚህ መንገድ አይተረጉሙም። ደግሞም የእግዚአብሔርን ሕዝብ በውጫዊ አካላዊ ባሕሪያት አይገልጹም። ይልቁንም የእግዚአብሔርን ሕዝብ የሚገልጹት በውስጣቸው ባለው ነገር ነው (ለምሳሌ ሮሜ 2፡28–29 ይመልከቱ)። ይህ እግዚአብብሔር በሱ የሚያምኑትን ሕዝቡን (አይሁድም ይሁኑ አሕዛብ) ወደ "መሠረት ያላትን እግዚአብሔር የሠራትንና የፈጠራትን ከተማ ወደሆነችው" ለማምጣት የገባው ተስፋ ነው (ዕብራዉያን ፲፡

10 ይመልከቱ)። ሕዝቡን ወደ “ትውልድ አገሩ” የተሻለ አገር ማለትም ወደ ሰማያዊትዋ” አገር ለማምጣት የተሰጠ ቃል ኪዳን ነው (ዕብራውያን 11፡16)። ስለዚህ ይህ የእግዚአብብሔርን ሕዝብ ወደ እግዚአብሔር ወደ አዘጋጀው ቦታ ለማምጣት እና በዚያ ለዘላለም ሊተክላቸው የገባው ቃል ኪዳን ነው (ራዕይ 21 እና 22 ይመልከቱ)።

ልክ እንድ ጤናማ ዛፎች የእግዚአብሔር ሕዝቦች “በውሃ ፈሳሾች” ዳር ይተከላሉ (መዝሙረ ዳዊት 1፡3 ይመልከቱ) እናም እግዚአብሔር ካዘጋጀው አዲስ አፈር ውስጥ ይበቅላሉ ፍሬያማም ይሆናሉ (መዝሙር ዳዊት 1፡3፣ ሕዝቅኤል 47፡1–12 ራዕይ 22፡1–2 ይመልከቱ)። ይህም አዳምና ሔዋን በኤደን ገነት “እንደተተከሉ” ሰዎችን ማስታውስ ይኖርበታል!

በሆሴዕ ዘመን እሥራኤላዊ ብሆን ወይም ከአገልግሎቱ በኋላ በጨለማው ዘመን (እና በእግዚአብሔር ቸርነት ቃሉን የተቀበልኩ ብሆን) ይህ መልዕክት የሚፈጸምበት ቀን (ማለትም ጊዜው) የሚርበኝ ይመስለኛል። ደግሞም በእኔ ዘመን “የእሥራኤልን መጽናናት” ለማየት ታላቅ ፍላጎት የሚፈጥርብኝ

ይመስለኛል (ሉቃስ 2፡25 ይመልከቱ)። እግዚአብሔር ራሱ ሕዝቡን የሚያድንበትና ወንዶችና ሴቶች ልጆቹን ባዘጋጀው መልካም ስፍራ ላይ የሚተክልበት ቀን ይናፍቀኝ ነበር።

ወደኋላ እንደሚመለከት ሰው እነዚህ ትንቢቶች፣ እነዚህ ቃላት በልቤ ደስታን ያመጣሉ እናም ለአባቴ ለንጉሴ ያለኝን ፍቅር ይጨምራሉ። ደግሞም በእግዚአብሔር ላአይ ያለኝን እምነት ይጨምራሉ። እግዚአብሔር የገባውን ተስፋ ሁሉ አድርጓል ደግሞም (እያደረገም ነው)! ደግሞም ከሚጠበቀው በላይ በሆነ መንገድ አድርጓል። እዚህ ጋ በማየው ምሕረት ተመስጫለሁ። ማለት ምሕረት ለእሥራኤላውያን (ከሞት በቀር ምንም የማይገባቸው) እና ለእኔም ቢሆን (ከሞት በቀር ምንም የማይገባኝ) ነበርኩ ግን ምሕረትን አገኘሁ። ስለዚህ በእምነት በእነዚህ ተስፋዎች ውስጥ ተካትቻለሁ ማለት ነው። በሆሴዕ 1 (እና በሌሎችም ብዙ የብሉይ ኪዳን ምንባቦች) ከተጠቀሱት ጥቅሶች ውስጥ ያስተጋባል ከተባሉት ውስጥ የሐዋሪያው ጴጥሮስ መልዕክት በሕይወቴ ተፈጽመዋል።

> *እናንተ ግን ከጨለማ ወደ ሚደነቅ በርሃኑ የጠራችሁን የእርሱን በጎነት እንድትናገ፤ሩ የተመረጠ ትውልድ የንጉሥ ካህናት ቅዱስ ሕዘብ ለርስቱ የተለየ ወገን ናችሁ። እናንተ ቀድሞ ወገን |*

*አልነበራችሁም አሁን ግን የእግዚአብሔር ወግን ናችሁ፤ እናንተ ምሕረት ያገኛችሁ አልነበራችሁም አሁን ግን ምሕረትን አግኝታችኋል።* **1 ጴጥሮስ 2፡9–10**

## *ሆሴዕ* 1፡1–3[18]

**2፡1 ገና[19] የእሥራኤልም ልጆች ቁጥር[20]**

---

[18] የዕብራይስጡ ጽሑፍ (አንዳንድ ጊዜ ማዞረቲክ ቴክስት፣ MT በመባል የሚታወቀው ማለት ነው) እና የብሉይ ኪዳን የግሪክ ጽሑፍ (አንዳንድ ጊዜ ሱፐታጀንት LXX በመባል የሚታወቀው) ምዕራፍ አንድን በቁጥር 9 ላይ ይደመድማል። በ MT እና LXX *ሆሴዕ* 2፡1–3 በሆሴዕ ምዕራፋ 2 ላይ ይገኛል። ይህም ምዕራፎችን ለመከፋፈል የበለጠ ምክንያታዊ መንገድ ነው። እንደዚሁም በአማርኛው የ1962 መጽሐፍ ቅዱስም ላይም በቁጥር 9 ላይ ያበቃል። ስለዚህ ቁጥር 10–11 በምዕራፍ 2፡ 1–2 ባለው ክፍል ላይ ተጽፏል።

[19] በእንግሊዥናው ESV መጽሐፍ ቅዱስ የመጀመሪያውን ቃል "ገና" ብሎ ተርጉሞታል። ይህ ቃል በ በሆሴዕ 1፡9 እና በሆእሴዕ 1፡10 ክስተቶች መካከል የተለየ ሽግግርን ያመለክታል። በ 1፡1–9 እና 2፡1–3 መካከል ያለውን ልዩነት በሁለት መንገዶች ሊታይ ይችላል፦ (1) **በእያንዳንዱ ክፍል ውስጥ ያሉትን የትንቢቶች ቃና ወይም ክብደት** በተመለከተ (2) **በእያንዳንዱ ክፍል ውስጥ የተነገሩት ትንቢቶች የሚፈጸሙበትን ጊዜ** በተመለከተ።

**የትንቢቶቹን ቃና በተመለከተ** በሆሴዕ 1፡1–9 አሉታዊ ነበር፤ ነገር ግን በሆሴዕ 2፡1–3 ደግሞ አዎንታዊ ነው። በጽሑፉ ውስጥ ኣንባቢን ለዚህ ፈጣን ለውጥ ከአሉታዊ ወደ አወንታዊነት የሚያዘጋጀው ምንም ነገር የለም። የዕብራይስጥ የተለመደ ገፅታ ደግሞ ትንቢቱ የእስራኤልን የወደፊት ሁኔታ በሚመለከት በአሉታዊ እና በአዎንታዊ መግለጫዎች መካከል በተደጋጋሚ እንደሚገለባበጥ ነው። ይህ በአሉታዊና በአዎንታዊ መግለጫዎች መካከል ያለውን ፈጣን የመገለባበጥ ዑደት በሆሴዕ ውስጥ ራሱን ይደግማል። *ሆሴዕ* 1፡1–9 አሉታዊ ነው። የእሥራኤልን መንግሥት ጥፋትና ፍጻሜ ተንብዮአል። እግዚአብሔርና እሥራኤል ከአሁን በኋላ አንዳቸው ከሌላው ምንም ዓይነት ልዩ ዝምድና እንደሌላቸው ይናገራል። *ሆሴዕ* 2፡1–3 ደግሞ አዎንታዊ ነው። ይህም ደግሞ ስለ እሥራኤል ከባርነት ነጻ መውጣቷንና የእግዚአብሔር ሕዝብ ደግሞ ታላቅ መባዛት በተመረጠው መሪ ወደፊት ስለሚኖረው ጊዜ ይናገራል። በሆሴዕ 2፡4–15 ትንቢቱ እንደገና አዎንታዊ ይሆናል። ዳግመኛም ይህ ንድፍ በሆሴዕ (እና በሌሎች የነቢያት መጻሕፍት) ተደግሟል።

**የፍጻሜውን ጊዜ በተመለከተ** 1፡1–9 ቃሉ ከተነገረ በኋላ ብዙም ሳይቆይ የተፈጸሙትን ክንውኖች መተንበይ ነበር። በቁጥር 1–9 የተነገረው ፍርድ በሆሴዕ ዘመን ይኖሩ የነበሩትን እሥራኤላዋያንን ይመለከታል። ይሁን እንጂ በሆሴዕ 2፡1–3 ሆሴዕ ትንቢት በተናገርበት ወቅት የሚኖሩትን እሥራኤላውያን አይመለከትም። ይልቁንም ክፍሉ ከርጅም ጊዜ በኋላ ካለው ጊዜ ጋር ይዛመዳል። የሆሴዕ የመጀመሪያ አድማጮች ይህ ጊዜ መቼ እንደሚመጣ አያውቁም ነበር። ይህንን የተሃዶሶ ጌዜ በእምነት እንዲጠብቁ ተገደዱ። ዛሬ ሆሴዕን የሚያነቡ ሰዎች በሆሴዕ 2፡1–3 ላይ የተነገረው ጊዜ እንደ ደረሰ ማወቅ አለባቸው። መፈጸም የጀመረውም ኢየሱስ ሞቶ በተነሳ ጊዜ ነው። ደግሞም ዛሬም እየተፈጸመ ነው። ወደ ፊት ኢየሱስ በሚመለሰበት ጊዜ ደግሞ ይጠናቀቃል። በሆሴዕ 2፡1–3 ላይ ያለውን የተስፋ ቃል በብሉይ ኪዳን በሌሎች ብዙ ቦታዎች ተገልጾዋል። ለምሳሌ ዘዳግም 4፡30–31፣ ኢሳይያስ 2፡2–5፣ ሆሴዕ 3:5 እና ሚክያስ 4፡1–5 ይመልከቱ።

[20] "የእሥራኤል ልጆች" የሚለው እንደ ሐዋሪያት አባባል ከሆነ የአይሁዳውያን ዘር ብቻ አያመለክትም። ነገር ግን የሚያመለከተው በእምነት "የአብርሃም ልጆች" ተብለው የተቆጠሩቱ ነው (ገላትያ 3፡7፣ 14 እና 28–29 ይመልከቱ)። ሐዋሪያው ጳውሎስም እንደገለጸው ከሆነ "በውጫዊው መገረዝ አይሁዳዊ የሆነ ማንም የለም፤ መገረዝም ደግሞ በውጫዊና በሥጋ የሚደረግ አይደለም" ነው የሚለው። በመንፍስ ቅዱስ "የተገረዙት" ሁሉ ግን እውነተኛ "የእሥራኤል ልጆች" እነሱ ናቸው (ሮሜ 2፡28–29 ይመልከቱ)። ይህም "የዲስ ኪዳን" እውነት ብቻ አይደለም። ነገር ግን በብሉይ ኪዳን ውስጥ በብዙ ማስረጃ ተገልጾ ይታያል። ለምሳሌ ጋለሞታይቱ ረዓብ (አህዛብ ሴት) ወደ እሥራኤላውያን ተጨምራለች (ኢያሱ 2 እና 6፡ 22–25) እና በእሥራኤልም ምድር ኖረች። ደግሞም የጌታ የኢየሱስ ቅድመ አያት የመሆን ክብር እንኳን ተሰጥቷታል (ማቴዎስ 1፡5 ይመልከቱ)። አካን (አይሁዳዊ ሰው) ባለመታዘዙ ምክንያት ከሕዝቡ ተለይቷል (ኢያሱ 7፡10–26 ይመልከቱ)። በእነዚህ ከአዲስ ኪዳን በፊት ባሉት ዘመናት እንኳን አንባቢው እምነት ያለው እና በታዛዥነት የሚራመድ

እንደማይሰፈና እንደማይቆጠር[21] እንደ ባሕር አሸዋ ይሆናል፤ እንዲህም ይሆናል፤ እናንተ ሕዝቤ አይደላችሁም ተብሎ በተነገረበት በዚያ ስፍራ የሕያው አምላክ ልጆች ይባላሉ።[22]

**2 የይሁዳ ልጆችና የእስራኤል ልጆች በአንድነት ይሰበሰባሉ፤**[23]

---

"እውነተኛ አይሁዳዊ"ን እንዲያይ እየተመራ ነው። እንደዚሁም በዮሐንስ 11፡51–52 ያለውን የየሐንስን ክፍል በጥንቃቄ ይመለከቱ።

[21] "የእሥራኤል ልጆች" እንደ "ባሕር አሸዋ" መሆናቸውን መግለጹ፣ እግዚአብሔር ለአብርሃም፣ ለይስሐቅ እና ለያዕቆብ የገባውን የቃል ኪዳን ተስፋ ወደ ኋላ ተመለሶ ሲታይ ግልጽ ነው (ዘፍጥረት 13፡16፣ 22፡17–18፣ 26፡3–5፣ 28፡14 እና 32፡12 ይመልከቱ)። ሆሴዕ 1፡10 በሆሴዕ 1፡1–9 ላይ የተነገረው ጥፋትና ፍቺ ቢኖርም ይህ የተስፋ ቃል በእርግጥ እንደሚፈጸም ይጠቁማል። በቃል ኪዳኑ መሠረት እግዚአብሔር የአብርሃምን ዘር–"የእሥራኤል ልጆች" "እንደ ባሕር አሸዋ" ያበዛቸዋል። ስለ ቤተ ክርስቲያን ፈጣን እድገት የሉቃስ መግለጫዎች የዚህ ትንቢት ፍጻሜ አካል ሆነው መታየት አለባቸው (ለምሳሌ የሐዋሪያት ሥራ 2፡41፣ 5፡14 እና 6፡1 ይመልከቱ)።

[22] ይህ ትንቢት በሚፈጸምበት "ቀን" በእስራኤል ውስጥ ያሉት ሰዎች "ሕዝቤ አይደሉም" ተብሎ አይገለጽም። ይልቁንም **"የሕያው እግዚአብሔር ልጆች"** ተብለው ይገለጻሉ። ይህ ክፍል ከዕብራይስጡ MT የተተረጎሙ ናቸው። ግሪኩ (LXX) ይህንን ሐረግ **"የሕያው እግዚአብሔር ልጆች"** በማለት ይተረጉመዋል። ደግሞ ትክክለኛው ተመሳሳይ ሐረግ (ከነጠላው በስተቀር) በማቴዎስ 16፡16 ጴጥሮስ ኢየሱስን **"የሕያው እግዚአብሔር ልጅ"** ብሎ የጠራበት ክፍል መጠቀሙ ትኩረት የሚስብ ነው። ስለዚህ የማቴዎስ ወንጌል በዚህ በሆሴዕ 1 እና በኢየሱስ ትንቢት መካከል ግኑኝነት እየፈጠረ ያለ ይመስላል። ኢየሱስ ግን ብቻውን አይደለም። ክርስቶስ የእግዚአብሔር ሕዝብ ራስ ሆኖ ክፍ ስላደረገው "ብዙ ልጆችን ወደ ክብር እያመጣ ነው" (ዕብራውያን 2፡10)። እርሱ "በብዙ ወንድሞች መካከል በኩር ነው" (ሮሜ 8፡29 ይመልከቱ)። ይህ ትንቢት የተፈጸመው በክርስቶስ መምጣት ምክንያት ነው። ደግሞም "የሕያው እግዚአብሔር ልጆች" ተብለን የምንጠራበትም ምክንያት እርሱ ነው (ሕዝቅኤል 37፡27፣ ሮሜ 9፡26፣ 2 ቆሮንቶስ 6፡16 እና 1 ጢሞቴውስ 3፡15 ይመልከቱ)!

"ሕያው አምላክ" የሚሉት ቃላት ጥንቃቄ የተሞላ ትኩረት ይፈልጋሉ። ምክንያቱም በሆሴዕ ዘመን ይኖሩ የነበሩት ሰዎች የብር፣ የወርቅና የድንጋይ አማልክት ያመልኩ ነበር። እነዚህም አማልክት ሕይወት አልነበራቸውም። እንደ እውነቱ ከሆነ ሰዎች እነዚህን አማልክት የሠሩት "በገዛ እጆቻቸው" ነው (ኢሳይያስ 2፡8 ይመልከቱ)። ስለዚህ ሰው ሰራሽ አማልክት ማምልክ በእጅጉ ሞኝነት እንደሆነ ግልጽ ነው። እንዲህ ያለውን አምላክ ምንም የማዳን ኃይል የለውም። ሌላው ይቅርና ራሱን እንኳን ማዳን አይችልም። ሕልውናውም በሰው ላይ የተመሰረት ነው! የእሥራኤል አምላክ ግን እርሱ "ሕያው አምላክ" መሆኑን ዘወትር ያውጃል። እንደ እርሱ ያለ ሌሎች አምላክቶች የሉም። እግዚአብሔር በሰው ላይ በፍጹም አይደገፍም (የሐዋሪያት ሥራ 1፡25 ይመልከቱ)። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ "ሕያው አምላክ" የሚለው ሐረግ በብዙ ምንባቦች ውስጥ ጥቅም ላይ ውሏል፤ (ለምሳሌ ዘዳግም 5፡26፤ ኢያሱ 3፡10፤ 1 ሳሙኤል 17፡26፣ 17፡36፤ 2 ነገሥት 19፡4፣ 19፡16፤ መዝሙረ ዳዊት 42፡2፣ 84፡2፤ ኢሳይያስ 37፡4፣ 37፡17፤ ኤርሚያስ 10፡10፣ 23፡36፤ ዳናኤል 6፡20 እና 6፡26 ይመልከቱ)። እነዚህ ጥቅሶች ሁሉ በግልጽ እንደሚያሳዩት "ሕያው አምላክ" የሚለው ስም እግዚአብሔር በእርግጥ ሕያው ከመሆኑ እውነታ ጋር የተያያዘ መሆኑን ነው። እግዚአብሔር በዓለም ሁሉና በሁሉም ሰዎች ሕይወት ውስጥ ንቁ ነው። የሚጠሉትን ሁሉ ቃላት ሰምቶ ለክፋታቸው ምላሽን ይሰጣል። የሚወዱትን ሰዎች ጩኸት ደግሞ ሰምቶ ለሕዝቡ ሲል ይሠራል። ማንም ከሕያው አምላክ ሊሰውር አይችልም። ይህም ለሚወዱት ታላቅ በረከት ነው። እግዚአብሔር ለማይፈልጉ ደግሞ ታላቅ ኀዘን ነው።

[23] ዮሐንስ 11፡51–52 እና ኤፌሶን 2፡11–22 ይመልከቱ።

ለእነርሱም አንድ አለቃ ይሾማሉ፤[24] ከምድሪቱም ይወጣሉ፤[25] የኢይዝራኤል ቀን ታላቅ ይሆናልና።[26]

---

[24] "አንድ መሪ" የሚለው የእግዚአብሔርን ሕዝብ **ከባርነት ምድር ነጻ አውጥቶ** በሁለተኛ ዘጸአት የሚመራ አንድ የተለይ መሪን የሚያመለክት ነው። የዚህ "መሪ" መምጣት በሆሴዕ2:1–3 ላይ ከተገለጹት ክንውኖች ጋር በጣም የተያያዘ እንደሆነ ግልጽ ነው። በሌላ አነጋጋር ምንም "መሪ" ከሌለ እዚህ የተገለጹት የተቀሩት ክስተቶች አይከሰቱም። አብረው የሚሄዱ ናቸውና። "መሪ" ("ንጉሥ" ከሚለው ቃል ይልቅ) እዚህ ላይ ተስማሚ ነው ምክንያቱም በዘጸአት ጊዜ የመሪዎች ጥቅም ላይ ከዋለበት ቋንቋ ጋር ተመሳሳይ ነው። ልክ ሙሴ (በኋላም ኢያሱ) ለእግዚአብሔር ሕዝብ መሪ እንደ ነበሩ እና በግብፅ ምድረ በዳ ወደ ተስፋይቱ ምድር እንዲወስዱዋቸው እንደ ታዘዙበት መንገድ (ዘዳግም 10:11 ይመልከቱ) ሁሉ ማለት ነው፤ ይህ የወደፊቱም መሪ የእግዚአብሔርን ሕዝብ ከባርነት ምድር አውጥቶ "በመድረ በዳ" በኩል በመምራት በእግዚአብሔር ቃል ተስፋ የተገባላቸውን ምድር እንዲወርሱ ይረዳቸዋል ማለት ነው። ስለዚህ ክርስቶስ በእርግጥ እንደ ሙሴ ነው። እንደ ሙሴም እግዚአብሔርን  ፊት ለፊት የሚያይ ነቢይ ነው (ዘዳግም 18:15–19፣ 34:10–12 እና ዮሐንስ 1:18 ይመልከቱ)። ይህም ደግሞ ልዩ በሆነ መንገድ የእግዚአብሔርን ሕዝቦች ለመምራት ብቁ ያድርገዋል። ክርስቶስ ደግሞ ኢያሱንም ይመስላል። ኢያሱ ሕዝቡን በተሳካ ሁኔታ ወደ ተስፍይቱ ምድር መርቷል (ዘዳግም 31:3 ይመልከቱ)። በሙሴ መጽሐፍ (ከፍጥረት እስከ ዘዳግም) ውስጥ **"መሪ"** የሚለው ቃል የእግዚአብሔር ህዝብ መሪ የሚያመለክት ስያሜ ነው። ይሁን እንጂ ለእግዚአብሔር ሕዝብ ንጉሥ የተደረገውን ሰው የሚያመለክት ስያሜ አይደለም። ምክንያቱም በዚያ ዘመን በእሥራኤል ውስጥ ነገሥታት አልነበሩምና። ነገር ግን ከሙሴ ዘመን በኋላ ባለው ጊዜ "መሪ" የሚለው ቃል ለእሥራኤል ነገሥታትም ጥቅም ላይ መዋል ጀመረ (1 ሳሙ 15:17፤ 2 ሳሙኤል 22:44 ይመልከቱ)። ስለዚህ በዚህ በሆሴዕ ክፍል መሪ የሚለው ቃል በጣም ተገቢ ነው። አንባቢዎችን ስለ መውጣት ያስታውሳልና እንደዚሁም በአንጻሩ ደግሞ በተመሳሳይ ጊዜ አንባቢዎችን መጽሐፈ ነገሥትንም የሚያነቡት ያስታውሳል። ኢየሱስ ሕዝቡን ከባርነት ምድር እያውጣ በመድረበዳ በመምራት በሰላም ወደ በእግዚአብሔር ቃል ተስፋ ወደ ተገባችው ምድር የሚያወጣ ንጉሥም ነው።

በሆሴዕ ስለ "አንድ መሪ" የተነገረው ትንቢት አስደናቂ ተስፋ ነው፤ ምክንያቱም ሆሴዕ በተጻፈበት ወቅት በእግዚአብሔር ህዝብ ላይ የተሾሙ ሁለት "መሪዎች" ነበሩ፤ እነሱም የይሁዳ ንጉሥና የእስራኤል ንጉሥ ነበሩ። እዚህ ጋ የእግዚአብሔር ሕዝብ የሚገዛቸው እና የሚምራቸው አንድ ንጉሥ የሚመረጥበት ጊዜ እንደሚመጣ እናነባለን (ሕዝቅኤል 37:15–28 ይመልከቱ)። ይህ የሆነው በክርስቶስ ኢየሱስ ነው! ክርስቶስ የሚለው ቃል የግሪክ ቃል ሲሆን ትርጉሙም የተቀባ ማለት ነው። ኢየሱስ የተቀባ ንጉሥ ነውና። እሱም በሁሉም የእግዚአብሔር ህዝብ ላይ አንድ ንጉሥ ነው። እናም እሱ ቀድሞውኑም እየገዛ ነው! ኢየሱስ ከሙታን በመነሣቱ "በኃይል የእግዚአብሔር ልጅ" እነደሆነ ታውጇል (ሮሜ 1:4)። "ስልጣንም ሁሉ በሰማይና በምድር" ተሰጥቶታል (ማቴዎስ 28:18 ይመልከቱ)። የእግዚአብሔር ህዝብ ደግሞ ንጉሣቸው እንዲሆን ይፈልጋሉ (ዮሐንስ 20:28 ይመልከቱ) እና በደስታ ለእርሱ አመራር እየተገዙ ነው። ይህ በሆሴዕ ውስጥ ስለመጣው  የእግዚአብሔር ሕዝብ ንጉሥ የተነገረ ብቸኛ ማጣቀሻ አይደለም (ለምሳሌ ሆሴዕ3:5 ይመልከቱ)።

ሆሴዕ ስለእነዚህ ትንቢቶች በጥልቀት እንደሚያስብ ልብ ማለት ያስፈልጋል። ትንቢቶቹ ሲፈጸሙ ለማየት የጓጓ ይመስላልና። ሆሴዕ ስለ ወደፊቱ የእግዚአብሔር ሕዝቦች ንጉሥ ትንቢት መናግሩ ብቻ ሳይሆን ትንቢቱም ለራሱ ጥቅም ጭምር መሆኑን ያምን ነበር! ስለዚህ ስለ ራሱ ንጉሥ ትንቢት እነደሚናገርም ጭምር ነበር! በመሆኑም ሆሴዕ ልክ እንደ ሊሎችም ነብያት ስለ ክርስቶስ ያውቅ ነበር፤ ክርስቶስን ይወድ ነበር፤ እናም የክርስቶስንም መምጣት ይጠባበቅ ነበር (የሐዋሪያት ሥራ 3:18፣ 21፣ 24 እና 1 ጴጥሮስ 1:10 ይመልከቱ)። ስለሚመጣው ንጉሥ የተለዩ ትንቢቶች በብሉይ ኪዳን ውስጥ ይገኛሉ። ሆኖም ሆሴዕ ትንቢት በተናገረበት ዘመን ሁሉም የብሉይ ኪዳን ክፍል አልተጠናቀቀም ወይም ተሰብስቦ አላለቀም ነበር። ስለዚህ ሆሴዕ ሁሉንም ብሉይ ኪዳን የማንበብ ዕድል አላገኘም ነበር። ይሁን እንጂ ሆሴዕ ብዙ ክፍሎች ደግሞ የማግኘት ዕድል ነበረው። ስለ ክርስቶስ መምጣት በሙሴ መጽሐፍ ውስጥ ማንበብ ይችል ነበርና (ዘፍጥረት 49:8–12፤ ዘኁልቁ 24:1–9 እና 14–19 ይመልከቱ)። በመዝሙረ ዳዊትም ውስጥ ብዙዎቹን ያሰላስል ነበር ማለት ይቻላል። እነዚህ መዝሙሮች ስለ ክርስቶስ ብዙ ብዙ ማጣቀሻዎች የያዙ ናቸውና (ለምሳሌ መዝሙር 2፣ 22፣ እና 110 ይመልከቱ)።

[25] የእግዚአብሔር ሕዝብ "በመሪው" (ማለትም በንጉሣዊ መሪው) እየተመራ **"ካለበት ምድር ይወጣል"**። ይህ አባባል መጀመሪያ ጥቅም ላይ የዋለው እሥራኤላውያን ከግብጽ **ምድር በወጡበት ጊዜ ነበር** (ዘጸአት 32:1፣ 4፣ 33:1፤ ዘኁልቁ 32፡

**2፡3 ወንድሞቻችሁን ዓሚ እህቶቻችሁንም ሩሃማ በሉዋቸው።**[27]

---

11፤ ኢያሱ 24፡17፣ 24፡32 ፤ መሳፍንት 2፡1፣ 11፡13፣ 19፡30፤ 2 ነገሥት 17፡7፤ ኢስይያስ 11፡16፤ ኤርምያስ 2፡6፤ አሞጽ 9፡7፣ ሚክያስ 6፡4 ይመልከቱ)። **"ከምድር ለመውጣት"** ቢያንስ **ሦስት ሀሳቦችን ያካትታል። በመጀመሪያ** እግዚአብሔር ያዳናቸው ከባርንት ምድር የሚወጡትን ሰዎች ሃሳብ ያጠቃልላል። **በሁለተኛነት** ደግሞ ሰዎች ከባርነት ከምድረ በዳ ወጥተው ወደ አዲስ ቦታ ሲሄዱ በእግዚአብሔር ስለሚጠበቁበት እና በሰላም ስለሚጓዙበት ሃሳብ ያካትታል። **በሦስተኛ** ደረጃ ደግሞ ወደ አዲስ ምድር የመግባት ሐሳብን ይጨምራል፤ ምክንያቱም እግዚአብሔር መሬት አዘጋጅቶላቸዋል ደግሞም ምድሪቱን እንዲወርሱ እየረዳቸው ነውና። በሆሴዕ 2:1–3 ላይ ሆሴዕ ስለ ዘጸአት ወይም ስለ መውጣት ክስተት እየተናገረ ነው! ነገር ግን እየተናገረ ያለው ስለመጀመሪያው ዘጸአት ወይም መውጣት አይደለም። ያ ክስተት አስቀድሞ የተድረገ ነውና። ነገር ግን ሆሴዕ እየተናገረ ያለው ስለ "ሁለተኛው ዘጸአት" ወይም መወጣትን ነው። ይህም የሚመራው የእግዚአብሔርን ሕዝብ አንድ ባደርገው በአንድ "መሪ" ነው። ይህ "ሁለተኛው መውጣት" ክርስቶስ ሕዝቡን ከባርነት "ምድረ በዳ" በማስወጣት ወደ እግዚአብሔር መልካም ቦታ የሚመራበት መወጣት ነው። ስለዚህ "በክርስቶስ" ያሉቱ ሁሉ የዚህ የሁለተኛው ዘጸአት ወይም መውጣት አካል ናቸው። ስለ "ሁለተኛው መውጣት" ቋንቋ በነቢያት ውስጥ ተደጋግሞ ተጠቅሷል (ለምሳሌ ኢሳይያስ 55፡12–13 እና ኤርሚያስ 16:4–15 ይመልከቱ)።

[26] በሆሴዕ 1፡4–5 ላይ "ኢይዝራኤል" የሚለው ቃልም ጥቅም ላይ ውሏል። ይሁን እንጂ በዚህ ጥቅስ ውስጥ ስሙ በሆሴዕ 1፡4–5 ላይ ከተጠቀሰው በተለየ መንገድ ጥቅም ላይ ውሏል። በሆሴዕ 1፡4–5 ላይ "ኢይዝራኤል" የሚለው ስም በአሉታዊ መልኩ ጥቅም ላይ ውሏል። በኢዝራኤል የተከሰተውን ክፋት እና እሥራኤል ሁሉ በኢይዝራኤል የሚደርስባቸውን ሽንፈት የሚያስታውስ ነበር። በተጨማሪም ኢይዝራኤል የሚለው ስም እሥራኤል ከሚለው ስም ጋር ይመሳሰላል። ስለዚህ መላው የእሥራኤል መንግስት እንደሚጠፋ ማሳሰቢያ ነበር ማለት ነው። በሌላ መልኩ ደግሞ በሆሴዕ 2፡2 ላይ ኢይዝራኤል የሚለው ስም በአዎንታዊ መልኩ ነው ጥቅም ላይ የዋለው። በ በሆሴዕ 2፡2 ላይ ያለው የስሙ ትርጉም አጠቃቀም በርግጥ ከስሙ ትርጉም ጋር የተያያዘም ነው። ኢይዝራኤል የሚለው ስም "እግዚአብሔር ይዘራል" ማለት ነው። ይህ "የሁለተኛው መውጣት" ትንቢት በተፈጸመ ቀን "እግዚአብሔር በመልካም ቦታ ወንዶችና ሴቶች ልጆቹን ይዘራል። "ይህ እግዚአብሔር አዳምን ወስዶ በኤደን ገነት ካስቀመጠበት ሂደት ጋር ተመሳሳይ ነው። አዳም የተፈጥረው ከኤደን ገነት ውጪ ነበር ነገር ግን እግዚአብሔር ወደ መልካም ሥፍራ አምጥቶ "በዚያ ተከልው።" ይህ ትንቢት ዛሬም እየተፈጸመ ነውና። "መሪው" (ኢየሱስ) ሕዝቡን ከባርነት ምድር እያወጣቸው ወደ እግዚአብሔር መልካም ቦታ እያመጣቸው ነውና!

[27] እግዚአብሔር ለእሥራኤል ሕዝብና ለይሁዳ ሕዝብ የተሐድሶ እና የሕይወት ተስፋዎችን ሰጥቷል (ሆሴዕ 2፡1–2 ይመልከቱ)። ሆሴዕ 2፡3 ደግሞ ለእነዚህ ተስፋዎች ትክክለኛ ምላሽ ይሰጣል። ስለዚህም በሰሙት የከበረ ተስፋ ላይ በመመስረት መልዕክቱን የሚሰሙ ሰዎች በእምነት ምላሽ እንዲሰጡ ተጠርተዋል። በሆሴዕ ዘመን ሆሴዕ 2፡3 ን መታዘዛቸው እሥራኤልውያን ይህን መልዕክት ሲሰሙ በእሥራኤል ውስጥ ወደሚኖሩት "ወንድሞቻቸው" እና "እህቶቻቸው" ሄደው እነዚህን የእምነት መልዕክት እንዲነግሩዋቸው ያስገደድ ነበር። ከዚህም ባሻገር ወደ ይሁዳ ድንበር ተሻግረው ይህንን መልዕክት በይሁዳ ለሚኖሩ "ወንድሞቻቸው" እና "እህቶቻቸው" ያውጁ ነበር። ስለሚመጣው "መሪ" የሚሰጠውን ተስፋና ስለወደፊቱ የእግዚአብሔር ሕዝቦች ባርነት፣ ተመልሶ መታደስና ስለዕርቅ ማወጅ ነበረባቸው። በሌላ አነጋገር (ምንም እንኳን ገና ክርስቶስ ባይመጣም) ታማኝ የሆኑ እሥራኤላውያን ወንጌልን እንዲሰብኩ ተጠርተዋል! ታዲያ ለዚህ ትዕዛዝ የእስራኤል ሕዝብ ምላሽ ምን ነበር? ሆኖም በሆሴዕ ዘመን ይኖሩ ከነበሩት በጣም ጥቂት ሰዎች መካከል የሆሴዕን ቃል ሰምተው እዚህ ስለተነገሩት ተስፋዎች ለሌሎች እሥራኤላውያን በይሁዳ ለሚኖሩት ሰዎች መናገር የጀመሩት በጣም ጥቂት ሰዎች ብቻ ሳይሆኑ አይቀርም። ነገር ግን ይህንን ትእዛዝ መታዘዝ በሆሴዕ ዘመን የተለመደ ባይሆንም ከክርስቶስ ሞትና ትንሣኤ በኋላ የተለመደ ሆነ። የክርስቶስ ሞት በእግዚአብሔር ሕዝብ ላይ ትልቅ ለውጥ አምጥቷልና! በኢየሱስ ሞትና ትንሣኤ ብዙ ሰዎች ተመልሶ የመታደስ የሕይወት ዘመን እንደ መጣ ማወጅ ጀመሩ! ለምሳሌ ሐዋሪያው ጳውሎስና ጴጥሮስ በሮሜ 11፡30–32 እና 1 ጴጥሮስ 2፡10 ላይ ስለ እነዚህ ተስፋዎች እንዴት እንደተናገሩ እስቲ ልብ ይበሉ። እርግጥ ነው በሆሴዕ ዘመን የሚኖሩ ሰዎች የወንጌልን ክስተት በጉጉት ሲጠባበቁ በእምነት ይናገሩ ነበር። ከክርስቶስ ሞትና ትንሳኤ በኋላ የሚኖሩ ሰዎች ግን በሕይወታቸው ስለተለማመዱት ነገር እየተናገሩ ነው! ይህ እስኪፈጸም እየጠበቁ አይደለምና። በክርስቶስ ተፈጽሟልና!

**ሆሴዕ 2፡4–15**

ቀደም ሲል እንደተገለጸው የዕብራይስጥ ትንቢት አንዱ ገጽታ የእስራኤልን እጣ ፋንታ (ወይም በሆሴዕ የእሥራኤልና የይሁዳ እጣ ፋንታ) በሚመለከት በአሉታዊ እና በአዎንታዊ እንድምታዎች መካከል በተደጋጋሚ መቀያየር ነው። አሁን የምንመለከተው የሆሴዕ ክፍል ደግሞ  አሉታዊ ነው።

በሆሴዕ 2፡2–13 ላይ እንደተገለጸው በዚህ ጊዜ ውስጥ እሥራኤላውያን ያመልኩት የነበረውን "ተቀናቃኝ" አምላክ የሆነውን ስለ ባኣል ለመነጋገር ትንሽ ጊዜ መውሰድ ጠቃሚ ነው። እንደ ሆሴዕ 2፡8 ባሉት ጥቅሶች አንዳንድ ጊዜ ባኣል በነጠላነት ጥቅም ላይ ይውላል።

> *"እርስዋም እህልንና ወይንን ጠጅ*
> *ዘይትንም ሰጠኋት*
> *ለባኣልም የተሠራውን ብርና ወርቅ ያበዛሁላት*
> *እኔ እንደ ሆንሁ አላወቀችም።"* **ሆሴዕ 2፡10**

አንድንድ ጊዜ ደግሞ ቃሉ በሆሴዕ 2፡13 ላይ እንዳለው በብዙ ቁጥር ጥቅም ላይ ይውላል።

> *"እኔን ረስታ ውሽሞችዋን እየተከተለች በጉትቾችዋና በጌጥዋም ኢያጌጠች ለበኣሊም ያጠነችበትን ወራት እበቀልባታለሁ ይላል እግዚአብሔር።"* **ሆሴዕ 2፡15**

ባኣል የሚለው ቃል ባል ወይም ጌታ ማለት ነው። ስለዚህ እሥራኤላውያን ከእግዚአብሔር ጋር "የተጋቡ" ሆነው ሳለ፤ በሚያስገርም ሁኔታ ደግሞ "ባል" ከሚባል ከሌላ አምላክ ጋር ግኑኝነት ነበራቸው። እሥራኤልውያን ባኣልን ወደ ውድመት የሚመራቸው ክፉ አምላክ መሆኑን አላስተዋሉም ነበር። እንዳውም ባኣል ለሕይወታቸው አስፈላጊ እንደሆነ ያምኑ ነበር። እግዚአብሔር ያልደረሰላቸው በሚመስላቸው ቦታ ባኣል እንደሚረዳቸው ይቀጥሩ ነበር። ደግሞም የባኣል ድርጊቶች ለስኬቶቻቸው

---

ስለዚህ ሰባኪዎችና አስተማሪዎች በሆሴዕ 2፡1 ላይ ያለውን ትዕዛዝ አንጻኦት ሊሰጡበት ይገባል! ይህን መልዕክት "ለወንድሞቻችን" እና "ለእህቶቻችን" ማወጅ አለብን።

ወይም ለውጤታማነታቸው ወሳኝ ተደርጎ ይቆጠር ነበር። ልክ ባልሆን ግንዛቤያቸውም ምክንያት ዝናብን ማዝንብም ሆነ መንሳት የሚችል ባኣል እንደሆነ አድርገው ይወስዱ ነበር። ለዚህም ነው የባኣል ሐውልቶች ላይ በእጁ መብረቅን ይዞ የሚታየው።

እሥራኤላውያን ባኣልን እያመለኩ በተመሳሳይ ሁኔታ እግዚአብሔርንም ለማምለክ ይሞክሩ ነበር። የባኣልን ቀናቶች ያከብሩ ነበር መስዋዕትንም ያቀርቡ ነበር። በራሳቸውም መንገድ እግዚአብሔርን ለማስደሰት ይሞክሩ ነበር። ይሁን እንጂ እንደዛ ዓይነት "አምልኮ" ያከናውኑ የነበሩት እግዚአብሔር ባዘዛቸው መንገድ ሳይሆን እሥራኤልውያን ራሳቸው በሚፈልጉት መንገድ ነበር። ስለዚህ እሥራኤላውያን ባኣልንም ያመልኩ ነበር ደግሞም በተመሳሳይ መንገድ እግዚአብሔርንም በሐሰት ያመልኩ ነበር።

የባኣልን አምልኮት በተወሰነ ደረጃም ቢሆን ከሴትኛ አዳሪዎች ጋር የሚደርግም ለአምልኮት የፆታ ግንኙነት የሚፈጽሙ ሰዎችን ይጨምራል። እነዚህ ሕገወጥ የፆታ ግንኙነቶች የሚፈጸሙት ባኣል አናት ከተባለች አምላክ ጋር ተመሳሳይ ነገር በማድረግ ለእነዚህ ድርጊቶች ምላሽ ይሰጣል ተብሎ ስለሚታሰብ ነው (አናት የባኣል ሚስት ነበረችና)። ስለዚህ እሥራኤላውያን በምድር ላይ ያሉትን ሰዎች የአምልኮት የፆታ ግንኙነት ሲያደርጉ አማልክትም በሰማይ ውስጥ የግብረ ሥጋ ግንኙነት እንዲፈጽሙ ያነሳሳቸዋል፤ ይህም ደግሞ ተስማሚ የአየር ጸባይንና የእርሻ ብልጽግናን ያስገኛል ብለው ያምኑ ስለነበረ ነው። ከዚህም ባሻገር የእሥራኤል ሰዎች በእንደዚህ ዓይነቱ ኃጢአቶች እጅግ ይደሰቱ ነበር። በእንደዚህም ክፍ መንገዶች ማምለክ ይፈልጉ ነበር፤ ስለዚህ በእነዚህ ክፉ መንገዶች እንዲሄዱ የሚፈቅድላቸውን አማልክት አገኙ ማለት ነው።

የእሥራኤላውያን በባኣል መታመናቸው እግዚአብሔርን እንደማይታመኑ ያሳያል። እግዚአብሔር እንደ እሥራኤል ባል ሚስቱን እንደሚንከባከብ ቃል ገብቶ ነበር። ይህም ቀድሞውንም ከእሥራኤል ጋር የገባው ቃል ኪዳን አካል ነበር። እሥራኤል ግን በእግዚአብሔር እንክብካቤ አልታመነችም። ምግብና ወሃ እንደዚሁም ደግሞ ከበዓል መጽናናት የምታገኝ መስሏት ነበር። እሥራኤል ባኣልን በማምለክ ባድረገችው እንቅስቃሴ እግዚአብሔርን እንደ ጥሩ ባል እንደምትቆጠረው አሳይታለች። ስለዚህ ይህ ምዕራፍ እግዚአብሔር ለእስራኤል የሰጠውን ምላሽ ነው ምክንያቱም በባኣል ታምናለችና።

ሆሴዕ 2፡4–15 በመጀመሪያ የተጻፈው ከክርስቶስ መምጣት በፊት ስለሚኖሩ እሥራኤላውያን ቢሆንም ሰባኪ ወይም አስተማሪ እነዚህን ክፍሎች በዚህ ዘመን ለሚገኙት ክርስቲያኖች እንዴት እንደሚሡሩ

መመርመር ይኖርብታል። በዚህ ዘመን ላሉ ክርስቲያኖች እነዚህን ክፍሎች መስበክ የሚስገኙትን ስድስት ጥቅሞች ከዚህ በታች ተዘርዝረዋል።

1. **እነዚህ ክፍሎች እግዚአብሔር በሆሴዕ ጊዜ በእሥራኤል ላይ ያደረገውን ለምን እንዳደረገ ለክርስቲያኖች ማምብራሪያ ይሰጣሉ።**

እነዚህ ክፍሎች እግዚአብሔር እሥራኤል በአሦራውያን እንድትጠቃ የፈቀደበት ምክንያት ያብራራሉ። ደግሞም በመላው አለም ለምን እንደተበተኑ ያስረዳል። እየተቀጡ ነበርና። አንባቢው በእነዚህ የሆሴ መልዕክቶች ሲያነብ ለእሥራኤል ሊራራላቸው አይገባውም። እሥራኤል የእግዚአብሔር ሰለባ አልነበረችምና። በተቃራኒው ግን የእሥራኤል ሰለባ የነበረው እግዚአብሔር ራሱ ነበርና። እሥራኤል እንደ "ሚስቱ" ሆና ሳለች ግልሙትና ትፈጽም ነበርና! ግጥሙ እሥራኤልን በክፉ መልኩ ይስላታል። እሷ እንደ ጋላሞታ ነበረችና የተቀበለችው ቅጣት ሁሉ የሚገባት ነበር። ስለዚህ አንባቢው ከእግዚአብሔር ጎን ሊቆም ይገባዋል።

2. **ይህ ግጥም በእግዚአብሔርና በሕዝቡ መካከል ያለውን ግኙኘነት በግልፅ ይዘረዝራል። የትዳር ጉድይ ነውና።**

ለዚህም ነው ጳውሎስ ስለ ምድራዊ ጋብቻ ሲናገር በክርስቶስና በቤተ ክርስቲያን መካከል ስላለው ታላቅ ጋብቻ ከመናገር ውጪ ሊያልፍ ያልቻለው።

> *ሚስቶች ሆይ ለጌታ እንደምትገዙ ለባሎቻችሁ ተገዙ፤ ክርስቶስ ደግሞ የቤተ ክርስቲያን ራስ እንደ ሆነ እርሱም አካሉን የሚያድን እንደ ሆነ ባል የሚስት ራስ ነውና። ዳሩ ግን ቤተ ክርስቲያን ለክርስቶስ እንደምትገዛ እንዲሁ ሚስቶች ደግሞ በሁሉ ለባሎቻቸው ይገዙ።*
>
> *ባሎች ሆይ ክርስቶስ ደግሞ ቤተ ክርስቲያንን እንደ ወደዳት ሚስቶቻችሁን ውደዱ፤ በውኃ መታጠብና ከቃሉ ጋር አንጽቶ እንዲቀድሳት ስለ እርስዋም ራሱን አሳልፎ ሰጠ። እድፈት ወይም የፊት መጨማደድ ወይም እንዲህ ያለ ነገር ሳይሆንባት ቅድስትና ያለ ነውር ትሆን ዘንድ ክብርት የሆነችን ቤተ ክርስቲያንለራሱ እንዲያቀርብ ፈለገ። እንዲሁም ባሎች ደግሞ እንደ ገዛ ሥጋቸው አድርገው ሚስቶቻቸውን ሊወዱአቸው ይገባቸዋል። የገዛ ሚስቱን የሚወድ ራሱን ይወዳል፤ ማንም የገዛ ሥጋውን የሚጠላ ከቶ የለመና ነገር ግን የአካሉ ብልቶች ስለሆንን ክርስቶስ ደግሞ ለቤተ ክርስቲያን እንዳደረገላት ይመግበዋል ይንከባከበውማል። ስለዚህ ሰው አባቱንና እናቱን ይተዋል ከሚስቱም ጋር ይተባበራል ሁለቱም አንድ ሥጋ ይሆናሉ። ይህ ምሥጥር ታላቅ ነው እኔ*

*ግን ይህ ስለ ክርስቶስና ስለ ቤተ ክርስቲያን እላለሁ። ሆኖም ከእናንተ ደግሞ እያንዳንዱ የገዛ ሚስቱን እንዲህ እንደ ራሱ አድርጐ ይውደዳት ሚስቱም ባልዋን ትፍራው።* **ኤፌሶን 5፡22–33**

ምድራዊ ጋብቻ በእግዚአብሔርና በሕዝቡ መካከል ያለውን ግንኙነት የሚያሳይ ትንሽ ምስል ነው። በወንድና በሴት መካከል ያለውን ጋብቻ መከበርና መጠበቅ ያለበት ለዚህ ነው።

3. **ይህ ግጥም እግዚአብሔር ከሕዝቡ ጋር ባደረገው ጋባቻ ላይ ሌሎች ፍቅረኛሞች እንደማይታገስ ያሳያል።**

ስለዚህ እግዚአብሔር በሆሴ ዘመንም ቢሆን መንፈሳዊ ግልሙትና አይታገሥም ነበር። እንደዚሁም በዚህ ዘመንም ቢሆን እግዚአብሔር በሕዝቡ መካከል የሚደርግ ግልሙትና እንደማይቀበል ማወቅ አለብን። ከእግዚአብሔር ጋር ያለንን ግንኙነት እንደ ትዳር መመልከትና በዚያ እውነታ መሰረት መኖር በጣም አስፈላጊ ነው። የእግዚአብሔር ቃል ደግሞ የቃል ኪዳናችን ሰነድ ነው። እንደ ክርስቲያን ሌሎች ፍቅረኛሞችን ተከትለን የምንሮጥ ከሆነ እና የቃል ኪዳናችንን ሰነድ ችላ የምንል ከሆነ እንደ እሥራኤልም እንቀጣለን። ይህ በሆሴዕ ውስጥ የሚገኘው ግጥም እንግዲህ በሕይወታችን ውስጥ ጤናማ የሆነ እግዚአብሔርን መፍራት ሊያሳድርብን ይገባል።

በሆሴዕ ውስጥ ያሉት እነዚህ ልዩ ጥቅሶች በአዲስ ኪዳን ውስጥ ባይጠቀሱም ከዚህ በታች እንደሚታየው የአዲስ ኪዳን ጸሐፊዎች በውስጣቸው ከሚገኙት ሐሳቦች በተደጋጋሚ ይወስዱ ነበር።

*በእግዚአብሔር ቅናዓት እቀናላችኋለሁ እንደ ንጽሕት ድንግል እናንተን ለክርስቶስ ላቀርብ ለአንድ ወንድ አጭቻችኋለሁና፤ ነገር ግን እባብ በተንኮሉ ሔዋንን እንዳሳታት አሳባችሁ ተበላሽቶ ልክርስቶስ ከሚሆን ቅንነትና ንጽሕና ምናልባት እንዳይለወጥ ብዬ እፈራለሁ።* **2 ቆሮንቶስ 11፡2–3**

*አመንዝሮች ሆይ ዓለምን መውደድ ለእግዚአብሔር ጥል እንዲሆን አታውቁምን? እንግዲህ የዓለም ወዳጅ ሊሆን የሚፈቅድ ሁሉ የእግዚአብሔር ጠላት ሆኖአል።* **ያዕቆብ 4፡4**

ቤተ ክርስቲያን የክርስቶስ ሙሽራ ናት። ከክርስቶስ ጋር ልንጋባ እና በተመሳሳይ ጊዜ ደግሞ በዓለም ላይ በግልሙትና መሮጥ አንችልም። ይህም ምንዝርና ነውና! እነዚህ ሁሉ ክፍሎች እግዚአብሔር ከሕዝቡ ጋር የሚያደርገውን ጋብቻ በቁም ነገር እነደሚመለከተው ያሳያል። ፍቅሩን ለየትኛውንም ተቀናቃኝ አያካፍልምና። እውነተኛ አምልኮም ምን እንደሚመስል እንድናብራራ አይፈቅድም። የእሥራኤል መንገድ

በመማር እግዚአብሔርን እንዴት እንደ ምናመልክ መወሰን የለብንም። በመልካም ቃሉ የተጻፈውን መከተል አለብን እንጂ።

4. **ደግሞም ይህ ግጥም እኛ ዛሬ አማኞችን እንደመሆናችን መጠን ለባለቤታችን እንክብካቤ ሙሉ ዋስትና እንዲኖር ያስታውሰናል። እሥራኤልውያን እንዳደርጉት ወደ ሌላ መመልከት በእርሱ ላይ በደል እንደመፈጸም ነው።**

ይህን ስናደርግ እግዚአብሔርን እንደ መጥፎ ባል መቁጠራችን ነው። ኢየሱስ ለእኛ ስላቀረበልን መንገድ ማጉረምረም በእርሱ ላይ ጥፋት ነው (ኤፌሶን 5፡29 ይመልከቱ)። አሁንም እንደዚህ ስናደርግ መጥፎ ባል ነው እያልን ነው ማለት ነው።

5. **ይህ ግጥም በሕይወታችን ውስጥ የእግዚአብሔርን ጸጋ ሊያስታውሰን ይገባል።**

እኔ በበኩሌ ብዙ ጊዜ ከመንፈሳዊ ታማኝነት የጎደልኩ ነኝ እናም እሥራኤላውያን የደረሰባቸው ቅጣት ይገባኛል። ሌሎች አማልክቶችን ተከትዬ ሮጬያለሁ (ከባኣል የተለየ ስም ያላቸው)። እንደ እሥራኤልም እግዚአብሔርን የማምለክ አዲስ መንገድ ፈልስፌያልሁ። በሕይወቴም ወስጥ ስለ እግዚአብሔር መግቦት አጉረመርማለሁ። ታዲያ እግዚአብሔር እንዴት ማረኝ? ለምንድር ነው እንደዚህ ደግነት ያሳየኝ? ጸጋው ለምን ወደ እኔ መጣ? የእግዚአብሔር ብዙ ቸርነቱ የእርሱን ቸርነት ስላገኘሁ አይደለም።

6. **በመጨረሻም እና ከሁሉም በላይ ይህ ግጥም የእግዚአብሔርን ክብር ያሳያል።**

ማንኛውንም ሰው ወይም ማንኛውንም ነገር የእርሱ ቦታ ሲይዝ አይታገሥም ምክንያቱም በእሱ ምትክ የሆነ ነገር ስህተት ነውና።

> *“. . . ስሙ ቀናተኛ የሆነ እግዚአብሔር ቅናዓት ያለው አምላክ ነውና ለሌላ አምላክ አትስገድ . . .”*
> **ዘጸአት 34፡14**

እግዚአብሔር ለስሙ ቀናተኛ ነው። በዚህም በጣም ድስ ሊለን ይገባል! እሱ ታላቅ ሆኖ መታየቱን ያረጋግጣልና። ደግሞም ያ ታላቅነት ጠማማ ሰዎችን እንዴት እንደሚቀጣ ያሳያል። በሆሴዕ 2፡14–23 ላይ እንደምንመለከተው ዓመፀኛ ሰዎችንም ቢሆን እንዴት ይቅር እንደሚላቸው ያሳያል።

2:4

እናታችሁ ሚስቴ አይደለችምና–[28]

እኔም ባልዋ አይደለሁምና –[29]

ተምዋገቱ፤ ከእናታችሁም ጋር ተምዋገቱ።

ግልሙትናዋን ከፊትዋ

ምንዝርናዋንም ከጡቶችዋ መካከል ታስወግድ፤ –[30]

5

ዕራራቁትዋን እንዳልገፋት

---

[28] እግዚአብሔር በእነዚህ ጥቅሶች ውስጥ አሁን ግን እሥራኤልን እንደ ሚስቱ አልተናገራትም። እንዳውም በቀጥታ እንኳን አላናገራትም። ሌላው ይቅርና በቃሉ እንኳን ሲናገር ከራሱ እራቅ አድርጎዋት ነበር፤ ይልቁንም “ልጆችን” “እናታቸውን” ወደ ንስሐ እንዲጠሩ ሲነግራቸው እንመለከታለን። “እናት” የተባለችው ባጠቃላይ የእሥራኤል ሕዝብ ከሆነ “ልጆች” በእሥራኤል ውስጥ ይኖሩ የነበሩት ግለሰቦች ናቸው። እናቲቱ (በድጋሚ ሕዝቡ በአጠቃላይ) እግዚአብሔርን ስለማይሰሙ፤ እግዚአብሔር በእስራኤል ውስጥ ያሉ ፈሪሃ እግዚአብሔር ያላቸውን ሰዎች ሕዝቡን ስለእርሱ እዲናገሩ እየጠራ ነበር። የቀድሞ ባለዋን (እግዚአብሔርን ስለማትሰማ) ልጆችዋ ትሰማ ይሆናልና፤ ስለዚህ ለንስሐ እንዲጥሩዋት ይናገራቸዋል። እነዚህ ፈሪሃ እግዚአብሔር ያላቸው ቅሬታዎች ለእግዚአብሔር መልዕክት በእምነት ምላሽ እንዲሰጡና ከሆሴም ጋር በመተባበር ሕቡን ንስሐ እንዲገባ መማጸን ይኖርባቸው ነበር። በእርግጥ ግን ይህ የሆነው በሆሴዕ ዘመን ነውን? ስለዚህ ለሆሴዕ መልዕክት ምላሽ እንዲሰጡና ሕዝቡም ንስሐ እንዲገባ የተማጸኑዋቸው ግለሰቦች ይኖሩ ይሆንን? በምድሪቱ ላይ ምንጊዜም ቅሬታ የሆኑ አማኞች መኖራቸው ስለማይቀር እነዚህ ጥቂት ሰዎች ለሆሴዕ መልእክት ምላሽ በመሰጠት እሥራኤልን ንስሐ እንድትገባ በመጥራት ከእርሱ ጋር ሳይተባበሩ አልቀሩም። እነዚህ እሥራኤላውያን ይህንን ትዕዛዝ ለመታዘዝ ታላቅ ድፍረት የሚጥይቅ ነበር። ነቢያትንም በተጣሉበት መንገድ እነሱም ደግሞ በተጣሉዋቸው ነበር።

[29] **እግዚአብሔር እሥራኤልን ከእንግዲህ ሚስቱ እንዳይደለች ተናግሯል።** የሚቀጠልው መስመርም ከዚህ ጋር ትይዩ ነው። ይህ ማለት የቀጣዩም መስመር ሀሳብ ተመሳሳይ መሆን አለበት ነገር ግን ቀጣዩ መስመር ከመጀመሪያው ይልቅ የበለጠ ሀሳቡን ማጠናከር አለበት። እዚህም ጋ የሆነው ያው ነው። በመጀመሪያው መሰመር **እግዚአብሔር የእሥራኤል ባል እንዳልሆነ ተናግሯል።** እሥራኤል ለብዙ መቶ ዓመታት ከእግዚአብሔር ተለይታ ትቅበዘበዝ ነበር፤ ነገር ግን በነዚያ ጊዜያት ሁሉ ነቢያቱ አመፀኛዋ እሥራኤል ወደ እውነተኛው ባሏ እንድትመለስ ይጥሩ ነበር። እግዚአብሔር ምንጊዜም ታማኝ ባልዋ ነበርና። እዚህ ጋ ግን በእግዚአብሔርና በእሥራኤል መካከል ያለውን የጋብቻ ግኑኝነት እንደተለወጠ ግልጽ ነው። ስለዚህ እግዚአብሔርም ከእንግዲህ ባልዋ እንዳልሆነ ይናገራል። በሙሴ ሕግ መሠረት ባል ሚስቱን የመንከባከብ ግዴታ ነበረበት (ዘጸአት 21፡10 ይመልከቱ)። እዚህ ጋ ግን እግዚአብሔር እስራኤል ከእንግዲህ ሚስቱ እንዳልሆነች ይናገራል። ስለዚህ ይህችን አመንዝራ ወይም ጋለሞታ ሴት የመንከባከብ ግዴታ የለበትም።

[30] እሥራኤል ልክ እንደ ዝሙት አዳሪ ውይም ጋለሞታ ሴት ትመስላለች። ዓይኖችዋ እንኳን እንደ ዝሙት አዳሪ ሴት ዓይኖች ተመስለዋል። ይህም እሷ ሁልጊዜ የተለያዩ ፍቅረኛሞችን ትፈልጋልች የሚለው የግጥም አባባል ዓይነት ነው። በዓይኖችዋ ውስጥ ምንም እፍረት የለም። ደግሞም ከዝሙት አዳሪ ከመምሰል ያለፈ ነገር ታደርግ ነበር። ምክንያቱም በትይዩ መስመሩ ላይ የሚያመለክተው እነዚያን ፍቅረኛሞችዋን ለማርካት ሰውነትዋን ማለትም “ጡቶችዋን” ትጠቀም እነደነበረ ይናገራል። ይህ አባባል ደግሞ የእስራኤል ሕዝብ ከሌሎች አማልክቶች ጋር በትጋት ግኑኝነት (ማለትም ታመልክ) እነደነበረ የሚናገር ቅኔያዊ አነጋገር ነው።

እንደ ተወለደችበትም ቀን እንዳላደርጋት

እንደ ምድረ ባዳና [31]

እንደ ደረቅ ምድር እንዳላድራጋት

በጥማትም እንዳልገድላት፤[32]

6

የግልሙትናዋ ልጆች ናቸውና[33]

ልጆችዋን አልምርም።[34]

7

እናታቸው አመንዝራለች፤ የፀነሰቻቸውም እንጀራዬንና ውኃዬን

ጥጤንና የተልባ እግሬን ዘይቴንና መጠጤን[35]

---

[31] እሥራኤል ከመንፈሳዊ ምንዝርናዋ ንስሐ መግባት አለባት፤ አለዚያ ከእግዚአብሔር ተጨማሪ ቅጣት ይጠብቃታል። ስለዚህ እሥራኤል እንደ ተተወ ሕፃን ትሆናለች። ይህም ማለት ሙሉ በሙሉ አቅመ ቢስ ትሆናለች ማለት ነው። እሥራኤል "እንደ ምድረ በዳ" ትሆናለች። ይህ ማለት አንድ ሰው ለመንብኘትና በውበቱም መደነቅ እንደሚፈልግ ዓይነት ምድረ በዳ አይደለም። ነገር ግን ይህ ምድረ በዳ "ደረቃማ ምድር" ነው። እቺ ምድር እንደ ድንጋይ የጠነከረች ናት። ምንም ነገር አታበቅልም። በምድሩ ላይ ያለው ሙቀት የሚያውክ ነው። ምንም እንኳን ውሃ በጣም አስፈላጊ ቢሆንም ዝናብ በጭራሽ አይዘንብም። መንግሥተ ሰማያት በዚህ ቦታ ላይ ምሕረት የላትም። እግዚአብሔር በጥማት ሊገድላት ስላሰበ ዝናቡ ሆን ተብሎ የተከለከለ ነበርና።

በሆሴዕ 2፡5 ላይ " ምድረ በዳ" የሚለው ቃል በአሉታዊ መልኩ ጥቅም ላይ ሲውል "ምድር በዳ" በ ሆሴዕ 2፡16 ላይ ደግሞ በአዎንታዊ መልኩ ጥቅም ላይ ውሏል። ስለዚህም በተመሳሳይ መልኩ ኢይዝራኤል የሚለው ቃል በሆሴዕ ውስጥ በሁለት የተለያዩ መንገዶች ጥቅም ላይ ውሏል፤ "ምደረ በዳ" የሚለውም ቃል በሁለት የተለያዩ መንገዶች ጥቅም ላይ ውሏል። የተደጋገሙ ቃልቶች መጽሐፉን አንድ ላይ ለማያያዝ ያገለግላሉ። የቃላት አጠቃቅምን በዜዴ መቀያየር ወደ አስደናቂው የእግዚአብሔር ሥራ ትኩረትን ይስባል። እግዚአብሔር ሁሉንም ነገር ወደ መልካም ነገር መለወጥ ይችላልና።

[32] በዚህ ምንባብ እና በሕዝቅኤል 16፡1–7 (በይሁዳ ላይ በተነገረው መልዕክት) መካከል ያለውን ጠንካራ ትይዩነት ይመልከቱ።

[33] እንደገና "ልጆች" የሚለው በእሥራኤል ምድር ውስጥ ያሉ ግለሰቦች ናቸው። በአጠቃላይ እሥራኤል ደግሞ እንደ "እናት" ነች። እግዚአብሔር ግን በሀገሪቱ ውስጥ ባሉ ግለሰቦች እና በአጠቃላይ በሀገሪቱ መካከል ምንም ልዩነት አይታይም። ማለትም በዚህ ጌዜ ምንም እንኳን ፈሪሃ እግዚአብሔር ያላቸው ቅሬታዎች ቢኖሩም ቅሉ ሁሉም ማለት ይቻላል "ልጆች" የተባሉት በመምንፈሳዊ ምንዝርና "እናታቸውን" ይከተሉ ነበር። ስለዚህ ከእናታቸው ጋር ባላቸው ግኑኝነት ምክንያት እነሱም ይቀጣሉ።

[34] ሆሴዕ 1፡6 ይመልከቱ።

[35] እንግዲህ የእሥራኤል ግልሙትና እዚህ ላይ ይገለጣል ። እሷም "ከውሽሞችዋ" (ባኣላውያንን) በአሳፋሪ ሁኔታ ተከትላ ትሮጣለች ምክንያቱም እነሱ ናቸው መጽናትዋን እንደሚያቀርቡላት አስባለችና። እግዚአብሔር ከዓይኗ የራቀ ነውና።

ከሚሰጡኝ ከውሽሞቼ በኋላ እንሄዳለሁ[36]

ብላ አስነወረቻቸው።

8

ስለዚህ እነሆ መንገድሽን በእሾህ እዘጋለሁ

መንገድዋንም እንዳታገኝ

ቅጥርን እቅጥርባታለሁ።

9

ውሽሞችዋንም ትከተላለች

ነገር ግን አትደርስባቸውም፤

ትፈልጋቸዋለች

ነገር ግን አታገኛቸውም፤[37]

---

የምታፈቅራቸው አካላት ሁሉንም ሥጋዊ ፍላጎቶቿ እንድሚያቀርቡላት እርግጠኛ ነበረች። ጠቢብ ሰባኪ ወይም አስተማሪ በዛሬ ጊዜ ያለውንም የእግዚአብሔርን ሕዝብ ከመንፈሳዊ ምንዝርና እንዲርቅ በማስጠንቀቅ እነዚህን ጥቅሶች ይጠቀማል።

[36] ከውሽሞቼ በኋላ እሄዳለሁ" የሚለው ቃል እሥራኤል የምታመልካቸውን ባዕድ አማልክቶችን የሚያመለክት ነው። ባኣል በሆሴዕ ዘመን እሥራኤላውያን ያመልኳቸው ከነበሩት ተቀናቃኝ አማልክት አንዱ ነበር። ባኣል የሚለው ቃል ባል ወይም ጌታ ማለት እንደሆነ ተመልክተናል። ስለዚህ ከእግዚአብሔር ጋር የተጋቡ እሥራኤላውያን "ባል" ብለው ከሚጠሩት ሌላ አምላክ ጋር ግኑኝነት ነበራቸው። እሥራኤላውያን ለሕይወት የሚያስፈልጉትን ነገሮች ማለትም ዳቦ፣ ውኃ፣ የበግ ፀጉር፣ ተልባ፣ ዘይትና መጠጥ ባኣል እንደሚሰጣቸው ያምኑ ነበር።

ባኣልን ማምለክ በተውሰነም ደረጃ ቢሆን ከሴትኛ አዳሪዎች ጋር አምልኮታዊ ዝሙት የሚፈጽሙ ሰዎች ጋር ይካተታል። እንደዚሁም ደግሞ እነዚህ ህገወጥ የፆታ ግንኙነት የተፈፀሙት ባኣል ከአናት (ባኣል ያገባት ሴት አማልክት ማለት ነው) ጋር ተመሳሳይ ነገር በማድረግ ለእነዚህ ድርጊቶች ምላሽ ይሰጣል ተብሎ ስለሚታሰብ ነበር። ስለዚህ በምድር ላይ ያለ የሰው ልጅ የግብረ ሥጋ ግኑኝነት ሲያደርግ አማልክትም በሰማይ ውስጥ የግብረሥጋ ግኑኝነት እንዲፈጽሙ ያነሳሳቸዋል ይህም ደግሞ ተስማሚ የአየር ጸባይንና የእርሻ በረከት ያስገኛል ተብሎ ይታመን ስለነበረ ነው። ባኣልን የሚመለከት ብዙ ቁጥር ያላቸው ጥንታዊ ታሪኮች በቁፋሮ በአርኪኦሎጂስቶች ተገኝቷል። እነዚህም ታሪኮች የባሕር አምላክ ከያም ጋር ያደረገውን ጦርነት እና በበጋ ወቅት ድርቅን ከሚያመጣው አማልክ ከሞት ጋር ያደረገውን ጦርነት ይተርካሉ። የባኣል ዋንኛ ረዳት አናት የተባለች ሴት አማልክት እሷም ባኣል የፆታ ግኑንኝት የፈጸመባት ነበረች።

የእሥራኤልውያን ባኣልን ማምልክ እና በባኣልም መታመናቸው እሥራኤል በእግዚአብሔር ላይ እንዳልታመነች ያሚያሳይ ማረጋገጫ ነው። እግዚአብሔር እንደ ባል ሚስቱን እሥራኤል እንደሚንከባከብ ቃል ገብቶ ነበር። ይህም ደግሞ ከእርሷ ጋር የገባው ኪዳን አካል ነበር። ነገር ግን እሥራኤል በእግዚአብሔር እንክብካቤ አልታመነችም። ምግቡንም መጠጡንም የሚያሟላላት ባኣል መስሏት ነበር። እሥራኤል ለባኣል ባላት ታማኝነት እግዚአብሔርን እንደ ጥሩ ባል እንደማትመለከተው አሳይታለች።

[37] ምንም እንኳን እሥራኤላውያን ባኣልን ለማምለክ ቢሞክሩም እሥራኤል እነዚህን "ውሽሞችዋ" ማግኘት እንዳትችል ያህዌ እርምጃ ይውስዳል። እዚህ ጋ እሥራኤል ከጋለሞታ ጋራ ተነጻጽራለችና ከማንንም ጋር ግኑኝነት ማድረግ አትችልም። መደበኛ ጋለሞታዎች ወደ እነርሱ የሚመጡ ደንበኞች አሏቸው። በመንገድም ጥግ ላይ ቆመው ይጠብቃሉ። እሥራኤል ግን

እርስዋም

ከዛሬ ይልቅ የዚያን ጊዜ ይሻለኝ ነበርና[38]

ተመልሼ ወደ ቀደመው ባሌ እሄዳልሁ ትላለች።

10

እርስዋም እህልንና ወይንን ጠጅ ዘይትንም ሰጠኋት

ለበኣልም[39]

የተሠራውን ብርና ወርቅ[40]

ያበዛሁላት እኔ እንደ ሆንሁ

አላወቀችም።

11

ስለዚህ እህሌን በጊዜዋ

ወይን ጠጄንም በወረትዋ

እወስዳሉ፤

ዕራቁትዋንም እንዳትሸፍን

---

ውሽሞችዋን ፍለጋ ትሄዳለች። እነዚህ ጥቅሶች እግዚአብሔር ባዕድ አማልክቶችን እንድታገኛቸው እንደማይፈቅድላት ያመለክታሉ። ምንም እንኳን ፍለጋ ወጥታ ብታስስም በፍጹም አታገኛቸውም። ውሽሞችዋን ትፈልጋለች ነገር ግን አታገኛቸውም። ስለዚህ እንድምታው ማንም አይፈልጋትም ማለት ነው። እንዴት ያለ አሳዛኝ ነገር ነው – ታማኝ ያልሆነች ሚስት ተስፋ ቆርጣ በየመንገዱ እየሮጠች ሰውን . . . ማንንም . . . አብረዋት የሚያመነዝር ስትፈልግ። የቀድሞ ውሽሞችዋ ደግሞ አይፈልጉዋትም። ምክንያቱም ተጠቅመውባታል እና አስጸያፊ ሆና አግኝተዋታል። አሁን እሷ ብቻዋን ቀርታለች።

[38] ስለዚህ ከብቸኝነትዋ የተነሳ “ወደ መጀመሪያው ባለቤቴ እሄዳሉ ወደ እሱም እመለሳለሁ!” የሚል ሃሳብ አላት። ይኼ ንስሐ አይደለም። እንዳውም ሆሴዕ ከቀድሞ ውሽሞችዋ በኋላ ከከንቱ እሩጫዋ እስካሁን እንዳላባትና በመተንፈስ ላይ እንዳለች አድርጎ ስሏታል። እግዚአብሔር መልሶ ሊወስዳት እንደሚችል ወደ መረዳት ነገር መጥታለች። ለነገሩ እግዚአብሔር ወደ ኋላ ውስዷታል (ለምሳሌ፤ እሥራኤል በመሳፍንት መጽሐፍ ውስጥ ንስሃ ገብታ ወደ እግዚአብሔር – ለአጭር ጊዜ “የተመለሰችባቸውን” ብዙ እና ብዙ ጊዜያት አስብ። ጋላሞታ ሚስት በፈለገችው ጊዜ መተው እንደምትችልና ደግሞም ስትፈልግ መመለስ እንደምትችል ታምናለች። ስለዚህ እግዚአብሔርም ስትፈልገው ልታገኘው ትችላለች። እንደዚሁም ደግሞ ሌሎች ውሽሞችዋንም ስትፈልግ ልታገኛቸው ትችላለች። ይህ የእስዋ ውሳኔ ነው (ስለዚህ ታስባለች)። ምናልባት ደግሞ ከእግዚአብሔር ጋር ያላት ሕይወት መጥፎ እንዳልሆነ ወስና ይሆናል። ቀጥለው ያሉትን ጥቅሶች እግዚአብሔር ጥሩ መጋቢ እንደነበር በግልጽ እንደሚያሳዩ አሁንም አልተረዳችም። አሁንም እንኳን የሚንከባከባት ባኣል ሳይሆን እግዚአብሔር መሆኑን አልተረዳችም።

[39] እግዚአብሔር ጥሩ ባል ነበር። የሚስቱንም ፍልጎት ያሟላ ነው። እህል ወይንና ዘይትም ሰጥቷታል። ከዚህም በላይ “ብርና ወርቅም አበዛላት”። እሥራኤል ጥሩ እንክብካቤ ተደርጉላታል።እሷ ግን ምንድር ነው ያደረገችው? እግዚአብሔር የሰጣትን ስጦታ ለውሽማዋ ለባኣል ሰጠች!

[40] እግዚአብሔር ለሰዎች መልካም ነገርን የሚሰጥ ነው (ያዕቆብ 1፡17 ይመልከቱ)።

ጥጤንና የተልባ እግሬን እገፍፋታለሁ።

12

አሁንም ውሽሞችዋ እያዩ

ነውርዋን እገልጣለሁ፤

ከእጄም ማንም አያድናትም።[41]

13

ደስታዋንም ሁሉ

በዓላቶችዋንም መባቻዎችዋንም ሰንበቶችዋንም

የተቀደሱትም ጉባኤዎችን ሁሉ አስቀራልሁ።[42]

14

እርስዋም ውሽሞቼ የሰጡኝ

ዋጋዬ ይህ ነው ያለችውን

ወይንዋንና በለስዋን አጠፋለሁ፤

ዱርም አደርገዋለሁ

የምድረ በዳም አራዊት ይበሉታል።[43]

---

41 እግዚአብሔር እንዴት ነው ለእሥራኤል አዲስ የመመለስ ፍላጎት ምላሽ የሰጠው? እግዚአብሔር የቀድሞ ሚስቱን ወደ እሱ በድንገት ዞራ እንድትመለስ አላሳመናትም። እንዳውም ወደ እሷ ከመቅረብ ይልቅ ከእርሷ የበለጠ ርቋታል። ከዚህም በኋላ የቀድሞ ሚስቱ ስጦታዎችዋን ለውሽሞችዋ እንድትጠቀም አይፈቅድም። መብልዋና ልብሷንም ጭምር ሁሉ ይወሰዳሉ። ለብስዋንም አውልቆባት የቀድሞ ፍቅረኛሞችዋ ሴሰኛና ጋለሞታ እንደሆነች ያዩዋታል። ማንም ሰው ሊያያት አይፈልጋትም። ስለ እርስዋም ቢዋጉ ውሽሞችዋ ሊያገኙዋት አይችሉም ነበር ምክንያቱም እግዚአብሔር እንዳያገኙዋት ይከለክላቸዋልና።

42 ነገር ግን እግዚአብሔርና የቀድሞ ሚስቱን የሚያራቁታት ምግብና ልብስ ብቻ አልነበረም። እደዚሁም በእግዚአብሔር ስም የተደረጉትን ነገሮች ኃይማኖታዊ ልማዶችዋንም ሳይቀር ያስወግድባታል። ከዚህ በኋላ በዓላቶችዋንና ሰንበታቶችዋን አታከብርም። ለማንኛውም እነዚህ ልዩ ቀናት ከአሁን በኋላ ለእግዚአብሔር ቀልዶች ነበሩና። ከአሁን በኋላም በእግዚአብሔር በተመረጡት በዓላት እና ሰንበት ላይ መሳለቂያ ማድረግ አትችልም። ከእግዚአብሔርም ሆነ ከባኣል ለእስራኤልውያን መታወቂያ የተሰጣቸው ሁሉ ከእርስዋ ይወሰዳሉና።

43 እሥራኤል ባኣልን በመከተልዋ ምክንያት አሁን ብልጽግናዋን ያገኘች መስሏታል። ባኣል የምታገለግልበትን ወሮታዋን እየከፈላት ለመሆኑ የወይን እርሻዎችዋና የበለስ ዛፎችዋ ማስረጃዎች ናቸው። ደግሞ እነዚህ ነገሮች በሃሳብዋ ከባኣል ጋር በመተኛትዋ ያገኘችው ክፍያ መስሎዋት ነበር። እንግዲህ የወይኑንና የበለሱንም ዛፎች ከጠፉስ በኋላ ምን ታስብ ይሆን? ኩርንችትና እሾህ ምድሪቱን ሲሞላው ምን ታስብ ይሆን? እሥራኤል በዚህ ጊዜ በኃይማኖት ግራ ተጋብታ ነበር፤ ነገር ግን ማንም እግዚአብሔር ሆነ ነቢያቱ (ምናልባትም ጥቂት ታማኝ ሊሎችም) ግድ የሰጣቸው አይመስልም። ነዋሪዎችዋም የባኣልን ልዩ ቀናትም እያከበሩ ነበር ደግሞም የእግዚአብሔርንም (ሰንበት፣ በዓላት ፣ ወዘተ) ያከብሩ ነበር። እግዚአብሔር የእስራኤልን ግማሽ ትኩረት በማግኘቱ እራሱን እንደ እድለኛ አድርጎ አልቆጠረም። እሥራኤል ለከፊል ታማኝነትዋ ሽልማት አይሰጣትም። ይልቅስ ትቀጣለች እንጂ።

15

እኔን ረስታ

ውሽሞችዋን እየተከተለች

በጉትቾችዋና በጌጥዋም እያጌጠች

ለበኣሊም እያጠነችበትን ወራት

እበቀልባታለሁ[44] ይላል እግዚአብሔር።[45]

---

[44] የእሥራኤል ቅጣት አስፈሪ ነው። እርስዋ ከእግዚአብሔር እነደተለየች እንደዚሁም ከውሽሞችዋም (ከባኣልም) እንድትለይ ትደረጋለች። ራቁትዋንም ብቻዋን ትቀራለችና። በዚህ ግጥም ውስጥ ያሉትን የመጀመሪያ መስመር ላይ ("እኔን ረስታ ውሽሞችዋን እየተከተለች") የሚለው በጥልቀት ማሰላሰል የሚገባ ነገር ነው። እሥራኤል ውሽማዋን ተከትላ የሄደችበት ድርጊት እግዚአብሔርን ከረሳችበት ድርጊትዋ ጋር እኩል ነው። አንዱን ተከትሎ መሮጥ ማለት ሌላውን መርሳት ማለት ነውና። ሁለቱ የተያያዙ ነገሮች ናችው። ከሁለቱም ማለትም  ከእግዚአብሔርና ከባኣል ጋር ያለውን ወሳኝ ግኑኝነት መጠበቅ አይቻልም። ይህ ዛሬም እውነት ነው። ክርስቲያኖችም ቢሆኑ እግዚአብሔርንና ሌላ አምላክን በአንድ ጊዜ ለማገልገል መሞከር ስለሚያስከትለው አደጋ ማስጠንቀቂያ ሊሰጣቸው ይገባል።

[45] "ይላል እግዚአብሔር" የሚሉት ቃላት በዚህ የቃል ንግግር ውስጥ ያሉትን ቃላት የእግዚአብሔር ይፋዊ መግለጫ መሆናቸውን ለማጉላት ነው። እንደ አለመታደል ሆኖ የእንግሊዝኛው ትርጉም "ይላል እግዚአብሔር" የሚለው ትንሽ ግልጽ አይደለም። "ይላል እግዚአብሔር" ወደ እግዚአብሔር የንግግር ድርጊት ትኩረትን ይስባል። ነገር የእንግሊዝኛው ESV መጽሕፍ ቅዱስ እዚህ ጋ ግስ ሲጠቀም "ይላል" ለሚለው በዕብራይስጥ ምንም ግስ የለውም። ይልቁንም ይህ የሁለት ስሞች ማለትም "ይላል" የሚለውና "እግዚአብሔር" የሚለው "የተገነባበት ሰንሰለት" ነው። ("የግንባታ ሰንሰለት" ሀሳብ ዕብራይስጥ ሁለት ስሞች አንዳንድ ጊዜ እንዴት እንደሚጣመሩ የሚገልጽ ቴክኒካዊ ቃል ነው።) በዕብራይስጥ ሰዋሰው ሕግ ላይ በመመስረት "እግዚአብሔር" ትክክለኛ ስም ስለሆነ "ይላል" የሚለው ቃልም የተውሰነ መሆን አለበት። ከዕብራይስጥ ጋር በይበልጥ የሚስማማው ትርጉም "የእግዚአብሔር መግለጫ" የመሰለ ነገር ይሆናል። በሌላ አነጋገር በዕብራይስጥ ጽሑፍ ውስጥ ያለው አጽናዖት በእግዚአብሔር በፈጸመው ድርጊት ላይ ሳይሆን እግዚአብሔር ባዘጋጀው በመግለጫው ላይ ነው። "ይላል እግዚአብሔር" የሚሉት ቃላት ለአዋጁ ተጨማሪ ትኩረት ይስባሉ። በተወሰነ መልኩ እነዚህ ቃላት በጽሑፉ ውስጥ ቢሆኑም እነዚህ ቃላት ግን ቀጥታ ጽሑፉ አይደሉም። የጽሑፉ ማረጋገጫ ናቸው እንጂ።

"ይላል እግዚአብሔር" የሚሉት ቃላት በዚህ ክፍል ውስጥ የሚገኙትን የእግዚአብሔር ቃላት የበለጠ አስገዳጅ አያደርጓቸውም፤ ምክንያቱም ቃላቱ ሁል ጊዜ እውነት ናቸው፤ እናም ያለዚህ መግለጫም ቢሆን ሁል ጊዜ አስገዳጅ ናቸው። በሌላ መልኩ ደግሞ እነዚህ ቃላት በአንድንድ መንገዶች አስፈላጊ አይመስሉም። ደግሞም አንባቢው እግዚአብሔር እየተናገረ እንደሆነ አስቀድሞ ተነግሮታል። አንባቢው የእግዚአብሔር ቃላት እውነትና አስገዳጅ መሆናቸውን ማወቅ አለበት፤ እናም ለቃላቱ ትክክለኛ ምላሽ ሁል ጊዜ መፈለግ ያስፈልጋል። ደግሞም ምንም እንኳን እነዚህ ቃላት አላስፈላጊ ቢመስሉም በነቢያት ውስጥ በተደጋጋሚ ይገለጣሉ። ደግሞም አናባቢው የተወሰኑ የቃላት ስብስብ "የእግዚአብሔር መግለጫ" እንደሆነ ያስታውሳል። እነዚህ ቃላት በተገለጡበት ጊዜ ብዛት ላይ በመመስረት "የእግዚአብብሔር መግለጫ" እንደሆነ ያስታውሳል። ደግሞም እነዚህ ቃላት በተገለጡበት ጊዜ ብዛት ላይ በመመስረት "የያህዌ መግለጫ" የሚሉት ቃላት ለአንባቢው ጥቅም የግድ አስፈላጊ መሆናቸው ግልጽ ነው። ለዚህም ሊሆን ይችላል መንፈስ ቅዱስ እንዲካተቱ ያደረጋቸው።

ደግሞም በጽሑፉ ውስጥ "የእግዚአብሔር መግለጫ" ጥቅም ላይ የዋለበት ምክንያት ምናልባት እግዚአብሔር በአንዳንድ አጋጣሚዎች መሐል ከፈጸመበት ምክንያት ጋር ተመሳሳይ ሊሆን ይችላል (ዕብራውያን 6፡13–20 ይመልከቱ)። ሆኖም በግልጽ ለማየት እንደሚቻለው እግዚአብሔር ቃሉን ለማረጋገጥ መሐላ አያስፈልገውም። እግዚአብሔር በመሐላም ሆነ ያለ መሐላ እውነት ነው። አልፎ አልፎም "ለተስፋው ወራሾች የዓላማውን የማይለወጥ ባህሪ አሳማኝ በሆነ መልኩ ለማሳየት" መሐላ ያደርጋል። እግዚአብሔር ሕዝቡን በእምነት ጸንቶ እንዲቆም ለመርዳት ምሏል! "የእግዚአብሔር መግለጫ" ከእግዚአብሔር ቃላት ጋር ሲጣመር አንዳች ተመሳሳይ ነገር ይፈጸማል። ይህ ለእግዚአብሔር ሕዘብ ጥቅም ነው! ስለተባለው ነገር በጥልቀት ማሰብ እንዳለባቸው ያረጋግጣል ምክንያቱም "የእግዚአብሔር መግለጫ" ነውና። ከዚህ ባሻገር በዚህ ልዩ የእግዚአብሔር ቃል ስብስብ ማመን ይችላሉ ማለት ነው። ነገር ግን "የእግዚአብሔር መግለጫ" ለአማኞች ብቻ አይደለም።

**ሆሴዕ 2፡16–25**

ሆሴዕ 2፡4–15 ሙሉ በሙሉ አሉታዊ ነበር። የሆሴዕ ቃል በመንፈሳዊ ምንዝርናዋ የተነሳ በእሥራኤል ላይ ያለውን የእግዚአብሔርን ቅጣት ይገልጻል። እነዚህ አሉታዊ ጥቅሶች ጥቅሶቹን ወዲያውኑ ተከትለው እንዲሄዱ ያደርጉታል። እግዚአብሔር በእስራኤል ላይ የሚያመጣው ሌላ አሰቃቂ ቅጣት እንደሚያበስር ስትጠብቅ እሱ ተቃራኒውን ያደርጋል (ይህ በትንቢት የተለመደ መሆኑን ማስታወስ ተገቢ ነው)!

> "ስለዚህ እንሆም አባብላታልሁ
>
> ወደ ምድረ በዳም አመጣታለሁ
>
> ለልብዋም እናገራልሁ።" **ሆሴዕ 2፡16**

"ስለዚህ" የሚለው ቃል አስገራም ነው። የእግዚአብሔርን ድርጊት ከእሥራኤል ግልሙትና ጋር ያገናኛል። የስዋ መንፈሳዊ ግልሙትና ፈጽሞ ያልተጠበቀ ነገር እንዲፈጽም አድርጎታልና። ባቃል ኪዳንዋ ላይ



ስልማትጸና፣ ባኣልንም ከእግዚአብሔር ይልቅ የሚስብ አማራጭ ሆኖ ስላገኘችው፣ ባኣልንም ተከትላ ስለሮጠች ነቢያትንና መጽሕፍትንም አልሰማም ስላለች እርሱም "ወደ ምድረበዳ ሊወስዳት" እና እሷንም ለማሳመን ወሰነ። እሱም በሌላ አነጋገር ፍቅሯን በፍቅር ለማሸነፍ ("አባብላታለሁ" እናም "ለልብዋም እናገራልሁ") ይላል

---

ለሚጠራጠሩም ስለምሕረት ነው የሚናገረው። ተጠራጣሪ አንባቢዎች ለእግዚአብሔር ቃል በእምነት ምላሽ እንዲሰጡ አንድ ተጨማሪ እድል ይሰጣል።

"የእግዚአብሔር መግለጫ" በነቢያት ሁሉ ጥቅም ላይ ውሏል። በእሥራኤልና በይሁዳ የሚኖሩ ሰዎች የእንዚህን ቃላት ክብደት እንደተገነዘቡ ግልጽ ነው፤ ምክንያቱም እነዚህ ቃላቶች በሐሰተኛ ንግግራቸው ላይ ትክክለኛነት ለመጨመር በሐሰተኛ ነቢያት ተጠቅመዋል (ኤርምያስ 23፡31 እና ሕዝቅኤል 13፡7 ይመልከቱ)! "የእግዚአብሔር ቃል" የሚለው በመጀመሪያ በሙሴ መጻሐፍ ውስጥ ነው የሚገኘው፤ በዚያም ሁለት ጊዜ ብቻ ጥቅም ላይ ውሏል (ዘፍጥረት 22፡16 እና ዘኍልቁ 14፡28)። በሙሴ መጽሐፍ ውስጥ ያሉትን ሁለቱም አጠቃቀሞች የእግዚአብሔር ጠንካራ ቃል በገባባቸው ምንባቦች ውስጥ ነው። እነዚህ ቃላት የእግዚአብሔር ቃላት እነደሚፈጸሙ ተጨማሪ ማረጋገጫ ሆነው ያገለግላሉ። "የእግዚአብሔር መግለጫ" (ይላል እግዚአብሔር) የሚለው በሆሴዕ ደግሞ አራት ጊዜ ያህል ተጠቅሷል (ሆሴዕ 2፡15፣ 2፡18፣ 2፡23 እና 11፡11)።

16

ስለዚህ እነሆ[46] አባብላታለሁ

ወደ ምድረ በዳም አመጣታለሁ[47]

ለልብዋም እናገራለሁ።[48]

17

ከዚያም የወይን ቦታዋን፤[49]

የተስፋ በርም እንዲሆንላት የአኮርን ሸለቆ እሰጣታለሁ፤[50]

---

46 "እነሆ" የሚለው ቃል ብዙውን ጊዜ ለማጉላት ያልተጠበቀ ነገርን ለማስተዋወቅ የአንባቢውን ትኩረት ወደ አዲስ ነገር ለመሳብ ወይም ለአንባቢውን ስለ አንድ ነገር ለማብራራት ያገለግላል። እዚህ ጋ ቃሉ ወደ አልተጠበቀ ነገር ትኩረትን ይስባል። በተጨማሪም ሆሴዕ 9፡6 ይመልከቱ።

47 በሆሴዕ 2፡5 ላይ " ምድረ በዳ" የሚለው ቃል በአሉታዊ መልኩ ጥቅም ላይ ውሏል። እንደዚሁም ደግሞ በአሉታዊ መልኩ በሆሴዕ 13፡15 ጥቅም ላይ ውሏል። እዚህ ጋ ግን አዎንታዊ ነው። እግዚአብሔርም እሥራኤልን ወደ ምድረ በዳ ያመጣታል ለራሱ እነድትሆን ያሸንፋታል። መጥመቁ ዮሐንስ በምድረ በዳ እየሰበከ መምጣቱ አስፈላጊ ነገር ነበር (ኢሳይያስ 40፡30 እና ማቴዎስ 3፡1–3 ይመልከቱ)። የዮሐንስ ስብከት የእግዚአብሔር መንግሥት እንደመጣች እና ይቅርታም ለሁሉም ክፍት እነደ ሆነ ማስታወቅ ነበር!

48 ይህ የመጨረሻው ሐረግ ("ለልቧም እናገራሉ") የሚለው በዕብራይስጡ (MT) እና በግሪኩ (LXX) ተመሳሳይ ነው። ሁለቱም "እና ለልቧ እናገራሉ" በሚል ይነበባሉ። ሕዝቅኤል 36፡24–27 ይመልከቱ።

49 በሆሴዕ ውስጥ "የወይን ቦታዋን" የሚለው በዘይቤነት ጥቅም ላይ ውሏል። እዚህ ጋ በሰዎች የሚመረተውን ፍራፍሬ ዓይነት የሚያመለክት ነው። በሌላ መልኩ ደግሞ ፍሬን የሚገለጽበት ሌላውን መንገድ "ሕይወት ሰጪ ከሆነው ከእግዚአብሔር መንፈስ ጋር የተገናኘና ዘላቂ ዘላላማዊ **ወጤት**" ሊሆን ይችላል። በምድረ በዳ እሥራኤል በመጨረሻ በእውነት ፍሬያማ ትሆናለች። በመጽሐፍ ቅዱስ ከመጀመሪያ ጀምሮ የእግዚአብሔር ሕዝብ "ፍሬ እንዲያፈራና እንዲባዛ" ተጠርቷል (ዘፍጥረት 1፡28፤ 8፡17፤ 9፡1፣ 7፤ 28፡3፤ 35፡11፤ 48፡4 እና ዘሌዋውያን 26፡9 ይመልከቱ)። እንደ አለመታደል ሆኖ በኃጢአት ምክንያት እሥራኤላውያን በእውነት እግዚአብሔር ያሰበውን ያህል ፍሬያማ አልነበሩም። ኃጢአት ሁልጊዜ ዘላቂ ፍሬ እንዳይፈጠር አድርጓል። እንዳውም በሆሴዕ እሥራኤል በከፉ መንገድ ፍሬያማ መሆኗን እናነባለን! ይሁን እንጂ ይህ በሆሴዕ ውስጥ ያለው ጥቅስ የእግዚአብሔር ሕዝብ ፍሬያማ እምቅ ችሎታ በመጨረሻ ይህ ትንቢት በሚፈጸምበት ጊዜ እውን እንደሚሆን አስደናቂ ተስፋ ይሰጣል። ነቢያት ስለ እግዚአብሔር ሕዝብ የወደፊት ፍሬያማነት በብዙ መንገድ ይናገራሉ (ለምሳሌ ኤርምያስ 23፡3 ይመልከቱ)። ነገር ግን ይህ ፍሬያማነት ወደ ፊት አይሆንም። ምክንያቱም ተስፋው በወንጌል ክስተት ምክንያት ወደ እግዚአብሔር ሰዎች መጥቷል። የክርስቶስ ሕይወት፣ ሞት፣ ትንሣኤ እና ዕርገት የእግዚአብሔር ሕዝብ ታላቅ ፍሬ እንዲያፈራ አድርጓልና። ይህም የሆነው መንፈሱ አሁን በውስጣቸው ስለሚኖር ነው። "የመንፈስ ፍሬ" (ገላትያ 5፡22–23 ይመልከቱ) በወንጌል ክስተት ምክንያት የመጣው የእግዚአብሔር ሕዝብ ፍሬያማነት አንዱ ገጽታ ነው ( በተጨማሪም ኢየሱስ በታማኝነት በእርሱ ውስጥ "በሚኖሩት" ሁሉ ያለውን ፍሬያማነት በተመለከተ የተናገረውን ይመለከቱ ዮሐንስ 15)።

50 ይህ በጣም ጥሩ ግጥም ነው፤ ይህም አንባቢው (ወይንም የሆሴዕ የመጀመሪያ ተደራሲ ከሆነ ሰሚው) በምሳሌያዊ አነጋገር ትርጉም ላይ በጥልቀት እንዲያሰላስል ያስገድዳል። **"የተስፋ በር"** የሚለው ሐረግ **"ከአኮር ሸለቆ"** የበለጠ ለመረዳት ቀላል ነው። **"የተስፋ በር"** ተስፋ ወደሚገኝበት ቦታ ይጠቁማል። ተስፋ የሚመጣበት በር ወይም አንድ ሰው ተስፋን ለማግኘት የሚያልፍበት በር ማለት ትርጉሙ በመሠረቱ አንድ ነው። ተስፋ በዚህ ቦታ ይገኛል። **"የአኮር ሸለቆ"** ግን ትንሽ ለመረዳት አስቸጋሪ ነው በተለይም ለአሁን ዘመን አባንቢዎች። የአኮር ሸለቆ እሥራኤል በመጀመሪያ የከነዓንን ምድር

በዚያም ከግብፅ ምድር እንደ ወጣችበት ቀን እንደ ህፃንነትዋ ወራት ትዘምራለች።[51]

18 በዚያ ቀን ባሌ ብለሽ ትጠሪኛለሽ እንጂ ባኣሌ ብለሽ አትጠሪኝም ይላል እግዚአብሔር፤[52]

---

ሲቆጣጠሩ በኢያሱ ዘመን የመጣ ስም ነው (ኢያሱ 7፡22–26 ይመልከቱ)። ይህ ሸለቆ እሥራኤላውያን አካን የተባለውን ሰው እግዚአብሔርን ባለመታዘዙ በድንጋይ የወገሩበት ሸለቆ ነበር እሥራኤል ኢያሪኮን በወረረ ጊዜ ያገኘውን ካባና ብርና ወርቅ ወስዷል።

የአኮር ሸለቆ ስሙ እንደሚያመልክተው የችግር ሸለቆ ነበር። በዚህ ሸለቆ ውስጥ የእሥራኤልን ኃጢአት እና በሕዝቡ ላይ ያስከተለው ችግር የሚያስተውስ የድንጋይ ክምር ቆሞ ነበር። የድንጋይ ክምሩ ለእሥራኤል የእግዚአብሔርን ፍርድ ማታወሻ ነበር። አሁን ግን የእሥራኤል ኃጢአት እና የእግዚአብሔርንም ፍርድ ቦታ የነበረው ወደ ተስፋ በር ተቀይሮ ነው የሚታየው። የእሥራኤል ተስፋ በሌላ አነጋገር ከኃጢአቷ እና ከእግዚአብሔር ቁጣ ጋር የተያያዘ ነው። ይህ እንዴት ሊሆን ይችላል?

ይህንን ምንባብ በወንጌል መነፅር ስንመለከተው የእኛ "የተስፋ በር" – ተስፋ ወደ እኛ የመጣበት – ኃጢአታችን እና የእግዚአብሔር ቁጣ በግልጽ በሚታውቅበት – መስቀል ላይ እንዳለ እናስተውላለን። መስቀል ኃጢአት የተገለጠበት ነው። መስቀል እግዚአብሔር በዚያ ቁጣውን ያፈሰሰበት ነው። መስቀል ለእያንዳንዳችን ተስፋ የተገኘበት ነው።

*እኛ በእርሱ ሆነን የእግዚአብሔር ጽድቅ እንሆን ዘንድ ኃጢአት ያላወቀውን እርሱን ስለእኛ ኃጢአት አደረገው።* **2 ቆሮንቶስ 5፡21**

ወንጌል በግጥም እየተመለከትን ነው! እግዚአብሔር ትንቢት እንዴት እንደሚፈጽም በሆሴዕ ዘመን ማንም ሊያወቅው አይችልም። እንዴት አድርገው ሊመለከቱት ይችላሉ? የሆሴዕ ትንቢት መለስ ብለን ስንመለከት ግን ይህ የሆነው እግዚአብሔር ኃጢአታችንን በኢየሱስ ላይ አድርጎ በእርሱ ላይ በፈረደበት ጊዜ እንደሆነ እንመለከታለን። ኢየሱስ በመስቀል ላይ ሲሰቀል ቁጣውን አፈሰሰ፤ በዚያም የእግዚአብሔርን ሕዝብ ኃጢአት በሕዝብ ፊት በተገለጠበት ቦታ እግዚአብሔር የተስፋን በር ከፈተላቸው።

[51] ምንም እንኳን የእግዚአብሔር ሕዝብ በጥንት ጊዜ "በምድረ በዳ" ውስጥ ስለሚፈጽሙት ክንውኖች እግዚአብሔርን ቢቃወሙትም ከዚያ በኋላ ሕዝቡ እግዚአብሔርን ሊቃወሙት አልቻሉም። ይልቁንም ከግብጽ ሲወጡ እንደተከተሉት ይከተሉት ጀመር።

እግዚአብሔር እሥራኤላውያንን በግብፅ በባርነት የነበሩበትን የቀድሞ ዘመን አስታውሷቸዋል። ከባርነት ወደ ነፃነት አመጣቸው። እዚህ ጋ እግዚአብሔር የተናገረው ቃል ይህን ከእርሷ ዳግም እንደሚያደርግ ፍንጭ ይሰጣል። ከባርነት አውጥቶ ይመራታል እሷም ትከተላለች። ብዙ የነቢያት ምንባቦች እግዚአብሔር ሕዝቡን በ**ዳግም ዘጸአት** ተብሎ እንደሚመራ ይናገራሉ (ለምሳሌ ኢሳይያስ 11፡10–16 እና ኤርምያስ 16፡14–15 ይመልከቱ)። በነቢያቱ መልዕክት እንደተገለጸው ይህ የዳግም ዘጸአት ከመጀመሪያው ዘጸአት እጅግ የላቀ እንደሆነ ተመለከቷል። ብዙ ሰዎችን ያሳትፋል (ማንም ሊቆጥረው የመይችለው ማለት ነው) ስለዚህ የበለጠ ውጤታማ ይሆናል። ከባርነት ነፃ የሚወጡት ሰዎች በእውነት እግዚአብሔርን የሚወዱ ይሆናሉ እንደዚሁም እንደ እግዚአብሔር ሰዎችም ይኖራሉ። ይህ ዳግም ዘጸአት ከወንጌል ክስተት ጋር የተያያዘ ነው። ለዚህም ነው ራዕይ 15፡2–4 ክርስቲያኖች በእግዚአብሔር ነፃ ከወጡ በኋላ "የሙሴን መዝሙር" እንደሚዘምሩ የሚናገረው (በተጨማሪም ኢሳይያስ 12 ን ይመልከቱ)። ይህ እሥራኤላውያን ቀይ ባሕርን ሲሻገሩ የዘመሩት መዝሙር ነው (ዘጸአት 15 ይመልከቱ)! ይሁን እንጂ በራዕይ መጽሕፍ ግን "የሙሴ መዝሙር የእግዚአብሔር አገልጋይ እና **የበጉ መዝሙር** ተብሎ ተገልጿል። ሙሴ ከመጀመሪያው ዘጸአት ጋር የተያያዘ ነው። የእግዚአብሔር በግ –ኢየሱስ– ደግሞ ከዳግም ዘጸአት ጋር የተያያዘ ነው።

[52] ከዚህ ከዳግም "ዘጸአት" በኋላ የእግዚአብሔር ሕዝብ ሳይወድዱ አይከተሉም። ይልቁንም እንደ ተወደደ ባል አድርገው ይከተሉታል። ነገር ግን "በመጀመሪያው ዘጸአት" የሆነው ይህ አይደለም። እሥራኤል ገና ከጥንት ጀምሮ ለእግዚአብሔር ያላትን "ፍቅር" ከሌሎች አምልክቶች ፍቅር ጋር የተደባልቀ ነበር። በሚመጣው ዘመን ግን ሆሴዕ የእግዚአብሔር ሰዎች

19 የበኣሊምን ስም ከአፍዋ አስወግዳለሁና በስማቸውም እንግዲህ አይታሰቡምና።[53]

እግዚአብሔርን ብቻ እንደሚወዱ ተናግሯል። የሚቀጥለው ጥቅስ የእግዚአብሔር ሰዎች ለምን ለእግዚአብሔር ታላቅ ፍቅር እንዳላቸው ያብራራል።

[53] እግዚአብሔር ራሱ ሕዝቡን በማነሳሳት መሰጠትን ለራሱ ያነሳሳል! የባኣልንም ስም ከእሥራኤላውያን አንደበት ያጠፋል። ከእንግዲህ ስለ ባኣል አትናገርም (ወይም አታናግራቸውም) ምክንያቱም እንደገና ስለነሱ ስለማታስብ ነው። እሷም በእግዚአብሔር ፍቅር ትነዳለች። እግዚአብሔርም የቀድሞ ወዳጆቿን ያስረሳታል። እሱም በፍቅሩ እሷን ለራሱና ለራሱ ብቻ ያሸንፋታል። ትኩረትዋንም በእግዚአብሔር ላይ ብቻ እንዲሆን የጣዖት አምልኮትዋን ከእርስዋ ያስወግዳል። ይህ እንዴት ያለ ለውጥ ነው!

እግዚአብሔር በወንጌል የሚሰራው ይህንኑ መሆኑን ማወቅ አለብን። እሱ ወደራሱ ይስበናል እናም እንድንወደው ያደርገናል። ከጣዖት ፍቅራችንንም ያነጻናል። ይህም የሚሆነው በራሳችን ፈቃድ ወይም ቅድስና ምክንያት አይደለም። ይህም የሚሆነው በምሕረቱና በቸርነቱ ነው። ለእርሱም ብቻ የምንሰጥበትም ምክንያት እርሱ ራሱ ብቻ ይሆናልና። ይህ እውነት በሕዝቅኤል መጽሐፍ ውስጥ እንዴት እንደታወጀ ልብ ይበሉ።

> *ከአሕዛብ መካከል አወጣችኋለሁ ከየአገሩም ሁሉ እሰበስባችኋሉ ወደ ገዛ ምድራችሁም አመጣችኋለሁ። ጥሩ ውኃንም እረጭባችኋለሁ እናንተም ትጠራላችሁ ከርኩሰታችሁም ሁሉ አጠራችኋለሁ። አዲስም ልብ እሰጣችኋለሁ አዲስም መንፈስ በውስጣችሁ አኖራለሁ፤ የድንጋዩንም ልብ ከሥጋችሁ አወጣለሁ፤ የሥጋንም ልብ እሰጣችኋሁ። መንፈሴንም በውስጣችሁ አኖራለሁ በትእዛዜም አስሄዳችኋለሁ ፍርዴንም ትጠብቃላችሁ ታደርጉትማላችሁ።* **ሕዝቅኤል 36፡ 24–27**

“የድንጋዩንም ልብ ከሥጋችሁ አወጣለሁ” የሚለው ቃል ኪዳን ጠማማ እና ከፉ ልብን ለማስወገድ የተሰጠ ተስፋ ነው። ”የሥጋንም ልብ እሰጣችኋሁ” የሚለው ቃል ኪዳን እግዚአብሔርን ለመከተል እንቢ ያለውን የደነደነ ልብ ለስለስ ያለ እና ለጥሪው ምላሽ በሚሰጥ ልብ ለመተካት የተሰጠ ተስፋ ነው። ይህ ሁሉ የሆነው ኢየሱስ በሕይወቱ፣ በሞቱ እና በትንሣኤው ባከናወነው ሥራ ነው። ሆሴዕ በእነዚህ ጥቅሶች ውስጥ የተለያዩ ቃላት እየተጠቀመ ሳለ በትክክል ተመሳሳይ ነገር እየገለጸ ነው!

20 በዚያም ቀን ከምድር አራዊትና ከሰማይ ወፎች ከመሬትም ተንቀሳቃሾች ጋር ቃል ኪዳን
አደርግላቸዋለሁ፤[54] ቀስትንና ሰይፍን ሰልፍንም ከምድሩ እሰብራለሁ ተከትለውም እንዲኖሩ
አስችላቸዋልሁ።[55]
21 ለዘላለምም ለእኔ እንድትሆኚ አጭሻለሁ፤ በጽድቅና በፍርድ በመሕረትና በርኅራኄ አጭሻለሁ።

---

[54] ነገር ግን የእግዚአብሔር ተስፋዎች በእሱና በሕዝቡ መካከል ስለሚያመጣው ፍቅር ብቻ አይደለም። የሚያደርጋቸው ለውጦች ከዚህ የበለጠ ሰፊ እንደሆኑ በሆሴዕ 2፡20ሀ ላይ ይጠቁማል። በሕዝቡ ውስጥ በመጣውም ለውጥ ምክንያት ሁሉንም ነገር ይለውጣል። **በዘፍጥረት 1** ላይ ካለው የመጀመሪያው የፍጥረት ዘገባ የተወሰደውን ቋንቋ በመጠቀም እግዚአብሔር እሥራኤልን ወደ አዲስ ፍጥረት እንደሚያመጣት ተናግሯል! ይህ አዲስ ሥራ በሰዎች ላይ ብቻ ሳይሆን በሁሉም የተፈጠሩ ነገሮች ላይ ተጽዕኖ ያደርጋል። ደግሞም ይህ "የአዲስ ፍጥረት" ቋንቋ በመላው መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የወንጌልን ክስተት ውጤቶች ለመግለጽ ጥቅም ላይ ውሏል። ጳውሎስ "የእግዚአብሔር ልጆች" በሚገለጡበት ጊዜ እግዚአብሔር ለተፈጥሮ ሳይቀር ራሱ ስለሚያመጣቸው በረከቶች እንዴት እንደተናገረ ልብ ይሏል።

> *ለእኛም ይገለጥ ዘንድ ካለው ክብር ጋር ቢመዛዘን የአሁን ዘምን ሥቃይ ምንም እንዳይደለ አስባለሁ። የፍጥረት ናፍቆት የእግዚአብሔርን ልጆች መገለጥ ይጠባበቃልና። ፍጥረት ለከንቱነት ተገዝቶአልና በተስፋ ስላስገዛው ነው እንጂ በፈቃዱ አይደለም፤ ተስፋውም ፍጥረት ራሱ ደግሞ ከጥፋት ባርነት ነፃነት እንዲደርስ ነው። ፍጥረት ሁሉ እስከ አሁን ድረስ አብሮ በመቃተት በምጥ መኖሩን እናውቃለንና።* **ሮሜ 8፡18–22**

[55] እግዚአብሔር "ለመስበር" ወይም "ለመሰባበር" ቃል ገብቷል ይህ ሁለቱም የዕብራይስጥ (MT) እና የግሪክ (LXX) ቀስት እና ሰይፍ አልፎም ተርፎም ጦርነትም የሚያመለክት ነው። "መስበር" ወይም "መሰባበር" የሚለው ቃል በESV ትርጉም ውስጥ ጥቅም ላይ የዋለው "መሰረዝ" ከሚለው በጣም ተንካራ ነው። የቀስት መሰበር ማለት ጦርነት ማድረግ አይቻልም ምክንያቱም የጦር መሣሪያዎቹ እራሳቸው በእግዚአብሔር ይወድማሉና። ጦርነት በእግዚአብሔር በራሱ ይወገዳል። ከዚህ በተጨማሪ እዚህ ላይ "ሰበረ" የሚለው ቃል መጠቀም በዚህ ቁጥር እና ሆሴዕ 1፡5 መካከል ያለውን ግንኙነት ያሳያል። በሁለቱም ክፍሎች ወስጥ ተመሳሳይ ቃላት ጥቅም ላይ ይውላሉ። ሆሴዕ ብቻውን አይደለም ይህንን ቋንቋ የእግዚአብሔር ድል ለመግለጽ የተጠቀመበት (ለምሳሌ መዝሙረ 46፡9 ይመልከቱ)። ስለዚህ ሆሴዕ እነዚህን ቃላት ሲጽፍ ቢያስን አንዳንድ ከሱ ቀደም ተብሎ የተጻፉትን "ቀስትን ስበሩ" የሚሉትን ምንባቦች እያሰበ ሊሆን ይችላል። ይህም እንደነዚህ ያሉትን **የስነጽሁፍ ትስስሮች** ለማጥናት ጠቃሚ ናቸው። ክርስቶስ በግልጽ ባይጠራም እንኳ የክርስቶስን ድል በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እንደተገለጸ ያሳያሉ። አንባቢውም ሌሎች ተጨማሪ ዝርዝሮችን በሚሰጡ አንቀጾች ላይ በመመስረት የተነገሩትን ነገሮች በተወሰነ መልኩ ከእሱ ጋር የተገናኙ መሆናቸውን ያውቃል።

ይህ ጥቅስ ከሆሴዕ 1፡5 ጋር አወዳድር። በዚያ ጥቅስ ውስጥ እግዚአብሔር የእሥራኤልን ቀስት ይሰበራል የሚለው አሉታዊ ነበር። የእሥራኤልን ኃይል በሙሉ ያስወግዳል ማለት ነውና። በዚህኛው ጥቅስ ደግሞ አዎንታዊ ነው። ለእግዚአብሔር ሕዝቦች ፍጹም ሰላም ያመጣል ማለት ነው። "በዚያም ቀን" በሠራው ሥራ ምክንያት ከአሁን በኋላ ቀስት አያስፈልጋቸውም ወይም ሰይፍ አይፈሩም ወይም እጅ ላይ ባለ ሰይፍ ወይም ቀስት አይወድቁም! አሁንም ያንኑ ቃል ሆሴዕ በተለያየ መንገድ ይጠቀመዋል። ሰባኪው ወይም መምህሩ የሆሴዕን ቃላት በመደጋገም ለእሱ ወይም ለእሷ አላማ ሊጠቀሙበት ይገባል! የሆሴዕ "ቀስትን ስበሩ" የሚለው በሆሴዕ 2፡18 ላይ ድግግሞሽ ሰባኪው ወይም አስተማሪው በሆሴዕ 1፡5 ላይ ያለውን ቃል ሕዝቡን በድጋሚ እዲያስታውሱና እነዚህንም ቃላት የግዚአብሔር ሕዝብ በሆሴዕ 2፡20 ካገኙት ለውጥ ጋር እንዲያወዳድሩ ጥሩ አጋጣሚ ይፈጥርላቸዋል። ይህም ለክርስቶስና ለሥራው ምስጋናን ያመጣልና።

"ተከልለውም እንዲኖሩ" የሚሉት ቃላት በተመለከተ መዝሙር 4፡8ን ይመልከቱ። ይህ በእግዚአብሔር ብቻ የሚሆን ነገር ነውና።

22 ለእኔም እንድትሆኚ በመታመን አጭሻልሁ፤ አንቺም እግዚአብሔርን ታውቂያለሽ።[56]

23

በዚያም ቀን እመልሳለሁ ይላል እግዚአብሔር፤

ለሰማይ እመልሳለሁ

ሰማይም ለምድር ይመልሳል፤

24 ምድርም ለእህልና ለውይን ጠጅ ለዘይትም ትመልሳለች፤ እነርሱም ለኢዝራኤል ይመልሳሉ።[57]

---

[56] ግን ወደ ኋላ መመለስን ለመከላከል ምን መሆን አለበት? ይህ በእርግጥ መመለስ ያለበት ጥያቄ ነው። አዲስ የቀረበችውን ሚስት እንደገና እንዳትስት መከልከል የሚቻለው እንዴት ነው? እግዚአብሔርስ ደግሞ ሚስቱን እንዳይፈታ የሚከለክለው ምንድር ነው? ለነገሩ እሥራኤል በጥንት ዘመን ለተሃድሶ ብዙ ሙከራዎችን አድርጋለች (ለምሳሌ መጽሐፈ መሳፍንት ይመልከቱ)። እንደ አለመታደል ሆኖ ግን እነዚህ ለውጦች መቼም ቢሆን አልዘለቁም። ታዲያ በዚህ ጊዜም ቢሆን ምን የተለየ ሊሆን ይችላል?

> *ለዘላለምም ለእኔ እንድትሆኚ አጭሻለሁ፤ በጽድቅና በፍርድ በምሕረትና በርኅራኄ አጭሻለሁ።*
> *ለእኔም እንድትሆኚ በመታመን አጭሻለሁ፤ አንቺም እግዚአብሔርን ታውቂአለሽ።* **ሆሴዕ 2፡21–22**

ዘላቂ ግንኙነት እንዲኖር ማድረግ የሚቻለው እንዴት ነው? ማወቅ ያለብን ነገር መልሱ እግዚአብሔር መሆኑን ነው። የእግዚአብሔር ድርጊት የዚህን ጋብቻ ስኬት ያረጋግጣል። እነዚህ ጥቅሶች ደግሞ የግንኙነቱን መጀመሪያ ያመለክታሉ። እግዚአብሔርም ራሱን ለሙሽሪት ሲሰጥ እናያለን። እንደዚሁም ደግሞ ይህ ግንኙነት እንዲለመልም ለሙሽሪት ስጦታ ሲሰጥ እናያለን። ጽድቅን፣ ፍትሕን፣ ጽኑ ፍቅርን፣ ምሕረትንም ይሰጣታል። ታማኝ ልብ ይሰጣታል። የእሱንም ድርጊቶች ሙሽራዋ እሱን እንድታውቀው ያደርጋታል።

እግዚአብሔር ለሙሽሪት መታጨቱም ረጅም እና አስደሳች ትዳር ዋስትና ይሰጣል። እሷም እንደምታውቀው ቃል ግብቷል። “ማወቅ” የሚለው ግስ ብዙ እንድምታዎች አሉት። ስለዚህ እግዚአብሔርን ትረዳለች ማለት ነው። ከእርሱም ጋር በቅርበት ትተዋወቃለች ማለት ነው። ይህም ብቻ አይደለም የሱንም ሀሳብና ሀልሙንም ታውቀዋለች። ይህ ቃል የጾታ ግንኙነት አይነት ነገር ያመለክታል። የእግዚአብሔር ሚስት እንደ ያዕቆብ ሚስት እንደ ሊያ ያልተወደደች አትሆንም። እግዚአብሔር ይህችን ሙሽራ ይፈልጋል! እና ይህች ሙሽራ የደስታዋ ፍላጎት የት እንደሚገኝ ግራ አይገባትም። ምኞትዋ ሁሉ በባልዋ ይሟላልና።

[57] በዚህ የቃል ንግግሮች ውስጥ ያሉት የመጨረሻ መስመሮች በእግዚአብሔርና በህዝቡ መካከል ስላለው የወደፊት ጋብቻ ክብር ይናገራሉ። ከእንግዲህ እግዚአብሔር እሩቅ አይሆንም። ከእንግዲህ ወዲህ የህዝቡን ጩኸት አልሰማም አይልም። ይህ ጋብቻ ሲፈጸም ምድሪቱ ትበለጽጋለች። ወይን፣ ዘይትንና እህልንም ይበዛሉ። ተመሳሳይ የብልጽግና ተስፋዎች በትናንሽ ነቢያትም ጽሑፍ ውስጥ ይገኛል (ለምሳሌ ኢዩኤል 2፡24፣ 3፡18 እና አሞጽ 9፡13 ይመልከቱ)።

እነዚህ የተትረፈረፈ ተስፋዎች (ተራሮች ወይን ያንጠበጥባሉ ከሚሉት የሚበልጥ የተትረፈረፈ ምሳሌ ምን ሊሆን ይችላል?) ነገር ግን ፍጻሜያቸው የሚሆነው በኢየሱስ መሆኑን ማወቅ ያስፈልጋል። የመጀመሪያ ተአምር – በቃና ዘገሊላ ሰርግ ላይ ውሃውን ወደ ወይን ጠጅ መቀየሩ – እነዚህን ትንቢቶች የሚፈጸሙበት እርሱ መሆኑን ያመለክታል (ዮሐንስ 2፡1–11 ይመልከቱ)። ለዚህም ነው ሐዋሪያው ዮሐንስ ኢየሱስ ይህን ተአምር በፈጸመ ጊዜ “ክብሩን ገለጠ” ያለው (ዮሐንስ 2፡11)። ኢየሱስ በዚህ ተአምር አማካኝነት ማንነቱን በትክክል አሳይቷል። እርሱ የእነዚህ ታላላቅ ተስፋዎች ፍጻሜ ነው። ለእሥራኤላውያን ቃል የተገባለትን ብልጽግናን እና ፍሬያማነትን ያመጣ እርሱ ነው። ያለእሱ ወይን የለም። ይህ የእሥራኤል

25
በምድርም ላይ ለእኔ እዘራታለሁ፤
ምሕርትም የሌላትን እምራለሁ
ሕዝቤም ያልሆነውን አንተ ሕዝቤ ነህ እለዋለሁ፤
እርሱም አንተ አምላኬ ነህ ይለኛል።[58]

---

ፍሬ አልባነት ምሳሌ ነበር። ከእሱ ጋር ግን ምርጡ ወይን በነፃነት ፈሰሰ። ይህ በክርስቶስ የመጣው ታላቅ ፍሬያመነት ምሳሌ ነው።

ሆሴዕ 2፡24 እንደገና ወደ ሆሴዕ 1 እንደሚመልሰን ያስተውሉ። "በእህሉ በወይኑ እና በዘይቱ" በተሰጠው "መልስ" ወደ ሆሴዕ 1 መልሶናል። እህል ወይንና ዘይት መናገር እንደማይችሉ ግልጽ ነው። ይሁን እንጂ ይህ ግጥም ነው። ግጥም ከትረካ የተለየ ህግጋት አለው። ይህ ሰዎች በጥልቀት እንዲያስቡ ለማድረግ ነው። እህሉ፣ ወይኑና ዘይቱ ለምን እንዲህ ይመልሳሉ? እግዚአብሔር ሕይወት ሰጪ ዘሮችን ስለዘራ ነው! ኢይዝራኤል ማለት አስቀድመን እንዳየነው "እግዚአብሔር ይዘራል" ማለት ነው። ኢይዝራኤል የሚለው ቃል በሆሴዕ 1፡4–5 ላይ አሉታዊ በሆነ መልኩ ጥቅም ላይ ውሏል። በሆሴዕ 1፡11 ላይ ደግሞ "ከምድሪቱ ይወጣሉ የኢይዝራኤል ቀን ታላቅ ይሆናልና" በማለት በአዎንታዊ መልኩ ጥቅም ላይ ውሏል። ታዲያ እዚህ ጋ ምን ማለት ነው? እህሉ ወይኑ እና ዘይቱ የድል እልልታ እያቀረቡ ያሉ ይመስላል። "እንዲህ እያሉ ነው እዚህ ነው! ታላቁ የኢይዝራኤል ቀን ደርሷል! እግዚአብሔር የገባውን ቃል እንደሚጠብቅ ማረጋገጥ እንችላለን! ከምድር ምን እንደሚበቅል ይመልከቱ!" እኛ የእግዚአብሔር ሰዎች በክርስቶስ የእግዚአብሔር ድል በማሰብ እንደ እህል ወይን እና ዘይት ደስተኞች እንሁን! መቼም ምድር ከእግዚአብሔር ሕዝብ ይልቅ እግዚአብሔርን በማመስገን የተሻለች ነበረች ማለት አይቻልም።

[58] ሆሴዕ 2፡25 ከሆሴዕ 1፡1–9 ጋር አወዳድር። በቀደሙት ጥቅሶች ላይ እሥራኤልን ከምድሪቱ ነቅሎ ለማስወጣት እግዚአብሔር ቃል ገብቶ ነበር። በእነዚህ ጥቅሶች ደግሞ በመድሪቱ ላይ እንደሚተክላት ቃል ገብቷል። እሥራኤልም የእርሱ ትሆናለች ምሕርትም ያደርግላታል እናም የእሱ ብቻ እንደሆነች በደስታ ያውጃል። እሷም በእሱ የተመረጠች ትሆናለች። የእግዚአብሔርም ሕዝብ ሌሎችን አማልክት ተከትሎ መሮጥ ያቆማል። ይልቁንም ለዓለሙ ሁሉ እንዲሰማ "አምላኬ ነህ" ብለው እየጮሁ በደስታ ከእግዚአብሔር ጋር ይስማማሉ።

ይህ አስደናቂ የወንጌል ክፍል ነው። ጴጥሮስ እነዚህን ጥቅሶች ለቤተ ክርስቲያን እንዴት እንደሚጠቀምባቸው ይመልከቱ።

> *እናንተ ቀድሞ ወገን አልነበራችሁም አሁን ግን የእግዚአብሔር ወገን ናችሁ፤ እናንተም ምሕረት ያገናችሁ አልነበራችሁም አሁን ግን ምሕረትን አግኝታችኋል።* **1 ጴጥሮስ 2፡ 10**

ጴጥሮስ እነዚህ ነገሮች ቀደም ሲል እነደተፈጸሙ አጥብቆ ይናገራል። ነገር ግን እነዚህ ነገሮች ተፈጽመዋል የሚለው በግልጽ ያልተፈጸመ ትልቅ ነገር ያለ በሚመስልበት ጊዜ እነዴት ሊናገር ቻለ? ደግሞስ የእግዚአብሔር ልጆች  በተሰጣቸው ምድር ላይ ገና አልተተከሉም አይደል? ይህ የአዲስ ኪዳን ትርጓሜ የምንመለከትበት ሌላ ምሳሌ ነው። የአዲስ ኪዳን ጸሐፊዎች እነዚህ ተስፋዎች እንደተፈጸሙ እና እየተፈጸሙም መሆናቸውን ያውጃሉ። የእብራውያን መልዕክት ለአማኞች  "ወደ ጽዮን ተራራና ወደ ሕያው እግዚአብሔር ከተማ ደርሳችኋል ወደ ሰማያዊ ኢየሩሳሌም በደስታም ወደ ተሰበሰቡት ወደ አእላፋት መላዕክት" (ዕብራውያን 12፡22) ማለቱን ልብ ማለት ያስፈልጋል። በሌላ አነገጋር የእግዚአብሔር ሕዝቦች የሆኑቱ በምድራቸው ማለትም በሰማያዊቷ ኢየሩሳሌም ተተክለዋል። እውነተኛውንም የዘላለም ቤታችን ወይም ሀገራችን በሥጋዊ ዓይኖቻችን ማየት አንችልምና ይሁን እንጂ በእምነት ዓይን ግን ማየት እንችላለን።

በእነዚህ ጥቅሶች ውስጥ ስላሉት ሌሎች ተስፋዎችም ተመሳሳይ ነው። ለአማኞች "ተራሮች" ቀድመውንም "ወይን" ያንጠባጥባሉ። ይህ የትልቅ ፍሬያማነትና ብልጽግና ምሳሌ ነው። ፍሬያማነትና ብልጽግና ኢየሱስ አሁን ያመጣልን ነገር ነው። በቃና ዘገሊላ እነዚህ ተስፋዎች የሚፈጸሙበት እሱ መሆኑን በሚያስገርም ሁኔታ አሳይቷል። በእሱ በኩል የእግዚአብሔር የተትረፈረፈ በረከት በነፃ ይፈሳልና። በክርስቶስ ውስጥ "የማይመረመር ሀብት" አለ (ኤፌሶን 3፡8)። በእሱ

## ሆሴዕ 3

ሆሴዕ 3 አንባቢን ወደ ሆሴዕ እና ስለ ጋብቻው ታሪክ የሚመልስ ክፍል ነው። በሆሴዕ ታሪክ ውስጥ አንድ አስፈሪ ነገር የተከሰተ ይመስላል። የሆሴዕ ሚስት ከእርሱ ጋር ለመኖር እንደማትችል ያሳያል። እንዳውም በዚህ ክፍል ውስጥ የሆሴዕ ሚስት ተብላ እንኳን አትጠራም። ይልቁንስ "በሌላ ሰው የተወደደች ሴት" ተብላ ትጠራለች። ስለዚህ ሆሴዕ ከጎሜር ጋር የነበራትን ግኑኝነት እግዚአብሔር ከእሥራኤል ጋር ያለውን ግኑኝነት ይመስላል። የሆሴዕ ጋብቻ በእግዚአብሔርና በእሥራኤል መካከል ስላለው ግኑኙት ትንሽ ስዕል ያስታውሰናል። በዚህ ክፍል ውስጥ ደግሞ እግዚአብሔር የቀድሞ ሚስቱን ወደ ራሱ እንዴት እንደሚመልስ ለሆሴዕ ነግሮታል። ይህ ያደረገው ሆሴዕ ጎሜርን መልሶ መውሰዱ እግዚአብሔር እሥራኤልን እንዴት ወደ ራሱ እንደሚመልስ የሚያሳይ ሥዕል ነው። ሆሴዕ ከጎሜር ጋር ባለው ግኑኙነት ላይ ሰባኪው ወይም መምህሩ በጣም ትኩረት እንዳይሰጥ መጠንቀቅ አስፈላጊ ነው። ምክንያቱም ጽሑፉ አንባቢው በዚህ ላይ በጣም እንዲያተኩር አይፈቅድለትም ምክንያቱም የተሰጡት በጣም ጥቂት ዝርዝሮች ብቻ ነውና። ሆሴዕ እና ትዳሩ የታሪኩ ዳራ አድርጎ መጠቀም የተሻለ ነው፤ ምክንያቱም በሆሴዕ እና በጎሜር መካከል ያለውን ግንኙነት የዚህ ክፍል ዋና ነጥብ አይደለምና። ነገር ግን የዚህ ክፍል ዋና ነጥብ እግዚአብሔር ከእሥራኤል ጋር ያለው ግኑኝነት የሚመለከት ነው። እግዚአብሔር ከእሥራኤል ጋር ያለውን ግኑኝነት በተመለከተ ዋና ነጥብ መሆኑን ከቁጥር 4–5 ተመልክቷል።

---

ውስጥ መከሩ በጣም ብዙ ከመሆኑ የተነሳ ዘሪውና አጫጁ እርስ በርሳቸው እየተጣደፉ ነው (አሞጽ 9፡13 እና ኢየሱስ ደግሞ ይህን እንዴት እንደ ተረጎመው በዮሐንስ 4፡34–38 ይመልከቱ)። እነዚህ ለቅዱሳን እጅግ የተትረፈረፉ ቀናት ናቸው። ለእነርሱ ምንም ነገር አልተከለከለም። እግዚአብሔር በሰማያዊ ሥፍራ በመንፈሳዊ በረከት ሁሉ በክርስቶስ ባርኮናልና (ኤፌሶን 1፡3)።

የወንጌል ክስተቶች እኛ ማወቅ ያለብን እዚህ የተነገሩትን ጨምሮ የእግዚአብሔርን ተስፋዎች ሁሉ ወደ ፍጻሜ አምጥቷል (የሐዋሪያት ሥራ 13፡32–33 እና 2 ቆሮንቶስ 1:20 ይመልከቱ)። በክርስቶስ ሁሉም ነገር ተፈጽሟል። ሆኖም በአሁኑ ጊዜ የእነዚህ ተስፋዎች ሁሉ ፍጻሜ የምናስተውለው በእምነት ነው። ነገር ግን አንድ ቀን በዓይናችን ደግሞ እናያለን። በሌላ አነጋገር የዳግም ምጽአቱ አማኝ በክርስቶስ ያላየውንና ያልቀመሰውን "አዲስ" ነገር አያመጣም። እነዚህ ነገሮች በእምነት ብቻ ከመሆን ወደ መታየት ያመጣቸዋልና።

አሁን የምንኖረው በክርስቶስና በቤተ ክርስቲያን በከበረ ጋብቻ ዘመን ላይ ነው። ቤተ ክርስቲያን የጋብቻ ቃሏን መፈጸም እንድትችል የጋብቻ ስጦታውን ሰጣት። ሌሎች ፍቅረኛሞችን አትከተልም፤ ደስታዋ ሁሉ በክርስቶስ ነውና።

## ሆሴዕ 3

1 እግዚአብሔርም የእሥራኤል ልጆች ወደ ሌሎች አማልክት ቢመለሱና የዘቢብ ጥፍጥፍን ቢወድዱ[59]
እንኳ እግዚአብሔር እንደሚወዳቸው አንተም ውሽማዋን የምትወድደውን አመንዝራይትን ሴት ውደድ
አለኝ።[60]2 እኔም በአሥራ አምስት ብርና በአንድ ቆሮስ መስፈሪያ ተኩል ገብስ ገዛኋት።[61]
3 ከእኔ ጋር ብዙ ወራት ተቀመጪ አታመንዝሪም ለሌላ ሰውም አትሁኚ እኔም እንዲሁ እሆንልሻለሁ
አልኋት።[62]

---

[59] እሥራኤል ስለ ጣዖት አምልኮ ማስጠንቀቂያ ቢሰጣትም ሌሎች አማልክቶችን ማምለክ አልተወችም። እሥራኤል ሌሎች አማልክትን ማምለክ መውደድዋ እና ሌሎች አማልክትን ማምልከ እና በሌሎች አማልክቶች በማምለክ ሂደት ውስጥ የተካተቱ ነገሮች (ምናልባትም እንደ የዘቢብ ጥፍጥፍ መውደዳቸውን አልተውም ነበር)። የዜቢብ ጥፍጥፍ እዚህ ጋ የተጠቀሰው ምናልባትም ሰዎች መንፈሳዊ ግልሙትና እንዲፈጽሙ ከሚያደርጉዋቸው ዋና ዋና ምክንያቶች መካከል አንዱን ከእግዚአብሔር ከራሱ ይልቅ የዓለምን ደስታ መውደዳቸውን ለማመልከት ይሆናል። ሰዎች ፍላጎቶቻቸውን እንዲያረኩ የሚፈቅዱ አማልክቶችን ያገኛሉ። ይህም በሆሴ ዘመን በእሥራኤል ውስጥ የተፈጸመ እውነት ብቻ አይደለም። ሔዋን የተከለከለውን ፍሬ “ለመብላት ያማረ እንደ ሆነ ለዓይንም እንደሚያስጎመጅ ለጥበብም መልካም እንደ ሆነ” ካየችበት ጊዜ አንስቶ (ዘፍጥረት 3፡6) ሰዎች ከእግዚአብሔር ደስታ በላይ በራሳቸው ተድላ ደስታ ሲደሰቱ ቆይተዋል። ከጳውሎስ የአገልግሎት ባልደረቦች አንዱ የሆነው ዴማስ የሚባል ሰው ጳውሎስንና የጌታን ሥራ ትቶአል ምክንያቱም “ይህንን ዓለም ወዶ ነበርና” (2 ጢሞቴዎስ 4፡10)። በሆሴዕ ዘመን የነበሩት የእሥራኤል ሕዝቦች እና በጳውሎስ ዘመን የነበሩት የዴማስ ምሳሌዎች እግዚአብሔርን ለምድራዊ ተድላ ሲሉ የሚተው እያንዳንዱ ሰው ምን እንደሚደርስበት ለማስታወስ ይጠቅማል።

[60] በዚህ ምዕራፍ ውስጥ “ጎሜር” የሚለው ስም ጥቅም ላይ አልዋለም። የጎሜር ስም ያልተጠቀሰበት ምክንያት ምናልባት ከሆሴዕ ጋር ያላትን ርቀት ለማጉላት ይሆናል። በቁጥር አንድ ላይ የሆሴዕ “ሚስት” ሳይሆን “ሴት” ተብላ የተጠራችው ለዚህም ሊሆን ይችላል። እሥራኤል ከጎሜር ጋር ትመሳሰላለች። ከእግዚአብሔር በጣም የራቀች ሆናለችና። እሥራኤል ባደረገችው ተደጋጋሚ ግልሙትና ምክንያት እግዚአብሔር እንደ ሚስቱ አድርጎ አይቆጥራትም። እስዋም እንደ ተራ “ሴት ተቆጥራለች”። እግዚአብሔር ግን እንደ ሆሴዕ መልሶ ይገዛታል ስምም ያወጣላታል።

[61] ሆሴዕ ጎሜርን እንደገና “እንዲወድ” ታዝዟል። ይህንንም ለማደርግ “በአሥራ አምስት ብርና በአንድ ቆሮስ መስፈሪያ ተኩል ገብስ” እንዲገዛት ተገድዷል (ሆሴዕ 3፡2)። ሆሴዕ ጎሜርን መግዛት ለምን እንዳስፈለገው ለአንባቢው ሊነገረው ይገባል። ምናልባትም ሆሴዕን ትታ ስለነበር አሁን ባሪያ ሆና ነበር ይሆናል፤ ስለዚህም ሆሴዕ ከአሳዳሪዋ ሊገዛት ተገዶ ይሆናል። ሆሴዕ ሊከፍል ከሚያስፈልገው ዋጋ በመነሳት ስንገምት ጎሜር ብዙም ዋጋ እንደ ማታወጣ ግልጽ ነው። በእርግጥ ማንም አይፈልጋትም ነበር። ሆሴዕም ቢሆን አይፈልጋትም። ነገር ግን ጎሜርን “እንዲወዳት” ታዝዟል ምክንያቱም ሆሴዕ ከጎሜር ጋር ያለውን ግንኙነት እግዚአብሔር ከእሥራኤል ጋር ስላለው ግንኙነት ብዙ እውነቶችን ለማሳየት እየተጠቀመበት ስለበረ ነው።

[62] ሆሴዕ ጎሜርን መልሶ ሲገዛት እንደገና “ግልሙትና እንዳትፈጽም” ነገራት። ቢያንስ ለተወሰነ ጊዜ ከእርሱ ጋር ትኖራችለች ግን እሱ ከእሷ ጋር ምንም ዓይነት የግብረ ሥጋ ግኑኝነት አይፈጽምም (ይህም የሚያመለክተን “ እኔም እንዲሁ እሆንልሻለሁ” የሚለው ሐረግ ነው። ከዚህ በፊት እርካታን ያመጡላት የነበሩት ነገሮች አሁን ማግኘት አትችልም።

4 የእሥራኤል ልጆች ያለ ንጉሥና ያለ አለቃ ያለ መሥዋዕትና ያለ ዓምድ ያለ ኤፉድና ያለ ተራፊም ብዙ ወራት ይቀመጣሉና፤[63]

5 ከዚያም በኋላ የእሥራኤል ልጆች ተመልሰው አምላካቸውን እግዚአብሔርንና ንጉሣቸውን ዳዊትን ይፈልጋሉ፤[64] በኋለኛውም ዘመን ፈርተው ወደ እግዚአብሔርና ወደ በረከቱ ይመጣሉ።[65]

---

[63] የጎሜር በግዳጅ የተመለሰችበት ጊዜ ከሆሴዕ ጋር ግኑኝነት አልነበረውም ይህም በእሥራኤልና በእግዚአብሔር መካከል ካለው ግኑኝነት ጋር ተመሳሳይ ነው። ሆሴዕም ጎሜርን መልሶ እንዳመጣት፤ እግዚአብሔርም እሥራኤልን ወደራሱ ይመልሳል። ሆሴዕ ለጥቂት ጊዜ ከጎሜር ጋር ግኑኝነት እንዳልነበረው ሁሉ እግዚአብሔርም ከእስራኤል ጋር ለተወሰነ ጊዜ ግኑኝነት አልነበረውም። ስለዚህ በዚህ ጊዜ ውስጥ ከዚህ በፊት እርካታን ያመጡላት የነበሩት ነገሮች አሁን ግን ሳታገኝ ትቀራለች ማለት ነው። ሁሉም ነገር ማለትም–ነገሥታት፣ መስዋዕቶች፣ የቤተሰብ አማልክቶች (እናም ምንም ጥርጥ በሌለው ሁናቴ የዘቢብ ጥፍጥፍ) የመሳሰሉትን ሁሉ–ከእርስዋ ተከልክሎ ነበር። እሥራኤል ከሚያጽናኑዋት ነገሮች ሁሉ በግዳጅ በተለያየችበት ወቅት ያለፈውን በመመኘት የተገባላትን የእግዚአብሔርን የተስፋ ቃል እስኪፈጸም ድረስ እየጠበቀች ነበር። በአዲስ ኪዳን ውስጥ ያሉ አንዳድ ሰዎች (እንደ ስምዖን ያሉትን ማለት ነው) "የእሥራኤልን መጽናናት እየጠበቀ" እነደነበር ተጽፏል (ሉቃስ 2፡25)። እነዚህ ሰዎች እሥራኤል ከእግዚአብሔር ጋር የተራራቀችበት ጊዜ እስኪያበቃ ድረስ እየጠበቁ ነበር። እንደ ሆሴዕ 3፡5 ባሉ ቁጥሮች ላይ ደግሞ ቃል የተገባውን ከእግዚአብሔር ጋር የሚኖራቸውን ቅርርብ እየናፈቁ ነበር።

[64] ወደ እግዚአብሔር መመለስ ከ "ንጉሣቸው ከዳዊት" አመራር ጋር እንዴት እንደሚገናኝ ያስተውሉ። ይህ ማለት እግዚአብሔር እሥራኤልን ወደ ራሱ ለመመለስ የገባውን ቃል ከዳዊት ጋር ግኙኝነት ያለው አንድ የተለየ ንጉሥ ያመለክታል ማለት ነው። ይህ ማለት ጎልያድን የገደለው ዳዊት እንደገና እሥራኤልን ለመግዛት ይነሳል ማለት አይደለም። ይልቁንም ይህ በመጀመሪያ በ2 ሳሙኤል 7፡1–17 የተገለጸውን "የዳዊት ልጅ" በመጨረሻ ወደ ስልጣን መምጣቱ የሚያመለክት ነው እንጂ። የዚህ ጥቅስ አንዱ እንድምታ እግዚአብሔርን መከተል የዳዊትን እውነተኛ ልጅ የሆነውን ኢየሱስን የተቀበውን ንጉሥ መከተልን ይጠይቃል ማለት ነው። ሰዎች እግዚአብሔርን መከተል ካልቻሉ በተመሳሳይ መንገድም ኢየሱስ ክርስቶስንም ይክዳሉ ማለት ነው። ኢየሱስ የዳዊት ዙፋን ወራሽ ነው (ማቴዎስ 1፡1 እና ሉቃስ 1፡26–33 ይመልከቱ)። ሆሴዕ ስለ ወደፊቱ የእግዚአብሔር ሕዝቦች ንጉሥ ሲናገር ይህ ለሁለተኛ ጊዜ ነው። በሆሴዕ 2፡2 ላይ "ለእነርሱም አንድ አለቃ ይሾማሉ"ይላል። ይህ ጥቅስ "አንድ አለቃ" በሆሴዕ 3፡5 ላይ ደግሞ "ንጉሳቸው ዳዊት" ተብሎ ከተገለጸው ጋር ተመሳሳይ ሰው መሆኑን ማረጋገጫ ነው።

[65] ይህ የተስፋ ቃል በኋለኛው ዘመን ይፈጸም ነበር። ከትንቢተ ሆሴዕ አንጻር የኋለኛው ቀን ተብሎ የተገለጸው ዘመን ዛሬ ይህን መልዕክት የሚያነቡ ሰዎች ይህ ጊዜ ወደፊት ነው ማለት እንዳልሆነ መረዳት አስፈላጊ ነው። ምንም እንኳን እነዚህ "የኋለኛው ዘመን" ለሆሴዕ ወደፊት የሚፈጸም ቢሆንም ነገር ግን የወደፊት ነገር አይደሉም። "የኋለኛው ቀን" እና በኋለኛው ቀናት ውስጥ የሚፈጸሙት ክስተቶች ቀድሞውኑ መጥተዋልና!

ሌሎች ምንባቦች እሥራኤላውያን ከኃጢአት ነጻ የሚወጡበትን እና ለእግዚአብሔር የመታዘዝ የሚጀመርበት አዲስ ጊዜ ለመግለጽ እነዚህን ተመሳሳይ ቃላት ይጠቀማሉ (ለምሳሌ ዘዳግም 4፡30፣ ኢሳይያስ 2፡2 እና ሚክያስ 4፡1 ይመልከቱ)። በሆሴዕ 3፡5 ላይ የሚገኙት "በኋለኛውም ዘመን" ስለሚፈጸሙት አስደናቂ ክንውኖች የሚነገሩት ቃላት በመጨዎቹ ቀናት በእውነተኛው እሥራኤላውያን ዘንድ ታላቅ ጉጉት ፈጥሮላቸው ነበር። ለዚህ ሳይሆን አይቀርም፤ በአዲስ ኪዳን ውስጥ ታማኝ ሰዎች አንዳንድ ጊዜ የእግዚአብሔር ተስፋዎች የሚፈጸሙበትን ቀን "በመጠባበቅ" ላይ እነደነበሩ የተገለጸው። ለምሳሌ ያህል ኢየሱስ ከተወለደ ብዙም ሳይርቅ በቤተ መቅደሱ ውስጥ ስላዩት ሁለቱ ሽማግሌዎች ሉቃስ የገለጸበትን መንገድ ይመልከቱ። ሉቃስ ስማዖንን "የእሥራኤልን መጽናናት እየጠበቀ" እንደ ነበረ ሰው አድርጎ ግልጾታል (ሉቃስ 2፡25 ይመልከቱ)። እንደዚሁም ሉቃስ ሐና ስለ ኢየሱስ ስንታናገር "የኢየሩሳሌምን ቤዛ ለሚጠባበቁ ሁሉ" በማለት እንደተናገረች ጠቅሷል (ሉቃስ 2፡38 ይመልከቱ)። ስለዚህ ስማዖንና ሐና እግዚአብሔር የገባውን የተስፋ ቃል የሚፈጸምበትን ጊዜ እየጠበቁ ከነበሩት ታማኝ ሰዎች መካከል ጠቂቶቹ ቅሬታዎች ተብለው ሊገለጹ ከሚችሉት መካከል ሁለቱ ነበሩ ማለት ነው። እንደዚሁም የአርማትያሱ ዮሴፍም የእግዚአብሔር የተሰፋ ቃል እንዲፈጸም ከሚጠባበቁት ከነዚህ ቅሬታዎች መካከል አንዱ እንደ ነበር ቃሉ ያስረዳል (ማርቆስ 15፡43 ይመልከቱ)። የሚገርመው ነገር ደግሞ እነዚህ ሰዎች ኢየሱስን ሲያገኙት

## ሆሴዕ 4–5

ሆሴዕ 4 እንደ ፍርድ ቤት ዓይነት ትይንት ነው። እግዚአብሔር በእሥራኤል ሕዝብ ላይ ክስ ሲያቀርብ እንመለከታለንና። እሱ ከተጠቂው በላይ ነው። አቃቤ ሕጉም እሱ ነው። ዳኛውም እሱ ነው። ምንም እንኳን ይህ በሆሴዕ ዘመን በእሥራኤል ሕዝብ ላይ እግዚአብሔር ያቀረበው ክስ ቢሆንም እግዚአብሔር አይለወጥምና ሁሉም ሰዎች በዚህ ዘመንም ያሉት ማለት ነው የእግዚአብሔርን ቃል በትኩረት ሊከታተሉ ይገባል። በዚያ ዘመን እሥራኤል “ታማኝ ወይም የቀደመውን ፍቅሯን የጣለች በመሆንዋና እግዚአብሔርንም ማወቅ በምድሪቱ ስላልነበረ” ከተቀጣች ዛሬም በሰዎች ላይ ተመሳሳይ ነገር ሊሆን ይችላል። እኛ ግን በሆሴዕ ዘመን እንደነበሩት እሥራኤላውያን “የእግዚአብሔርን ቃል መስማት” ያስፈልገናል። ጠንቃቃ ሰባኪ ወይም አስተማሪ ሰዎች በሆሴዕ ዘመን የሆነውን ነገር እንዲረዱ እና ዛሬ ሰዎች ከእግዚአብሔር ጋር ምን ግኑኝነት ሊኖራቸው እንደሚገባ እንዲገነዘቡ ያደርጋል።

እንደዚሁም በሆሴዕ 5 ላይም እግዚአብሔር በእሥራኤል ላይ ክሱን ማቅረቡን ቀጥሏል። እሥራኤልና ይሁዳ ይቀጣሉ። ከዚህም ባሻገር እግዚአብሔር “እኔ ነጥቄ እሄዳለሁ እወስድማለሁ የሚያድንም

---

ለእነዚህ ተስፋዎች ፍጻሜ ቁልፍ እሱ እንደሆነ ተገንዝበዋል! በሌላ አነጋገር **የመጨረሻው ዘመን የጀመረው** ኢየሱስ በተወለደበት ጊዜ ነው። ይህም ማለት **የመጨረሻዎቹ ቀናት** ወደፊት አይደሉም ማለት ነው። እነዚህ ተስፋዎች ዛሬ እየተፈጸሙ ናቸውና! አማኞች አሁን በኋለኛው ዘመን ይኖራሉ ማለት ነው (ለምሳሌ የሐዋሪያት ሥራ 2፡17 እና ዕብራውያን 1፡2 ይመልከቱ)።

ይህ **የእሥራኤል ልጆች** ወደ **ንጉሣቸው ወደ ዳዊት** መምጣት እና የእግዚአብሔር ቸርነት የተገባላቸው የተስፋ ቃል የመጀመሪያው መፈጸም የጀመረው ኢየሱስ በተጠመቀ ጊዜ ነው። ሰዎች አንድ አንድ እያሉ ወደ አዲሱ “የዳዊት ልጅ” ወደ ሆነው መምጣት ጀመሩ (ማቴዎስ 1፡1፣ 9፡27፣ እና 20፡30 ይመልከቱ)። ከኢየሱስ ትንሣኤ በኋላ ቁጥሩ ጨምሯል። ለምሳሌ ያህል 3,000 ሰዎች በጰንጠቆስጤ ዕለት ወደ “ንጉሣቸው ዳዊት” መጡ። ምንም እንኳን ኢየሱስ ወደ ሰማይ ቢያረግም ሕዝቡ ግን እርሱን በስልጣን የሚገዛ እንደ ንጉሣቸው ቆጠሩት (ሮሜ 1፡4 ይመልከቱ)። ስለዚህ ይህ በሆሴዕ የተነገረው ትንቢት መቼ እንደሚፈጸም እና ሰዎችም ወደ ንጉሣቸው ወደ እግዚአብሔር ቸርነት የሚመለሱበት ጊዜ በተመልከተ የአንደኛውን መቶ ክፍለ ዘመን ክርስቲያን ቢጠየቅ ኖሮ ምናልባት ይህ ሰው “ወደ ዳዊት መንግሥት እኮ መጥተናል” በማለት ይመልስ ነበር ይሆናል! አሁን እየገዛ ነው፣ አሁን እሱን እየተከተልን ነው፣ ቸርነቱንም እየቀመስን ነው ይሉ ነበር። ለምሳሌ ጳውሎስ እግዚአብሔር በሰማያዊ ስፍራ በመንፈሳዊ በረከት ሁሉ በክርስቶስ ባርኮናል በማለት ጽፏል (ኤፌሶን 1፡3)። ጳውሎስ ገና ወደ ፊት ወደ እግዚአብሔር ቸርነት ለመምጣት እየጠበቀ አልነበረም። ነገር ግን ቀድሞውንም እንደተባረከ ነው የተናገረው።

በሆሴዕ የተነገረው ትንቢት መጀምሪያ ላይ አይሁድን ብቻ የሚያመለክት ቢመስልም አዲስ ኪዳን ግን ይህን ክፍል በዚህ መንገድ እንድንተረጉመው አይፈቅድልንም። አይሁድም ይሁኑ አሕዛብ በንጉሣቸው በዳዊት ሥር የሚኖሩ የእግዚአብሔር ሕዝብ አካል ናቸው። በአዲስ ኪዳን ውስጥ እንደ ተገለጸው አሕዛብ በእምነት እንደ እሥራኤል ልጆች ተደርገው ተቆጠሩ። ይሁን እንጂ አሕዛብ በምንም መልኩ እሥራኤልን አይተካም። ነገር ግን በእግዚአብሔር ቸርነት ለእሥራኤል የተገባውን የጽሑፋ ቃል ተቀባይ ለመሆን በቅተዋል። እንግዲህ ከዚህ በፊት ብዙ ጊዜ እንደገለጽነው እነዚህ ተስፋዎች በኢየሱስ ተፈጽመዋል (የሐዋሪያት ሥራ 13፡32–33, እና ገላትያ 3፡7–9፣ 26–29 ይመልከቱ)።

አይኖርም” ብሏል። እነዚህ ቀደመ ሲል በሆሴዕ ክፍል እንዳየነው ሁሉ አስፈሪ ቃላት ናቸው። ይሁን እንጂ ምዕራፍ አምስት የሚያበቃው ተስፋ በመናገር ነው። እግዚአብሔር እንዲህ ይላል “በደላቸውንም እስኪያውቁ ድረስ ፊቴንም እስኪሹ ድረስ ሄጄ ወደ ስፍራዬ እመለሳለሁ፤በመከራቸውም ጊዜ እጅግ አድርገው ፊቴን ይፈልጋሉ።” የሚለው ቃል ሁሉም ለዘላለም እንደማይጠፉ ያመለክታል። እግዚአብሔርም ሕዝቡ ንስሐ እኪገቡ ይጠብቃል ማለት ነው። በሆሴዕ 5 መጨረሻ ላይ ያሉትን ተስፋ ሰጪ ቃላት አንባቢን በሆሴ 6 መጀመሪያ ላይ ለተጻፍት የከበረ ቃላት ያዘጋጃሉ።

እንደ ሌሎች የሆሴዕ ምዕራፎች ሁሉ ሰባኪ ወይም አስተማሪ ለሆሴዕና ለትውልዱ ስለ ወደፊት ጊዜ የተነገረው ትንቢት ዛሬ ለአንባቢያን የወደፊትን ጊዜ የሚያመለክት ትንቢት እንዳልሆነ ለሕዝቡ ማሳሰብ ይኖርበታል። ሰባኪ ወይም አስተማሪ ሁል ጊዜ የተስፋው ቃል ተፈጽሞ ከሆነ ወይም ገና ያልተፈጸመ ከሆነ በሂደት ላይ መሆኑን ማጤን ይኖርበታል። ስለዚህ ይህንን ለመወሰን የሚበጀው መንገድ ሐዋሪያት እነዚህን የመሰሉ ክፍሎችን በአዲስ ኪዳን እንዴት እንደተረጎሙ ማጥናት ጠቃሚ ነው።

# ሆሴዕ 4–5[66]

**4፡ 1**

እናንተ የእስራኤል ልጆች ሆይ፤ እውነትና ምሕረት

እግዚአብሔርንም ማወቅ በምድር ስለሌለ[67]

እግዚአብሔር በምድሩ ላይ ከሚኖሩ[68] ጋር ክርክር አለውና[69] የእግዚአብሔርን ቃል ስሙ።

---

[66] ሆሴዕ 3 ወደፊት የእግዚአብሔር ሕዝቦች የሚታደሱበት ግሩም ተስፋ ያካተተ ነው። (በሆሴዕ 3 ላይ የተካተተው ተስፋ በሆሴዕ ዘመን ለነበሩት ሰዎች ወደፊት እንደነበረ ልብ ማለት ያስፈልጋል። ይህ ማለት ደግሞ ዛሬ ለሚኖሩ ሰዎች የወደፊት እጣ ፈንታ ነው ማለት አይደለም። በሆሴዕ 3 ላይ የተነገሩት ተስፋዎች ተፈጽመዋል እናም በአሁኑ ጊዜ ደግሞ በክርስቶስ እየተፈጸሙ ናቸው።) ይሁን እንጂ ሆሴዕ 4 ደግሞ በምዕራፍ 3 ላይ የሚገኘውን ውብ ትንቢት አልቀጠለም። ይልቅስ ሆሴዕ 4 አስፈሪ የሆነ ስለጥፋት ተስፋ ነው። ያስታውሱ፣ እንዲህ ዓይነቱ በአዎንታዊና በአሉታዊ ትንቢቶች መካከል መቀያየር በትንቢታዊ ጽሑፎች ውስጥ የተለመደ ነገር ነው። ትንቢት ጸሐፊዎቹ በአዎንታዊና አሉታዊ ትንቢቶች መካከል ሲቀያይሩ ለአንባቢ አይነግሩም። ሆኖም አንባቢው በተጠቀሱት ቃላቶች ላይ በመመስረት ይህንን መወሰን አለበት።

[67] የእግዚአብሔር "ክስ" ***ታማኝነት*** ያለው **የተሰጠ ፍቅር** ወይም **እግዚአብሔርን ማወቅ** በመድሪቱ ሁሉ ላይ የለም የሚል ነው። ይህ ማለት ግን በምድሪቱ ላይ ጥቂት ታማኝ ሰዎች አልነበሩም እንደማለት አይደለም (ከሁሉም በኋላ ሆሴዕ በምድሪቱ ይኖር ነበርና!)። ሁል ጊዜም ታማኝ የሆኑ ***ቅሬታ*** ሰዎች ነበሩ። ለምሳሌ ያህል በኤልያስ ዘመን ኤልያስ ብቸኝነት ተሰምቶት ነበር። እግዚአብሔርን የሚከተል ሰው እንደሌለ አድርጎ ተናግሮ ነበር። እግዚአብሔር ግን በእሥራኤል ውስጥ ጉልበታቸውን ለባኣል ያላንበረከኩትን ሁሉ በአፋቸውም ያልሳሙትን ሁሉ ሰባት ሺህ ሰዎች ለእኔ አስቀራለሁ።" በማለት በተግሳጽ መለሰለት (1 ነገሥት 19፡18 ይመልከቱ።) ይሁን እንጂ በዛ ያለ ቁጥር የነበራቸው ሰዎች እግዚአብሔርን አያመልኩም ነበር። ስለዚህ ከዚህ አንጻረ ስንመለከት በየትኛውም ቦታ ለእግዚአብሔር አምልኮ "ታማኝነት" አልነበረም ማለት ይቻላል። የእሥራኤል ሕዝብ በትዕዛዛቱ ድስ ብሎት ከእግዚአብሔር ጋር መኳዝ ነበረባቸው። የእግዚአብሔርን መልክና አምሳል ማንጽባረቅ ነበረባቸው (ዘፍጥረት 1፡26–28 ይመልከቱ)። ይልቁንም በቁጥር 2 ላይ ተመስርተው የሚያመልኩትን የአማልክትን ምስል ያንጸባርቁ ነበር። ስለ እግዚአብሔር ምንም እውቀት የለም ስንል በእስራኤል የሚኖሩ ሰዎች ስለ እግዚአብሔር የሚያውቁት ነገር አልነበረም ማለት አይደለም። በእርግጥ ስለእርሱ የሚያውቁት ነገር ነበር። ነገር ግን እርሱን በትክክል አያውቁትም ነበር። ሐዋሪያው ዮሐንስ "ከእርሱ ጋር ሕብረት አለን ብንል በጨለማም ብንመላለስ እንዋሻለን እውነትንም አናደርግም" (1 ዮሐንስ 1፡6 ይመልከቱ)።ይህ ዛሬም ቢሆን ለሰዎች አደገኛ ነው። ሰዎች እግዚአብሔርን እናውቃለን ይላሉ ነገር ግን በስራቸው እርሱን ይክዱታል (ቲቶ 1፡16 ይመልከቱ)።

[68] እዚህ ጋ እግዚአብሔር ሕዝቡን "ልጆቼ" ወይም ሕዝቤ ብሎ እንደማይገልጽ ልብ ይበሉ። "በምድሩ ላይ የሚኖሩ" ሲል ነው የጠራቸው። እግዚአብሔር ሕዝቡን የሚያመለክትበት ራቅ ያለ አገላለጽ በእግዚአብሔርና በሰዎች መካከል ያለውን ግኑኝነት የተበላሸበትን ሁኔታ ያሳያል። ይህ ሕዝቡን የሚያመለክተው ራቅ ያለ አጠራር የእስራኤል ሕዝብ በሆሴዕ 2፡4 ላይ "እናታችሁ" ተብሎ መጠራትዋንን እና ጎሜርን በሆሴዕ 3፡1 ላይ እንደ ሌላ "ሴት" ተደርጋ ከተጠራችበት ጋር ተመሳሳይ ነው።

[69] በቁጥር አንድ ላይ "ክርክር" የሚለው ቃል አንድንድ ጊዜ እርስ በርስ ለሚጣሉ ሰዎች ያገለግላል። እደዚሁም ደግሞ የሕግ ጉዳይን ( እንደ ክስ) ያሉትን ነገሮች ለመግለፅ ሊያገለግል ይችላል። እዚህ ላይ ደግሞ እግዚአብሔር በእሥራኤል ላይ የሚያመጣውን  የሕግ ጉዳይ ለመግለጽ ጥቅም ላይ ውሏል። ቃሉ በቁጠር 4 ላይም (በተለየ መልኩ) ጥቅም ላይ ውሏል። እግዚአብሔር "የእሥራኤልን ልጆች" በብዙ የወንጀሎች ክሶች እየከሰሳቸው ነው። ወንጀሎቹም ከቁተር 1–2 ተዘርዝረዋል።

2

እርግማንና ሐሰት ግዳይና ስርቆት ምንዝርናም ወጥተዋል፤[70]

ደምም ወደ ደም ደርሶአል።

3

ስለዚህ ምድሬቱ ታለቅሳለች

በእርስዋም የሚቀመጡ ሁሉ

ከምድር አራዊትና

ከሰማይ ወፎች ጋር ይደክማሉ፤

የባሕሩም አሦች ያልቃሉ።[71]

4

ነገር ግን ሕዝብህ ከካህን ጋር

እንደሚከራከሩ ናቸውና

---

ሁሉም ሰዎች የእግዚአብሔርን የክስ ዝርዝር በጥንቃቄ ማጤን አለባቸው፤ ምክንያቱም ሁሉም ሰዎች እነዚህን ተመሳሳይ ወንጀሎች ፈጽመዋልና (ሮሜ 3፡9–18፣ 23 ይመልከቱ)።

[70] እነዚህ ሁሉ “ወንጀሎች” በአሥርቱ ትዕዛዛት ውስጥ ተጠቅሰዋል (ዘጸአት 20፡1–17 ይመልከቱ)። ሆሴዕ የሙሴን ጽሑፎች በተደጋጋሚ ይጣቅሳል ምክንያቱም ሙሴ እሥራኤላውያን ሊኖሩባቸው የሚገቡባቸውን ሕጎች መዝግቦ ነበር።

[71] ይህንን በዘፍጥረት 1 ላይ ካለው የፍጥረት ዘገባ ጋር ያወዳድሩ። ፍጥረት በተገላቢጦሹ እየተገለጸ ያለ ይመስላል። ሁሉም ነገር ከመበልጸግ ይልቅ ሁሉም ነገር “እየደከመ” ሲሄድ ይታያል። እስሳቶች እንኳን ልክ እንደ ሰዎችም “ይወሰዳሉ” ይላል። ፍጥረት እግዚአብሔር የሚመለከበት ቦታ እንዲሆን የተዘጋጀ ከሆነ እዚህ ጋ ደግሞ በተቃራኒው ፍጥረት እንዳይኖር ሲደረግ ነው የምንመለከተው። ሁሉም ነገር እየተወገደ ነው! በዘዳግም ውስጥ ሙሴ የእሥራኤል ሕዝብ እግዚአብሔርን ካልታዘዙና ሌሎችን አማልክቶች ደግሞ ካመለኩ ሊድረስባቸው የሚቻለውን እርግማን ገልጿል (ዘዳ 32፡15–33 ይመልከቱ)። በዘዳግም ውስጥ የተገለጹት ነገሮች ሁሉ አሁን እየተፈጸሙ ነው። የሚገርም ቢመስልም የእሥራኤል ምድር እየደከመች መሆኗ ደግሞ የእግዚአብሔር ጸጋ እንድሚያስፈልጋት የሚያስረዳ ነበር። ማለትም ሕዝቡ ንስሐ እንዲገባ የሚያስጠነቅቅ ነበር። ይሁን እንጂ እንደ አለመታደል ሆኖ ይህን የእግዚአብሔርን ቸር ማስተንቀቂያ አልሰሙም።

በሥነ-መለኮት ደረጃ የሰዎች መንፈሳዊ ሁኔታ እና የተቀረው ፍጥረት አካላዊ ሁኔታ የተገናኙ መሆናቸውን ማወቅ አስፈላጊ ነው። በሰዎች ምክንያት በመረገሙ ፍጥረት እየተዳከመ ነው። የመጀመሪያው አዳም በፈጸመው ድርጊት ምክንያት መበስበስና ጥፋት በፍጥረት ሁሉ ላይ እንዲመጣ አድርጓል። የኋለኛው አዳም (ኢየሱስ) ግን ሁሉን እያስተካከለ ነው ማለትም ፍጥረታት ጨምሮ ሁሉንም ነገር ትክክል በማድረግ ያስተካክላል። ይህን የሆሴዕ ጥቅስ ከመዝሙር 8፡6–8 ጋር ያወዳድሩ። በዚህ በሆሴዕ ቁጠር ፍጥረት ሁሉ የተዘበራረቀ ነው። በመዝሙር 8 ግን ሁሉም ነገር ሥራዓት ያለው ነው። መዝሙሩ ስለ ክርስቶስ ትንቢት ስለሆነ እና በእርሱም በኩል የሚመጣ ሙሉነት ስለሆነ በሥርዓት የተሞላ ነው። የእግዚአብሔርን መልክ በትክክል የሚያንጸባርቀው “የኋለኛው አዳም” ነው። ስለዚህ በክርስቶስ በኩል ( እና “በእርሱ ያሉትን”) ፍጥረት ሁሉ ከመበስበስ ባርነት ይላቀቃሉ (ሐዋሪያው ጳውሎስ ይህን በሮሜ 8 ላይ በጥንቃቄ ሲመረምር ይመልከቱ)። ከዚህ በሆሴዕ ክፍል ባሻገር ያሉ ሌሎች ክፍሎች በሰዎች ክፋት እና በተቀረው የፍጥረት መዳከም መካከል ያለውን ትስስር ያሳያሉ። ለምሳሌ ዘፍጥረት 6፡11–17፤ ዘዳግም 28–32፤ ኢሳይያስ 24: 4–6 እና ኤርሚያስ 14 ን ይመልከቱ።

ማንም አይከራከር ማንም አይዝለፍ።[72]

5

በቀንም ትሰናከላለህ

ነቢዩም[73] ከአንተ ጋር በሌሊት ይሰናከላል፤

እናትህንም አጠፋታለሁ።[74]

6

ሕዝቤ እውቀት ከማጣቱ የተነሳ ጠፍቶአል፤[75]

አንተም እውቀትን ጠልተሃልና

እኔ ካህን እንዳትሆነኝ እጠላሃለሁ፤

የአምላክህንም ሕግ ረስተሃልና

እኔ ደግሞ ልጆችህን እረሳለሁ።

7

እንደ ብዛታቸው መጠን[76]

ኃጢአት ሠሩብኝ፤

እኔም ክብራቸውን ወደ ነውር እለውጣለሁ።

8

የሕዝቤም ኃጢአት መብል ሆኖላቸዋል

---

72 በዚህ ቁጥር ወስጥ በእግዚአብሔርና በሕዝቡ መካከል ሊሄድ የነበረው ካህኑ መከላከያ ሊሰጥ ያለ ይመስላል። እግዚአብሔር ለካህናቱ የመናገር መብት እንደሌላቸው ነገራቸው ምክንያቱም እግዚአብሔር በእነርሱ ላይ የሆነ ነገር ተቃርኖ ስላገኘባቸው ነው።

73 ይህ በእሥራኤላውያን የሚወደዱትን ሐሰተኛ ነቢያትን የሚያመለክት ነው። ስለዚህ በእስራኤል ያሉት ሁለቱ “ቅዱስ” ተብለው የሚታወቁት ቡድኖች (ካህናትና ነቢያት) በአንድነት ተወግዘዋል። ምክንያቱም ከእነዚህ “ቅዱስ” ከተባሉት ቡድኖች አንዳቸውም ለእግዚአብሔር ታማኝ አልነበሩምና። ሁለቱም የማይታዘዙ በመሆናቸው ምክንያት እንደ ሌሎችም ሰዎች ለፍርድ ቀርበዋል።

74 “እናትህንም” የሚለው አጠቃላይ ሐገሩን የሚወክል ነው (በተጨማሪም ሆሴዕ 2፡2 ይመልከቱ)።

75 ይህ በአጠቃላይ ተራ እውቀት (ማለትም የሳይንስ እውቀት፣ ጥበብ፣ ስነ-ጽሑፍ፣ ወይም የዓለም ክስተቶች ወዘተ አይደለም። እዚህ ጋ የሚናገረው ግን እግዚአብሔርን ስለማወቅ እውቀት ነው (ቁጥር 1 ይመልከቱ፤ በተጨማሪም 1 ሳሙኤል 2፡12 ይመልከቱ)።

76 የእግዚአብሔር ሕዝብ ገና ከመጀመሪያው “ብዙ ተባዙ” ተብሎ ተጠርቷል። ስለዚህ እግዚአብሔርን መምሰል ወደ ምድር ሁሉ መውሰድ ነበረባቸው (ዘፍጥረት 1፡26–26 ይመልከቱ)። ይሁን እንጂ የእሥራኤል ሕዝብ ግን ክፋት እያፈሩ ክፋታቸውንም እያበዙ ነበር።

ልባቸውንም ወደ በደላቸው አድርገዋል።
9
እንደ ሕዝቡም እንዲሁ ካህኑ ይሆናል፤
በመንገዳቸውም እበቀላቸዋለሁ
ሥራቸውንም እመልስባቸዋለሁ።
10
እግዚአብሔርንም መጠበቅ ትተዋልና
ሲበሉ አይጠግቡም
ሲያመነዝሩም አይበዙም።
11
ግልሙትናና የወይን ጠጅ ስካርም አእምሮን ያጠፋል።
12
የግልሙትና መንፈስ ሕዝቤን አስቶዋቸዋልና
እነርሱም ከአምላካቸው ርቀው አመንዝረዋልና
በትራቸውን ይጠይቃሉ
ዘንጋቸውም ይመልስላቸዋል።
13
በተራሮችም ራስ ላይ ይሠዋሉ፤
ጥላውም መልካም ነውና
ከኮምቦልና ከልብን ከአሆማም ዛፍ በታች
በኮረብቶች ላይ ያጥናሉ፤
ስለዚህ ሴቶች ልጆቻችሁ ይገለሙታሉ
ሙሽሮቻችሁም ያመነዝራሉ።
14
ወንዶችም ደግሞ ከጋለሞቶች ጋር ይጫወታሉና
ከጋለሞቶችም ጋር ይሠዋሉና
ሴቶች ልጆቻችሁ በገለሞቱ ጊዜ
ሙሽሮቻችሁም ባመነዘሩ ጊዜ አልቀጣቸውም፤
የማያስተውለው ሕዝብ ይገለበጣል።

15

እሥራኤል ሆይ አንተ ብታመነዝር

ይሁዳ አይበድል፤[77]

እናንተም ወደ ጌልገላ አትግቡ

ወደ ቤተአዌንም አትውጡ[78]

ወይም ሕያው እግዚአብሔር! ብላችሁ አትማሉ።[79]

16

እሥራኤል እንደ እልከኛ ጊደር

---

[77] ከሙሴ ዘመን ጀምሮ እስከ ሰሎሞን (የዳዊት ልጅ) ዘመን ድረስ የእግዚአብሔር ሕዝብ እንደ አንድ ሕዝብ ነበር። በዳዊት የልጅ ልጅ በሮብአም ዘመን ግን አንዱ የእሥራኤል ሕዝብ ለሁለት ማለትም እሥራኤልና ይሁድ ተብሎ ተከፈለ። ይሁዳ በደቡብ በኩል ነበረ። እሥራኤል ደግሞ በሰሜን በኩል ይገኝ ነበር። በዚህ ጥቅስ ላይ ያለውን ማስጠንቀቂያ የተነገረው ለይሁዳ ነው። ወደ እሥራኤል ወጥተው በዚያ ለነበሩት የወርቅ ጥጆች እንዳይሰግዱ የሚያስጠነቅቅ ነው። ሆሴዕ ለይሁዳ መናገሩ የተለመደ ነገር ነው። ምንም እንኳን ሆሴዕ በዋንኛነት ትንቢት የተናገረው በሰሜን ላሉት እሥራኤላውያን ቢሆንም፣ ሆኖም ሆሴዕ የይሁዳም ሰዎች ቃሉን እንዲሰሙና እዲታዘዙ ይጠብቅ ነበር። እንደዚሁም በወደፊቱም ዘመን የሚኖሩ ሰዎችንም ቢሆን ቃሉን እንዲሰሙና ምላሽ እንዲሰጡ ይጠብቅ ነበር (1 ጴጥሮስ 1፡10–12 ይመልከቱ)።

[78] ቤተአዌን የምትባል ከተማ ነበረች (ኢያሱ 7፡2፣ 18፡12፣ 1 ሳሙኤል 13፡5 እና 14፡23 ይመልከቱ)። **ሆኖም ይህ ጥቅስ የሚያመለክተው ትክክለኛውን የቤተአዌን ከተማ አይደለም። ይልቁንም ይህ የተነገረው የቤቴል ከተማን ለማሽሟጠጥ ነው።** ቤቴል ማለት **"የእግዚአብሔር ቤት"** ማለት ነው (በዕብራይስጥ "ቤት" = "ቤት" እና "ኤል" = "እግዚአብሔር") ማለት ነው። ቤቴል በአንድ ወቅት የእግዚአብሔር ሰዎች እግዚአብሔርን ለማምለክና ለመጠየቅ የሚሄዱበት ቦታ ነበር። ሰዎች በዚህ ሥፍራ በእውነት ያመልኩም ነበር። ይህ ቦታ ያዕቆብ በሕልሙ በሰማይና በምድር መካከል የተዘረጋውን መሰላል ያየው በዚህ ቦታ ነበር። በዚህ ምክንያት ያቆብ ይህንን ስፍራ ቤቴል ብሎ ጠርቶታል ይህም የእግዚአብሔር ቤት ማለት ነው (ዘፍጥረት 28፡10–22 ይመልከቱ)። ነገር ግን የእሥራኤል ሕዝብ ለሁለት ይሁዳና እሥራኤል ተብሎ ከተከፈለ በኋላ የመጀመሪያው የእሥራኤል ንጉሥ የነበረው ኢዮርብዓም የያዕቆብን ፈለግ አልተከተለም። በቤቴል እግዚአብሔርን አይመለክም ነበር። ይልቁንም በዚያ የወርቅ ጥጃ አሰርቶ አኖረ። የራሱንም ክህነት አቋቁሞ የራሱንም ህግጋት ፈጠረ (1 ነገ 12፡29–32 ይመልከቱ)።

ቤቴል ለእሥራኤል በጣም አስፈላጊ ቦታ ነበር። "የመንግሥታቸው ቤተ መቅደስ" የሚገኝበት ቦታ እንደሆነ ይቆጥሩ ነበር (አሞጽ 7፡13 ይመልከቱ)። እግዚአብሔር በነብያቱ በኩል ስለ ጣዖት እሥራኤልን ደጋግሞ አስጠንቅቆል፤ እሥራኤል ግን ንስሐ አልገባችም። ቤቴል የሚካሄደው የጣዖት አምልኮ እግዚአብሔር በዚህ ጥቅስ ("ቤት"= "ቤት" እና "አዌን" = "ጣዖት አምልኮ") ቤተአዌን ብሎ የጠራበት ምክንያት ይህ ነው። ቤቴል የእግዚአብሔር ቤት አልነበረችምና። ይልቅስ አሁን የጣዖት አምልኮት ቤት ነበር እንጂ። ይህ ስም በሆሴዕ 5፡8 እና 10፡5 ላይ በቴል ለሚለው ጥቅም ላይ ውሏል።

[79] ይሁዳ እንደ እሥራኤል እንዳትሆን ማስጠንቀቂያ ተሰጥቷታል። አንዳንድ ቃላት እንደ "ሕያው እግዚአብሔርን" የመሳሰሉትን ነገሮች በመናገር እሥራኤል እግዚአብሔርን የሚያመልኩ በመምሰል ያስመስሉ ነበር። ነገር ግን ልባቸው ከእርሱ በጣም የራቀ ነበር። የእግዚአብሔርን ስም በከንቱ ይጠቀሙ ነበር (ዘጸአት 20፡7 ይመልከቱ)። ስለዚህ ነው ሆሴዕ ለይሁዳ ሰዎች ከእሥራኤል እንዲለዩ የነገራቸው።

እንቢ ብሎአል፤[80]

እግዚአብሔርስ በሰፊው ቦታ

እንደ ጠቦት ያስማራዋለን?

17

ኤፍሬም[81] ከጣዖታት ጋር ተጋጠመ፤

ተወው።[82]

18

ስካርን ፈጽመዋል ግልሙትናንም አብዝተዋል፤[83] አልቆቾዋም ነውርን እጅግ ወደዱ።

19

ንፋስ በክንፍዋ አስሮአታል፤ ከመሥዋዕታቸውም የተነሣ ያፍራሉ።

5፡1

ካህናት ሆይ ስሙ፤

የእሥራኤል ቤት ሆይ ልብ አድርጉ፤

በምጽጳ ላይ ወጥመድ

በታቦርም ላይ የተዘረጋ አሽክላ ሆናችኋልና

በእናንተ ላይ ነው።

---

[80] ይህ ምሳሌ ነው። በዚህ ቅኔያዊ ንግግር እሥራኤል ከሌላ ነገር ጋር እየተነጻጸረች ነው። እዚህ ጋ እሥራኤል ወደ ተሻለ የግጦሽ መስክ መንቀሳቀስ ከማይችል ግትር ላም ጋር ተነጻጽራለች። እግዚአብሔር ለእሥራኤል ወደ ተሻለ የግጦሽ መስክ ቢኖረውም ለመንቀሳቀስ ፈቃደኛ አልነበረችም።

ነቢያት በትንቢት መጻሕፍት ውስጥ ብዙ ጊዜ ምሳሌዎችን ይጠቀማሉ። ከሰዎች ልበ ደንዳናነት አንፃር ምሳሌዎችን በብዛት መጠቀማቸው የሚያስደንቅ አይደለም። ሰዎች በተለመደው የንግግር ዘይቤ ውስጥ "የተለመደ" ቃላትን መስማት በማይችሉበት ጊዜ ምናልባት "ከፍያለ ንግግር" (እንደ ምሳሌያዊ እና ግጥሞች) የመሳሰሉትን ሲጠቀሙ ያዳምጡ ይሆናል። ምሳሌዎች ልብን የመስበርና ኃጢአትን የማጋለጥ መንገድ አላቸው። ምላሽ እንዲሰጥ ያነሳሳሉ።

[81] ኤፍሬም ከእሥራኤል ነገድ የአንዱ ስም ነው። አፍሬም ደግሞ በሰሜናዊው የእሥራኤል መንግሥት ትልቁ ነገድ ነበር፣ ስለዚህ ኤፍሬም የሚለው ስም አንዳንድ ጊዜ የእስራኤልን ሕዝብ ለመግለጽ ግጥም ይሠራበት ነበር (ለምሳሌ ኢሳይያስ 7፡2፣ 7፡17፣ 11፡13 እና ኤርምያስ 31፡18 ይመልከቱ)። ኤፍሬም የሚለው ስም በሆሴዕ ውስጥ 37 ጊዜ ተጠቅሷል። ይህ የኤፍሬም አዘውትሮ መጠቀሱ፣ ሆሴዕ በተለይም በሰሜናዊው የእሥራኤል መንግሥት ላይ እንዳተኮረ ማሳያ ነው።

[82] ይህ እያንዳንዱ ግለሰብ ከእሥራኤል እንዲሸሽና ይሁዳም ቢሆን ከእሥራኤል ጋር እንዳይተባበሩ የቀረበ ጥሪ ነው። እንደገና ሆሴዕ ቃሉን እንዲሰሙ እና በእምነት ምላሽ እንዲሰጡ ሰዎችን እየጠራ ነው።

[83] ካህናት፣ ነቢያት፣ እና ገዥዎች በሆሴዕ 4 ላይ ሁሉም ተወግዘዋል።

2

ዓመጸኞችም እርድ አብዝተዋል፤

እኔ ግን እነዚህን ሁሉ እዘልፋለሁ።[84]

3

ኤፍሬም አውቀዋለሁ

[84] ቁጥር 1–2 ተያይዘዋል እና በጥንቃቄ በንድፍ የተደረደሩ ናቸው። ይህን ንድፍ በተለይም በእንግሊዝኛው መጽሐፍ ቅዱስ ESV ግልጽ ሆኖ እንዳልተቀመጠ ልብ ሊባል የሚገባው ነገር ነው። ንድፉ በESV (እና በሌሎችም ታዋቂ ትርጉሞች CSB፣ NET፣ NIV ጨምሮ) ሊታይ አይችልም ምክንያቱም ሁሉም የተከተሉት ESV የቁጥር 2 የመጀምሪያ አጋማሽ የተተረጎመበት መንገድ ስለሆነ። ነገር ግን ከዚህ በታች ያለውን ማብራሪያ ESV፣ CSB፣ NTE፣ እና NIV መንገድ አይከተልም።

በእነዚህ ቁጥሮች ውስጥ ያለውን ንድፍ የተገነባው ባለ ሶስት ንድፎችን በመጠቀም ነው (ይህም በቁጥር 8 ላይ ይታያል)። በእነዚህ ቁጥሮች ውስጥ ሦስት ነገሮች ተጠቅሰዋል ከዚያም የእግዚአብሔር ቃል ተሰጥቷል። ይህም በሁለት የተለያዩ ጊዜያት ይከሰታል። በመጀመሪያ ለሦስት የተለያዩ **አድማጮች** ተነግሯቸው ነበር፡- (1) ካህናት፣ (2) ቤተ እሥራኤል፣ (3) ለንጉሥ ቤት። ለእነዚህ ሦስት ታዳሚዎች ከተነገራቸው በኋላ "ፍርዱ ለእናንተ ነው" የሚል አዋጅ በእግዚአብሔር ተነገረ። ሁለተኛው ሦስት የተለያዩ **ቦታዎች** ተጠቅሰዋል፡- (1) ምጽጳ፣ (2) ታቦር፣ (3) ሰጢም። ከዚህ በኋላ "እኔ ግን ሁሉንም እቀጣቸዋለሁ" የሚል የእግዚአብሔር ፍርድ ተነግሯል።

መልዕክቱ **ሦስት ሰዎች**፣ ማብራሪያ እና **ሦስት ቦታዎችን** እና ፍርዱን በጥሩ ሁኔታ ያሳያል፡-

*ካህናት ሆይ ስሙ፤*
*የእሥራኤል ቤት ሆይ አድምጡ፤*
*የንጉሥ ቤት ሆይ ልብ አድርጉ፤*

*በምጽጳ ላይ ወጥመድ*
*በታቦርም ላይ የተዘረጋ አሽክላ ሆናችኋልና*
*ፍርድ በእናንተ ላይ ነው።*
*ዓመጸኞችም እርድ አብዝተዋል፤*
*እኔ ግን እነዚያን ሁሉ እዘልፋለሁ።*

የእነዚህ ጥቅሶች አጠቃላይ ትርጉም ሁሉም የእሥራኤል ሕዝብ ከመሪዎች ጀምሮ እስከ ተራ ሕዝብ ድረስ ትልቅ ኃጢአት ሠርተዋልና ይህም በእሥራኤል እና በዙሪያው ያሉትን የተለያዩ ቦታዎችን ሁኔታ በመመልከት በቀላሉ ሊገለጽ ይችላል። በዚህ ምክንያት እግዚአብሔር እሥራኤልን ይቀጣል። የ ESV የቁጥር ሁለት ትርጉም ትክክል ሊሆን ይችላል (አመፀኞቹ እርድ ውስጥ ገብተዋል") ይላል። ሆኖም ይህ መስመር "በሰጢም ውስጥ ጥልቅ ጉድጓድ ቆፈሩ" ሌክሳም እንግሊዝኛው መጽሕፍ ቅዱስ) ወይም "በሰጢም ውስጥ ጥልቅ የተቆፈረ ጉድጓድ" (NRSV) በማለት ተርጉመውታል። እሥራኤል የጣዖት አምልኮዋን ባደረገችባቸው ቦታዎች ዝርዝር ውስጥ የተጠቀሰው ሦስተኛው ቦታ ስለሆነ የሰጢም ማጣቀስ በግጥሙ ትርጉም አለው። ይህ በቁጥር 1 የመጀመሪያ አጋማሽ ላይ ከተቀመጠው ንድፍ ጋር አብሮ የሚሄድ ይሆናል። በቁጥር 1 ላይ ሦስት የሰዎች ቡድኖች ተጠቅሰዋል። ከዚያም ሦስት ቦታዎች በ 1ለ እና 2ሀ ውስጥ ተጠቅሰዋል። በእሥራኤላውያን ላይ የቀረበው ክስ ሰጢም እሥራኤላውያን የጣዖት አምልኮ ጉድጓድ የቆፈሩበት ቦታ ነው የሚል ነው። ሦስቱም በቁጥር 8 ላይ መጠቀሱ ቁጥር 1 እና 2 ደግሞ በሦስት ጥቅሶች ላይ የመገንባቱን እድል ይጨምራል። ይህም ትርጉሙ በESV (CSB፣ NET እና በ NIV) ያነሰ ዕድል እንዲኖረው ያደርጋል።

እሥራኤልም ከእኔ አልተሰወረም፤
ኤፍሬም ሆይ ዛሬ አመንዝረሃል
እሥራኤልም ረክሶአል።

4
ወደ አምላካቸው ይመለሱ ዘንድ
ሥራቸውን አላቀኑም፤
የግልሙትና መንፈስ በውስጣቸው አለና፤
እግዚአብሔርም አላወቁምና።

5
የእሥራኤልም ትዕቢት በፊቱ ይመሰክራል፤
ስለዚህ እሥራኤልና ኤፍሬም በኃጢአታቸው ይሰናከላሉ፤
ይሁዳም ደግሞ ከእነሱ ጋር ይሰናከላል።[85]

6
እግዚአብሔርንም ለመሻት፤[86]
በጎቻቸውን ነድተው ይሄዳሉ፤
ነገር ግን እርሱ ከእነርሱ ተመልሶአልና
አያገኙትም።

7
ዲቃሎችን ልጆች ወልደዋልና
እግዚአብሔርን ወንጅለዋል፤
አሁንም አንድ ወር እነሱንና ርስታቸውን ይበላቸዋል።

8
በጊባዓ መለከትን[87]

---

[85] ይሁዳም በደለኛ ነውና እግዚአብሔር ለእሥራኤል የተናገረውን አዋጅ ማዳመጥ ይኖርበታል። ይህም ሆሴዕ የይሁዳ ሰዎች ቃሉን እንዲሰሙ እና በእምነት እንዲመልሱ እንደሚጠብቅ በድጋሚ የሚያሳይ ማስረጃ ነው።

[86] ይህ የሀሰት አምልኮን የሚያመለክት ነው።

[87] ቀንደ መለከቱን (ወይም መለከትን) ነፋ እና ማንቂያውን ነፋ የሚለው ማጣቀሻ ሁሉም እሥራኤላውያን አንድ ላይ እንዲሰበሰቡ የሚያደርግ ነበር። በጥንት ጊዜ ይህ በጣም አስፈላጊ በሆኑ ጊዜያት የሚደረግ ነበር። ለምሳሌ በጦርነት ጊዜ ሕዝቡን ወደ ጦርነት ለመጥራት መለከት ይነፋ ነበር። በጊባዓ እና በራማ የሚነፋውን ቀንደ መለከት በመጥቀስ

በራማ እንቢልታን ንፉና።[88]

ብንያም ሆይ ከአንተ በኋላ እያላችሁ

በቤተ-አዌን ላይ እሪ በሉ።[89]

9

ኤፍሬም በዘለፋ ቀን

የፈረሰ ይሆናል።

በእሥራኤል ነገዶች ዘንድ

በእርግጥ የሚሆነውን ነገር ገልጫለሁ።

10

የይሁዳ አለቆች

ድምበርን እንደሚነቅሉ ሆነዋል፤[90]

እኔም መዓቴን

---

እግዚአብሔር እሥራኤልውያን በመሳፍንት ዘመን ስለተከሰተው ክስተት ያስታውሳቸው ይመስላል (መሳፍንት 19–21 ይመልከቱ)። በመሳፍንት ዘመን የብንያም ሰዎች በጊብዓ ታላቅ ኃጢአት ሠሩ። በዚህ ኃጢአት ምክንያት እሥራኤል ሁሉ ተሰበሰቡ። የብንያምም ሰዎች ከዚህ ኃጢአት አልተመለሱም (መሳፍንት 20፡13 ይመልከቱ)። በዚያም ጊዜ የእሥራኤል ሕዝብ በብንያም ነገድ ለተፈጸመው ኃጢአት ምን ምላሽ መስጠት እንዳለባቸው እግዚአብሔርን ለመጠየቅ ወደ **ቤቴል** ወጡ (መሳፍንት 20፡18 ይመልከቱ)። በዚህ በሆሴዕ ጥቅስ ግን የእሥራኤል ሕዝብ በቤተ-አዌን (የቤቴል የፌዝ ቅጽል ስም ነው) ተሰብስበው "ብንያም ሆይ እንከተልሃለን" ብለው አውጀው ነበር። የእሥራኤልም ሕዝብ ኃጢአትን ለመዋጋት እየተሰበሰቡ አልነበረም። ይልቁንም ኃጢአታቸውን ተቀብለው ለኃጢአታቸው እየተዋጉ ነበር። ለዚህም ይመስላል ጥቅሱ "ብንያም ሆይ እንከተልሃለን" የሚለው።

[88] መሳፍንት 19፡13ን ይመልከቱ።

[89] ይህ ሦስት ቦታዎችን በማጣቀስ ምዕራፉ በሦስት ንድፎች ላይ የተገነባ መሆኑን እና ከላይ ከቁጥር 1–2 ያለውን ማብራሪያ የበለጠ ዕድል እንዳለው የሚያረጋግጥ ይመስላል።

ቀደም ሲል እንደ ተገለጸው በእሥራኤል ውስጥ ቤተ-አዌን የምትባል ከተማ ነበረች። **ሆኖም ይህ ጥቅስ ስለ ቤተ-አዌን ትክክለኛ ከተማን የሚያመለክት ላይሆን ይችላል። ይልቁንም ይህ የቤቴልን ከተማ የሚያመለክት ነውና።** ስለ ቤተ-አዌን ስምና ለቤቴል ተስማሚ ቅጽል ስም የሆነው ለምን እንደሆነ ተጨማሪ መርጃ ለማግኘት በሆሴዕ 4፡15 ላይ የሚገኘውን ማስታወሻ ይመልከቱ። ደግሞም በሆሴዕ 10፡5 በቤተ-አዌን የሚለው ስም ተጥቅሷል።

[90] ብዙ ጊዜ እንደተገለጸው ሆሴዕ ለሰሜን የእሥራኤል መንግስት ነቢይ ቢሆንም፤ ለደቡባዊው የይሁዳ መንግሥትም እየተናገረ ነበር። እዚህ ይሁዳ የጥንቱን ምልክት ከሚያንቀሳቅስ ሰው ጋር ተነጻጽሯል (ዘዳግም 19፡14፣ 27፡17 እና ምሳሌ 22፡28 ይመልከቱ)። ምሳሌ 22፡18 "አባቶች የሠሩትን የቀድሞውን የድንበር ምልክት አታፍልስ" ይላል። የይሁዳ ሰዎች ከአምልኳዋቸው ጋር በትያያዘ ያድረጉት ይህንኑ ነበር። የቀድሞ አባቶቻቸው የእግዚአብሔርን እውነተኛ አምልኮ በተመለከት "ድንቅ ምልክት" አዘጋጅተው ነበር። በሆሴዕ ዘመን የነበሩት የይሁዳ ሰዎች ግን አምልኮ በትመለከተ ይህን ጥንታዊ ምልክት ወደ አዲስ ቦታ "አንቀሳቅሰዋል"። አሁን አባቶቻቸው በማያውቁት ወይም ባልፈቀዱት መንገድ ያምልኩ ጀመር።

እንደ ውኃ አፈስስባቸዋለሁ።[91]

11 ኤፍሬም ከትእዛዝ በኋላ መሄድን ወድዶአልና የተገፋና በፍርድ የተጎዳ ሆኖአል።

12

እኔም ለኤፍሬም እንደ ብል

ልይሁዳም ቤት እንደ ነቀዝ ሆኜአለሁ።[92]

13

ኤፍሬም ደዌውን

ይሁዳም ቁስሉን ባየ ጊዜ

ኤፍሬም ወደ አሦር ሄደ፤[93]

ወደ ንጉሡም ወደ ኢያሪም መለከተኛን ላከ፤[94]

እርሱ ግን ይፈውሳችሁ ዘንድ

ከቁስላችሁም ያድናችሁ ዘንድ አልቻለም።[95]

14

---

[91] ይሁዳም እንደ እሥራኤል በእግዚአብሔር ይቀጣል። ይህ በሆሴዕ 1:7 ላይ ካለው ትንቢት የሚለይ ሊመስል ይችላል እግዚአብሔር "ነገር ግን የይሁዳን ቤት እምራሉ" ሲል ተናግሮ ነበርና። በሆሴዕ 1:7 ላይ ለይሁዳ የተነገረው መዳን በሕዝቅያስ የግዛት ዘመን በይሁዳ የተፈጸመ መሆኑን ልብ ማለት ያስፈልጋል። ይሁን እንጂ በዚያ ጊዜ ነፃ ቢወጡም በኋላ ላይ በባቢሎናውያን ተገዙ። ይሁዳም እንደ እሥራኤልም ኃጢአትንና የሐሰት አምልኮን ይወድ ነበር። 2 ነገሥት 23 በዚህ ጊዜ ውስጥ በይሁዳ ይፈጸሙ የነበሩትን የክፋት ዓይነቶች ለአንባቢው ጥሩ ምሳሌ ይሆናል።

[92] ብልና ነቀዝ የሚበሰብሱ ቁሶችን እንደሚያወድሙ ሁሉ እግዚአብሔር እሥራኤልንና ይሁዳን እያጠፋ ያለው እርሱ ነው እያለ ነው። እነዚህ እግዚአብሔር ስለ ራሱ የሚጠቀምባቸው አስገራሚ ምሳሌዎች ናቸው!

[93] እሥራኤላውያን ወደ መንግሥት ሰምያት ሳይሆን ለእርዳታ ወደ ምድራዊ መንግሥታት ዘወር ብለው ነበር። ወደ አሦርና ግብፅ (ለምሳሌ 7:11 ይመልከቱ)፤ በተለይም እሥራኤል የምትታመንባቸው ምድራዊ መንግሥታት ተብለው ተጠቅሰዋል። አሦር እዚህ በ 5:13 ተጠቅሷል (በተጨማሪም ሆሴዕ 7:11፣ 8:9፣ 9:3፣ 10:6፣ 11:5፣ 11:11፣ 12:1፣ እና 14:3 ላይ ይመልከቱ)።

[94] እሥራኤል እርዳታ እንደሚያስፈልጋት ተገነዘበች። ይሁን እንጂ ወደ እውነተኛው ታላቁ ንጉሥ (እግዚአብሔር) ከመዞርና ሞገሡን ከመፈለግ ይልቅ ወደ አሦር "ታላቅ ንጉሥ" ልከው የእሱን ሞገስ ፈለጉ። የእሥራኤል ነገሥታት ከአሦር ጋር ኅብረት መፍጠር የምትፈልጉትንና የሚመኙትን ሰላም እንደሚያመጣላቸ ተስፋ አድርገው ነበር። አሦራውያን እንደ ሚያጠፉዋቸው ግን አልተገነዘቡም ነበር።

[95] የእሥራኤል ቁስል የመጣው በጣዖት አምልኮ ነው፤ ስለዚህ አሦራውያን የእሥራኤልን መንፈሳዊ ሕመም መፍታት አልቻሉም ነበር። መንፈሳዊ ዝሙት የሚፈውሰው እግዚአብሔር ብቻ ነው። የመንፈሳዊ ምንዝርና ፈውስ በሆሴዕ 6:1 ላይ ይታያል። እነዚህ ጥቅሶች በወንጌል ክስተት አማካኝነት ወደ እግዚአብሔር ሕዝብ የሚመጣውን ፈውስ የሚያመለክቱ ናቸው። በተጨማሪም ሕዝቅኤል 36:24–27 ይመልከቱ።

እኔም እንደ አንበሳ
ለይሁዳም ቤት እንደ አንበሳ ደቦል እሆናለሁ፤[96]
እኔም ነጥቄ እሄዳለሁ እወስድማለሁ፤[97]
የሚያድንም አይገኝም።

15
በደላቸውንም እስኪያውቁ ድረስ ፊቴን እስኪሹ
ድረስ ሄጄ ወደ ስፍራዬ እመለሳለሁ፤
በመከራቸው ጊዜ እጅግ አድርገው ፊቴን ይፈልጋሉ።[98]

---

[96] እሥራኤልም ሆነች ይሁዳ መንፈሳዊ በሽታ አለባቸው። ሁለቱም በእግዚአብሔር “መፈውስ” ያስፈልጋቸዋል። እዚህ እንደገና ይሁዳ ከእሥራኤል ምንም የተለየ እንዳልሆነ እናነባለን። ሆሴዕ ለሁለቱም ሕዝቦች እየተናገረ ነው።

[97] እግዚአብሔርም ሕዝቡን እንደሚቀጣና “እንደሚተዋቸው” እየተናገረ ነው። ይህ ሊከሰት ከሚችለው በላይ እጅግ አሳዛኝ ነገር ነው! እግዚአብሔር ከሕዝቡ እየራቀ ነውና። የእስራኤል በአሦራዎያን መሸነፍ እና በኋላም ይሁዳ በባቢሎናውያን የተሸነፉበት ሽንፈት ከዚህ ጥቅስ በመነሳት መታየት አለበት። እግዚአብሔር ሕዝቡን “ለመቅደድ” እነዚህን ሁለት መንግስታት (አሦርና ባቢሎንን) ተጠቅሟል።

[98] ይህ በሆሴ የተነገረው የመጀመሪያው ተስፋ ሰጪ መልዕክት ነው። “በደላቸውንም እስኪያውቁ ድረስ ፊቴንም እስኪሹ ድረስ ሄጄ ወደ ስፍራዬ እመለሳለሁ፤” ሲል እግዚአብሔር በሕዝቡ ንስሐ ላይ በመመስረት እንደገና የቅርብ ግኑኝነት ከእነርሱ ጋር እንደሚፈጥር እያወጀ ነው። እግዚአብሔር ሕዝቡን ለመመለስ የገባውን ቃልኪዳን ለሆሴዕ አስገራሚ አይሆንም ነበር። የእሥራኤል ንሰሐና የእግዚአብሔር ወደ ሕዝቡ መመለስ ቃል ተገብቶአልና (በዘዳግም 4፡25–31 እና 30፡ 1–10 ይመልከቱ)። ሌሎች ነቢያት ደግሞ በሕዝቡ ንስሐ ተመስርቶ እግዚአብሔር ተመልሶ እንደሚመጣ የገባውን ቃል ይናገራሉ (ለምሳሌ ኢሳይያስ 1፡16–31 ይመልከቱ)። የመጥመቁ ዮሐንስ አገልግሎት መታየት ያለበት ከዚህ አንጻር ነው። በመጠመቁ ዮሐንስ ዘመን የእሥራኤል ንስሐ ሕዝቡን ከጌታ ጋር ለአዲስ ግኑኘነት አዘጋጅቶ ነበር።

## ሆሴዕ 6፥1–3

የሆሴዕ 6 የመጀመሪያዎቹ ሦስቱ ቁጥሮች የከበረ የወንጌል አቀራረብ ናቸው! ሆሴዕ ትንቢቱን የሰሙትን በእምነት ምላሽ እንዲሰጡና ወደ እግዚአብሔር እንዲመሱ ይጠራቸዋል። ሆሴዕ የእምነት ሰው ነው። እርሱ ራሱ የሰበከውን ቃል እየሰማ በእምነት መለሰላቸው። እስራኤልና ይሁዳም ምላሽ እንዲሰጡ ይፈልግ ነበር። ስለዚህ እስራኤልና ይሁዳ ንስሐ ከገቡ፣ እግዚአብሔር እንደሚያድናቸው እና በፍጥነት እንደሚያስነሣቸው ያውቅ ነበር። ሆሴዕ እግዚአብሔር ሕዝቡን መቼ እንደሚያስነሳ ሲናገር፡ "በሦስተኛው ቀን" የሚለውን ልብ ማለት ያስፈልጋል። ይህ ለወንጌል ክስተት ግልጽ ማጣቀሻ ነው! ኢየሱስ በሦስተኛው ቀን ከሙታን ተነሣ በሦስተኛውም ቀን ስለ ተነሣ በእርሱ የሚያምኑትን ሁሉ ከእርሱ ጋር ደግሞ እንደ ሚነሱ እርግጥ ነው ማለት ይቻላል። የእግዚአብሔር ሕዝብ ሁሉ ከእርሱ ጋር ይነሣ ዘንድ ክርስቶስ ስለ እግዚአብሔር ሕዝብ ሁሉ ሞትን ቀመሰ። ስለዚህ፣ ሦስተኛው ቀን የክርስቶስ ትንሣኤ ቀን ብቻ አልነበረም። ነገር ግን በእርሱ የሚያምኑትን ሁሉ የትንሣኤ ቀንም ነውም እንጂ (ቆላስይስ 3፥1–4 ተመልከት)።

## ሆሴዕ 6፥1–3

1

ኑ፤ ወደ እግዚአብሔር እንመለስ፤[99]

እርሱ ሰብሮናል እርሱም ይፈውሰናል፤[100]

እርሱ መትቶናል እርሱም ይጠግነናል።[101]

2

ከሁለት ቀን በኋላ ያድነናል፤[102]

በሦስተኛውም ቀን ያስነሣናል[103]

በፊቱም በሕይወት እንኖራለን።[104]

---

[99] ይህ ከአሁን በኋላ የእግዚአብሔር ቃል አይደለም። ይልቁንም የሆሴዕ ቃል ነው እንጂ ("እንመለስ" የሚለውን ሐረግ ያስተውሉ። በሆሴዕ 5:15 ላይ የእግዚአብሔርን የተስፋ ቃል ሰምቷል እናም በዚያ ጥቅስ ውስጥ እግዚአብሔር ሕዝቡን የጠራበት ጉዳዮች እንዲያደርጉ ሆሴዕ ደግሞ ሕዝቡን ይጠራል። ሆሴዕ ሕዝቡን "በደላቸውን እንዲያውቁ" "የእግዚአብሔርን ፊት ፈልጉ" ሲል ጠራቸው።ሆሴዕ እግዚአብሔርን ከልብ ከፈለጉት እንደሚያገኙት ደግሞ ያውቃል።

[100] ሆሴዕ እግዚአብሔር እስራኤልን "የሚሰብረው" ይሁዳ ደግሞ "እንዲፈውሰ" **እንደሆነ** ያውቃል። ይህ ማለት የእስራኤል ቅጣት እና የይሁዳ ቅጣት የእግዚአብሔር ምሕረት የሚገለጥበት መንገድ ነበር ማለት ነው። እየቀጣቸው ነበር ምክንያቱም በመጨረሻ እስራኤልን የሚፈውስበት መንገድ ይህ በመሆኑ ነበር። ይህም ፈውስ የሚከናወነው በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል ነው። እንደገና ሕዝቅኤል 36፥24-27 ይመልከቱ።

[101] የእስራኤል ቅጣት በእግዚአብሔር እጅ እንደ ነበር ሁሉ፤ በተመሳሳይም ሁኔታ የእስራኤልም መዳን በእግዚአብሔር እጅ ነበር። ምክንያቱም እስራኤል ራሷን መፈወስ አትችልም ነበርና።

[102] በዕብራይስጥ በግጥሞች ላይ ቁጥሮች በተለምዶ ከአንድ መስመር ወደ ቀጣዩ መስመር ይጨምራሉ። በዚህ ግጥም ውስጥም ቁጥሩ በመጀመሪያው መስመር ላይ ከ "ሁለት ቀናት" ወደ "ሦስተኛው ቀን" በሁለተኛው መስመር ላይ መጨመር ተፈጥሯዊ ነው።

[103] በሦስተኛው ቀን የሚነሱት የእግዚአብሔር ሰዎች በወንጌል ክስተት ውስጥ በግልጽ ተፈጽመዋል። ክርስቶስ **በሦስተኛው ቀን** ተነሥቷልና። ሆኖም ትንሣኤው በኢየሱስ ላይ ብቻ ተጽዕኖ አላሳደረም። ይልቁንም፣ "በእርሱ ያሉት" ሁሉ በሦስተኛው ቀን ከእርሱ ጋር ተነሥተዋል (ቆላስይስ 3፥1 ይመልከቱ)። 1ኛ ቆሮንቶስ 15፥4 ኢየሱስ "ቅዱሳት መጻሕፍት እንደሚሉት **በሦስተኛው ቀን** እንደተነሣ" ይገራል። በእርግጥም ሆሴዕ 6:2 ላይ ደግሞም ጳውሎስ በዚህ ጥቅስ ላይ ከጠቀሳቸው ቅዱሳን ጽሑፎች ውስጥ አንዱ ነው ለማለት ይቻላል። በግልጽ እንደምናየውም ጳውሎስ ይህንን ጥቅስ በሆሴዕ ውስጥ አንብቦ ወዲያው ከወንጌል ክስተት ጋር አገናኝቶታልና።

[104] ክርስቶስ የተነሣበት ምክንያት እኛም እንድንነሣ ነው። እግዚአብሔር ይህን ያደረገው ደግሞ "በፊቱ በሕይወት እንድንኖር" ነው። ከክርስቶስ ጋር ካልተነሳን በእግዚአብሔር ፊት በሕይወት መኖር አንችልምና።

3

እንወቅ፤ እናውቀውም ዘንድ እግዚአብሔርን እንከተል፤

እንደ ወገግታም ተዘጋጅቶ እናገኘዋለን፤

እንደ ዝናብም ምድርንም እንደሚያጠጣ

እንደ መጨረሻ ዝናብ ይመጣል።

## ሆሴዕ 6፥4–11ሀ

የሆሴዕ 6 የመጀመሪያዎቹ ሦስቱ ቁጥሮች የሆሴዕ ቃላት ነበሩ። በሆሴዕ 5፥15 ላይ ለተናገረው የእግዚአብሔር ቃል በእምነት የተሞላ ምላሽ ነበር። ሆሴዕ የእግዚአብሔርን ሕዝብ ንስሐ እንዲገቡ እየጠራቸው ነበር በምዕራፍ 5፥15 ላይ ባለው የእግዚአብሔር ቃል ላይ ተመርኩዞ፣ እግዚአብሔር ለንስሐቸው ምላሽ እንደሚሰጥ እና እንደሚፈውሳቸው፣ እንደሚያነቃቃቸው እና እንደሚያስነሳቸው ስለሚያውቅ ነበር። እነዚህ ሁሉ ነገሮች ክርስቶስ በሕይወቱ፣ በሞቱ እና በትንሣኤው ያደረገውን ሥራ ያመለክታሉ።

ሆሴዕ 6፥4 ላይ ግን ሆሴዕ ከእንግዲህ አይናገርም። አሁንም እግዚአብሔር እየተናገረ ነው። በእነዚህ ጥቅሶች ውስጥ፣ እግዚአብሔር ስለ እስራኤል እና ይሁዳ ለእሱ ያላቸውን ፍቅር ሁኔታ ይናገራል። እነዚህ ሕዝቦች ኃጢአታቸውን ተመልክተው ንስሐ እንዲገቡ እና በሚያስደስት መንገድ እንዲያመልኩ ነቢያትን እንደላካቸው ተናግሯል። ነገር ግን ይህን አላደረጉም።

እንደገና፣ በተስፋ መልእክቶች (ሆሴዕ 6፥1–3) እና በኩነኔ (ሆሴዕ 6፥4–11ሀ) መካከል ያለው የማያቋርጥ ለውጥ በነቢያት የተለመደ ነው። ሰባኪው ወይም መምህሩ በመጽሐፉ ውስጥ ለውጦች የት እንደሚደረጉ ለማሳየት በምዕራፍ ቁጥሮች ላይ መተማመን አይችልም። ይልቁንም ጽሑፉን በቅርበት ማንበብ ይጠይቃልና።

**6፡ 4**

ምሕረታችሁ እንደ ማለዳ ደመና

በማለዳም እንደሚያልፍ ጠል ነውና [105]

ኤፍሬም ሆይ ምን ላድርግህ?

ይሁዳ ሆይ ምን ላድርግህ? [106]

**5**

ስለዚህ በንቢያት እጅ ቆረጥኋችሁ

በአፌም ቃል ገደልኋችሁ፤

ፍርዴም እንደ ብርሃን ይወጣል። [107]

---

[105] በእስራኤልና በይሁዳ ላይ የነበረው እውነት ክርስቲያን ነን በሚሉ ሰዎች ላይም ሊከሰት የሚችል ነው። ለእግዚአብሔር ያላቸው ፍቅር እንደ ደመና ነው። ፍቅራቸው እውነተኛ እና ጠቃሚ ይመስላል ነገር ግን በማለዳም እንደሚያልፍ ጠል ነው።

[106] የእግዚአብሔር ሞቅ ያለ “ልብ” እዚህ ሊሰማ ይችላል። አንድን ወንድ ወይም ሴት ልጁን ለማረም ሁሉንም ነገር እንደሞከረ እንደ ተበሳጨ ወላጅ እግዚአብሔርም በሕዝቡ ላይ ያለውን የፍቅር ብስጭት እየገለጸ ነው። ይህ ግጥም፣ የሆሴዕ ቃል ለይሁዳ እና ለእስራኤል እንደሆነ በድጋሚ ማስረጃ ነው። እነዚህ ሁለቱም ዓመፀኛ ሕዝቦች ከኃጢአታቸው ንስሐ መግባት አለባቸው። አፍቃሪ አባታቸው ወደ ራሱ እየጠራቸው ነው።

[107] እነዚህ ሦስት የግጥም መስመሮች **ነቢያት እነማን እንደሆኑ** እና **ነቢያት የሚያደርጉትን** ለመረዳት በጣም ኢጋዥ ናቸው። በዚህ ጥቅስ (እና ሌሎች) ላይ በመመስረት ነቢያት እንደ ተፈቀደላቸው የእግዚአብሔር ቃል አቀባይ ሆነው መታየት አለባቸው። ነቢይ ሲናገር ለሕዝቡ የሚናገረው እግዚአብሔር ነውና። ነቢዩ ለሰዎች ከባድ የሚመስሉ ቃላትን ሲናገር፣ እነዚህን ክፉ የሚመስሉ ቃላት ለህዝቡ የሚናገረውም እግዚአብሔር ነው።ነቢዩ የመጽናናትን ቃል ሲናገር እግዚአብሔር የሚያጽናና ቃል ነው የተናገረው ማለት ነው። ደግሞም የነቢዩ የፍርድ ቃል እግዚአብሔር በሕዝቡ ላይ ብርሃኑን የሚያበራበት መንገድ ነው። ስለዚህም ነቢያት የእግዚአብሔር የጸጋ መሣሪያዎች ናቸው። የእግዚአብሔርን ብርሃን ወደ ጨለማ ቦታዎች ያመጣሉ ማለት ነው። ሆሴዕ ለእስራኤል (እና ለይሁዳ) የተናገረው የእግዚአብሔር ቃል ለእስራኤል ነው። እንደዚሁም ኢሳይያስ ለይሁዳ የተናገረው የእግዚአብሔር ቃል ለይሁዳ፣ ወዘተ፣ ወዘተ፣ ወዘተ፣ ወዘተ። ነቢያት የእግዚአብሔርን ቃል ስለሚናገሩ፣ በሚናገሩት ነገር ሁልጊዜ ትክክል ናቸው (ዘዳግም 18፡19–22 ይመልከቱ)።ነቢያት የእግዚአብሔር ቃል አቀባይ በመሆናቸው፤ ነቢይ መግደል ማለት እራሱን እግዚአብሔርን ዝም ለማሰኘት የሚደረግ ሙከራ መሆኑን ያሳያል። ለእግዚአብሔር፡ “አንሰማህም” ማለት ነው። በይበልጥ በጠንካራ ሁኔታ ለማስቀመጥ፣ ነቢይን መግደል እግዚአብሔርን ራሱን ለመግደል የሚደረግ ሙከራ ነው።

አሁን የብሉይ ኪዳን ነቢያት በምድር ላይ የሉም። ሆኖም ግን በእግዚአብሔር ቸርነት ምክንያት በቅዱሳት መጻሕፍት በኩል በጻጋው ነቢያት አሁንም ይናገራሉ። ስለዚህ ለእነሱ አሁንም መታዘዝ ያስፈልጋል። ትንቢታቸው፣ ከሐዋርያት ቃል ጋር፣ ቤተ ክርስቲያን የምትታነጽበትን መሠረት ይመሠርታልና (ኤፌሶን 2፡20 ይመልከቱ)። ነቢያት የእግዚአብሔርን እቅድ በተመለከተ ምን ያህል ያውቁ እንደነበር፣ 1ኛ ጴጥሮስ 1፡10–12 ይመልከቱ።

6

ከመሥዋዕት ይልቅ ምሕረትን

ከሚቃጠልም መሥዋዕት ይልቅ እግዚአብሔርን ማወቅ እወዳለሁና።[108]

7

እነርሱ ግን እንደ አዳም ቃል ኪዳንን ተላልፈዋል፤[109]
በዚያም ላይ ውንጅለውኛል።

8

ገለዓድ ኃጢአትን የሚሠሩ ሰዎች ከተማ

በደምም የተቀባ ነው።[110]

---

[108] ይህ ጥቅስ እግዚአብሔር ነቢያትን የላከበትን ምክንያት ያስረዳል። ሕዝቡ በእውነት እግዚአብሔርን እንዲወዱትና እንዲያመልኩት ላካቸው። ሕዝቡ በመንፈስና በእውነት እንዲሰግዱ ነቢያትን ተላኩ። ሕዝቡን ከባዶ ሃይማኖት ለማዳን ነቢያትን ተላኩ። ኢየሱስ ይህንን ጥቅስ በማቴዎስ 9፡13 እና 12፡7 ጠቅሷል።ኢየሱስ አንድን አንቀጽ ሲጠቅስ እሱን የሚያዳምጡት ሰዎች እሱ እየጠቀሰ ካለው ጥቅስ በላይ እንዲያስቡበት ይፈልጋል። እሱን የሚያዳምጡት ሰዎች ጥቅሱ የሚገኝበትን ክፍል በሙሉ እንዲያስቡበት ይፈልጋል። ለፈሪሳውያን ሲነግራቸው፡- “ሂዱና ይህ ምን ማለት እንደሆነ ተማሩ። ምሕረትን እንጂ መሥዋዕትን አይደለም አልፈልግም” በማለት ሆሴዕን በጥንቃቄ እንዲያጠኑና ትክክለኛ ትርጉሙን እንዲያውቁ እየነገራቸው ነበር። ኢየሱስ በእሱ ዘመን ይኖሩ የነበሩት የሆሴዕን ትንቢት እንዲያነቡና በሕይወታቸው ውስጥ እንዲተገበሩ ይጠብቅባቸው ነበር። ዛሬም ሁኔታው ተመሳሳይ ነው። ኢየሱስ ዛሬ ሆሴዕን የሚያነቡ ሰዎች የሆሴዕን ትንቢት ከድርጊታቸው ጋር እንዲያስተያዩ ይጠብቅባቸዋል። እግዚአብሔር በመሥዋዕት ብቻ አይደሰትምና፣ በተጨማሪም ኢሳይያስ 1:10–17ን ይመልከቱ።

[109] በቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ በእግዚአብሔር እና በአዳም መካከል ያለው **ቃል ኪዳን** በግልፅ የተጠቀሰበት ቦታ ይህ ነው። ይህ በእግዚአብሔር እና በአዳም መካከል ስላለው ግንኙነት እና የአዳም አለመታዘዝ ለምን እንደዚህ ዓይነት አሳዛኝ መዘዝ እንዳስከተለ የበለጠ ግልፅ ያደርገዋል። አዳም ቃል ኪዳኑን አፈረሰ! ይህ መረጃ ሰባኪው ወይም መምህሩ በዘፍጥረት 3 ላይ ያለውን የአዳምን ኃጢአት ከባድነት እንዲረዱ ይረዳቸዋል። ሆሴዕ እስራኤላውያንን ከአዳም ጋር ሲያወዳድር የተናገረው ሐሳብ እስራኤል እንደ አዳም ለመሆኑ ተጨማሪ ማስረጃዎችን ይሰጠናል። ሁለቱም የሚኖሩት እግዚአብሔር በሚመለከበት በእግዚአብሔር ቦታ ነበር። ሁለቱም የእግዚአብሔርን መልክና አምሳል እንዲይዙ እና እንዲያፈሩ እና እንዲበዙ የታሰቡ ነበሩ። ሁለቱም ከእግዚአብሔር ጋር ቃል ኪዳን ነበራቸው። ደግሞም እስራኤል እንደ አዳም የእግዚአብሔር ልጅ ተብሎ ተገልጿል (ዘጸአት 4፡22 እና ሉቃስ 3፡38 ይመልከቱ)። እስራኤላውያን ግን ልክ እንደ አዳም የእግዚአብሔርን ቃል ማክበር ተስኗቸዋል። ሁለቱም የእግዚአብሔር ልጆች ቃል ኪዳኑን አፍርሰዋል። ሰዎች ሁሉ አንድ ቀን ተመልሰው ይመጡ ዘንድ ልክ አዳም ከገነት እንደተባረረ እስራኤልም ከምድሪቱ እየተባረሩ ነበር። ኢየሱስ ግን ከአዳምና ከእስራኤል የተለየ ነው። በእውነት የእግዚአብሔር ልጅ መሆኑን በማሳየት ቃል ኪዳኑን ይጠብቃል። ፍጹም ታዛዥ ስለሆነ የእግዚአብሔር ሕዝብ ከእግዚአብሔር ፊትና ቦታ እንባረራለን የሚል ፍርሃት ሊያድርባቸው አያስፈልግም።

[110] ሆሴዕ ገለዓድን ያነሳው እስራኤል ቃል ኪዳኑን ያፈረሰበት ቦታ ምሳሌ ስለሆነ ነው። በቁጥር 9 ላይ ሌላ ምሳሌ ይጠቀማል። የእነዚህ ቦታዎች ማጣቀሻዎች ለሰባኪው ወይም ለአስተማሪው እርዳታ ነው። በእነዚህ ቦታዎች ስለሚፈጸሙ ክፉ ድርጊቶች ስናነብ እነዚህ ቦታዎች ከሕያው አምላክ ጋር ቃል ኪዳን የገቡ ሰዎች እንደሚኖሩበት ማስታወስ አለብን! እግዚአብሔር የቃል ኪዳኑን መፍረስ አይቶ ያስታውሰዋልና። ገለዓድ በሆሴዕ 12፡11 ላይም ተጠቅሷል።

9

ለሰውም እንደሚያደቡ ወንበዴዎች

እንዲሁ የካህናት ወገኖች

በሴኬም መንገድ ላይ ይገድላሉ፤[111]

ሴሰኝነትንም ያደርጋሉ።

10

በእሥራኤል ቤት የሚያስፈራን ነገር አይቻለሁ፤

በዚያም በኤፍሬም ውስጥ ግልሙትና ተገኘው እሥራኤልም ረክሶአል።

11

ለአንተ ደግሞ መከር ተወስኖልሃል።[112]

---

111 ይህ እስራኤል ቃል ኪዳኑን ያፈረሰበት ሌላ ቦታ ነው። ይሁን እንጂ እስራኤል ቃል ኪዳኑን ያፈረሰባቸው ጊልያድ እና ሴኬም ብቻ አይደሉም። በምድሪቱ ውስጥ በሁሉም ቦታ ይካሄድ የነበረው የቃል ኪዳን ማፍረስ የሚወክሉ ናቸው እንጂ። እግዚአብሔር ቃል ኪዳኑ በየጊዜው የሚፈርስባቸውን ብዙ እና ሌሎች ምሳሌዎችን ሊሰጥ ይችል ነበር።

112 እንደገና፣ ሆሴዕ በአገልግሎቱ ጊዜ ዋና "አድማጩ" እስራኤል ነበረች። እሱ ግን ለይሁዳም እየተናገረ ነበርና ለመልእክቱ ምላሽ መስጠት ያስፈልጋቸው ነበር። እነሱም እንደ እስራኤል ቃል ኪዳኑን ያፈርሱ ነበርና። ሆሴዕ እስራኤልና ይሁዳ ለስብከቱ በእምነት ምላሽ እንዲሰጡ እየጠራቸው ነበር። ዛሬ የሆሴዕ ዋና "አድማጭ" ቤተ ክርስቲያን ናት። እንዲያውም፣ በ 1 ጴጥሮስ 1፡10–12 መሠረት፤ ሆሴዕ እየተናገረ ያለው ከራሱ ዘመን በላይ ለሆኑ ታዳሚዎች መሆኑን ያውቅ ነበር። ወደፊት ለሚኖሩ ሰዎች እየተናገረ መሆኑን ያውቅ ነበርና።ቤተክርስቲያን ለተናገረው ቃል ምላሽ መስጠት አለባት።

## ሆሴዕ 6፡11ለ–7፡16

በእነዚህ ጥቅሶች ውስጥ፣ እግዚአብሔር እየተናገረ ነው። እስራኤልን እንዴት መፈወስ እንደሚፈልግ ገልጿል እስራኤል ግን መፈወስ አትፈልግም። በዚህ ምክንያት ጥፋት እየመጣባቸው ነው።

አንድን ጥቅስ በግማሽ "መክፈል" እንግዳ ነገር ሊመስል ይችላል። ሆኖም ሆሴዕ 6፡11 ለሁለት መከፈል አለበት። ቁጥር 11ሀ በተፈጥሮ ከፊቱ ያለውን ነው። ቁጥር 11ለ በተፈጥሮው ከእርሱ በኋላ ካለው ጋር ነው። እንደገና በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ያሉት የምዕራፍ ክፍሎች በመጀመሪያው ጽሑፍ ውስጥ አልነበሩም። ሆሴዕ አልጻፋቸውም። ደግሞም አጋዥ ቢሆኑም ተመስጧዊ አይደሉም። ስለዚህ ሰባኪው ወይም መምህሩ በቁጥር እና በምዕራፍ ቁጥሮች ላይ ሳይሆን በጽሑፉ ላይ ማተኮር ይኖርባቸዋል።

## ሆሴዕ 6፡11ለ–7፡16

**6፡11ለ**

ይሁዳ ሆይ የሕዝቤን ምርኮ በምመልስበት ጊዜ[113]

[113] ሆሴዕ 6:11 አዎንታዊ መስሎ ሊታይ ይችላል ነገር ግን ወደ አሉታዊነት ሊያደላ የሚችል ነው። ምናልባት ሰባኪው ቁጥር 11ን "ለመክፈል" በሁለት ክፍሎች ማስቀመጥ ይረዳዋል። የ11ኛው ቁጥር የመጀመሪያ አጋማሽ በቁጥር 10 ካሉት ሁለት የግጥም መስመሮች ጋር መያያዝ አለበት። አብረው የሚሄዱ ናቸውና። ሆሴዕ 6፡10 በእስራኤል ላይ የቀረበ ክስ ሲሆን የሆሴዕ 6፡11 የመጀመሪያ አጋማሽ ደግሞ የይሁዳ ክስ ነው። ሁለቱም ሕዝቦች ጥፋተኞች ናቸው እና በመንፈሳዊ ግልሙትና ምክንያት ይቀጣሉ። ለሁለቱም ሕዝቦች የተሾመው "መኸር" (ቁጥር 11) ላይ ነው። የፍርድ አዝመራ ነው።

በተመሳሳይ የ6፡11 የመጀመሪያ አጋማሽ ከ6፡10 ጋር እንደሚሄድ፣ የ6፡11 ሁለተኛ አጋማሽ ከ7፡1 የመጀመሪያ አጋማሽ ጋር ይስማማል። አብረው ይሄዳሉ። እግዚአብሔር ስለ ድርጊቱ ሲናገር ("እስራኤልን በምፈውስበት ጊዜ የሕዝቤን ምርኮ ደግሞ እመልሳለሁ") ይላል፤ እንዲሁም ስለ ሕዝቡ ድርጊት ("የኤፍሬም ኃጢአትና የሰማርያ ክፉ ሥራ ተገለጠ") ብሎ ይናገራል። እግዚአብሔር የህዝቡን ምርኮ ወደ ነበረበት ለመመለስ እየሰራ መሆኑን ገልጿል፤ ነገር ግን በኃጢአታቸው ምክንያት ጥረቱን ያለማቋረጥ ሲያከሽፉ ኖረዋል።

እግዚአብሔር ለህዝቡ (በእስራኤልም ሆነ በይሁዳ) ፈውስ ለማምጣት እየሞከረ ነበር ነገር ግን ምላሽ አልሰጡም። ሌሎች ነቢያትም ስለ እስራኤል ለእግዚአብሔር ፀጋ ምላሽ ለመስጠት ፈቃደኛ አለመሆናቸውን ይናገራሉ (ለምሳሌ ኢሳይያስ 65፡2፣ ይህም በሮሜ 10፡21 ተጠቅሷል)። የ NET ትርጉም ይህንን የግጥሙ ክፍል እንዲህ አስቀምጦታል፡- "የሕዝቤን ምርኮ መመለስ በፈለግሁ ጊዜ፣ እስራኤልንም መፈወስ በፈለግኩ ጊዜ፣ የኤፍሬም ኃጢአት ደግሞ ይገለጣል..."። እንደገና፣ እግዚአብሔር ጸጋን ያፈስ ነበር በተቃራኒው ደግሞ ህዝቡ ከጊዜ ወደ ጊዜ ኃጢአት እየጨመሩ በመሄድ ምላሽ ይሰጡ ነበር።

**7፡ 1**

በሐሰት አድርገዋልና

ሌባም ገብቶአልና

በውጭም ወንበዴዎች ቀምተዋልና

እሥራኤልን እፈውስ ዘንድ በወደድሁ ጊዜ

የኤፍሬም ኃጢአትና

የሰማርያ ክፋት ተገለጠ።[114]

**2**

እኔም ክፋታቸውን ሁሉ እንዳሰብሁ[115]

በልባቸው አያስቡም

አሁንም ሥራቸው ከብባቸዋለች

በፊቴም አለች

**3**

ንጉሡን በክፋታቸው

አለቆቹንም በሐሰታቸው ደስ አሰኝተዋል።[116]

---

114 ሰማሪያ የእሥራኤል ዋና ከተማ ነበረች።

115 የእግዚአብሔር ሰዎች እግዚአብሔር ኃጢአትን ሁሉ እንደሚያይ እና ጻድቅ ስለሆነ ኃጢአትን ችላ ማለት እንደማይችል ረስተውት ነበር። እንሱ ጻድቅ ዳኛ ነውና። የእግዚአብሔር ሕዝብ በቅድስና መመላለስ አለበት። ዛሬ ሰባኪዎች ይህንኑ እውነት ለህዝቡ ማሳሰብ አለባቸው (ለምሳሌ ገላትያ 6፡7 እና 1 ጴጥሮስ 1፡15–16 ይመልከቱ)።

116 የእሥራኤል ገዥዎች በሕዝቡ አለመታዘዝ ተደስተው ነበር። ጌታ ኢየሱስ ግን የዚህ ተቃራኒ ነው።እግዚአብሔርን መታዘዝን ይወዳል (ዮሐንስ 14፡31 ይመልከቱ)፤ እና ሰዎች ደግሞ እግዚአብሔርን ሲታዘዙ ይወዳል። የእግዚአብሔር ሕዝቦች እግዚአብሔርን በማይታዘዙበት ጊዜ ያዝናል። እንዲያውም ኢየሱስ አብን ሕዝቡ እንዲታዘዙ መንፈስ ቅዱስን እንዲሰጣቸው ጠይቋል! መንፈስ ቅዱስ ደግሞ “ሌላ ረዳት” ነው (ኢየሱስም ረዳታችን ነው!) በመታዘዝ እንድንመላለስ የሚረዳን (ዮሐንስ 14፡15–17 ይመልከቱ)። የእግዚአብሔር ሰዎች ጽድቅን ስለሚወድ ወደ ክፋት ፈጽሞ እንደማይመራቸው ስለሚያውቁ ንጉሣቸውን (ኢየሱስን) በደስታ ሊከተሉ ይችላሉ (ዕብራውያን 1፡9 ይመልከቱ)። መታዘዝ በዮሐንስ 14–16 ውስጥ ያለው ዋና ጭብጥ ነው። እነዚህ ጥቅሶች በጥንቃቄ መጥናት አለባቸው። እንዲሁም በራዕይ 2–3 ያሉትን ለአብያተ ክርስቲያናት የተላኩትን ሰባቱንም ደብዳቤዎች ይመልከቱ። እነዚህም ታዛዥነትን ያጎላሉ።

4

ሁሉም አመንዝራዎች ናቸው፤

ጋጋሪ እንደሚያነድበት እንደ ምድጃ ናቸው፤

ሁሉ እስኪቦካ ድረስ

እሳትን መቆስቆስና

እርሾን መለወስ ይቆያል።

5

በንጉሣችን ቀን አለቆች

ከወይን ጠጅ ሙቀት የተነሣ ታመሙ፤

እርሱም ከዋዘኞች ጋር እንጁን ዘረጋ።

6

እያደቡ ልባቸውን እንደ ምድጃ አዘጋጅተዋል፤

አበዛቸውም ሌሊቱን ሁሉ አንቀላፋ፤

በጠባም ጊዜ እንደ እሳት ነበልባል ይነድዳል።

7

ሁሉም እንደ ምድጃ ግለዋል

ፈራጆቻቸውም ሁሉ ወደቁ፤

ከእነርሱም ወደ እኔ የሚጮኽ የለም።

8

ኤፍሬም ከአሕዛብ ጋር ተደባለቀ፤[117]

ኤፍሬም እንዳልተገላበጠ ቂጣ ነው።

9

እንግዶች ጉልበቱን በሉት[118]

---

117 የእግዚአብሔር ሰዎች ሁል ጊዜ የተጠሩት ከዓለም እንዲለዩ ነው (2 ቆሮንቶስ 6፡17 ይመልከቱ)። ይልቁንም የእስራኤል ሕዝብ እግዚአብሔርን እንደማያውቁ ሰዎች አደረጉ። ዛሬም ተመሳሳይ ነው። ለዚህም ነው ያዕቆብ ዓለማዊ ክርስቲያኖችን "አመንዝሮች" በማለት የገለጻቸው (ያዕቆብ 4፡4 ይመልከቱ)። ያዕቆብ የጻፈላቸው ክርስቲያኖች በሆሴዕ ዘመን እንደነበሩት እስራኤላውያን መንፈሳዊ ግልሙትና ይፈጽሙ ነበር።

118 በሆሴዕ ዘመን ለእሥራኤል ሕዝብ መንፈሳዊ ጥንካሬ ማጣት እውን ነበር። በዛሬው ጊዜ ያሉ ክርስቲያኖችም ይህ ሊሆን ይችላል። ከሕያው አምላክ ጋር ከምንሠራው ይልቅ "ከእንግዶች" ጋር ስለምንገናኝ በእግዚአብሔር የነበረን ኃይላችን ተበላ።

እርሱም አላወቀም፤
ሽበትም ወጣበት
እርሱም አላወቀም።[119]
10
የእሥራኤል ትንቢት በፊቱ መሰከረ፤
ወደ አምላካቸው ወደ እግዚአብሔር ግን አልተመለሱም
በዚህም ሁሉ አልፈለጉትም።
11
ኤፍሬም አእምሮ እንደሌላት
እንደ ሰነፍ ርግብ ነው፤
ግብጽን ጠሩ ወደ አሦርም ሄዱ።[120]
12
ሲሄዱ አሽክላዬን አዘረጋባቸዋለሁ፤
እንደ ሰማይ ወፎች አወርዳቸዋለሁ፤
መከራቸውን ሲሰሙ እገሥጻቸዋለሁ።
13
ከእኔ ፈቀቅ ብለዋልና ወዮላቸው!
በእኔም ላይ ዐመፀዋልና ጥፋት ይምጣባቸው!
እኔ ልታደጋቸው ወደድሁ[121]
እነርሱ ግን በሐሰት ተናገሩብኝ።

---

ንስሐ ስንገባ እና "እግዚአብሔርን መጠበቅ" ስንጀምር መንፈሳዊ ጥንካሬያችንን እና ጉልበታችን እንመልሳለን ወይም ይታደሳል (ኢሳይያስ 40፡29–31 ይመልከቱ)።

119 እሥራኤል ድክመቷን አላወቀችም። በዛሬው ጊዜ ያሉ ክርስቲያኖችም ተመሳሳይ ናቸው። እራሳችንን በመንፈሳዊ ነገራችን ጠንካራ እንደሆንን እናምናለን፣ ነገር ግን ደካሞች፣ ሰነፎች እና ግማሽ ልብ መሆናችንን አናውቅም ( በራዕይ 3፡14–22 ውስጥ የኢየሱስን የቸርነት ማስጠንቀቂያ ለሎዶቅያ ቤተክርስቲያን የተባለውን ይመልከቱ)።

120 እሥራኤል ከጠላቶቿ ለመዳን ያለማቋረጥ ወደ የሌሎች ነገሥታት እርዳታ ትፈልግ ነበር።

121 እንደገና፣ 6፡11ለ–7፡1 ይመልከቱ። የእግዚአብሔር ፍላጎት ሕዝቡን ማዳን ነበር። ነገር ግን እነርሱ በእግዚአብሔር መዳንን አልፈለጉም። ይልቅስ እነሱ ከበኣል እርዳታ ይፈልጉ ነበር።

14

በመኝታቸውም ላይ ሆነው ያለቅሱ ነበር እንጂ

በልባቸው ወደ እኔ አልጮኹም፤[122]

ስለ እህልና ወይን ጠጅ ይሰበሰቡ ነበር፤

በእኔም ላይ ዐመፁ።

15

እኔም ክንዳቸውን አስተማርሁና አጸናሁ፤[123]

እነርሱ ግን ክፉ ነገርን መከሩብኝ።

16

ወደ ከንቱ ነገር ተመለሱ፤

እንደ ተንኮለኛ ቀስት ሆኑ፤[124]

ከአለቆቻቸው ቁጣ የተነሣ በሰይፍ ይወድቃሉ፤

ይህ በግብፅ ምድር ውስጥ መሳለቂያ ይሆንባቸዋል።[125]

---

122 የእግዚአብሔር ፍላጎት እውነተኛ ንስሐ ነበር።

123 እግዚአብሔር ፍሬ እንዲያፈሩ ሕዝቡን አበረታ። ያበረታቸውም የእግዚአብሔር መልክና አምሳል ወደ ምድር ሁሉ ለማምጣት እንዲችሉ ነበር። ነገር ግን እነሱ ያደረጉት ይህ አይደለም።

124 ይህ ኃይለኛ ምሳሌ ነው። ተንኮለኛ ቀስት ሲመወንጨፍ ወደታሰበው አቅጣጫ በትክክል አይወነጨፍም። ይልቁንም በተገላቢጦሹ ወደ ቀስተኛው ሊዞርም ይችላል። እግዚአብሔር እሥራኤላውያን ለእሱ ዓላማ በእጁ የሚገኙ “መሣሪያ” እንዲሆኑ አስቦ ነበር። ነገር ግን እግዚአብሔርን ተቃወሙ! በእግዚአብሔር ላይ ክፉትን እያሰቡ ነበርና (ቁጥር 15 ይመልከቱ)።

125 ሕዝቡ ወደ "ግብፅ" ይመለሳሉ። ይህ ማለት ግን አብዛኞቹ የእስራኤል ሰዎች ወደ ግብፅ ተመለሱ ማለት አይደለም። በእርግጥም በአሦር ተገዙ እንጂ። ይህ ምሳሌአዊ ነው። ሕዝቡም እግዚአብሔር ወደ አዳናቸው ባርነት ዳግም ይመለሳሉ። ከዚህ አንፃር ደግሞ “ግብፅ” በዓለም ውስጥ በየትኛውም ቦታ ሊሆን ይችላልና!

## ሆሴዕ 8–10

በእነዚህ ሦስት ምዕራፎች ውስጥ አንባቢው ትልቅ “አዎንታዊ” ክፍል አያገኝም። በእነዚህ ምዕራፎች ውስጥ እንደ ሆሴዕ 2፡1–3፣ 2፡16–23፣ 3፡1–5፣ ወይም 6፡1–3 ያለ ነገር የለም። በእርግጥ፣ ከ 10፡12 በስተቀር በእነዚህ ሶስት ምዕራፎች ውስጥ ከእግዚአብሔር ምንም አይነት የማጽናኛ መልእክቶች የሉም። ይልቁንስ ከግጥም በኋላ እግዚአብሔር፣ እስራኤልና ይሁዳ በኃጢያታቸው በደለኛ መሆናቸውን እና እንደሚቀጡ አሳይቷል። በእነዚህ ምዕራፎች ውስጥ ከሞላ ጎደል አጠቃላይ የመጽናኛ እጥረት ቢኖርም “ጸጋ ቢስ” ተብለው ሊፈረጁ ደግሞ አይገባም። የእግዚአብሔር ጸጋ ማስረጃዎች ናቸውና። ሰዎች መጥፎ ዜናን በሰሙ ጊዜ ንስሐ እንዲገቡ መጥፎ ዜና እየነገራቸው ነውና። ሰባኪው ወይም መምህሩ ወንጌልን እንዴት መስበክ እንደሚችሉ ከእንደዚህ ዓይነት የቅዱሳት መጻሕፍት ክፍሎች መማር አለባቸው።

**8፡1**

መለከትን ወደ አፍህ አቅርብ፤[126]

 ቃል ኪዳኔን ተላልፈዋልና[127]

በሕጌም ላይ ዐምፀዋልና

በእግዚአብሔር ቤት ላይ እንደ ንስር ይመጣል።[128]

**2**

እነርሱም አምላክ ሆይ እኛ እሥራኤል አወቅንህ[129]

ብለው ወደ እኔ ይጮኻሉ።

**3**

እሥራኤል ደግነትን ጥሎአል፤

ጠላትም ያሳድዱታል።

**4**

ለራሳቸው ነገሥታትን አነገሡ ከእኔም ዘንድ አይደለም፤[130]

 አለቆችንም አደርጉ እኔም አላወቅሁም፤

ለጥፋታቸውም

ከብራቸውና ከወርቃቸው፤ጣዖታትን ለራሳቸው አደርጉ።

**5**

ሰማሪያ ሆይ እምቦሳህን፤ ጥሎአል፤[131]

ሆሴዕ 8–10

---

126 አንዳንድ ጊዜ በጦርነት ጊዜ ጥሩንባ ይነፋ ነበር። እዚህ ያለው ጉዳይ ይህ ነው። ሆኖም ጠላት ከእግዚአብሔር ምድር ውጪ ለመግባት እየሞከረ አይደለም። ይልቁንም ጠላት የሚገኘው በእግዚአብሔር ምድር ውስጥ ነው እንጂ!

127 ሆዕሴ 6፡7 ይመልከቱ።

128 እንደ ንስር የሚለው በእስራኤል ላይ ስለሚመጣው ጥፋት ተስማሚ ምስል ነው። አሞራዎች ሙታንን ይመገባሉ። እስራኤል በመንፈሳዊ ነገር ሞታለችና።

129 እሥራኤል እግዚአብሔርን እንደ ምትወደው ትናገር ነበር። ነገር ግን ይህ “ፍቅር” ውሸት ነበር።

130 ይህም በ 1-2 ነገሥት የተገለጹትን የእስራኤል ነገሥታት ምንነት ያስረዳል።

131 ይህ በሰማርያ የነበረውን የወርቅ ጥጃ የሚያመለክት ነው (1 ነገሥት 12፡25–13፡34 ይመልከቱ)።

ቁጣዬ በላያቸው ነድዶአል፤
እስከ መቼ ድረስ ንጹሕ ሊሆኑ አይችሉም?
6
ይህ ደግሞ ከእሥራኤል ዘንድ ነው፤
ሠራተኛ ሠራው
እርሱም አምላክ አይደልም፤
የሰማሪያም እምቦሳ ይቆራረጣል።[132]
7
ነፋስን ዘርተዋ
ዐውሎ ነፋስንም ያጭዳሉ፤
አገዳ የለውም
ከፍሬውም ዱቄት አይገኝም፤
ቢገኝም እንግዶች ይበሉታል።
8
እሥራኤል ተውጦአል
በአሕዛብም መካከል
ዛሬ እንደረከሰ እቃ ሆኖአል።[133]
9
ለብቻውም እንደሚቀመጥ እንደ ምድረ በዳ አህያ
ወደ አሦር ወጥተዋል፤
ኤፍሬምም ወዳጆቹን በእጅ መንሻ ገዛ።[134]
10
ነገር ግን ለአሕዛብ እጅ መንሻ ቢሰጡ

---

[132] እስራኤላውያን የወርቅ ጥጃዎቻቸው አምላክ ነው ብለው ነበር። ነገር ግን አምላክ አልነበሩም።

[133] እስራኤል አላማዋን እየፈጸመች አልነበረም። በመጀመሪያ እግዚአብሔር ለእስራኤል የካህናት ሕዝብ ይሆናል ብሎ ተናግሮ ነበር (ዘጸአት 19፡6 ይመልከቱ)። ነገር ግን ለመታዘዝ ፈቃደኛ ባለመሆናቸው ከንቱ ሆኑ።

[134] ይህ እስራኤላውያንን ለማዳን የሚከፈላቸው ሃገራት የሚያመለክት ነው። ይህ ለጊዜው የተሳካ ቢሆንም፣ የእስራኤልን መንፈሳዊ ድህነት ግን አሳይቷል። እግዚአብሔር እንደሚጠብቃቸው አላመኑምና።

እኔ አሁን እሰበስባቸዋለሁ፤
ከንጉሥና ከአለቆችም ሸክም
የተነሣ ይደክማሉ።

11
ኤፍሬም ኃጢአትን ለመሥራት መሠውያ አብዝቶአልና
መሠውያ ለኃጢአት ይሆንለታል።

12
የሕጌን ብዛት ጽፌለታለሁ፤
እነርሱ ግን እንደ እንግዳ ነገር ቆጥረውታል።[135]

13
መሥዋዕቴን ያቀርባሉ
ሥጋንም ያርዳሉ ይበላሉም፤
እግዚአብሔር ግን አይቀበላቸውም፤[136]
በደላቸውንም ያስባል
ኃጢአታቸውንም ይቀጣል፤
እነርሱም ወደ ግብፅ ይመለሳሉ።[137]

---

[135] ይህ የሚያሳየው ሕጎች የሰውን ልብ እንደማይለውጡ ነው (ገላትያ 3፡10-11 ይመልከቱ)።ተጨማሪ ሕጎች ታዛዥ ያልሆኑትን እስራኤላውያንን አያድኑም። እስራኤልን የሚያድነው ብቸኛው ነገር ሕጎች የተጻፉበት አዲስ ልብ ነው። በዚህ መንገድ ሕጎቹ እንደ እንግዳ ነገር አይታዩም። ይልቁንም በልብ ላይ ስለተጻፉ ተፈጥሯዊ ይሆናሉ እንጂ። ይህ በትክክል ለክርስቲያኖች በክርስቶስ የተሰጠ ነው (ገላትያ 3፡12–14 ይመልከቱ)! የኢየሱስ ሞት መቀበርና እና ትንሳኤ የአዲስ ኪዳን መመስረትን አምጥቷል (ሕዝቅኤል 36፡24–27 እና ዕብራውያን 8፡8–12 ይመልከቱ)። ይህ አዲስ ቃል ኪዳን ደግሞ ሰዎች በደስታ እንዲታዘዙት ያስችላቸዋል።

[136] እስራኤላውያን እግዚአብሔርን እንደሚያመልኩ ተናግረዋል። ለእግዚአብሔር "መሥዋዕትን" ያቀርቡ የነበረው በዚህ ምክንያት ነበር። ስለዚህ እስራኤላውያን በጠማማ መንገድ ሁልጊዜ እግዚአብሔርን ያመልኩ ነበር። ለእነሱ እግዚአብሔርም ከብዙ አማልክት እንደአንዱ ነበር። እግዚአብሔር ግን ይህን የሐሰት አምልኮ አይቀበለውም ነበር። እግዚአብሔር አይለወጥምና። አሁንም ቢሆን የሐሰት አምልኮን አይቀበልም። ክርስቲያኖችም የሐሰት አማልክቶቻቸውን ጥለው እግዚአብሔርን ብቻ ማምለክ አለባቸው።

[137] እግዚአብሔር ሕዝቡን ከግብፅ አድኖዋቸው ነበር። አሁን ግን በኃጢአት ምክንያት እንደገና ወደ "ባርነታቸው" ይመለሳሉ። ምክንያቱም ሕዝቡ ወደ "ግብፅ" እየተመለሰ ነውና መዳን ካለባቸው ወደፊት ሌላ ዘጸአት ሊያስፈልጋቸው ነው ማለት ነው። ክርስቶስ የሚያመጣው መዳን ብዙ ጊዜ "ሁለተኛው መውጣት ወይም ዘጸአት" ተብሎ መነገሩ ጠቃሚ ነው። ምክንያቱም ህዝቡን ከኃጢአት ባርነት አውጥቷልና።

14

እሥራኤል ፈጣሪውን ረስቶአል

መስገጃዎችንም ሠርቶአል፤

ይሁዳም የተመሸጉትን ከተሞች አብዝቶአል፤[138]

እኔ ግን በከተሞች ላይ እሳትን እሰድዳለሁ

አዳራሾችንም ትበላለች።[139]

---

[138] እንደገና የቀደሙት ቃላት በዋነኝነት የተነገሩት ለእስራኤል ነው። ይሁን እንጂ ትንቢቱ በሙሉ ስለ እስራኤልም ሆነ ስለ ይሁዳ በግልጽ ይናገራል።

[139] እግዚአብሔር እስራኤላውያን የታመኑበትን ሁሉ ያስወግዳል። ይህ መልካም ተግባር ነበር። በግልጽ እንዲመለከቱ አስችሏቸዋል እናም በተስፋ ወደ ብቸኛው መታመኛቸው ዞር ማለት አለባቸው። ዛሬም ተመሳሳይ ነገር ነው። ንስሐ እንድንገባ እና በእርሱ እንታመን ዘንድ እግዚአብሔር የምንታመንባቸውን ነገሮች ሁሉ ያስወግዳል።

9:1

እሥራኤል ሆይ ከአምላክህ ተለይተህ

አመንዝረሃልና

እንደ አሕዛብ ደስ አይበልህ

ሐሴትንም አታድርግ፤ በእህሉ አውድማ ሁሉ ላይ

የግልሙትናን ዋጋ ወድደሃል።

2

አውድማውና መጥመቂያው አይመግባቸውም

ጉሽ ጠጅም ይጎድልባታል።[140]

3

በእግዚአብሔር ምድር ላይ አይቀመጡም፤[141]

ኤፍሬምም ወደ ግብጽ ይመለሳል፤

በአሦርም ርኩስን ነገር ይበላሉ።[142]

4

ለእግዚአብሔርም የወይን ጠጅን ቁርባን አያፈሱም፤

መሥዋዕታቸውም ደስ አያሰኘውም፤[143]

የኀዘንም እንጀራ ይሆንላቸዋል፤

የሚበላውም ሁሉ ይረክሳል፤

እንጀራቸውም ለሰዎነታቸው ይሆናል፤

---

140 በእስራኤል ጣዖት አምልኮ ምክንያት፣ ምድሪቱ በረከቷን ለእስራኤላውያን እንደማትሰጥ እግዚአብሔር ተናገረ። ይህ እስራኤላውያንን ሊያስደንቅ አይገባም። ይህ በዘዳግም 28፡15–68 ላይ ተስፋ ተሰጥቶ ነበር። ቀደም ብሎም፣ በቃየን ሕይወትም አቤልን ሲገድለው ታይቷል (ዘፍጥረት 4፡12 ይመልከቱ)። ይህ የበረከት መወገድ የእግዚአብሔር የጸጋ ስጦታ ነው። ከኃጢአቱ እንዲመለስ ሕዝቡ የበረከት እጦትን እንደተጨማሪ ማስጠንቀቂያ ሊመለከተው ይገባል።

141 እንደ አዳምና ሔዋን ሁሉ እስራኤላውያንም በእግዚአብሔር መልካም ቦታ ላይ አልቆዩም።

142 ግብፅ እና አሦር በሆሴዕ አንድ ላይ ተጣመሩ። ሁለቱም ከእግዚአብሔር መልካም ቦታ የራቁ የባርነት ምሳሌዎች ናቸው። እንደገና የእነዚህ ቦታዎች ማጣቀሻዎች የእግዚአብሔር ሕዝቦች ነፃ የሚወጡ ከሆነ ሁለተኛ ዘጸአት እንደሚያስፈልጋቸው አንባቢን ያስታውሳሉ።

143 እንደገና እስራኤል ቢያንስ በሆነ መልኩ እግዚአብሔርን ያመልኩ ነበር። ሌሎች አማልክትን ሲያመልኩ እንኳ በተከፈለ ልብ ለእግዚአብሔር መሥዋዕት ያቀርቡ ነበር። እግዚአብሔር ደግሞ ይህን ዓይነቱን አምልኮ አይቀበልም ነበር።

እንጂ ወደ እግዚአብሔር ቤት አይገባም።[144]

5

በዓመት በዓል ቀንና

በእግዚአብሔር በዓል ቀን ምን ታደርጋላችሁ?

6

እነሆ ከጥፋት ሸሽተው ሄዱ

ግብፅም ትሰበስባቸዋልች፤

ሜምፎስም ትቀብራቸዋለች፤[145]

ሳማም የብራቸውን ጌጥ ይወርሳል

እሾህም በድንኳኖቻቸው ውስጥ ይበቅላል።

7

የበቀል ወራት መጥቶአል

የፍዳም ወራት ደርሶአል

እሥራኤልም ያውቃል፤

ከኃጢአትህና ከጥላትነትህ ብዛት የተነሣ

ነቢዩ ሰንፎአል

መንፈስም ያለበት ሰው አብዶአል።

8

ኤፍሬም ከአምላኬ ጋር ተመልካች ነበረ፤

አሁን ግን ነቢዩ በመንገዱ ሁሉ ላይ የወፍ ወጥመድ ሆነ

በአምላኩም ቤት ጠላትነት አለ።

9

በጊባዓ ዘመን እንደ ነበረ፤[146]

---

144 እስራኤላውያን በኣልን በሚያመልኩበት ጊዜም የእግዚአብሔርንም አምልኮ ደግሞ ቀጥለው ነበር። ያህዌ ቀናተኛ አምላክ ነው። ከፊል አምልኮን አይፈልግም እና ይህን አይነት አምልኮ አይቀበልም ነበር። ዘጸአት 34፡14 ይመልከቱ።

145 ሜምፊስ በጥንቷ ግብፅ የምትገኝ ከተማ ነበረች። ግብፅ በሆሴዕ እንደ ዋና ጭብጥ ተወስዳለች።

146 የጊብዓ ዘመን በመሳፍንት መጽሐፍ መጨረሻ ላይ የተመዘገበውን ኃጢአት የሚያመለክት ይመስላል። መሳፍንት 19 ይመልከቱ።

እጅግ ረከሱ፤
እርሱም በደላቸውን ያስባል
ኃጢአታቸውንም ይበቀላል።
10
እሥራኤል በምድረ በዳ እንዳለ
ወይን ሆኖ አገኘሁት፤
አባቶቻችሁንም ከመጀመሪያዋ ዓመት
እንደ በለስ በኩራት ሆነው አየኋቸው፤
እነርሱ ግን ወደ በዔልፌጎር መጡ፤[147]
ለነውርም ተለዩ
እንደ ወድዱትም ርኩስ ሆኑ፤
11
የኤፍሬም ክብር እንደ ወፍ በርሮ ይጠፋል፤
መውለድና መፅነስ ማርገዝም አይሆንላቸውም!
12
ልጆቻቸውንም ቢያሳድጉ
ሰው እንዳይቀርላቸው ልጅ አልባ አደርጋቸዋለሁ፤
ከእነርሱም በራቅሁ ጊዜ
ወዮላቸው!
13
እኔ እንዳየሁ የኤፍሬም ልጆች ለምርኮ ተሰጥተዋል፤
ኤፍሬምም ልጆቹን ወደ ጋድዮች ያወጣል።
14
አቤቱ ስጣቸው፤
ምን ትሰጣቸዋለህ?
የሚጨነግፍን ማኅፀን
የደረቀውንም ጡት ስጣቸው።

[147] ዘዳግም 3፡9 እና 4፡3 ይመልከቱ።

15

ከፋታቸው ሁሉ በጌልገላ አለ፤

በዚያ ላይ ጠልቻቸዋለሁ፤[148]

ስለ ሥሩት ክፋት

ከቤቴ አሳድዳቸዋለሁ፤

ከእንግዲህ ወዲያ አልወዳቸውም፤[149]

አለቆቻቸው ሁሉ ዓመፀኞች ናቸው።

16

ኤፍሬም ተመታ

ሥሩም ደረቀ

ፍሬም አያፈራም፤[150]

ደግሞም ቢወልዱ

የማኅፀናቸውን ፍሬ እገድላለሁ።

17

አልሰሙትምና

አምላኬ ይጥላቸዋል፤

በአሕዛብም መካከል ተቅበዝባዦች ይሆናሉ።[151]

---

[148] እስራኤላውያን የዮርዳኖስን ወንዝ ከተሻገሩ በኋላ የሰፈሩበት የመጀመሪያ ቦታ ጌልገላ ነው።

[149] ይህ በሆሴዕ ዘመን ስለ እስራኤል የተነገረ ነው። እግዚአብሔር ያን ትውልድ ይቅር እንደማይለው እየተናገረ ነው። እነሱ ይጠፋሉና።

[150] እስራኤላውያን እግዚአብሔርን ለማምለክ እና እሱንም ለመከተል ፈቃደኛ ባለመሆናቸው መልካም ፍሬ ማፍራት አይችሉም። እውነተኛው እስራኤል የሆነው ኢየሱስ በሆሴዕ ዘመን እስራኤላውያን ያላደረጉትን አድርጓል። እርሱ ፍፁም ፍሬያማ ነው። ፍፁም ፍሬያማ ስለሆነ፣ በእርሱ ያሉት ሁሉ ደግሞ ፍሬያማ ናቸው (ዮሐንስ 15 ይመልከቱ)።

[151] በዘፍጥረት 4፡14 እንደምንመለከተው፤ እንደ ቃየን የእስራኤልም ሕዝብ ከቤታቸው ርቀው ይባረራሉ። በዘዳግም ውስጥ ሊበታተኑ እንደሚችሉ በትንቢት ተነግሯል (ዘዳ 4፡27 እና 29፡28 ይመልከቱ)። ነገር ግን፣ ዘዳግም ደግሞ በሚመጡት የወደፊት ቀናት እግዚአብሔር ህዝቡን መልሶ እንደሚሰበስብ የገባውን ቃል ያካትታል (ዘዳ 4፡28–31 እና 30፡1-10 ይመልከቱ)። ክርስቲያኖች ደግሞ የእግዚአብሔር ሕዝቦች በመሆናቸው ከአሕዛብ ውስጥ ከሚሰበሰቡት አካል ናቸው (1 ጴጥሮስ 1፡1 ይመልከቱ)። ኢየሱስ በዚህ ሁለተኛ ዘፀአት የእግዚአብሔርን ሕዝብ የሚመራ “መሪ” ነው (ሆሴዕ 2፡1–3 ይመልከቱ)።

**10፡1**

እሥራኤል ፍሬው የበዛለት[152]

የለመለመ ወይን ነው፤

እንደ ፍሬው ብዛት[153]

መሠዊያውን አብዝቶአል፤

እንደ ምድሩም ማማር መጠን

ሐውልቶችን አያሳመሩ ሠርተዋል።[154]

**2**

ልባቸው ተከፈለ፤

አሁንም በደላቸውን ይሸከማሉ፤

እርሱ መሠውያቸውን ያፈርሳል

---

[152] በብሉይ ኪዳን እስራኤል ብዙ ጊዜ ከወይን ተክል ጋር ትነጻጸራለች። ይህ ንጽጽር ምንጊዜም አሉታዊ ነው፤ ምክንያቱም እስራኤል ጥሩ ፍሬ አላፈራችምና (መዝሙር 80፡8–16፤ ኢሳ 5፡1–7፤ ኤርምያስ 2፡21፣ 5፡10፣ 12፡10፤ ሕዝቅኤል 15፡1–8 እና 17፡1–24 ይመልከቱ፡)። በዮሐንስ 15 ላይ ኢየሱስ ራሱን ከወይኑ ጋር ማነጻጸሩን ልብ ማለት ያስፈልጋል። እርሱ **እውነተኛው ወይን** ነውና። እንደ እውነተኛው የወይን ግንድ፣ የእስራኤል ያላደረገውን ያደርጋል። መልካም ፍሬ ያፈራልና። ይህ የሚያሳየው ኢየሱስ አዲሲቱ እስራኤል መሆኑን ነው። የእግዚአብሔርን ፈቃድ የሚፈጽም ፍጹም የእግዚአብሔር ልጅ ነው። በእርሱ የሆኑትም ሁሉ ደግሞ መልካም ፍሬ ያፈራሉ። ከኢየሱስ በቀር ሌላ የወይን ግንድ የለም። እንደ እውነተኛው የወይን ግንድ፣ እግዚአብሔር ሁልጊዜ ለእስራኤላውያን ያለውን “ፍሬ የማፍራት” ዓላማን ይፈጽማል። የአዲስ ኪዳን አንባቢዎች ይህን ግጥም በሆሴዕ እያነበብን እንደመሆናችን መጠን ስለ እውነተኛው እስራኤል—ኢየሱስ—ለአብ ክብር መልካም ፍሬ ሲያፈራ ልብ ልንል ይገባናል። ማንኛውም ሰው መልካም ፍሬ ማፍራት የሚችልበት ብቸኛው መንገድ ያ ሰው ከእውነተኛው የወይን ግንድ ማለትም ከኢየሱስ ጋር የተገናኘ በመሆኑ ነው።

[153] አንባቢው በፍራፍሬ የተሞላ የወይን ተክል በሚያምር ምስል ቀርቦለታል። ወይኑም እስራኤል ነው። የእስራኤል ምድር ልክ እንደ ወይኑም በየቦታው “ወይን” ይበቅልበታል። በእስራኤል ውስጥ የሚበቅሉት “የወይን ፍሬዎች” ግን ለበኣል መሠዊያነት ውለው ነበር! እነዚህ መሠዊያዎች ጤናማ በሆነ የወይን ግንድ ላይ እንዳሉ የወይን ፍሬዎች በብዛት ይገኛሉ እና ሌሎችም ሁልጊዜ እየተጨመሩ ነበር! ስለዚህ ጣዖት አምልኮ የእስራኤል “ፍሬ” እንደሆነ እንማራለን። ይህ በወቅቱ መድሪቱ የምታመርተው እና የምትታወቅበትም ነገር ሆኖ ነበር።

[154] አሁን የወይኑን ምሳሌ አልፈናል ስለዚህ ሁሉም ትኩረት በምድሪቱ ላይ ነው የተደረገው። ምድሪቱ እየተሻሻለች ስትሄድ የምንመለከተው (በእግዚአብሔር መልካምነት ምክንያት ነው!) የምድሪቱ ሰዎች ምሰሶዎችቻቸውን ለማሻሻል ተግተው ሲሰሩ እናያለን። "መሠዊያዎች" እና "ምሰሶዎች" የሚውሉት ግን ለሐሰት አማልክቶች ነው። ይህ ጥቅስ የሚያመለክተው ጣዖት አምልኮ ሁልጊዜ በእስራኤል እያደገ እንደ ነበር ነው። “ከፍ ባለ ኮረብታ ሁሉ ላይ ከለመለመውም ዛፍ ሁሉ በታች” (ኤርምያስ 3፡6 ይመልከቱ)፤ እስራኤላውያን ጣዖታትን ያመልካሉ ነበር።

ሐውልቶቻቸውን ያጠፋል።[155]

3

አሁንም ንጉሥ የለንም

እግዚአብሔርን አልፈራንምና፤

ንጉሥስ ምን ያደርግልናል?

ይላሉ።

4

የማይረባውን ቃል ይናገራሉ፤

ቃል ኪዳን በገቡ ጊዜ በሐሰት ይምላሉ፤

ስለዚ መርዛም ሣር በእርሻ ትልም ላይ እንደሚበቅል

መቅሠፍት ይበቅልባቸዋል።

5

የሰማሪያ ሰዎች

ስለ ቤታአዌን እምቦሳ ይፈራሉ፤[156]

ክብሩም ከእርሱ ዘንድ ወጥቶአልና

ሕዝቡ ያለቅሱለታል

የጣዖቱ ካህናትም በኀዘን ይንተባተባሉ።

6

ለንጉሡ ለኢያሪም እጅ መንሻ ይሆን ዘንድ[157]

---

155 የእስራኤል "ፍሬ" ማለትም መሠዊያዎችና ምሰሶዎቻቸው በእግዚአብሔር ይፈርሳሉ። መሠዊያዎቻቸውንም ለማፍረስ የሚጠቀምበት "መሣሪያ" አሦራውያን ይሆናሉ። በእስራኤል ውስጥ የጣዖት አምልኮ መሰውያዎችን ያጠፋል። በዚህ ግጥም ባይነገርም ነገር ግን በሆሴዕ ውስጥ የሚገኙት ሌሎች ክፍሎች ያህዌ የጣዖት አምልኮ መሳሪያዎችን እንደሚያስወግድ ብቻ ሳይሆን የጣዖት አምልኮ ፍቅርንም እንደሚያጠፋ ያመለክታሉ።

156 ይህ ሆሴዕ የሚናግረው የቤቴል የቅጽል ስም ነው። ቤቴል ማለት "የእግዚአብሔር ቤት" ማለት ነው። ቤት-አዌን ማለት ደግሞ "የዓመፅ ቤት" ማለት ነው። በዚያ ካለው የወርቅ ጥጃ የተነሳ ቤቴል የእግዚአብሔር ቤት መባልዋ ቀርቶ ቤተ-አዌን ሆና ነበርና።

157 ህዝቡ የታመነበት የወርቅ ጥጃ እንኳን ወደ ስደት ሊወሰድ ነበር! የወርቅ ጥጃው እስራኤልን ከግዞት ማዳን አልቻለም። ሌላው ቀርቶ ይህ "አምላክ" እራሱን እንኳን ማዳን አልቻለም ነበር! ወደ ስደትም ተወስዶ ነበር!

ወደ አሦር ይማርካል፤
ኤፍሬምን እፍረት ይይዘዋል
እሥራኤልም በምክሩ ያፍራል።
7
ሰማሪያ ከንጉሥዋ ጋር
በውኃ ላይ እንዳለ አረፋ ጠፍታለች።
8
የእሥራኤል ኃጢአት የሆኑት የአዌን[158]
የኮረብታው መስገጃዎች ይፈርሳሉ፤
እሾህና አሜከላ በመሠዊያቻቸው ላይ ይበቀላል፤
ተራሮችንም ክንደኑን
ኮረብቶችንም ውደቁብን ይሉአቸዋል።[159]
9
እሥራኤል ሆይ ከጊባዓ ዘመን ጀምረህ ኃጢአትን ሠርተሃል፤[160]
በዚያ ጸንተዋል፤
በጊባዓ ላይ ሰልፍ አይደርስባቸውምን?
10
በፈቀድሁም ጊዜ እገሥጻቸዋለሁ፤
ስለ ሁለቱም ኃጢአታቸው በታሰሩ ጊዜ
አሕዛብ ይሰበስቡዋቸዋል።

158 አሁንም ይህ ለቤቴል መሳለቂያ ነው።

159 እስራኤላውያን በአሦር በተያዙበት ዘመን እንዲህ እያለቀሱ እንደነበረ ሁሉ ሐዋርያው ዮሐንስም ሁሉም ሰዎች እግዚአብሔርን ለማምለክ ፈቃደኛ ባለመሆናቸው አንድ ቀን በዚህ መንገድ እንደሚጮኹ ተናግሯል (ራዕይ 6፡16 ይመልከቱ)። ስለዚህ ሁሉም ሰዎች በሆሴዕ ዘመን ከነበሩት እስራኤላውያን ምርኮኞች መማር አለባቸው ምክንያቱም ይህ በጣዖት አምልኮ ምክንያት ስለደረሰባቸው ቅጣት ለሚመጣው ጊዜም ማስጠንቀቂያ ነው።

160 በመሳፍንት 19፡22–30 ላይ የተገለጸውን አስከፊ ኃጢአት ተመልከት። እግዚአብሔር እያለ ያለው ኃጢአት ከተሠራበት ከዚያች ቀን አንስቶ እስከ ሆሴዕ ትንቢት ድረስ እስራኤልውያን ኃጢአት መሥራታቸውን አላቆሙም ነው የሚለው።

11

ኤፍሬም ማበራየት

እንደ ለመደች ጊደር ነው፤

እኔ ግን በአንገቱ ውበት እጫንበታሉ፤

በኤፍሬም ላይ እጥምድበታለሁ፤

ይሁዳም ያርሳል፤

ያዕቆብም አፍሩን ያለሰልሳል።

12

እግዚአብሔር መጥቶ ጽድቅን እስኪያዘንብላችሁ[161]

ደረስ እርሱን የምትሹበት ዘመን ነውና

ለእናንተ በጽድቅ ዝሩ፤

እንደ ምሕረቱም መጠን እጨዱ

ጥገታችሁንም እረሱ።

13

ክፋትንም አርሳችኋል፤

ኃጢአትንም አጭዳችኋል፤

የሐሰትንም ፍሬ በልታችኋል፤

በኃያላንህ ብዛት

በመንገድህም ላይ ታምነሃልና።[162]

14

በአሕዛብም ማከክል ሽብር ይነሣል፤

እናትም ከልጆችዋ ጋር በተፈጠፈጠች ጊዜ

ስልማን ቤትአርባኤልን በሰልፍ ቀን እንዳፈረሰ፤[163]

---

161 ይህ በሆሴዕ ዘመን ለእስራኤል ሕዝብ የተላከ መልእክት ነበር። በተጨማሪም ሆሴዕ ለእስራኤል የተናገረውን ቃል 'ለሰሙት' ለይሁዳ ሕዝብ የተላከ መልእክትም ነበር። ደግሞም ዛሬ ለሚኖሩ ሰዎችም የተሰጠ ቃል ነው። ጌታ የጽድቅን አዝመራ ይፈልጋል። ይህም ፍሬ እንዳናፈራ በልባችን ውስጥ ያለውን "ጠንካራ አፈር" መሰባበርን ይጠይቃል።

162 እስራኤል በእግዚአብሔር መታመን ሲገባው፤ ይልቁንም በራሱ ጥንካሬ ታምኖ ነበርና።

163 እዚህ ስለተጠቀሰው ጦርነት ምሁራን እርግጠኛ አይደሉም። ይሁን ምንም ችግር የለውም። ነገር ግን ያም ሆነ ይህ ጭካኔ የተሞላበት ጦርነት ነበር። እግዚአብሔር በቤቴል ስለ ተሠራው ኃጢአት በእስራኤልም ላይ ተመሳሳይ ነገር እንደሚሆን ይናገራል።

አምባዎችህ ሁሉ ይፈርሳሉ።

15

ከኃጢአታችሁም ክፋት የተነሣ

ቤቴል እንዲሁ ያደርግባችኋል፤

በነጋ ጊዜ የእሥራኤል ንጉሥ

ፈጽሞ ይጥፋል።

**ሆሴዕ 11፡1–11**

ይህ ምዕራፍ የእግዚአብሔርን "ልጅ" በሚመለከት በእግዚአብሔር ጠቃሚ መግለጫ ይጀምራል። ይህም መግለጫ በማቴዎስ 2፡15 ላይ በሐዋርያው ማቴዎስ የተጠቀሰ በመሆኑ ጠቃሚ ነው። ሰባኪው ወይም አስተማሪው ሆሴዕ 11፡1ን በጥንቃቄ መመርመር አስፈላጊ ነው ምክንያቱም ይህ ጥቅስ ሐዋርያት የነቢያትን ትምህርት እንዴት እንደተጠቀሙ ያሳያልና። ምእራፉ የሚያበቃው በሆሴዕ ከሚገኙት "አዎንታዊ ክፍሎች" በአንደኛው ነው። ደግሞም ይህ ክፍል በሆሴዕ ውስጥ ካሉት በጣም ውብ ግጥሞች መካከል ጥቂቶቹን ያካትታል።

ሆሴዕ 11:12 በተፈጥሮ በሆሴዕ 11 ላይ ካለው መልእክት ጋር ሳይሆን በሆሴዕ 12 ላይ ካለው መልእክት ጋር የተያያዘ ይመስላል። በዚህ ምክንያት ሆሴዕ 11፡12 በዚህ የሰባኪ መመሪያ ክፍል ውስጥ ተካቷል።

## ሆሴዕ 11፡1–11

**11፡1**

እሥራኤል ሕፃን በነበረ ጌዜ ወደድሁት

ልጄንም ከግብጽ ጠራሁት።[164]

**2**

አብዝቼ ብጠራቸው[165]

አጥብቀው ከፊቴ ራቁ፤

ለበኣሊምም ይሰው ነበር

ለተቀረጹ ምስሎችም ያጥኑ ነበር።

**3**

እኔም ኤፍሬምን ከንዱን ይዤ

በእግዝሩ እንዲሄድ መራሁት፤

እኔም እፈውሳቸው እንደ ነበርሁ አላወቁም።

---

[164] እስራኤል ሕዝብ በግብፅ በነበረበት ጊዜ እግዚአብሔር እስራኤልን “ልጄ” ብሎ ጠራት (ዘጸአት 4፡22 ይመልከቱ)። ስለዚህ እንደ እግዚአብሔር “ልጅ” እስራኤል የእግዚአብሔርን መልክና አምሳል ለቀሪው ዓለም ማንጸባረቅ ነበረባት (ዘፍጥረት 1፡26–28 ይመልከቱ)። ልክ እንደ አዳምም የመጀመሪያው “የእግዚአብሔር ልጅ” (ሉቃስ 3፡38 ይመልከቱ) በተግባሩ እንዳልተሳካለት እስራኤልም እንዲሁ በዚህ ተግባር ሳይሳካላት ቀርቶ ወድቃለች። ማቴዎስ 2፡15 የኢየሱስ መወለድ አስመልክቶ የሚናገረው ይህ ጥቅስ መፈጸሙ ይጠቁማል፡- “ይህም እግዚአብሔር በነቢዩ፡— ልጄን ከግብፅ ጠራሁት፡ የተባለው ይፈጸም ዘንድ ነው። (ማቴዎስ 2፡15 ይመልከቱ)። እርግጥ ነው ይህ የሆሴዕ ጥቅስ በመጀመሪያ እስራኤልን እንደሚያመለክት ማቴዎስ ያውቃል። ማለት ማቴዎስ የሆሴዕን የመጀመሪያ ትርጉም ተረድቶ ነበር ማለት ነው። ይሁን እንጂ ማቴዎስ ግን ይህን አንድ የተወሰነ ጥቅስ ብቻ እያሰበ አልነበረም። ስለ እግዚአብሔር ሕዝብ ከግብፅ መውጣታቸው የተነገረውን ሁሉ እያሰበ ነው። ከሆሴዕ 1፡10–2፡1 ወደ ግብፅ የመመለስ እና ከግብፅ የመውጣት ሃሳብ ታውጇል። ከዚህ ይልቅ ማቴዎስ አንባቢዎቹን እየጠራ ያለው ኢየሱስ እስራኤላውያን ያላከናወኑትን ነገር እንደሚፈጽም እንዲመለከቱ ነው። ከግብፅ የተጠራ እውነተኛው “የእግዚአብሔር ልጅ” ነውና። እንደ እውነተኛው “የእግዚአብሔር ልጅ”፣ ኢየሱስ አዳምና እስራኤል ያልፈጸሙትን ሁሉ ፈጽሟል አሁንም እያከናወነ ነው (በተጨማሪም በለዓም ስለ ክርስቶስ የተናገረውን ትንቢት በዘኁልቁ 24፡8 ያለውን ይመልከቱ)። ይህም ማቴዎስ በሆሴዕ 11፡1 ላይ ያለውን የሆሴዕን ቃል እንዳልሳተው ተጨማሪ ማረጋገጫ ነው።

[165] እግዚአብሔር ከእስራኤል ጋር የነበረው ግንኙነት ከግብፅ ሲጠራቸው ብቻ አልነበረም። ከዚያ ቀን ጀምሮ ሁልጊዜ ሲጠራቸው ነበር!

4

በሰው ገመድ

በፍቅርም እስራት ሳብኋቸው፤[166]

ለእነርሱም ቀንበርን ከጫንቃቸው ላይ እንደሚያነሣ ሆንሁ

ደርቆሽም ጣልሁላቸው።

5

ወደ እኔ ይመለሱ ዘንድ አልወደዱምና[167]

ወደ ግብጽ ምድር ይመለሳሉ[168]

አሦርም ንጉሣቸው ይሆናል።

6

ከመከሩትም ምክር የተነሣ

ሰይፍን በከተሞቻቸው ላይ ይወድቃል

ከበርቴዎችንም ያጠፋል።

7

ሕዝቤም ከእኔ ይመለሱ ዘንድ ወደዱ፤

ወደ ላይም ቢጠሩዋቸው

ማንም ከፍ ከፍ ያደርጋቸው ዘንድ አይችልም።[169]

8

ኤፍሬም ሆይ እንዴት እጥልሃለሁ?

እሥራኤል ሆይ እንዴጽ አሳልፌ እሰጥሃለሁ?

እንዴትስ እንደ አዳም እጥልሃለሁ?

---

166 እስራኤል በግብፅ ባሪያ ነበረች። እግዚአብሔር ግን እንደ ባሪያ አድርጎ አላያቸውም። ይልቁንም እርሱ እነርሱ የመራባቸው "መንገዶች" "የደግነት" ነበሩና።

167 ሃሳቡ እስራኤል ወደ ምርኮ ልትመለስ ነው የሚል ነው። በተመሳሳይ እግዚአብሔር በዘፀአት እስራኤልን ከግብፅ እንዳወጣቸው ሁሉ "ሁለተኛው መውጣት" ያስፈልጋል። ኢየሱስ በዚህ "በሁለተኛው ዘጸአት" ውስጥ ህዝቡን ከባርነት የሚያወጣ "አዲሱ ሙሴ" ነውና።

168 ሆሴዕ ግብጽን እና አሦርን በዚህ መጽሐፍ መጠቀሙን ቀጥሏል። እንደገና ሆሴዕ ፲፩:፲ ይመልከቱ።

169 እስራኤላውያን ዘወትር ለእግዚአብሔር ይሰው ነበር፤ ነገር ግን ስለእርሱ ይናግሩበት የነበረው የፍቅር ቃላት ሐሰት ነበረ። ይህ የውሸት ንስሐን የሚያመለክት ነው።

እንዴትስ እንደ ሲባዮ አደርግሃሉ?[170]

ልቤ በውስጤ ተናውጣለች

ምሕረቴም ተነሣሥታለች።[171]

9

እኔ አምላክ ነኝ እንጂ ሰው አይደለሁምና

በመካከልህም ቅዱስ ነኝና

የቁጣዬን መቅሰፍት አላደርግም

ኤፍሬምንም አጠፋ ዘንድ  አልመለስም፤

 በመዓትም አልመጣም።

10

እግዚአብሔርን ይከተላሉ

 እርሱም እንደ አንበሳ ያገሣል፤

ባገሣም ጊዜ

ልጆች እየተንቀጠቀጡ ከምዕራብ ይመጣሉ።[172]

11

እንደ ወፍም ከግብጽ

እንደ ርግብም ከአሦር ምድር እየተንቀጠቀጡ ይመጣሉ፤

በቤታቸውም አኖራቸዋለሁ ይላል እግዚአብሔር።[173]

---

170 አዳማ እና ሲባዮ ሰዶምና ገሞራ ሲጠፉ የወደሙ ትናንሽ ከተሞች ነበሩ (ዘፍጥረት 10፡19 እና ዘዳግም 29፡23 ይመልከቱ)።

171 ይህ አስገራሚ የንግግር ቃና ለውጥ ነው። በቁጥር 8-11 ላይ እግዚአብሔር ህዝቡን እንደሚያድን ቃል ገብቷል። ነቢያት ብዙ ጊዜ በወዮታ እና በማጽናናት ቃል መካከል አፈራርቀው ይናገራሉ።

172 በሆሴዕ 5 ላይ፣ እግዚአብሔር ራሱን እንደ አንበሳ መስሏል። በዚያም ህዝቡንም እንደ አንበሳ ሊቦጫጭቅ እንደሚችል ቃል ገብቷል። ደግሞም እንደ አንበሳ እንደሚያገሣ ሕዝቡንም ከግዞት እንደሚያወጣ ወደ ቤታቸውም እንደሚመልሳቸው ቃል ገብቷል። ምሳሌዎቹን እንደገና መጠቀም በመጽሐፉ ውስጥ ያሉትን የተለያዩ መልእክቶች ያገናኛል እና አንባቢው ለመልእክቱ የበለጠ ጥንቃቄ እንዲያደርግ ያደርጋል።

173 አሁንም እግዚአብሔር ሕዝቡን ከግብፅ (እና ከሌሎችም ቦታዎች) እንዳሰወጣ የሚገልጽ ማጣቀሻ አለን። ደግሞም ሁለተኛው ዘፀአት የሆሴዕ ዋና ጭብጥ ነው።

## ሆሴዕ 11፡12–13፡16

እንደገና ሆሴዕ 11:12 በተፈጥሮ በሆሴዕ 12 ላይ ካለው መልእክት ይልቅ በሆሴዕ 12 ላይ ካለው መልእክት ጋር የተያያዘ ይመስላል። በዚህ ምክንያት ሆሴዕ 11፡12 በዚህ የሰባኪ መመሪያ ክፍል ውስጥ ከሚቀጥለው ክፍል ጋር ተካቷል።

በሆሴዕ 11፡8–11 ካለው ውብ የተሃድሶ ግጥም በኋላ የሆሴዕ መጽሐፍ እንደገና ወደ መጪው የጥፋት መልእክቶች ተለውጧል። ዳግመኛም ከተስፋ መልእክት ወደ ጥፋት መልእክቶች መለወጥ በሁሉም ነቢያት ዘንድ የተለመደ ነገር ነው። በሆሴዕ 11፡12–13፡16 እግዚአብሔር ህዝቡን ታሪካቸውን ያስታውሳቸዋል። እሱ ታማኝ እንደነበረ እና እስራኤል እምነት እንዳጎደለች ያረጋግጣል። ምእራፉ የሚያበቃው በሚያሳዝን ትንቢት ነው፡- “ሰማርያ በአምላኳ ላይ ዐምፃለችና በደሏን ትሸከማለች። በሰይፍ ይወድቃሉ፤ ታናናሾቻቸው ይደቅቃሉ፤ እርጉዝ ሴቶቻቸውም ይቀደዳሉ።” እንደነዚህ ያሉት አስደንጋጭ ትንቢት ሕዝቡ ለሕይወታቸው እንዲፈሩና ወደ እግዚአብሔርም እንዲመለሱ ሊያደርጋቸው በተገባ ነበር። እንዲህ ዓይንቱ ትንቢቶች ዛሬም ቢሆን በሰዎች ላይ ተመሳሳይ ተጽእኖ ሊኖራቸው ይገባል።

## ሆሴዕ 12፡1–13፡16

**12፡1**

ኤፍሬም በሐሰት[174]

የእሥራኤል ቤት በተንኮል ከበበኝ፤

ይሁዳም ከታመነው

ቅዱሱ ከእግዚአብሔር ጋር አይጸናም።[175]

**2**

ኤፍሬም ነፋስን ይበላል፤

የምስራቅንም ነፋስ ይከተላል፤

ሁልጊዜም ሐሰትንና ተንኮልን ያበዛል፤

ከአሦር ጋር ቃል ኪዳን ያደርጋሉ፤[176]

ወደ ግብፅም ዘይት ይወስዳሉ።

**3**

እግዚአብሔርም ደግሞ ከዩሁዳ ጋር ክርክር አለው፤

ያዕቆብንም እንደ መንገዱ ይቀጣል፤

እንደ ስራውም ይመልስለታል።

**4**

በማኅፀን ውስጥ ወንድሙን በተረከዙ ያዘው፤[177]

በጎልማሳነቱም ጊዜ ከአምላኩ ጋር ታገለ፤

---

[174] የዚህ ምዕራፍ ቁጥር 1 በእንግሊዝኛው መጽሐፍ ቅዱስ በሆሴዕ 11 ውስጥ ቁጥር 12 ተደርጎ ተቀምጧል፤ ነገር ግን በትክክልም በተፈጥሮ ከሆሴዕ 12 ጋር የሚስማማ ስለሆነ በአማርኛ መጽሐፍ ቅዱስ ግን በሆሴዕ 12፡1 ላይ ተቀምጧል።

[175] አንዳንድ ጊዜ ይሁዳ አካሄዱን ከእግዚአብሔር ጋር ያደርግ ነበር። ለምሳሌ በሕዝቅያስ እና በኢዮስያስ የግዛት ዘመን ይሁዳ “በይፋ” ከኃጢአት ተጸጽቶ እንደገና ራሱን ለእግዚአብሔር ሰጥቶ ነበር። ሆሴዕ 12፡2 ይመልከቱ።

[176] በሆሴዕ መጽሐፍ ውስጥ አሦር እና ግብፅ አንድ ላይ ተጣምረዋል። በመጨረሻም አሦር እስራኤልን ድል አደረገ። በሆሴዕ የስብከት ዘመን ግን እስራኤላውያን ከአሦር ጋር ቃል ኪዳን ለመመሥረት እየሞከሩ ነበር።

[177] የእንግሊዝኛው ESV መጽሐፍ ቅዱስ ጽሑፍ ማስታወሻ እንደ ሚያመለክተው ከሆነ "ተረከዙን ይይዛል" የሚለው ያዕቆብ የስሙ ትርጉም ሊሆን ይችላል። ዘፍጥረት 25፡26 ን ይመልከቱ።

5

ከመላኩም ጋር ታግሎ አሸነፈ፤[178]

አልቅሶም ለመነው፤[179]

በቤተልም አገኘው፤

በዚያም ከእኛ ጋር ተነጋገረ።[180]

6

እርሱም የሠራዊት አምላክ እግዚአብሔር ነው፤[181]

የመታሰቢያው ስም እግዚአብሔር ነው።[182]

7

ስለዚህ ወደ አምላክህ ተመለስ፤[183]

ምሕረትንና ፍርድን ጠብቅ፤

ዘወትርም አምላካህን ታመን።[184]

8

ከከነዓን ወገን ነው በእጁ የተንኮል ሚዛን አለ፤

---

178 ዘፍጥረት 32፡22–32 ይመልከቱ።

179 በዘፍጥረት 32 ላይ ያለው የዚህ ክስተት ዘገባ ስለ ያዕቆብ ማልቀስ አይናገርም። ይሁን እንጂ ሆሴዕ ይህን ያለው የያዕቆብ አመለካከት ስለነበር ነው። እግዚአብሔርን ፈልጎ አይተወውም ነበር። እስራኤል ከያዕቆብ በጣም የተለየች ናት። እነሱ አያለቅሱም እና ወደ እግዚአብሔር አይመጡም። የእግዚአብሔርንም ምሕረት አይፈልጉም ነበር።

180 ዘፍጥረት 35፡1–15ን ይመልከቱ። እስራኤል ወደ ቤቴል በመጡ ጊዜ ያዕቆብ ለቤተሰቦቹ የተናገራቸውን ቃላት መከተል ነበረባቸው፡- “እንግዶችን አማልክት ከመካከላችሁ አስወግዱ፤ ንጹሐንም ሁኑ ልብሳችሁንም ለውጡ” (ዘፍጥረት 35፡2)። በዚያን ጊዜ ያዕቆብ ለቤተሰቡና ለአገልጋዮቹ ይናገር ነበር። ይሁን እንጂ ሆሴዕ “እግዚአብሔር በዚያ ከእኛ ጋር ተነጋገረ” ብሏል። ይህ በጣም ጠቃሚ ነገር ነው። ሆሴዕ እንዳለው እስራኤላውያን በዘፍጥረት ላይ የተጻፈውን ነገር መስማት ነበረባቸው ምክንያቱም እግዚአብሔር እየተናገራቸው ነበር! ዛሬም ተመሳሳይ ነው! እግዚአብሔር ለያዕቆብ የተናገረው ቃል ዛሬም ለክርስቲያኖች የሚናገረው ቃል ነው ምክንያቱም እኛ ደግሞ የአብርሃም ልጆች ነንና (ገላትያ 3፡7–9፣ 14 እና 29 ይመልከቱ)።

181 “የሠራዊት አምላክ” የሚለው የእግዚአብሔር ስም ነው። እግዚአብሔር የሰማይ ሠራዊት አምላክ ነው ማለት ነው።

182 ዘፀአት 3፡13–15 ይመልከቱ። እንደዚሁም እግዚአብሔር የተናገርው ቃል በዘፀአት 6፡2–8 ይመልከቱ።

183 ንስሐ የሚገቡት እግዚአብሔር ሕዝቡን ስለሚረዳ ነው። ከእርሱ ጋር በመታዘዝ እንድንሄድ ጸጋን ይሰጠናልና።

184 እስራኤላውያን እግዚአብሔርን እንዲጠሩና ወደ እርሱም እንዲመለሱ ለማድረግ፤ ሆሴዕ በቤቴል ያለውን የያዕቆብን ታሪክ ተጠቅሟል (ዘፍጥረት 28 ይመልከቱ)።

ሸንገላም ይወድዳል።

9

ኤፍሬምም ባለ ጠጋ ሆኜአለሁ፤

ሀብትንም አግኝቻለሁ፤[185]

በድካሜም ሁሉ ኃጢአት የሚሆን በደል አይገኝብኝም አለ።

10

እኔም ከግብፅ ጀምሬ

አምላክህ እግዚአብሔር ነኝ፤[186]

እንደ ዓመት በዓል ቀን እንደ ገና[187]

በድንኳን እንድትኖር አደርግሃለሁ።

11

ለነቢያት ተናግሬአለሁ፤

ራእይንም አብዝቻለሁ፤

በነቢያትም እጅ ምሳሌዎችን አውጥቻለሁ።[188]

12

ኃጢአት በገለዓድ አለ፤

ፈጽመው ከንቱ ናቸው፤

ወይፈኖች በጌልገላ ይሠዋሉ፤

መሠውያዎቻቸውም በእርሻ ትልም

ላይ የድንጋይ ክምር ይሆናሉ።

13

ያዕቆብ ወደ ሶሪያ አገር ሸሸ፤

---

185 በሎዶቅያ ላለች ቤተ ክርስቲያን የተላከውን መልእክት በራእይ 3፡14–22 ይመልከቱ። በተጨማሪም ራእይ 18፡7 ይመልከቱ።

186 ዘፍጥረት 32፡22–32 ይመልከቱ። ሆሴዕ ከሙሴ መጽሐፍ (ከዘፍጥረት እስከ ዘዳግም) ደጋግሞ ይጠቅሳል። የሙሴን ጽሑፎች በጥልቀት እያሰበ እንደነበር ግልጽ ነው።

187 አሁንም እግዚአብሔር የግብፅን ሕዝብ እያሳሰበ ነው። ወደዚያ ቦታ እንደሚመልሳቸው ነገራቸው። ይህን የሚያደርገው እነርሱን ለማዳን እና በእውነት እርሱን ማምለክ እንዲጀምሩ ለማድረግ ነው።

188 ዘዳግም 18 ይመልከቱ።

እሥራኤልም ስለ ሚስት አገለገለ፤
ስለ ሚስትም በግ ጠባቂ ነበር።[189]
14
እግዚአብሔርም በነቢይ እጅ እሥራኤልን ከግብጽ አወጣው፤
በነቢይም እጅ ጠበቀው።[190]
15
ኤፍሬም አስመርሮ አስቆጣው፤
ስለዚህ ደሙ በላዩ ላይ ነው
ጌታውም ስድቡን በራሱ ይመልሳል።
13፡1
ኤፍሬም በተናገረ ጊዜ ፍርሃት ነበረ፤
በእስራኤልም ዘንድ ታበየ፤[191]
ነገር ግን በኣልን በማምለክ በበደለ ጊዜ ሞተ።[192]
2
አሁንም ኃጢአትን ይሠሩ ዘንድ ጨመሩ፤
በብራቸውም ለራሳቸው ቀልጦ የተሠራ ምስልን
እንደ ጥበባቸውም ጣዖታትን ሠርተዋል፤
ሁሉም የሠራተኛ ሥራ ናቸው።

---

189 ሆሴዕ ለእስራኤላውያን ያለፈውን ታሪክ እያስታወሳቸው ነው። ያዕቆብ ከተስፋይቱ ምድር ውጭ በኖረበት ጊዜ የነበረውን ታሪክ እንዲያስታውሱ ይፈልጋል። ይህንም የሚያደርገው ለሰዎች እግዚአብብሔር ለእነርሱ ያለውን እንክብካቤ እንዲያስታውሳቸው ስለሚፈልግ ይመስላል።

190 ሙሴ የሚለው ስም እዚህ ጥቅም ላይ እንዳልዋለ ልብ ይሏል። ይልቁንም ይህ ጥቅስ የሚያጎላው እግዚአብሔር እስራኤልን ከግብፅ ለማስወጣት **ነቢይ** እንደ ተጠቀመና እና የጠበቃቸውም **በነቢይ** መሆኑን ነው። እነዚህ ጥቅሶች ትኩረትን ወደ ነቢያት አገልግሎት ይስባሉ። በእርግጥ ነቢያት በጥንት ዘመን ለእስራኤል በረከት ነበሩ። እግዚአብሔር አሁንም ነቢያትን እየሰጣቸው ነው። ሆሴዕም ነቢይ ነውና። ስለዚህ ሆሴዕን ሊሰሙ ይገባቸዋል።

191 ይህ የእስራኤል "ጥንካሬ" በኃጢአት ከመውደቋ በፊት የነበረ ምስክርነት ነው። እንደ ጠቢብ ሰው ቃል በአንድ ወቅት የእስራኤል ቃል በጣም ክብደት የነበርው ነበር። ነገር ግን በጣዖት አምልኮ ምክንያት ይህ ዘላቂ አልሆነም።

192 የበኣል አምልኮ ኤፍሬምን (እስራኤልን) "ገደለው"። የእግዚአብሔር ሕይወት በምድሪቱ ላይ አልታየም።ሮሜ 6፡23 ይመልከቱ።

ስለ እነርሱም የሚሠው ሰዎች እምቦሳውን ይሳሙ ይላሉ። [193]

3

ስለዚህ እንደ ማለዳ ደምና

በጠዋትም እንደሚያልፍ ጠል፤[194]

በዓውሎ ነፋስም ከአውድማ እንደሚበትን እብቅ፤

ከምስኮትም እንደሚወጣ ጢስ ይሆናሉ።

4

እኔ ግን ከግብፅ ምድር ጀምሬ[195]

አምላክህ እግዚአብሔር ነኝ፤

ከእኔም በቀር ሌላ አምላክ አታውቅም፤

ከእኔም በቀር ሌላ መድኃኒት የለም።[196]

5

በምድረ በዳ

እጅግ በደረቀ ምድር አውቄህ ነበር።[197]

6

ከተሰማሩ በኋላ ጠገቡ፤

---

[193] ይህ የእስራኤላውያንን የአምልኮ ልማዶች የሚያመለክት ነው። ልጆቻቸውን እየገደሉ ግን እንስሳትን ያመልኩ ነበር! የሐሰት አምልኮ ሁሌም እንደዚህ ነው የሚያደርገው። ሰዎችን ከሰብአዊነት በማዋረድ በተሳሳተ መንገድ የተቀረውን ፍጥረታት ከፍ ያደርጋል።

[194] "ጤዛ" በዚህ ጥቅስ ላይ አሉታዊ በሆነ መልኩ ጥቅም ላይ ውሏል። በማለዳ ሙቀት ጠል ተሎ እንደሚጠፋ በጣዖት አምልኮ ምክንያት እስራኤልም በፍጥነት ትጠፋለች ነው የሚለው። በሆሴዕ 14፡5 ላይ  ደግሞ "ጤዛ" የሚለው ቃል በተለየ መንገድ ጥቅም ላይ ውሏል። በዚያም እግዚአብሔር ለሕዝቡ እንደ "ጠል" እንደሚሆን ይናገራል። ይህም እግዚአብሔር ለህዝቡ የማያቋርጥ የእረፍት ምንጭ ይሆናል የሚለው ቅኔያዊ አነጋገር ነው።

[195] እግዚአብሔር እስራኤላውያንን ስለግብፅ ምድር ምን ያህል ጊዜ እንዳሳሰባቸው ይመልከቱ። ያለፈውን ታሪክ እንዲያስታውሱ ይፈልጋል። በግብፅ ባሪያዎች ከነበሩበት ጊዜ አንስቶ እግዚአብሔር ታማኝ አምላካቸው ነው። አንባቢው ወደ "ግብፅ" ስለመመለስ እና የሁለተኛ ጊዜ ስደት በተመለከተ እየተዘጋጀ ነው።

[196] ከእግዚአብሔር በቀር አዳኝ የለም። ይህ አሁንም እውነት ነው። ደግሞም ኢሳይያስ 43፡11 ይመልከቱ።

[197] በቁጥር 4 ላይ እግዚአብሔር እስራኤላውያንን በግብፅም አምላካቸው እንደ ነበር አሳስቧቸዋል። ደግሞም በዚህ ጥቅስ ውስጥ በምድረ በዳ እንደመራቸው አስታውሷቸዋል። ስህተት የሆነውን ነገር እንዲያስታውሱ ወደ መጀመሪያ ዘመናቸው እየመለሳቸው ነው።

በጠገቡም ጊዜ ልባቸው ታበየ፤[198]

ስለዚህ ረሱኝ።[199]

7

ስለዚህም እኔ እንደ አንበሳ ሆንሁባቸው፤[200]

እንደ ነብርም በመንገድ አጠገብ አደባባቸዋለሁ፤

8

ልጅዋ እንደ ተነጠቀባት ድብ እገጥማቸዋለሁ፤

የልባቸውንም ስድብ እቀድዳለሁ፤

በዚያም እንደ አንበሳ እበላቸዋለሁ፤

የምድረ ብዳም አውሬ ይነጥቃቸዋል።

9

እሥራኤል ሆይ

ሆሴዕ 12፡1–13፡16

በእኔ በረዳትህ ላይ በመነሳትህ ጥፋትህ ነው።

10

በየከተማህ ሁሉ ያድንህ ዘንድ ንጉሥህ ወዴት አለ?

ስለ እርሱም ንጉሥንና አልቆችን ስጠኝ[201]

ብለህ የተናገርኸው መሳፍንቶችህ ወዴት አሉ?

---

198 በዚህ ክፍል የተጻፈው በዘዳግም 32፡15 ላይ ያለውን የሙሴን ቃል ለእስራኤላውያን ለማስታወስ የታሰበ ነው። ሙሴ እንደተነበየው እስራኤላውያን ኩሩ ሆነዋል እናም በእውነት እግዚአብሔርን አያመልኩም።

199 ነህምያ 9፡25–26 ይመልከቱ።

200 በሆሴዕ ውስጥ እግዚአብሔር ራሱን እንደ አንበሳ ሦስት ጊዜ ገልጿል። የመጀመሪያው በሆሴዕ 5፡14 ላይ ነው። በዚያ ጥቅስ ውስጥ "እንደ አንበሳ"፣ "በመቅደድ እንደ ሂድ" ይናግራል። በእነዚህ ጥቅሶች ውስጥ፣ እግዚአብሔር እስራኤልን "እንደ አንበሳ" እንደሚበላት ቃል ገብቷል። ሆኖም ግን በሆሴዕ 11፡10 ላይ ያህዌ አንበሳ የሚለውን ቃል በአዎንታዊ መልኩ ተጠቅሞበታል። ገጣሚዎች በተደጋጋሚ ቃላትን በተለያየ መንገድ ይጠቀማሉና።መልእክታቸውን በብርቱ ከሚያቀርቡበት እና የትንቢት መጽሐፍን ከሚያገናኙባቸው መንገዶች አንዱ ነው። በተጨማሪም "ጤዛ" የሚለው ቃል በሆሴዕ 13፡3 በአሉታዊ እና በሆሴዕ 14፡5 ላይ በአዎንታዊ መልኩ እንዴት ጥቅም ላይ እንደዋለ ተመልከት።

201 በዚህ ጥቅስ ውስጥ፣ ያህዌ የእስራኤላውያንን ጥያቄዎች ይጠይቃል። ቀደም ሲል የሞከሩትን ያልተሳኩ ነገሮችን ይጠቅሳል።

11

በቁጣዬ ንጉሥን ሰጠሁህ፤

በመዓቴም ሻርሁት።

12

የኤፍሬም በደል ታስሮአል፤

ኃጢአቱም ተከማችቶአል።

13

ምጥ እንደ ያዛት ሴት ጭንቅ ይመጣበታል፤

በሚወለድበት ጊዜ በማኅፀን አፍ

ቀጥ ብሎ አይወጣምና[202]

አዕምሮ የሌለው ልጅ ነው።

14

ከሲኦል እጅ እታደጋችኋለሁ፤

ከሞትም እቤዣችኋልሁ፤[203]

---

[202] ታዛዥ ያልሆነው እስራኤል ዘጠኙ ወር ቢጠናቀቅም ለመወለድ ፈቃደኛ ካልሆነ ከሞኝ ሕፃን ጋር ተመሳሰሏል! እግዚአብሔር ለእስራኤላውያን ያሰበው ሕይወት በእስራኤል ውድቅ ተደረገ። እንደ ሞኝ ሕፃን እግዚአብሔር ለእነርሱ ወደ ነበረው ሕይወት ለመወለድ ፈቃደኞች አልሆኑም! በዚህም ዘመን ይህ በማይታዘዙ ሰዎች ላይ እውነት ነው!

[203] ከ 2016 የእንግሊዝኛው ESV እትም የተወሰደው ቃል እንዲህ ይላል፡- "ከሲኦል ኃይል **እቤዣቸዋለሁ**። ከሞት **እቤዣቸዋለሁ**።" ነገር ግን በ 2016 የጽሑፍ እትም ውስጥ ያለው የቃላት አወጣጥ የማይመስል ይመስላል (NIV (በአዲሱ መደበኛ ትርጉም) 2011 እና CSB በተመሳሳይ ቃል ተጽፈዋል)። በአጠቃላይ በሆሴዕ 13 ላይ ካለው አሉታዊ አውድ እና በሆሴዕ 13፡14 መጨረሻ ("ርኅራኄ ከዓይኖቼ ተሰውሯል") የሚለው በ2011 የ ESV  እትም ላይ ያለው ቃል የበለጠ ዕድል ያለው ይመስላል (በተጨማሪም NASB፣ NET፣ NLT ደግሞ ይመለከቱ)። የ2011 የESV የጽሑፍ እትም እግዚአብሔርን ራሱን ጥያቄ እንደጠየቀ አድርጎ ያቀርባል፡- "ከሲኦል ኃይል **ልቤዣቸውን**? ከሞት **እቤዣቸዋለሁን**? እስቲ ልብ በለው "እኔ አደርጋለሁ..."(2016 እትም) እና "እኔ ..." (2011  እትም) መካከል ያለውን ልዩነት ያስተውሉ። የ2011 የ ESV እትም ጽሑፍ ትክክል ከሆነ እግዚአብሔር በእነዚህ ጥቅሶች ውስጥ እስራኤልን ለማዳን **ቃል** እየገባ አይደለም። ይልቁንም ራሱን አንድ **ጥያቄ** እየጠየቀ ነው። እስራኤልን ከሞትና ከሲኦል ማዳን እንዳለበት ራሱን እየጠየቀ ደግሞም መልሱ "አይሆንም" የሚል ነው። ከዚህ ይልቅ "መቅሰፍቶቹን" በእስራኤል ላይ እንዲያመጣ፣ "ሞትን" እስራኤልንም 'እንዲወጋ' "ሲያልን"  ጠርቷል። እግዚአብሔር እስራኤልን እንዲያጠፉ "ሞትን" እና "ሲኦልን" ጠርቷል፤ ምክንያቱም በራሱ አነጋገር "ርኅራኄ ከዓይኔ ተሰውሯል" ይላላና። እግዚአብሔር ለእስራኤል የነበረው ትዕግስት አልቆ ነበር ማለት ነው። እስራኤል በጣዖት አምልኮቷ ምክንያት ተቀጣለች።

ጳውሎስ ይህንን በአዲስ ኪዳን በ 1 **ቆሮንቶስ 15፡54–55** ባለው ላይ ይህን ጥቅስ ጠቅሶታል። ይህንን ጥቅስ **ከኢሳይያስ 25፡ 8** ጋር በማጣመር ተጠቅሞበታል። እነዚህን ሁለቱን የብሉይ ኪዳን ክፍሎች አጣምሮ ክርስቲያኖች አዲስ ሥጋዊ አካል ስለሚያገኙበት ቀን ሲናገር፡- "ይህ ይሚበሰብሰው የማይበሰብሰውን ሊለብስ ይህም የሚሞተውም የማይሞተውን ሲለብስ ይገባዋል፤ በዚያን ጊዜ "ሞት ድል በመነሳት ተዋጠ" ተብሎ ይተጻፈው ቃል ይፈጸማል። "ሞት ሆይ መውጊያህ የት አለ?

ሞት ሆይ ቸነፍርህ ወዴት አለ?

ሲኦል ሆይ ማጥፋትህ ወዴት አለ?

ርኅራኄ ከዓይኔ ተሰወረች።[204]

15

በወንድሞቹ መካከል ፍሬያማ ቢሆን፤

የምሥራቅ ነፋስ ይመጣል፤

ሆሴዕ 12፡1–13፡16

የእግዚአብሔር ነፋስ ከምድረ በዳ ይመጣል፤

ምንጩንም ያደርቃል፤

ፈሳሹንም ያጠፋል፤

የተከበሩ ዕቃዎች ሁሉ

ያሉበትን መዝገብ ይበዘብዛል።

16

ሰማሪያ በአምላክዋ ላይ ዐምፃለችና

በደልዋን ትሸከማለች፤

በሰይፍ ይወድቃሉ

ሕፃኖቻቸውም ይፈጠፈጣሉ፤

እርጉዞቻቸውም ይቀደዳሉ።[205]

---

ሲኦል ሆይ ድል መንሳትህ የት አለ?"ጳውሎስ ሆሴዕን እንዴት እንደጠቀሰ ተመልከት። ይህ ቁጥር በሆሴዕ ጥቅም ላይ በዋለበት መንገድ በሚያስደንቅ ሁኔታ ጳውሎስ እዚህ ሞት ላይ ተሳለቀበት! ጳውሎስ ሞትን ኃይሉ የት እንደደረሰ በስላቅ ሲጠየቅ እናያለን። ሞት በክርስቲያን ላይ ምንም ስልጣን እንደሌለው ጳውሎስ ያውቃል! በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ሞት እና ትንሳኤ ምክንያት የሞት "መውጊያ" (በሆሴዕ "የሲኦል መውጊያ" ተብሎ የሚጠራው) ተሸሯልና። የጳውሎስ ኢሳይያስ 25:8 እና ሆሴዕ 13፡14 በጥምረት መጠቀም ሞት በክርስቶስ ላሉት ድል እንደሌለው ያሳያል። ለማጠቃለል ያህል በሆሴዕ 13፡14 ላይ እግዚአብሔር እስራኤልን ከሞት ያድናቸው እንደሆነ እየጠየቀ ነው መልሱ አይደለም ነው። በሌላ በኩል ደግሞ በ1 ቆሮንቶስ 15 ላይ ጳውሎስ ሞት በክርስቲያን ላይ ምንም ስልጣን ስለሌለው እያቀለደበት ነው።

[204] በሆሴዕ 1፡6 ላይ፣ እግዚአብሔር "የእስራኤል ቤት ከእንግዲህ ወዲህ አልምርም" አለ። እዚህ ጋ ደግሞ እግዚአብሔር አይራራላቸውም ይላል። እስራኤል እንደ ሕዝብ "የኃጢአታቸውን ደመወዝ" ይቀበላሉ ማለት ነው (ሮሜ 6፡23 ይመልከቱ)። ሆሴዕ ከተናገረ ብዙም ሳይቆይ እስራኤል በአሦራውያን ቁጥጥር ሥር ገባች።

[205] ይህ በጥንት ጊዜ ከተሞች በተወረሩበት ወቅት በሕዝቡ ላይ ምን እንደደረሰ የሚገልጽ በጣም አስፈሪ ስዕላዊ መግለጫ ነው። እዚህ ያሉት ሥዕላዊ መግለጫዎች የታሰቡት የእስራኤልን ሕዝብ ንስሐ እንዲገቡ ለማድረግ ነው። ነብያት አስደንጋጭ ቃላትን ይጠቀማሉ ምክንያቱም ህዝቡ "የተለመደ" ንግግርን አይሰሙም ነበርና።

## ሆሴዕ 14

የሆሴዕ የመጨረሻ ምዕራፍ የሚጀምረው እና የሚያበቃው ሕዝቡ የዚህን መጽሐፍ መልእክት እየሰሙ ስለነበር መመሪያ በመስጠት ነው። በሆሴዕ 14፡1–3 ላይ ሰዎቹ እንዴት ንስሃ መግባት እንዳለባቸው ተነግሯቸዋል። ሌላው ቀርቶ እግዚአብሔር በሚያድሳቸውም ጊዜ ሊያቀርቡት የሚገባውን የመሥዋዕት ዓይነት ይነገራቸዋል። በሆሴዕ 14፡9 ላይ “ጥበበኞች” እና “አስተዋይ” ለሆኑት ይህንን መጽሐፍ “እንዲረዱት” እና “እንዲያውቁት” ጥሪ ቀርቧል። አንድምታው አንድ ሰው ለዚህ መጽሐፍ "በማስተዋል" እና "በእውቀት" ምላሽ ካልሰጠ ያ ሰው ጥበበኛ ወይም አስተዋይ አይደለም ማለት ነው። ስለዚህ እሱ ወይም እሷ ሞኝ ናቸው። ይህ በሆሴዕ ዘመን እውነት ነበር። ዛሬም ደግሞ እውነት ነው። የአንድ ሰው ጥበብ (ወይም የጥበብ እጦት) አንድ ሰው ለዚህ መጽሐፍ እንዴት ምላሽ እንደሚሰጥ በማየት ይረጋገጣል።

በምዕራፉ መጀመሪያ እና መጨረሻ ላይ ለእግዚአብሔር ሰዎች በተሰጠው መመሪያ መካከል እግዚአብሔር በድጋሚ ልቡን ለህዝቡ ያፈሰሰበት የሚያምር ግጥም አለ። እንዴት እንደሚፈውሳቸውና እንዲበለጽጉ እንደሚያደርጋቸው ቃል ገብቷል። ስለ ንጉሡ ዘመንና በንጉሡ አገዛዝ ሥር ስለሚኖሩት ሰዎች አስደሳች ሕይወት ተናግሯል። እነዚህ ተስፋዎች በክርስቶስ ተፈጽመዋል (እና እየተፈጸሙም ናቸው)። አንድ ሰው እነዚህን ተስፋዎች መቀበል ወይም አለመቀበሉ ሙሉ በሙሉ የሚታወቀው አንድ ሰው "ጥበበኛ" እና "አስተዋይ" በመሆኑ ላይ ነው። ለዚህ መጽሐፍ መልእክት (እና ለመላው መጽሐፍ ቅዱስ) ምላሽ የሚሰጡ እና በእምነት ወደ ክርስቶስ የሚመጡት “ጥበበኞች” እና “አስተዋዮች” ብቻ ናቸውና።

## ሆሴዕ 14

**14፥1**

እሥራኤል ሆይ በኃጢአትህ ወድቀሃልና

ወደ አምላክህ ወደ እግዚአብሔር ተመለስ።[206]

**2**

ከእናንተ ጋር ቃል ውሰዱ፤[207]

ወደ እግዚአብሔርም ተመልሳችሁ ኃጢአትን ሁሉ አስወግድ፤

በቸርነትም ተቀበለን፤

በወይፈንም ፈንታ የከንፈራችንን ፍሬ እንሰጣለን።[208]

---

[206] በዚህ ቁጥር ውስጥ “መመለስ” ተብሎ የተተረጎመው የዕብራይስጥ ቃል በሆሴዕ በሙሉ ጥቅም ላይ ውሏል (ለምሳሌ 3፡5፣ 6፡1፣ 11፡5፣ 12፡6፣ 12፡9፣ 14፡7 ይመልከቱ)። በተለይም በዘዳግም 30፡1–10 ውስጥ በሁለተኛው ዘፀአት የእስራኤልን መመለስ በሚገልጽ ምዕራፍ ውስጥ ሰባት ጊዜ ጥቅም ላይ ውሏል። በሆሴዕ እና በዘዳግም መካከል ብዙ ግንኙነቶች አሉ።

[207] እስራኤል ለእግዚአብሔር የሚሠውት ወይፈንና ፍየሎችን ደጋግመው ያመጡ ነበር (ሆሴዕ 6፡6 ይመልከቱ)። እዚህ ጋ ደግሞ ሆሴዕ ለሕዝቡ እውነተኛ ቃል ወደ እግዚአብሔር ይዞ ማምጣት እንዳለባቸው ይነግራቸዋል።

[208] በመጀምሪያ እይታ “ በወይፈን ፈንታ የከንፈራችንን ፍሬ እንሰጣለን” በማለት ከተሀድሶ በኋላ የወይፈኖችን መሥዋዕት እንደሚያቀርቡ ሆሴዕ ለሕዝቡ ለእግዚአብሔር ቃል እንዲገቡ  እየነገራቸው ያለ ይመስላል፤ የእንግሊዝኛው ESV ትርጉም በዕብራይስጥ ጽሑፍ (MT ወይም የማሶሬቲክ ጽሑፍ) ላይ የተመሠረተ ነው። ሆኖም፣ አብዛኞቹ ዘመናዊ የእንግሊዝኛ ትርጉሞች በዚህ ጥቅስ ውስጥ የዕብራይስጥን ቋንቋን አያንጸባርቁም። ይልቁንም "የከንፈራችንን ፍሬ እንሰጣለን" የሚለውን የግሪክን (LXX) ያንፀባርቃሉ። ለምሳሌ፣ በአዲሱ መደበና ትርጉም (NIV) “የከንፈራችንን ፍሬ እንድናቀርብ” ይላል። ሌሎች ትርጉሞች የከንፈሮችን ፍሬ እንደ ምስጋና በመረዳት ይህን አንድ እርምጃ ወደፊት ወስደውታል። ስለዚህ CSB "ከከንፈራችን ውዳሴ እንመልስልህ ዘንድ" ይላል። በNLT “ውዳሴያችንን እናቀርብልሃለን” በሚል ይነበባል።

በእንግሊዝኛው ESV የነዚህ ቃላት ትርጉም ሰዎች በሁለተኛው ዘጸአት ላይ ስለተቀበሉት ፀጋ ወይፈኖችን በመስዋዕት እያቀረቡ ነው። በግሪክ (LXX) ላይ በተመሠረቱት ትርጉሞች ውስጥ ደግሞ ሰዎች ለእግዚአብሔር ምስጋና በማቅረብ ለተሰጣቸው ጸጋ ምላሽ እየሰጡ ነው። ከእነዚህ ንባቦች ውስጥ የትኛው ትክክል ሊሆን ይችላል? በብዙ ምክንያቶች፣ በግሪክ (LXX) ላይ የተመሠረቱ ትርጉሞች ተመራጭ ይመስላሉ። በመጀመሪያ የግሪኩ ንባብ በቁጥር ሁለት መጀመሪያ ላይ ከሚገኙት ቃላት ጋር ይስማማል። በጥቅሱ መጀመሪያ ላይ ቃላትን ወደ እግዚአብሔር ማምጣት ይናገራል። የጥቅሱ መጨረሻ ላይ ለወጥ ደግሞ ወይፈኖችን ወደ እግዚአብሔር ስለመማጣት የሚናገር ይመስላል። በሁለተኛ ደረጃ የግሪክኛው ጽሑፍ ወጥነት እንዲኖረው ለማድረግ ተጨማሪ ቃላትን አይፈልግም ነገር ግን ዕብራይስጥ በጽሑፍ ግራ የሚያጋባ ነው፤ ደግሞም ተጨማሪ ቃላትን ይፈልጋል። ይህ በESV (እና NET) ውስጥ ተንጸባርቋል። በሦስተኛ ደረጃ በግሪኩ ውስጥ ያለው ንባብ ሆሴዕ በመጽሐፉ ውስጥ ካቀረበው መከራከሪያ ጋር በተሻለ ሁኔታ ይስማማል። እግዚአብሔር የህዝቡን ልብ እንጂ የበሬ መስዋዕትን አይፈልግም (ለምሳሌ ሆሴዕ 6፡6 ይመልከቱ)። ደግሞም በግሪኩ ያለው ንባብ እንዲሁ ከሆሴዕ ውጭ ካሉ የብሉይ ኪዳን ምንባቦች ጋር ይስማማል (ለምሳሌ መዝሙረ ዳዊት 51፡14–17 ይመልከቱ)። በመጨረሻም በግሪኩ ውስጥ ያለው ንባብ ከወንጌል መልዕክት ጋር ይስማማል። እግዚአብሔር ራሱ በከፈለው የደም መሥዋዕት ማለትም በኢየሱስ አማካኝነት አዳነን። ስለዚህ እንደዚህ ዓይነቱ ተጨማሪ መስዋዕትነት አያስፈልግም። አሁን ልናደርገው የሚገባው ምስጋና ለእግዚአብሔር ማቅረብ ነው።ሌላው ሊታሰብበት የሚገባው ነጥብ ይህ ጥቅስ በአዲስ ኪዳን ውስጥ እንዴት ጥቅም ላይ እንደዋለ ነው። ዕብራውያን 13፡15 ወደ ከሆሴዕ 14፡2 ያጣቅሳል። በተለይም በዕብራውያን ውስጥ ያለው ንባብ የዚህን ቁጥር

3

አሦር አያድነንም፤

በፈርስ ላይ አንቀመጥም፤

ድሀ አደጉም በአነተ ዘንድ ምሕረትን ያገኛልና[209]

ከእንግዲህ ወዲህ ለእጆቻችን ሥራ

አምላኮቻችን ናችሁ አንላቸውም።

4

ቁጣዬ ከእርሱ ዘንድ ተመልሶአልና

ዓመፃቸውን እፈውሳለሁ፤[210]

በገዛ ፈቃዴም እወዳቸዋለሁ።

5

ለእሥራኤልም እንደ ጠል እሆነዋለሁ፤[211]

---

የግሪክ (LXX) ትርጉም ያንጸባርቃል፡ "እንግዲህ ዘወትር ለእግዚአብሔር የምስጋናን መሥዋዕት፥ ማለት ለስሙ የሚመሰክሩ **የከንፈሮችን ፍሬ**፥ በእርሱ እናቅርብለት።" ይህ የዕብራውያን ጸሐፊ ሆሴዕ 14፡2 በክርስቶስ ባደረገው ይቅርታ ላይ ተመርኩዞ እግዚአብሔርን ስለ ማመስገን መናገሩን እንደተረዳ የሚያሳይ ማስረጃ ነው።

209 በቁጥር 2 እና 3 ላይ ሆሴዕ ሰዎች ምን ማለት እንዳለባቸው ነግሯቸዋል። ሆሴዕ ሕዝቡ በአሦር ላይ ካላቸው እምነትና ("የእጃችን ሥራ") ከሚሉዋቸው ከሠሩዋቸው አማልክቶች ፍቅር መመለስ እንዳለባቸው ነገራቸው። በክርስቶስ በኩል ወደ እግዚአብሔር ለሚመጡ ሰዎች ሁሉ እንዲህ ያሉ ቃላት ሊነገራቸው ይገባል።

210 ከሁለተኛው ዘጸአት በኋላ የእስራኤል "ክህደት" (ማለትም፣ እስራኤል ከእግዚአብሔር ወደ ሐሰተኛ አማልክት መመለሷ) በያህዌ ሙሉ በሙሉ ይቀየራል። ይህም ማለት የእግዚአብሔር ህዝብ ከዚህ ኃጢአት እግዚአብሔር ስለሚፈውሳቸው ሌሎች አማልክትን ለማምለክ አይመርጡም (ሕዝቅኤል 36፡25 ይመልከቱ)። ይህ የሆነው በክርስቶስ ሥራ እና በእነርሱ በሚያድረው መንፈስ ቅዱስ አማካኝነት ነው (2ኛ ቆሮንቶስ 5፡17-21 ይመልከቱ)።

211 በሆሴዕ 14:5–7 ውስጥ የሚገኘውን የእግዚአብሔር ቃል በትኩረት ይከታተላሉ። ይህ የሆሴዕ መጽሐፍ መጨረሻ እየተቃረበ ነው፣ ስለዚህ እነዚህ የመጨረሻ ጥቅሶች የሚያተኩሩት እግዚአብሔር በክርስቶስ በኩል ለሕዝቡ በሚያመጣው ተሃድሶ ላይ መሆኑ ምክንያታዊ ነው። በቁጥር አምስት ላይ እግዚአብሔር "ለእስራኤል እንደ ጠል" እንደሚሆን ተናግሯል። ይህ በጣም ጥሩው ግጥም ነው፤ ስለ ምግብ፣ እረፍት፣ ሕይወት፣ ጉልበት፣ እርዳታ እና እንክብካቤ ይናገራል። ይህ የግጥም መስመር በመዝሙር 1 ላይ ያለውን የፍሬያማ ዛፍ ምሳሌ ወደ አእምሮ ያመጣል። ነገር ግን እግዚአብሔር ጉዳዩን በራሱ ላይ ከምድረግ ይልቅ ወደ ሌላ ሰው ይቀይረዋል። ይህንን ሰው ደግሞ በአምስት የተለያዩ መንገዶች ይገልፀዋል፡- "**እንደ አበባ** ያብባል"፣ "እንደ ሊባኖስ ዛፎች ሥር ይሰድዳል"፣ "**ቅርንጫፎችም** ይዘረጋል"፣ "**ውበቱ** እንደ ወይራ" እና "**መዓዛው** እንደ ሊባኖስ ነው"። ታዲያ ይህ ሰው ማን ነው? እንደነዚህ ያሉት ቃላት በነቢያትና በጽሑፎች ውስጥ በሌሎች ቦታዎች ጥቅም ላይ ከዋሉበት መንገድ በመነሳት እነዚህ የክርስቶስን ዝና፣ ክብር እና ፍሬያማነት የሚያመለክቱ መሆናቸው እርግጠኛ ነው! በተለይም፣ እግዚአብሔር ስለ ክርስቶስ እና ስለ ዝናው እና ፍሬያማነቱ ከአምስቱ ማጣቀሻዎች በኋላ፣ ስለ አንድ የሰዎች ስብስብ ሲናገር፡- "**ይመለሳሉ** ከጥላዬም በታች ይኖራሉ" ይላል። ይህ ስብስብ ማን ነው? የእግዚአብሔር ሕዝብ ነው! ይህ

እንደ አበባም ያብባል፤
እንደ ሊባኖስም ሥሩን ይሰድዳል።

6
ቅርንጫፎቹም ይዘረጋሉ፤
ውበቱም እንደ ወይራ
ሽታውም እንደ ሊባኖስ ይሆናል።

7
ከጥላውም በታች የሚቀመጡ ይመለሳሉ፤[212]
ከእህሉም የተነሣ ይጠግባሉ፤
እንደ ወይንም አረግ ያብባሉ፤
መታሰቢያውም[213] እንደ ሊባኖስ ወይን ጠጅ ይሆናል።

8
ከእንግዲህ ወዲህ ጣዖት ለኤፍሬም ምንድር ነው?[214]
እኔ ሰምቻለሁ፤ ወደ እርሱም እመለከታለሁ፤
እኔ እንደ ለመለመ ጥድ ነኝ፤

---

ጥቅስ የሚያወራው ስለ ንጉሡ (ክርስቶስ ኢየሱስ) እና ስለ ህዝቡ (በክርስቶስ ስለሆኑት ሁሉ) ሀሴት በማድረግ ስለሚደሰት ነው!

212 የእንግሊዝኛው መጽሐፍ ቅዱስ ESV በሆነ ምክንያት፣ ቁጥር 7ን በሚከተለው መንገድ ተርጉሟል፡- "ይመለሳሉ ከጥላዬም በታች ይኖራሉ"። ሆኖም፣ "የእኔ" የሚለው ቃል በዕብራይስጥ (MT) ወይም በግሪክ (LXX) ውስጥ የለም። በዕብራይስጡም ሆነ በግሪኩ "ተመልሰው በጥላው ሥር ይኖራሉ" የሚል ነገር ነው የሚናገሩት። እግዚአብሔር እየተናገረ ያለው የእግዚአብሔር ሕዝብ በሁለተኛው ዘጸአት ሲመለሱ በንጉሣቸው ጥላ ሥር ይኖራሉ! ይህ በንጉሣቸው እንክብካቤና ጥበቃ ሥር የሚኖሩትን የእግዚአብሔር ሰዎች የሚያመለክት ነው (በተጨማሪም በቁጥር 7 መጨረሻ ላይ ያለውን ማስታወሻ ይመልከቱ)።

213 የዕብራይስጡ (MT) እና የግሪክ (LXX) በሁለቱም ውስጥ "ዝና" ወይም ክብር የሚል አንድምታ አላቸው። ነገር ግን ስለ ክርስቶስን የሚናገር ነው። በነቢያትና በመጻሕፍት ውስጥ ስለ ክርስቶስ እንደዚህ ያለ ብዙ ቋንቋ አለ።

214 በቁጥር 8 እግዚአብሔር ስለ እስራኤል የጣዖት አምልኮ ያለውን ስሜት ጠቅለል አድርጎ ከመናገር ያለፈ ነገር ያደርጋል። ማለትም ሕዝቡን ለመንከባከብ ያለውን ፍላጎትም ያሳያል። ይህ በዚህ ዘመን ላሉ ሰዎችም ጠቃሚ ጥቅስ ነው። እግዚአብሔር ለሕዝቡ የሚያስብ አምላክ ነውና። እኛ ከምንጠመድባቸው ብዙ የሐሰት አማልክቶች ጋር የሚያመሳስላቸው ምንም ነገር የለም። እግዚአብሔር ሕዝቡን አማልክቶቻቸውን እንዲተውና ራሳቸውን ለእርሱ እንዲሰጡ እየጠራቸው ነው።

ፍሬህ በእኔ ዘንድ ይገኛል።

9

ይህን ነገር የሚያስተውል ጠቢብ[215]

የሚያውቃትም አስተዋይ ማን ነው?[216]

የእግዚአብሔር መንገድ ቅን ነው

ጻድቃንም ይሄዱበታል፤[217]

ተላላፊዎች ግን ይወድቁበታል።[218]

---

[215] ይህ ቁጥር የመላው የሆሴዕ መጽሐፍ ማጠቃለያ ነው። አስተዋዮች የሆሴዕን መልእክት ሰምተው ለመልእክቱ ምላሽ እንደ ሚሰጡ ይናገራል።

[216] ይህም ከዘዳግም 32:29 ጋር ተመሳሳይ ነው፡- "አእምሮ ቢኖራቸው ይህንን ያስተውሉ ነበር፤ ፍጻሜያቸውንም ያስቡ ነበር።" እንደገና፣ በሆሴዕ እና በዘዳግም መጽሐፍ መካከል ብዙ ግንኙነቶች አሉ።

[217] ሆሴዕ "የጻድቃን መንገድ" ስለመመላለሱ የጠቀሰው ይህንን መጽሐፍ በትክክል መረዳቱ ከእውቀት ያለፈ ነገርን እንደሚጨምር ያሳያል። ተግባርን ያካትታል። እምነት እና ተግባር ሁል ጊዜ አብረው ይሄዳሉ (ያዕቆብ 2፡26 ተመልከት)።

[218] በመጨረሻም ሆሴዕ ሁለት ዓይነት የሰዎች ቡድን ያመለክታል፡- ቅኖችና ተላላፊዎች። ለመጽሐፉ ምላሽ የምንሰጥበት መንገድ የየትኛው ቡድን አካል እንደሆንን ያሳያል ማለት ነው።

ማስታወሻ

## ማስታወሻ

# ሀንድስ ቱ ዘ ፕሎ አገልግሎት

Hands To ThePlow.org

ተጨማሪ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት

መርጃዎች ከሀንድስ ቱ ዘ ፕሎ አገልግሎት

Hands To ThePlow.org

እነዚህ መጣጥፎችንም ያካትታሉ . . .

- **የሰባኪ መመሪያ**

  **መዝሙረ ዳዊት (መዝሙር 1–19)**
- **የሰባኪ መመሪያ**

  **የማርቆስ ወንጌል**
- **የሰባኪ መመሪያ**

  **የ 1ኛ ጴጥሮስ መልዕክት**
- **የሰባኪ መመሪያ**

  **የራእይ መጽሐፍ**

Copyright© 2019 by Hands to the Plow, Inc.

የቅጂ መብት 2019 ሀንድስ ቱ ዘ ፕሎ አገልግሎት

ሀንድስ ቱ ዘ ፕሎ አገልግሎት

HandsToThePlow.org